# ክፍል 1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት መሠረታዊ ሃሳቦች

## 1.1. መግቢያ

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ከ 5-6 ዓመት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ህጻናት እንዲያድጉና እንዲዳብሩ ከደረጃቸው ጋር በተመጣጠነ መልኩ ዕገዛ ሊደረግላቸው ይገባል። በዚህ ዕድሜ የሚገኙ ህጻናት ስለ አካባቢያቸው ለማወቅና አዳዲስ መረጃዎች ለማግኘት ያላቸው ጉጉት ከመጨመሩ የተነሳ ብዙ ይጠይቃሉ፣ይፈትሻሉ፣ ከቁሳቁሶች ጋር ባለቸው ግንኙነት የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት ይጥራሉ የማወቅም ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነው።

በዘርፉ ያሉ መምህራን የህጻናቱን ባህሪ፣አቅም፣ ሊደረግላቸው የሚገባን እንክብካቤና ከህጻናቱ የሚጠበቅባቸውን ብቃት ተገንዝበው ህጻናቱን በደረጃቸው ከመንከባከብና ከማስተማር ባሻገር ለመደበኛ ትምህርት ቤት ማዘጋጀትን በተገቢው አቅጣጫ ሊያከናውኑ ይገባል። ከ 5-6 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ህጻናትን ለመደበኛ ት/ቤት ማዘጋጀት ነው። ከዚህ የተነሳ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ለመደበኛ ት/ቤት ማዘጋጀትን በተመለከተ ተጨማሪ ሐሳብ ተካቷል።

> ህጻናት በነጻነት እንዲንቀሳቀሱና መረጃዎችን በመሰብሰብ ስለአካባቢ ለማወቅ ያላቸው ፍላጎት እና ግንዛቤ እንዲዳብር ብሎም አዋቂዎችን ለመምሰል ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት ተገቢውን አቅጣጫ እንዲይዝና በአካል፣ በአእምሮ፣ በማህበራዊ እና በስሜት ዳብረው ለመደበኛ ትምህርት ቤት እንዲዘጋጁ ሁኔታዎችንና አካባቢን ማመቻቸት ያስፈልጋል።

ይህ አጋዥ ጽሁፍም ከ 5-6 ዓመት ዕድሜ ክልል ላሉ ህጻናት የተዘጋጀ ሲሆን በአምስት የእድገትና መዳበር ዘርፎች ላይ ማለትም በአካልና በእንቅስቃሴ፣ በማህበራዊና ስሜታዊ ክንዋኔ መዳበር፣ በቋንቋ፣ በሂሳብ እና አካባቢን በመፈተሸና በመረዳት ላይ ትኩረት በማድረግ በየዘርፉ ህጻናት ሊደርሱበት የሚገባውን የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች፣ የመርጃ መሳሪያዎች ዝርዝር እና የማስተማሪያ ዘዴዎች ጥቆማን አካቶ ቀርቧል። በተጨማሪም ህጻናቱ በቀሰሙት ልምድ በየዘርፉ ምን ያህል ክህሎት እንዳዳበሩ ለመገምገም የሚያስችል የመከታተያ /የመመዘኛ/ ቅጽ ግልጽ በሆነ መልኩ ተዘጋጅቷል። ይህ መመዘኛ መምህራንና ወላጆች ህጻናትን በማሳደግና በማዳበር ሂደት ላይ የሚያከናውኗቸውን ተግባራትና የሚጎድሉ ነገሮችን በጊዜ በማወቅ ለእያንዳንዱ ህጻን አስፈላጊውን ትኩረት እንዲሰጡ እገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል።

ይህ አጋዥ ጽሁፍ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ሲለበስን ስራ ላይ ለማዋል በአጋዥነት የተዘጋጀ እንጂ በራሱ ዕቅድ እንዳልሆነ በመገንዘብ ደረጃውን የጠበቀ እቅድ አዘጋጅቶ መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል።

## 1.2. የሕፃናት አስተዳደግና ትምህርት መሠረታዊ መርሆዎች

1. ልጅነት ከሰው ህይወት አንዱ ክፍል እንጂ ለወደፊት ህይወት ማዘጋጃ መንገድ ብቻ አይደለም።
2. ህጻናት የተሟላ የስብእና መዳበር /አካላዊ፣አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ/ ጤንነት ሊኖራቸው ይገባል።
3. ህጻናት በተቀናጀ መልኩመማር አለባቸው በመሆኑም የትምህርት ዓይነቶችን መበታተን ተገቢ አይደለም።
4. ህጻናት በራሳቸው ለመማር የውስጥ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው።
5. ህጻናት ራሳቸውን በራሳቸው በስርዓት መምራት እንዲለማመዱ እድል መስጠት አስፈላጊ ነው።
6. ህጻናት የተለያዩ ነገሮችን የሚቀበሉበት የዝግጁነት ጊዜ /ወሳኝ ጊዜ/ አላቸው።
7. ለህጻናት የትምህርት መጀመሪያ ሊሆን የሚገባው ማድረግ የሚችሉት እንጂ ማድረግ የማይችሉት አይደለም።
8. የህጻናት ፈጠራና ምናብ ሊዳብር የሚችለው በተመቻቸ ሁኔታና አካባቢ ነው።
9. ማህበራዊ ግንኙነት /ከእኩዮቻቸውና ከአዋቂ ሰዎች ጋር የሚደረግ መስተጋብር/ ለህጻናት ስብእና መዳበር አስፈላጊ ነው።
10. ጥራት ያለው ትምህርትለህጻኑ/ኗ ትምህርት በሚሰጥበት ተጨባጭ ሁኔታና ህጻኑ/ኗ ሊያውቅ በሚገባው ጭብጥ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል።

## **1.3.**ከ **5-6** ዓመትእድሜክልልየሚገኙሕፃናትባህርይናየመዳበር ለውጦች

- የሰውነት ሚዛናቸውን በመጠበቅ የተለያዩ የሰውነት ቅልጥፍናን የሚጠይቁ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን ይችላሉ
- ቀለል ያሉ ተግባራትን በራሳቸው ተነሳሽነት ያከናውናሉ
- ቀልጣፋ፣ ንቁ እና ጠንካራ እየሆኑ ይመጣሉ
- በራስ የሚተማመኑና ተግባቢ እየሆኑ ይመጣሉ
- ሀሳባቸውንና ፍላጎታቸውን አድማጭ ሊገባው በሚችል መልኩ መግለጽ ይችላሉ
- የስሜት ህዋሳቶቻቸውን በመጠቀም የነገሮችን መጠን፣ ቅርጽ፣ ቀለም፣ ጣዕም፣ ሽታ፣ ድምጽና ባህሪ ይለያሉ
- የቦታን፣ የጊዜንና የቁጥርን ጽንሰ ሀሳብ በደረጃቸው መረዳት ይችላሉ
- በህብረት ጨዋታ ላይ በአግባቡ መሳተፍ ይችላሉ
- አዳዲስ ነገርን ለመሞከር ለመፍጠር ፍላጎት ያድርባቸዋል
- ለሚያደርጓቸው ነገሮች ምክንያት ለመስጠት ጥረት ያደርጋሉ
- ለጨዋታ ህጎች ተገዢ እየሆኑ ይመጣሉ
- የነገሮችን መንስኤና ውጤት ለማወቅ ጥረት ያሳያሉ
- የየራሳቸውንና የሌሎችን ባህሪይ በተወሰነ ደረጃ መመዘን ይጀምራሉ
- የዓይንና የእጅ ቅንጅታቸው እየተሻሻለ ይሄዳል
- ንግግራቸው ማህበራዊ መልክ እየያዘ ይመጣል
- ሌሎች የሚገኙበትን ስሜት መረዳት ይጀምራሉ እንዲሁም ላለማስቀየም፣ ላለመጉዳት ወዘተ**…** ጥረት ያደርጋሉ
- አዳዲስ ተግባራቶችን ማከናወን መቻል ያስደስታቸዋል
- የሰውነት ቅርጻቸው እየተለወጠ ይመጣል
- አዲስ ነገርን ለማወቅ ጉጉ ናቸው
- ብዙ ይናገራሉ እንዲሁም ብዙ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ
- ብቃትና ችሎታ የሚጠይቁ ውድድር ያለባቸዉ ጨዋታዎች ይማርኳቸዋል

## 1.4. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ስለሕፃናት አስተዳደግና ትምህርት ሊገነዘቡ የሚገቧቸው አንኳር ነጥቦች

ሀ. በቅድመ መደኛ ትምህርት ቤት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ህጻናት አዲስ ነገርን ለመማር የሚያነሳሷቸው ምክንያቶች

- ፍላጎትና ጉጉት መኖር፡- ህጻናት ገና ሲወለዱ ጀምሮ ነገሮችን የመመልከት፣የመረዳት፣ የማወቅ ፍላጎት ያላቸው ሲሆን ይህ ፍላጎታቸው አካባቢያቸወን እንዲፈትሹና እንዲያውቁ ያነሳሳቸዋል። በመሆኑም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንና ወላጆች ህጻናት አካባቢያቸውን ለማወቅና ለመረዳት ያላቸውን ፍላጎትና ጉጉት ለማርካት በሚያደርጉት ጥረት እና እንቅስቃሴ እድሉን መስጠትና ማበረታታት ይኖርባቸዋል።
- ድርጊቶችን የማከናወንና ግብ ላይ የማድረስ ፍላጎት፡- ድርጊቶችን የማከናወንና ግብ ላይ የማድረስ ፍላጎት መኖር ህጻናት የተለያዩ ተግባሮችን ራሳቸውን ችለው ማከናወንን እንዲለማመዱ ያደርጋቸዋል። በተለይ ፈታኝ ከሆኑ ድርጊቶች /ተግባሮች/ ጋር መጋፈጣቸው በተሻለና በቶሎ ተግባሮችን እንዲያከናውኑና ግብ እንዲያደርሱ ይረዳቸዋል። በመሆኑም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንና ወላጆች ህጻናት ራሳቸውን ችለው የተለያዩ ተግባሮችን እንዲያከናውኑ እድሉን መስጠትና ከግብ እንዲደርሱ ክትትል በማድረግ ማገዝና ማበረታታት ይኖርባቸዋል።
- ወላጅንና መምህራንን ደስ የማሰኘት ፍላጎት፡- ህጻናት የሆነ ነገር በማድረግ ወላጆቻቸውንና መምህራኖቻቸውን በማስደሰት የእነሱን አድናቆት ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ። ስለዚህ ወላጆችና መምህራን ህጻናት የሚያደርጉትን መልካም ነገር ዕውቅና በመስጠት ማበረታታት ያስፈልጋል።
- አዋቂዎችን የመምሰል ፍላጎት፡- ህጻናት አዋቂዎችን የመምሰል ፍላጎት /ምኞት/ ብቻ ሳይሆን ያላቸው በሚችሉት አቅም እነሱን ለመምሰል ይጥራሉ። ይህንንም ፍላጎታቸውን ለማሟላት አዋቂዎችን በመኮረጅ ይማራሉ። ስለዚህ በህጻኑ አካባቢ የሚገኝ ሰው ለህጻኑ ጥሩ ሞዴል ሆኖ መገኘት ይኖርበታል።
- ሽልማትን ለማግኘት መፈለግ፡- ልጆች ሽልማትን መውደዳቸውበከፍተኛና በተሻለ ሁኔታ እንዲማሩ ይረዳቸዋል። ወላጆች፣ መምህራንና ሌሎች ሀላፊነት ያለባቸው ሰዎች ህጻናት በጣም ትንሽ መልካም ተግባር /ምግባር/ ሲያከናውኑ በመሸለም ጠንክረው እንዲማሩና ተፈላጊውን ባህርይ እንዲለማመዱ ማነቃቃት ይኖርባቸዋል። እንደዚሁም ወቀሳንና ቅጣትን በተቻለ መጠን መቀነስና ማስወገድ ያስፈልጋል። መምህራን ህጻናት እንዳይረበሹ፣ እንዳይሰጉ እና እንዳይፈሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ፍርሃት፣ስጋት እና ጭንቀት ህጻናት በአግባቡ እንዳይማሩ ያግዳቸዋል።

ለ. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዕድሜ ያሉ ህጻናት ሊማሩ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች

ህጻናት በዚህ ጊዜ ይማራሉ ለማለት አስቸጋሪ ቢሆንም ሁኔታዎች በተመቻቸ ጊዜ ሁሉ ግን መማር ይችላሉ። ይኸውም፡-

- <u>ደስተኛ ሲሆኑ፡-</u> ህጻናት የተለያዩ ተግባራቶችን በማከናወን እናበመለማመድ ሊማሩና ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት ደስተኛ ሲሆኑ ነው። ስለዚህ በቤትም ሆነ በአጸደ ህጻናት ፍቅር፣ እንክብካቤና ደስታ የተሞላበት አካባቢን በመፍጠር ደስተኛ ሆነው በጥሩ ሁኔታ እንዲማሩ ማድረግ ያስፈልጋል።
- <u>ፍላጎት ሲኖራቸው፡-</u> ህጻናት አንድን ነገር ለመማር የሚችሉት በመጀመሪያ ደረጃ ለመማር እና ለማወቅ ፍላጎት ሲኖራቸው ነው። ህጻናት ሁልጊዜ የሚያስደስታቸውን ነገር ሲያገኙ በተሻለ ሁኔታ ይማራሉ። ስለዚህ ለህጻናት የሚቀርቡ ማናቸውም ተግባራት አስደሳችና በየጊዜው ተለዋዋጭ መሆን እንደዚሁም ህጻናቱን በተገቢው ሁኔታ የሚፈትኑና የመማር እና የማወቅ ፍላጎታቸውን የሚያነሳሱ መሆን ይኖርባቸዋል።
- <u>ዝግጁ ሲሆኑ፡-</u> ህጻናት ሁሉን ነገር በአንድ ጊዜ መማር አይችሉም። ምክንያቱም የሚገኙበት የመዳበር ደረጃ የተለያዩ ተግባራትን ለመማርና ለማከናወን ያላቸውን ዝግጁነት ይወስነዋል። አብዛኛውን ጊዜ አዋቂዎች ህጻናት አዲስ ነገርን ለመማር ዝግጁ ባልሆኑበትና ባልደረሱበት ጊዜ እንዲማሩና እንዲያውቁ ይጫኗቸዋል። ይህ ደግሞ ህጻናቱ እንዲጨነቁ፣ እንዲሰላቹና በመማር ሂደቱ ላይ ጥላቻ እንዲያድርባቸው በማድረግ በወደፊት የመማር ሂደታቸው ላይ ትልቅ እንቅፋት ይፈጥርባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነገር እያንዳንዱ ህጻን የመማር ፍጥነቱ የተለያየ መሆኑን መገንዘብ ነው።

ሐ. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ህጻናት አዲስ ነገር የሚማሩባቸው መንገዶች

- <u>በድርጊት ፡-</u> ለህጻናትበማየትና በማዳመጥ ከመማር የበለጠ ምቹና የተሻለ መንገድ ድርጊቶችን በማከናወን መማር ነው። ህጻናት ትኩረት ሰጥተው በማዳመጥ ለረጅም ጊዜ መማር ይከብዳቸዋል። ነገር ግን ድርጊቶችን በማከናወን በንቃት የተሻለ ሊማሩ ይችላሉ።
- <u>በማሰስና በመፈተሽ ፡-</u> ህጻናት አካባቢያቸውን እንዲፈትሹ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል። ህጻናት የስሜት አካላቶቻቸውን በመጠቀም /በማየት፣ በመያዝ፣በመቅመስ፣ በማዳመጥ እና በማሽተት/ የሚያጋጥማቸውን ነገር ለማወቅ ጥረት ያደርጋሉ። ውጤቱ እርኪ ከሆነላቸው ይደግሙታል ካልሆነ መተውን ይመርጣሉ። ነጻ የሆነ ፍተሻና አሰሳ ህጻናት ነገሮች /ዕቃዎች/ እንዴት እንደሚሰሩና በቀጣይ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ እንዲረዱ ይረዳቸዋል።

- <u>ጥያቄ በመጠየቅ</u> **፦** በማዳመጥና በመናገር የህጻናት የማወቅ ፍላጎትና ጉጉት ብዙ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ የሚያደርጋቸው ሲሆን ህጻናት መልሱን እያወቁ እንኳን ለማረጋገጥ ይጠይቃሉ። ወላጅና መምህራን በተቻለ መንገድ ህጻናትን ማነጋገር፣ የሚሉትን ማዳመጥና ለጥያቄዎቻቸው በወቅቱ ተገቢውን መልስ በመስጠት የህጻናትን የመማርና የመመራመር ፍላጎት ማነቃቃትና ማበረታታት ይገባቸዋል።
- <u>በመኮረጅ</u> **፦** ህጻናት አዋቂዎችንና ታላላቆቻቸውን በመኮረጅ ይማራሉ። እንደ አዋቂዎች ለማድረግና ለመናገር ሙከራ ማድረግ ይወዳሉ። ህጻናት አዋቂዎችን መኮረጅ ብቻ ሳይሆን የአዋቂዎችን ሚና ወስደው ለመጫወትም ይሞክራሉ። በመሆኑም የህጻናት ወላጆች፣ መምህራንና ከህጻናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁሉ ለህጻናቱ ጥሩ ሞዴል መሆን ይኖርባቸዋል።
- <u>በመሞከር በመሳሳትና በመለማመድ</u> **፦** ህጻናት አንድን ተግባር ለማከናወን የተሻለውን መንገድ እስኪያገኙና ማከናወን እስኪችሉ ድረስ በተደጋጋሚ በመሞከር፣ በመሳሳት እና በመለማመድ ይማራሉ። በተለይ የዕድሜ እኩዮቻቸው ማድረግ የቻሉትን ነገር እስኪችሉ ድረስ ያለመሰልቸትና ያለማቋረጥ ይሞክራሉ። በዚህ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ህጻናት ከሚያስደስታቸው ነገር አንዱ አልችለውም ብለው ያሰቡትን ነገር መቻላቸውና ከዕድሜ እኩዮቻቸው ተሽለው መገኘታቸው ነው። በመሆኑም ወላጅና መምህራን ህጻናቱ ራሳቸውን ችለው የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን እንዲችሉ ማበረታታት ያስፈልጋል።

## 1.5. የወላጆች ተሳትፎ በህጻናት አስተዳደግና ትምህርት

ወላጆች የመጀመሪያዎቹ የህጻናትን አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የመጀመሪያዎቹ አስተማሪዎችና በቀጣይ ህይወታቸዉ ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ናቸው። ምንም እንኳን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ህጻናትን ተንከባክበው በማሳደግና በማስተማር ለመደበኛ ትምህርት ቤትና ለቀጣይ ህይወታቸው የማዘጋጀት ሀላፊነት ያለባቸው ቢሆንም ሀላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት የሚችሉት ግን ከሚያሳድጓቸው ህጻናት ወላጆች ጋር በጋራ በመስራት መሆኑ ግልጽ ነው።

ወላጆችም ሆኑ የህጻናት አሳዳጊዎች ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መመህራን ጋር የስራ አጋርነት በመፍጠር በህጻኑ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ የሚሳተፉ ከሆነ ሶስቱም አካሎች /ህጻናቱ፣ ወላጆችና መምህራን/ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ጥናቶች ይገልጻሉ።

ወላጆች ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር አብረው ሲሰሩ ህጻናቱ በትምህርት ብቻ ሳይሆን በወደፊቱ ህይወታቸውም ውጤታማ ይሆናሉ። በራስ መተማመንን፣ ስለራሳቸው አዎንታዊ አመለካከትንና ባህሪን ያዳብራሉ እንዲሁም ጥሩ ማህበራዊ ልምድን በመመስረትም ደስተኛ ይሆናሉ:: ወላጆችም ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ጋር በመጠኑ ይተዋወቃሉ፤ ከሌሎች ወላጆች ጋር ልምድን ይለዋወጣሉ፤ በወሳኝ የመዳበር ወቅት ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረጋቸው ደስተኞች ይሆናሉ እንዲሁም ለልጃቸው እድገትና መዳበር አስፈላጊውን ነገር አቅም በቻለ መጠን የማድረግና የሚከሰቱ ችግሮችንም በወቅቱ መፍትሄ የመሻት እድልን ያገኛሉ።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንም ወላጆች ህጻናትን በማሳደግና በማስተማር ስራ ላይ ከጎናቸው ሆነው እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሰሩ ከሆኑ በስራቸው ውጤታማና ደስተኛ ይሆናሉ፤ ስለ ህጻኑ እድገትና መዳበር መረጃ ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም ወላጆችን በማሳተፋቸው በሀሳብ፣ በእወቀት፣ በጉልበትና በማቴሪያል ድጋፍ ያገኛሉ።

በመሆኑም ወላጆች ይህንን ተመልሶ ሊገኝ የማይችለውን የህጻኑን ወርቃማ ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር በህጻናት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንወላጆች በህጻናት አስተዳደግና ትምህርት ፕሮግራም ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማበረታታት የሚከተሉትን መንገዶች ቢጠቀሙ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ።

- ወላጆች በልጆቻቸው የመማር ሂደት ላይ ተሳታፊ የመሆንና ልጆቻቸው በትምህርት ቤት ጥሩ ተማሪ እንዲሆኑላቸው ያላቸውን ፍላጎት መረዳት
- ወላጆችን የሚደግፍና የህጻናትን የመማር ሂደት ሊረዱ የሚችሉበትን ፕሮግራም መንደፍና መተግበር
- ቋሚ የሆነ ከወላጅ ጋር ግንኙነት መፍጠር /ህፃኑን በመቀበያና በመሸኛ ሰዓት፣ በመገናኛ ደብተር፣ በስልክ ወዘተ…/
- የተለያዩ የማንቂያና ግንዛቤ የማስጨበጫ ስልቶችን መንደፍ /የወላጆች ስብሰባ በመጥራት፣ የቡድን ውይይት በማካሄድ፣ አጫጭር ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ወዘተ…/
- ወላጆች በህጻናት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታት /በእረፍት ሰዓት ህጻናቱን እንዲያጫወቱ፣ ተረት እንዲተርቱ፣ በሽርሽር ወቅት እንዲረዱ በማደረግ ወዘተ…/
- ወላጆች ዕለት በዕለት ከልጆቻቸዉ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ስለተማሩት እንዲወያዩ በማደረግ
- የህጻናቱን የዕለት ተዕለት ለውጥና መሻሻልን እንዲያጤኑ በማድረግ

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት በተለያዩ ፕሮግራሞች ህጻናትን በመምራት የሚሳተፉት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ቢሆኑም ከላይ እንደተገለጸው የወላጅ ሚና ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ከተገለጸው በተጨማሪ ህጻናቱን ስለቀን ውሎዋቸዉ እንዲያወሩ እቤታቸዉ በሚገቡበት ጊዜ አብረው የሚሰሩትን /የሚያወሩበትን/ ስራ በመስጠትና እንደአስፈላጊነቱ ስለህጻናቱ ለመነጋገር ጊዜ በማመቻቸት ወላጆች አብረዉ የሚሰሩበትንና በህጻናቱ አስተዳደግ ላይ በተገቢው አቅጣጫ የሚንቀሳቀሱበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል።

## **1.6.** ለመደበኛ ትምህርት ቤት መዘጋጀት

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዓላማ ህጻኑን በአካል፣ በአእምሮ በስሜትና በማህበራዊ ግንኙነት ማነጽና ለመደበኛ ትምህርት ቤት ማዘጋጀት መሆኑ ግልጽ ነው። ከ 5-6 ዓመት ያለው ዕድሜ ለመደበኛ ት/ቤት የመዘጋጀት ተግባር ልዩ ትኩረት የሚሰጥበት ጊዜ ነው።

መዘጋጀት ምንድን ነው? ለመደበኛ ትምህርት ቤት መዘጋጀት ልጆች በቀዳማይ የልጅነት ዘመን በሚደረግላቸው እንክብካቤና የትምህርት በዕለት ተዕለት ህይወታቸው በሚያገኙት የመማር ተሞክሮዎችና በሚያዳብሩት የክህሎት ደረጃ የሚወሰን ነው። ለልጆች የሚደረግላቸው እንክብካቤና ትምህርት ጥራትና ተገቢ አቅጣጫ ይዞ መገኘት ለመደበኛ ትምህርት ቤት የዝግጁነት ብቃትን ሊወስን ይችላል።

ለመደበኛ ትምህርት መዘጋጀት ማለት ህጻኑ/ኗ በመደበኛ ትምህርት ቤት የተማሪነት ህይወቱ የሚያስፈልጉትን አካላዊ፣አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ክህሎቶች አዳብሮ መገኘትና መደበኛ ትምህርት ቤት ገብቶ ለመማር ጥሩ ዝንባሌ ይዞ መገኘት ላይ ያተኮረ ነው። ይህም ሊሆን የሚችለው ከላይ እንደተጠቀሰው በቀዳማይ የልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ነው።

> በህጻናት ዕድሜ የመጀመሪያዎቹ 5 ዓመታት የአንጎል መዋቅርና ጥንካሬ የሚገነባባቸው ወቅቶች ሲሆኑ ማንኛውም ህጻን የሚሰማው፣ የሚያየውና የሚያደርገው ድርጊት በአእምሮው ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ከሰዎች ጋር በሚያደርጋቸው መስተጋብሮች ማህበራዊ ህይወቱ ይዳብራል።
>
> በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቹና በተለያዩ የጨዋታና ሌሎች ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ሂደት አካሉ ይዳብራል። እነዚህንና የመሳሰሉ የህጻኑ/ኗ ተሞክሮዎች ለመደበኛ ት/ቤት በመዘጋጀት ሂደት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

ህጻናት መደበኛ ትምህርት ቤት ሲገቡ የሚፈለግባቸውን አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ እንዲሁም ስነልቦናዊ ዝግጁነት /ብቃት/ መረዳት እንክብካቤና ትምህርት ለሚሰጧቸው መምህራን አስፈላጊ ነው። የአእምሮአዊ ብቃት ትኩረት ማዳመጥ፣ ሀሳብንና ፍላጎትን በተገቢው መንገድ መግለጽ፣ የነገሮችን አንድነትና ልዩነት ማስተዋል፣ ክስተቶችን መገንዘብ፣ ትዕዛዝን መረዳት፣ ራስንና አካባቢን መገንዘብ፣ ለመማር መነሳሳትን ወዘተ…ያካትታል።

*የአካላዊ ብቃት ትኩረት የአካል እንቅስቃሴን መቆጣጠር መቻል /ሰዓትን ጠብቆ መመገብ፣ መጸዳዳት፣ ረዘም ላለ ጊዜ ተረጋግቶ መቀመጥ ወዘተ… /፣ የሰውነትን ሚዛንን መጠበቅ መቻል፣ የዓይንና የእጅ ቅንጅት መዳበር መቻልን ወዘተ… ያካትታል።*

*የማህበራዊ እና ስሜታዊ ብቃት ትኩረት ከእኩያ ጓደኞቻቸው ጋር ተባብሮና ተከባብሮ መስራት፤የመምህራኖቻቸውን እና የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ልምድን፣ የኑሮ፣ የስራ እና የትምህርት ስርዓቶችን ማክበር በደረጃቸው ሌሎችን ለመርዳት መንቀሳቀስ፤ ስሜትን በተገቢው መንገድ መግለጽን ወዘተ… ያካትታል።*

*የስነ ልቦናዊ ብቃት ትኩረት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ቆይታቸው እንዳለቀ ተገንዝበው በፍላጎትና በጥሩ ዝንባሌ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት ለመግባት መነሳሳት ይሆናል።*

ከላይ በተገለጹት የመዳበር አቅጣጫዎች አኳያ የተቀመጡትን ጥቆማዎች ተከትሎ ሰፋ ባለ መልኩ ለመደበኛ ትምህርት ቤት የማዘጋጀት ጽንሰ ሐሳብን መገንዘብ ያስፈልጋል። አንድ ህጻን ለመደበኛ ት/ቤት ተዘጋጀ የሚባለው ለአንደኛ ክፍል ብቁ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሳይሆን ለመደበኛ ትምህርት ቤት የተማሪነት ህይወት ዝግጁ ሆኖ ሲገኝ ነው። ይህም ተፈጻሚነት የሚያገኘዉ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ሲለበስ ላይ ከተቀመጡት ብቃቶች አኳያ በመስራትና ህጻኑን በማብቃት ነው። ይህ አጋዥ ጽሁፍም ይህ ተግባር የሚከናወንበትን አቅጣጫ ለመጠቆም ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ከዚህ በፊት ከ 3-4 እና ከ 4-5 ዓመት ዕድሜ ክልል ላሉ ህጻናት የተዘጋጁት አጋዥ ጽሁፎች ተከታይ ሲሆን ጥቅም ላይ ሊውል የሚገባው ለተዘጋጀለት ዕድሜ ማለትም ከ 5-6 ዓመት ዕድሜ ክልል ላሉ ህጻናት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

## **1.7.** የመጽሐፉ አጠቃቀም

በዚህ አጋዥ መጽሐፍ ላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ብቃቶች፣ ዓላማ፣ ተግባር፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማና ምዘና በሚል ትኩረት እንዲያገኙ ምልክቶችና ደመቅ ብለው የተቀመጡ ሐረጎች በመጽሐፉ ውስጥ ይገኛሉ። የእነዚህ ምልክቶችና ሐረጎች ትርጉም በተጠቃሚዎቹ የቅድመመደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ሊታወቁ ይገባል። ትርጉማቸውም እንደሚከተለው ተቀምጦአል።

ምልክቶች — በተጠቃሚዎች ሊታወቁ የሚገቡ ሐረጎች



የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ሕፃናት በተጠቀሱት የብቃት ደረጃዎች ላይ ሲደርሱ በእነሱ ላይ ሊታዩ የሚገባቸው ለውጦች ናቸው።



ብቃቶች፡- ብቃቶች ሕፃናት የተለያዩ ተግባራትን በመተግበር ወይም በማከናወን ሊደርሱባቸው የሚገቡ የብቃት ደረጃዎችን ያመለክታሉ።

ምልክቶች　　　　　በተጠቃሚዎች ሊታወቁ የሚገቡ ሐረጎች



ተግባር፡- በአንድ ክፍለ ጊዜ ሊታቀዱና (lesson plan) ሊተገበሩ ለሚችሉ ተግባራት በርዕስነት የተቀመጠ ቃል ነዉ። ተግባራቱ በአንድ ክፍለ ግዜ እንዲከወኑ ታሳቢ ተደርገው የተዘጋጁ ተከታታይነት ያላቸው ክንውኖች ሲሆኑ በአንድ ብቃት ሥር ከአንድ በላይ ተግባር ሲኖር ተግባራቱ እንደየአስፈላጊነቱ ሊደጋገሙ እና ከአንድ ክፍለግዜ በላይ ሊተገበሩ ይችላሉ።



ዓላማ፡- ተግባራቱ ከተተገበሩ ወይም ክፍለ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ሕፃናት ሊያገኙት የሚችሉትን ጥቅም ወይም ሊደርሱባቸው የሚችሉትን የብቃት ደረጃዎች የሚጠቁም ነው። የክፍለ ጊዜ ዕቅድ ዓላማ ሆኖም ሊያገለግል የሚችል ነው።



የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- ሕፃናት የሚፈለገው ብቃት ላይ እንዲደርሱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመደገፍ /ለማስተላለፍ/ ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸውንና እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ መሣሪያዎችን ያመለክታሉ:: መሣሪያዎቹ እንደሚከናወነው ተግባር፣ እንደሕፃናት ዕድሜ እና የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የተለያዩሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ በመምህራን ሊታወቅ የሚገባው ነገር በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቆሙት የመርጃ መሣሪያዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሣሪያዎችን መጠቀም እንደሚቻል ነው። መምህራን በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እንደ መርጃ መሣሪያ አድርገው መጠቀም ይኖርባቸዋል።



የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-___በዚህ ሐረግ ሥር የተቀመጡት ሐሳቦች /ተግባራት/ ተግባሩን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ለመምህራን እንደ ጥቆማ የተቀመጡ ሲሆን ተግባር ላይ ለማዋል መምህራን ዕቅድን በማዘጋጀት የሕፃናትን ስሜት ማሰባሰቢያ፣ የክፍለ ጊዜውን ርዕስ ማስተላለፊያ መንገዶችንና በተግባሩ መጨረሻ የማጠቃለያ ዘዴዎችን በማካተት ሊጠቀሙ ይገባል።



ምዘና፡- ሕፃናቱ በየብቃቱ ሥር የተቀመጡትን ተግባራት በመተግበር ሂደቱና ከተገበሩ በኋላ የደረሱበትን ደረጃ ለመገምገም የሚረዳ ነው።

የምልከታ መከታተያ ቅጽ፡- በዚህ አጋዥ ጽሁፍ በየመዳበር አቅጣጫዎቹ ወይም ጭብጦች መጨረሻ ላይ የምልከታ መከታተያ ቅጽ ተቀምጧል። ይህ ቅጽ በዓመት ውስጥ ሶስት ጊዜ /በዓመቱ መጀመሪያ፣ አጋማሽና መጨረሻ/ መሞላት ይኖርበታል። ሆኖም በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ላይ የሚገኙ ህጻናት የሚመዘኑት በተከታታይ ምዘና ሆኖ ምዘናው በየዕለቱ፣ በየሳምንቱና በወሩ መጨረሻ ላይ ሊደረግ ይገባል። በቅድመ መደበኛ ት/ቤት

ምልክቶች　　　　　　　በተጠቃሚዎች ሊታወቁ የሚገቡ ሐረጎች

የሚካሄደዉ ተከታታይ ምዘና በየጊዜዉ በህጻናት ላይ የሚታየዉን አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ የመዳበር ለውጦችን በመከታተል መመዘን እንጂ በጽሁፍ ፈተና የሚከናወን ምዘና እንዳልሆነ መገንዘብ ለመምህራንም ሆነ ለወላጅ በጣም አስፈላጊ ነው።

በዚህ አጋዥ ጽሁፍ ላይ በየጭብጡ መጨረሻ የተቀመጠዉ የምዘና ቅጽ የማጠቃለያ መሆኑን መምህራን ተገንዝበው የህጻናቱን እድገትና ለውጥ በየጊዜው መከታተልና መገምገም የሚኖርባቸው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም በአባሪዉ ላይ የተቀመጡትን የምዘና ናሙና እና በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተቀመጡትን የምዘና ጥቆማዎች መጠቀም ይቻላል።

መዝሙሮች እና ተረቶች፡- በየተግባራቱ ስር የተጠቀሱት መዝሙሮች እና ተረቶች በመጽሀፉ መጨረሻ ገጾች ላይ አባሪ ተደርገዋል።

## **1.7** የህጻናት አስተዳደግና ትምህርት እቅድ

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ለአስተዳደግና ትምህርት ስራ ሶስት ዓይነት ዕቅዶች ይታቀዳሉ። እነርሱም የዓመት፣ የወርና የዕለት ናቸው። ከዕለት ዕቅድ ጋር እንደ አባሪ ሆኖ የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅድ /Lesson plan/ ይዘጋጃል።

<u>የምልከታ መከታተያ ቅጽ፡-</u>

በዚህ አጋዥ ጽሁፍ በየመዳበር አቅጣጫዎቹ ወይም ጭብጦች መጨረሻ ላይ የምልከታ መከታተያ ቅጽ ተቀምጧል። ይህ ቅጽ በዓመት ውስጥ ሶስት ጊዜ /በዓመቱ መጀመሪያ፣ አጋማሽና መጨረሻ/ መሞላት ይኖርበታል። ሆኖም በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ላይ የሚገኙ ህጻናት የሚመዘኑት በተከታታይ ምዘና ሆኖ ምዘናው በየዕለቱ፣ በየሳምንቱና በወሩ መጨረሻ ላይ ሊደረግ ይገባል። በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የሚካሄደዉ ተከታታይ ምዘና በየጊዜዉ በህጻናት ላይ የሚታየዉን አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ የመዳበር ለውጦችን በመከታተል መመዘን እንጂ በጽሁፍ ፈተና የሚከናወን ምዘና እንዳልሆነ መገንዘብ ለመምህራንም ሆነ ለወላጅ በጣም አስፈላጊ ነው።

በዚህ አጋዥ ጽሁፍ ላይ የተቀመጠው ምዘና ግን ማጠቃለያ መሆኑን መምህራን ተገንዝበው የህጻናቱን እድገትና ለውጥ በየጊዜው መከታተልና መገምገም የሚኖርባቸው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም በአባሪዉ ላይ

የተቀመጡትን የምዘና ናሙናዎች መሰረት በማድረግ እና በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተቀመጡትን የምዘና ጥቆማዎች መጠቀም ይቻላል።

<u>መዝሙሮች እና ተረቶች፡-</u>

በየተግባራቱ ስር የተጠቀሱት መዝሙሮች እና ተረቶች በመጽሀፉ መጨረሻ ገጾች ላይ አባሪ ተደርገዋል።

## 1.8. የህጻናት አስተዳደግና ትምህርት እቅድ

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ለአስተዳደግና ትምህርት ስራ ሶስት ዓይነት ዕቅዶች ይታቀዳሉ። እነርሱም የዓመት፣ የወርና የዕለት ናቸው። ከዕለት ዕቅድ ጋር እንደ አባሪ ሆኖ የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅድ /Lesson plan/ ይዘጋጃል።



የዕለት ዕቅድ ማቀጃ ቅጽ አራት ክፍሎች አሉት። በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ለአስተዳደግና ትምህርት ስራ ሶስት ዓይነት ዕቅዶች ይታቀዳሉ። እነርሱም የዓመት፣ የወርና የዕለት ናቸው። ከዕለት ዕቅድ ጋር እንደ አባሪ ሆኖ የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅድ /Lesson plan/ ይዘጋጃል።

የዕለት ዕቅድ ማቀጃ ቅጽ አራት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ሰዓትን፣ ሁለተኛው የዕለቱን የስራ ይዘት፣ ሶስተኛው የክንውኑን ሂደት፣ አራተኛው ሊታረሙ የሚገባቸውን ማለትም በክንውኑ ሂደት ያጋጠሙ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ነገሮች የሚጠቀስባቸው ናቸው። የዕለት ዕቅድ በየዕለቱ ምን መሰራት እንዳለበት፣ የታቀደው እንዴት እንደተሰራ እና በህጻናቱ ላይ ምን ለውጥ እንደመጣ በጊዜው ያለተሸፈነ ችግር ካለ ወደፊት የሚታረምበት ሁኔታ እንዲመቻች የሚጠቁም ስለሆነ በየዕለቱ የህጻናትን ለውጥ ለመከታተልና ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ ስለሚጠቅም አስፈላጊ ነው።

የክፍለ ጊዜ ክንውን ዝግጅት፡- ይህ ሌሰን ፕላን በመባል የሚታወቀው ሲሆን በየዕለቱ ለሚከናወኑት ዋና ዋና ፕሮግራሞች የሚዘጋጅ ነው። ዝግጅቱ በህጻናት እድገትና መዳበር ላይ የተመሰረተና ዝርዝር አስፈላጊ ነጥቦችን የሚጠቁም ሊሆን ይገባል።

የክፍለ ጊዜ ክንውን /ትምህርት/ ዝግጅት ማዘጋጃ ቅጽ

| | |
|---|---|
| ቀን | |
| ቡድን | |
| ፕሮግራም | |
| ጭብጥ | |
| ብቃት | |
| ርዕስ | |
| ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት /ጨዋታ/ በኋላ ህጻናት<br>1. ________________<br>2. ________________<br>3. ________________ | |
| የመርጃ መሳሪያዎች | |
| የማስተማሪያ ዘዴዎች | |
| የፕሮግራሙ ዝርዝር ሂደት | |

| የመምህሩ ተግባር | ጊዜ | የህጻናቱ ተግባር |
|---|---|---|
| | | |

ቀን፣ ቡድን፣ ጭብጥና ርዕስ የሚወስደው ከዕለት ዕቅድ ውስጥ ሲሆን የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅዱ /ሌሰን ፕላን/ ለየትኛው እድሜ እንደተዘጋጀ እንዲታወቅ ነው።

ብቃት፡- የሚወሰደው ከዓመት ዕቅድ ላይ ሲሆን ህጻኑ ሊደርስበት የሚገባውን የለውጥ ደረጃ የሚያመላክት ነው።

ዓላማ፡- በክፍለ ጊዜው ህጻናቱን በማሳተፍ ከተከናወነ በኋላ ህጻናት የሚያሳዩትን ለውጥ የሚያመላክት ሲሆን ዓላማዎቹ ሲነደፉ በአንድ ክፍለ ጊዜ ተግባራዊ እንደሚሆኑ ታስቦ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ከርእሱ ጋር መሄድ አለመሄዳቸው ትኩረት ሊሰጠውና ከህጻናቱ አቅም አንጻር ሊተገበሩ የሚችሉ፣ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው ሊሰሩ የሚችሉ፤ ሊመዘኑ የሚችሉ እና ተገቢና ግልጽ መሆናቸውን በማሰብ ሊዘጋጁ ይገባል። በእቅድ ላይ ሲቀመጡም በተራ ቁጥር ተለይተው ቢቀመጡና ባይበዙ ለአፈጻጸም ምቹ ይሆናሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች፡- የመርጃ መሳሪያዎች ርዕሱን ከህጻናቱ ደረጃ አንጻር በቀላሉና ህጻናቱን ሊያሳትፉ፤ ሊያዝናኑና ሊያስደስቱ በሚችሉ መልኩ ለመተግበር እንዲቻል የምንመርጣቸው ሲሆኑ እንደአካባቢያችን ሁኔታ በቀላሉ ሊገኙ ከሚችሉ ቁሳቁሶች የተዘጋጁ ቢሆኑ ይመረጣል።

የማስተማሪያ ዘዴዎች፡- ዓላማዎችን ለመተግበር የምንጠቀምባቸው ስልቶች ሲሆኑ የሚመረጡት ከህጻናት ዕድሜና ደረጃ፣ ከክፍለጊዜው ርዕስና ከአላማዎቹ አንጻር ሊሆን ይገባል። የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅድ /ሌሰን ፕላን/ ዘዴዎች ሲቀመጡ ግልጽ በሆነ መልኩ እንዴት ልንጠቀምባቸው እንደሆነ በሚጠቁም ሁኔታ ቢሆኑ ትምህርቱን ለሚያቀርበው ሰው ይጠቅማሉ።

የፕሮግራሙ ዝርዝር ሂደት፡- ፕሮግራሙ እንዴት እንደሚጀመር፣ እንዴት ዓላማዎቹ እንደሚተገበሩ፣ እንዴት ፕሮግራሙ እንደሚጠቃለልና የመምህሩንና የህጻናቱን ተግባር የሚወስደው ጊዜም በዚሁ ላይ የሚቀመጥ ይሆናል።

ህጻናት ተማሪዎች ሳይሆኑ ለተማሪነት ህይወት የሚዘጋጁ እንደሆኑ ይታወቃል። ማንኛውም ፕሮግራም የህጻናቱን የማወቅ ተግባር የሚቀስቀስ፣ መርጃ የሚያስጨብጥና ክህሎትን የሚያለማምዱ ሊሆን ይገባል። ይህንን ለመተግበር የሚያስችለው ዕቅድ በመስራት ስለሆነ ስራዉን ለማሳለጥ ለዕቅድ ከፍተኛ ቦታ ልንሰጠው ይገባል።

# ክፍል 2. የመዳበር አቅጣጫዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

## 2.1. ለተገቢው ዕድገትና የአካል ጥንካሬ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ

### 2.1.1. ማብራሪያ

የአካልና የእንቅስቃሴ መዳበር ለሁሉም የመዳበር ዘርፎች መሠረት ነው። ሕፃናት የተሟላ መዳበር ላይ እንዲደርሱ ለማገዝ የአካል ለውጦችን በእድሜው መረዳት ይገባል። 5-6 ዓመት ያለው ዕድሜ የሕፃናት አካል መዳበር ከፍተኛ ለውጥ የሚያሳይበት ነው።

በቀጣይ ለሚጠብቃቸው የመደበኛ ትምህርት ቤት የተማሪነት ሕይወት ሊለምዱ የሚገባቸው ከአካል መዳበር ጋር የተያያዙ የሰውነት ቅልጥፍናን የሚጠይቁ በርካታ ክህሎቶች አሉ። እለት በእለት በሚያከናውኗቸው ተግባራት የአይንና የእጅ ቅንጅታቸው ሊዳብር ይገባል። ይህም የትምህርት ቤት ክህሎቶችን ማለትም መሳል፣ መቀባት፣ በዱልዱም መርፌ መስፋት፣ መፃፍ ወዘተ ማከናወን እንዲችሉ ያግዛቸዋል።

የተለያዩ ክህሎቶችን የሚጠይቁ ተግባራትን በየጊዜው የማከናወን/ የመልመድ/ እድል ያገኘ ህፃን የተሳካ ውጤታማ ተግባር ማከናወኑን ሲመለከት ስለራሱ ያለው አመለካከት በራስ መተማመን ላይ የተመሠረተ ይሆናል። ስለዚህ ከ 5-6 ዓመት ያሉ ሕፃናት መድረስ የሚገባቸው የአካል መዳበር /የጉልህና የረቂቅ ጡንቻዎች መዳበር/ ላይ እንዲደርሱ ሊያከናውኑ የሚገባቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ መርዳት አስፈላጊ ነው።

### 2.1.2 አጠቃላይ ዓላማዎች

1. ራሳቸውን በመገንዘብ በራስ መተማመን እና ራሳቸውን የመግለፅ አቅምን እንዲዳብሩ ለማድረግ
2. የሰውነት ክፍሎቻቸውን በመለየት መጥራት፣ ተግባራቸውን መናገር፣ የአካል ክፍሎቻቸውን የመንከባከብ ልምድ እንዲኖራቸው ለማድረግ
3. የስሜት ህዋሳቶቻቸውን በመጠቀም ነገሮችን የመለየት እና የግል ንፅህናቸውን የመጠበቅ ሥርዓትን እንዲያውቁ ለማድረግ
4. ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎቻቸውን በመጠቀም በአካባቢ ሊገኙ ከሚችሉ ቁሳቁሶች ልዩ ልዩ መጫወቻዎችን የመሥራት አቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ

### 2.1.3 የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመን እና ራስን የማክበር ስሜት መኖር
   1.1. ራሳቸውን መግለጽ ይችላሉ
   1.2. ራሳቸውን ከሌሎች ጋር በማወዳደር መግለጽ ይችላሉ
   1.3. በጨዋታ ሂደት የሚከሰቱትን አለመግባባቶችና ግጭቶች መፍታት ይችላሉ
2. የሰውነት ክፍሎችን መለየትና ተግባራቸውን መናገር
   2.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ
   2.2. የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚያከናውኗቸውን የተለያዩ ተግባራት በትክክል መግለጽ ይችላሉ
3. ዓይኖችን መንከባከብ
   3.1. ዓይኖቻቸውን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ
4. ጆሮዎችን መንከባከብ
   4.1. ጆሮዎቻቸውን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ
5. የማሽተት ስሜት አካልን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ
   5.1. መጥፎና ጥሩ ሽታን መግለጽ ይችላሉ
6. የመቅመስ ስሜት አካልን መጠቀምና አፍን መንከባከብ
   6.1. የተለያየ ጣዕም ያላቸውን የተለያዩ ምግቦች ማጣጣምና ማድነቅ ይችላሉ
   6.2. አፋቸውን በጥንቃቄና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ
7. በመዳሰስ ነገሮችንና ሁኔታዎችን መግለጽ
   7.1. በቁሶች መካከል ያለውን የባህሪ፣ የሙቀት መጠንና ቅርጽ መለየት ይችላሉ
8. ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ሥርዓቶችን መለማመድ
   8.1. ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን ለይተው መናገር ይችላሉ
   8.2. የግል ንጽህናን መጠበቅ ይለማመዳሉ
   8.3. የራሳቸውን ንጽህና መጠበቅ ይችላሉ
9. አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ
   9.1. አካላቸውን መጠበቅና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ
10. ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎችን መጠቀም
    10.1. ትላልቅና ትናንሽ ጡንቻዎቻቸውን በመጠቀም የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ይችላሉ
11. በነፃነት ፈጠራን መግለጽ
    11.1. በአካባቢ ሊገኙ ከሚችሉ ቁሳቁሶች ልዩ ልዩ መጫወቻዎችን መሥራት ይችላሉ

2.1.4. የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመን እና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | 1.1. ራሳቸዉን መግለጽ ይችላሉ። |

ዓላማ

ተግባር አንድ ፦ ራስን በቃላት መግለጽ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ስለ ሕፃናት የሚገልፁ ስንኞችን ማዘጋጀት እና እንዲለማመዷቸው ማድረግ

ለምሣሌ፦

እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ
ሰው ሁሉ የሚወደኝ
እኔ የምወደው ጨዋታ ነው
በሸርተቴ በመሰላል በሽክርክሮሽ
መውጣት መውረድ ደስታዬ ነው

በመቀጠል መምህር ስለራስዎ በአጭሩ በመንገር ሕጻናቱን ማነቃቃት
ሕጻናትም በየተራ እየተነሱ ስለራሳቸው እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፦ ሕጻናት ራሳቸዉን በቃላት መግለጽ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሁለት፦ ራስን በስዕል መግለጽ

ዓላማ፡- ራሳቸዉን በስዕል መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- እርሳስ፣ ወረቀት/የስዕል ደብተር/፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- እርሳስ፣ ወረቀት፣ባለቀለም እርሳስ ማዘጋጀት
- ክፍለ ጊዜው ስዕል የሚሠራበት እንደሆነ መንገርና ምን ሊስሉ እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ማወያየት
- ራሳቸውን እንዲስሉ በመንገርየተዘጋጁትን ወረቀቶች /የስዕል ደብተር/፣ እርሳስ፣ባለቀለም እርሳስመስጠት
- ሲጨርሱ የሳሉትን እንዲያሳዩ በማድረግ ስዕሎቻቸውን ማድነቅ

ምዘና ፡- ራሳቸውን በስዕል መግለጽ መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር ሶስት ፡- የቁሳቁሶችን መጠሪያ መለየት

ዓላማ፡- የቁሳቁሶችን መጠሪያ መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- ተአምረኛው ከረጢት፣ የተለያዩ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በክፍላቸው ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች ምን ምን እንደሆኑ በመጠየቅ እንዲናገሩ ዕድል መስጠት
- የተለያዩ የዕለት ተዕለት መጠቀሚያ ቁሳቁሶችን ስዕል በማሣየት በስም ለይተው እንዲናገሩ ማድረግ
- በመጨረሻም ተአምረኛው ከረጢት ጨዋታን እንዲጫወቱ ማድረግ
- የተለያዩ ቁሳቁሶችን የያዘ ከረጢት ዉስጥ እጃቸውን በመከተትና በመዳሰስ ያገኙት ዕቃ ምን እንደሆነ እንዲናገሩና አውጥተውም እንዲያሳዩ በማድረግ ማጫወት

ምዘና ፡- የቁሳቁሶችን መጠሪያ መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- ተረት መተረት

ዓላማ፡- ተረት መተረት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- የተረት መጽሀፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ተረት የመተረት ክፍለ ጊዜ ማዘጋጀት
- አጭር ተረት ለሕፃናት መተረት
- እነርሱም በየተራ የሚያውቁትን ተረት እንዲተርቱ ማበረታታት
- መናገር የማይችሉ ወይም አላስፈላጊ አቅጣጫ ይዘው የሚናገሩ ሕፃናት ሲያጋጥም ተገቢውን አቅጣጫ ይዘው እንዲናገሩ መምራትና ማገዝ

ምዘና ፡- ተረት መተረት መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር አምስት ፡- የንግግር ሥርዓትን መልመድ

ዓላማ፡- የንግግር ሥርዓትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- ሲዲ /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የንግግር ሥርዓትን የሚያስተምሩ ሲዲዎችን እንዲያዳምጡ ማድረግ
- ስዕል በመሳል፣ በጨዋታ እና ሌሎችንም ተግባራት ሲተገብሩ ቁሳቁስ ከጓደኞቻቸው /ከሌላ ሰው/ የመጠየቅ ሥርዓትን፣ እባክህ/ሽ/ እና ሲመልሱ አመሰግናለሁ ማለትን እንዲለማመዱ ማስተማር
- ሲሳሳቱ /ጓደኞቻቸውን ሲያስቀይሙ/ ይቅርታ መጠየቅ እና እነርሱም ይቅርታ ማድረግን እንዲለማመዱ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- የንግግር ሥርዓትን በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው እንዲተገብሩ ቀጣይ በሆነ መልኩ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። |

ምዘና ፡- ዕለት በዕለት እንቅስቃሴያቸው የንግግር ሥርዓትን መለማመዳቸውን መከታተል።



ተግባር ስድስት ፡- አካባቢን መግለጽ

ዓላማ፡- አካባቢያቸውን መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ አካባቢያዊ የሆኑ ነገሮችን የሚያሳዩ ሥዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ስለቤታቸው፣ ስለአፀደ ሕፃናታቸው፣ ስለጓደኞቻቸው እና ስለአካባቢያቸው በተለያየ ጊዜ ለየርዕሱ መነሻ የሚሆኑ ስዕሎችን በማሣየት እንዲናገሩማበረታታት

  ለምሣሌ፡- የቤት ስዕል ከነገቢው በመነሻነት በማሣየት ስለራሳቸው ቤት እንዲናገሩ ማድረግ

- እናንተስ ቤታችሁ ምን ይመስላል?እስቲ ስለቤታችሁ ተናገሩ በማለት እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- አካባቢያቸውን መግለጽ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሰባት ፡- ውሳኔ የመስጠት ክህሎትን ማዳበር

ዓላማ፡- ውሳኔ የመስጠት ክህሎትን ማዳበር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የእንቅስቃሴያዊ ጨዋታ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በነፃ ጨዋታ ጊዜ ምን መጫወት ትፈልጋላችሁ?፣ ከነማን ጋር ነው ለመጫወት የምትፈልጉት? በማለት መጠየቅ
- በመጫወቻ ምርጫ የቱ ኳስ ይሻላል? በጨርቁ ኳስ ነው በላስቲኩ በየትኛው ብትጫወቱ ይሻላል? ወዘተ... የመሳሰሉትን በመጠየቅ ውሳኔ መስጠትን ማለማመድ
- በተለያዩ አጋጣሚዎች በትምህርት ክፍለጊዜዎች ውሣኔ በመስጠት ሂደት የሚሳተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት

ምዘና ፡- ውሳኔ የመስጠት ክህሎት ማዳበር መለማመዳቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመን እና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | 1.2. ራሳቸውን ከሌሎች ጋር በማወዳደር መግለጽ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ስለልደት ቀን አከባበር መናገር

ዓላማ፡- ስለ ልደት ቀን አከባበር መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- ክላሰር፣ ኮላ፣ ባለቀለም ወረቀቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የልደት በዓል በሚከበርበት ጊዜ ዛሬ የማን ልደት ነው? የእናንተስ መቼ ነው የሚከበረው? በማለት መጠየቅ
- የራሳቸውን የልደት ቀን መቼ እንደሆነ እንዲናገሩ ማበረታታት
- ልደታቸው እንዴት እንደሚከበርላቸው በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግ
- ክላሰር በትናንሽ ካርድ መጠን ቆርጦ ማዘጋጀት
- ኮላ እና ባለቀለም ወረቀቶች በመጠቀም የልደት መጥሪያ ካርዶችን እና የመልካም ልደት መግለጫ ካርዶችን እንዴት እንደሚዘጋጁ ማሣየት
- አስፈላጊውን ቁሳቁስ በማደል ካርዶቹን እንዲያዘጋጁ መርዳት

> ማስታወሻ ፡- ይህን ይዘት በአንድ ቀን ማጠናቀቅ ስለማይቻል በተከታታይ ክፍለ ጊዜያት ሊተገበር ይገባል።

ምዘና ፡- ስለ ልደት አከባበር መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- ራስን ከሌሎች ጋር በማወዳደር መግለጽ

ዓላማ፡- ራሳቸውን ከሌሎች ጋር በማወዳደር መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መስታወት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መስታወት እንዲመለከቱ እና እርስ በእርሳቸው እንዲተያዩ ማድረግ
- ራሳቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር በማወዳደር እንዲናገሩ ማድረግ
- መናገር ከተቸገሩ ፍንጭ በመስጠት አንቺ ረዥምነሽ እሷስ? ወዘተ... በማለት እንዲያወዳድሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ራሳቸውን ከሌሎች ጋር በማወዳደር መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመን እና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | 1.3. በጨዋታ ሂደት የሚከሰቱትን አለመግባባቶችና ግጭቶች መፍታት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የቡድን ጨዋታ መጫወት

ዓላማ፡- የቡድን ጨዋታዎችን መጫወት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በግቢ ውስጥ እና ከግቢ ውጭ ያሉ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከክፍል ውጪ ህጻናቱን በሁለት ቡድን መመደብ
- የአካል ብቃታቸውን በማየት እና በማመጣጠን የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች ላይ ሁሉም ህጻናት እንዲሳተፉ ማድረግ

ለምሳሌ፡- "ዱላ ቅብብሎሽ"፣ "የመሀረብ ንጥቂያ"፣ "ጭራ ነቀላ"፣ ወዘተ…

- ለቡድን ውጤት በጋራ መስራትን፣ መተባበርን፣ መተሳሰብን ወዘተ… ለቡድን አባላት ድጋፍ /ሞራል/ መስጠትን እና ማበረታታትን እንዲያዳብሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የቡድን ጨዋታዎችን መጫወት መቻላቸውን መገምገም።

**ተግባር ሁለት ፡- በህብረት መዘመር**

ዓላማ፡- በህብረት መዘመር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በግቢ ውስጥ እና ከግቢ ውጭ ያሉ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በክፍል ውስጥ በቡድን በመመደብ እያንዳንዱ ቡድን የሚፈልገውን መዝሙር እንዲመርጥ ማድረግ
- መርጠው ሲጨርሱም የቡድኑ ተወካይ ለመምህር ቀስ ብሎ እንዲናገር ማድረግ /አንዴ ከመረጡ መለወጥ አይቻልም/
- በየተራ እያንዳንዱ ቡድን ከክፍል ጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው በመቆም የቡድኑ ተወካይ 1፣ 2፣ 3 ብሎ ሲቆጥር በተገቢው መንገድ እንዲዘምሩ ማድረግ
- የትኛው መዝሙር ጥሩ እንደተዘመረ ከህጻናቱ ጋር አብሮ መገምገም
- በዚህ ሁኔታ በህብረት መምረጥ፣ መዘመር እና የራሳቸውን ስራ መገምገም እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- በህብረት መዘመር መቻላቸዉን መከታተል፡፡

ዓላማ፡- በህብረት መሥራት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በሕብረት የሚሰሩ ልጆች/ሰዎች/ የሚያሳይ ፎቶግራፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በሕብረት የሚሰሩ ልጆች/ሰዎች/ የሚያሳይ ፎቶግራፍን በሕጻናቱ ፊት ለፊት መስቀል
- ስለ ስዕሉ/ፎቶግራፉ/ ሕጻናቱ እንዲወያዩ ማድረግ
- በመቀጠል ህጻናትን በየቡድን በመመደብ የተለያየ የስራ ድርሻ መስጠት

  ለምሳሌ፡- የግቢ ጽዳት፣ የክፍል ጽዳት፣ ወዘተ…
- የቡድን ሥራውን ሲያከናውኑ እየተዘዋወሩ ማየት
- በህብረት የመስራት ጠቃሚነትን እና ውጤት ላይ ለመድረስ እንዴት እንደሚረዳ እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- በህብረት መስራት መለማመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- የስራ ድርሻን መወጣት

ተግባር ሁለት ፡- በህብረት መዘመር

ዓላማ ፡- የስራ ድርሻን መወጣት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በሕብረት የሚሰሩ ልጆች/ሰዎች/ የሚያሳይ ፎቶግራፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህጻናት በቤት ውስጥ ከማን ጋር እንደሚኖሩ መጠየቅ
- በቤታቸው አብረዋቸው የሚኖሩትን ሰዎች በስራ ያግዙ እንደሆነና በምን ዓይነት ስራ ላይ ያግዟቸው እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- ህጻናት የተጫወቱበትን መጫወቻ መሰብሰብ፣ በቤት ውስጥ መታዘዝ፣ ወላጆቻቸው ስራ ሲይዙ ታናናሾቻቸውን ማጫወት፣ ወዘተ… እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ
- አዋቂዎች መልዕክት ሲልኳቸው በጥሞና ማዳመጥ እንዳለባቸው፣ መላክ እንዳለባቸው እና ሲታዘዙ እምቢ ማለት እንደሌለባቸው የተለያዩ ገጠመኞችን እና ተረቶችን በመንገር እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የስራ ድርሻን መወጣት መለማመዳቸውን መገምገም።

ተግባር አምስት ፡- ሌሎችን መርዳት

ዓላማ ፦ ሌሎችን መርዳት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ሰዎች እየተረዳዱ ስራ ሲሰሩ የሚያሳይ ፎቶግራፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የመማሪያ፣ የመመገቢያ እና የመኝታ ክፍልን በማሰናዳት ሂደት ላይ ህጻናት አብረው ከመምህራን ጋር በመተባበር እንዲሰሩ በማድረግ ሌሎችን የመርዳት ክህሎትን እንዲያዳብሩ ማድረግ
- በተጨማሪም በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት በተለያየ አጋጣሚ የተለያዩ መልዕክቶችን ለወላጅ በማድረስ መምህራንን እንዲረዷቸው ማድረግ

ምዘና ፦ ሌሎችን መርዳት መለማመድ መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ስድስት ፦ በህብረት መጫወት

ዓላማ ፦ በህብረት መጫወት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በግቢ ውስጥ እና ከግቢ ውጪ ያሉ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በግቢ ውስጥ ያሉት መጫወቻዎች የማን እንደሆኑ፣ ምን ምን ዓይነት መጫወቻዎች እንደሆኑ፣ ብዛታቸው ምን ያህል እንደሆነ ወዘተ... በመጠየቅ ማወያየት
- በተጨማሪም ህጻናት በግቢያቸው ውስጥ ባሉት መጫወቻዎች እንዴት መጫወት እንዳለባቸውና በይበልጥ በየትኛው መጫወቻ መጫወት እንደሚወዱ ማወያየት
- በግቢ ውስጥ ያሉት መጫወቻዎች የሁሉም ህጻናት እንደሆኑና ተራን ጠብቀው በስርዓት መጫወት እንዳለባቸው ማስገንዘብ
- በስርዓት መጫወት ካልቻሉ በቅድሚያ የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት በዚያ ካልታረሙ ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ በመጫወቻው ላይ እንዳይጫወቱ በማገድ ስርዓትን እንዲማሩ ማድረግ

ምዘና ፦ በህብረት መጫወት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ሰባት ፦ የዉድድር ጨዋታዎችን መጫወት

ዓላማ ፡- የዉድድር ጨዋታዎችን መጫወት ይችላሉ::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የግቢና የክፍል ውስጥ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በግቢ ውስጥ ልዩ ልዩ የውድድር እንቅስቃሴያዊ ጨዋታዎችን በቡድን ከፋፍሎ ማጫወት
- የውድድር እንቅስቃሴያዊ ጨዋታዎችን ከተጫወቱ በኋላ በውድድሩ አሸናፊ ከሆነዉ ቡድን ጋር አብረው እንዲዘምሩ እና እንዲጨፍሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸትእና ማበረታታት ለምሳሌ፡- ሩጫ፣ እግር ኳስ ፣ዱላ ቅብብሎሽ፣ወዘተ...
- ከተሸነፉ በሚሸነፉበት ወቅት መሸነፋቸውን በጸጋ መቀበል እንዳለባቸው እና እነርሱም ሌላ ጊዜ ማሸነፍ እንደሚችሉ ማሳወቅ

ምዘና ፡- የውድድር ጨዋታዎችን መጫወት መቻላቸውም መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. የሰውነት ክፍሎችን መለየትና ተግባራቸውን መናገር | 2.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የአካል ክፍሎችን የማዛመድ ጨዋታን መጫወት

ዓላማ ፡- የዉድድር ጨዋታዎችን መጫወት ይችላሉ::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎች ማዛመጃ ሰሌዳ/ሎቶ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የሰውነት ክፍሎች ማዛመጃ ሰሌዳ ለሕጻናቱ በየጠረጴዛቸው ማደል
- የማዛመድ ጨዋታን እንዲጫወቱ ማድረግ
- ሕጻናት ሲጫወቱ እየተዘዋወሩ ማየት
- ምን ምን የሰውነት ክፍሎችን እንዳዛመዱ በመጠየቅ እንዲናገሩ እድሉን መስጠት



ምዘና ፡- የአካል ክፍሎችን የማዛመድ ጨዋታ መጫወት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- የሰውነት ክፍሎችን ከተግባራቸዉ ጋር ማዛመድ

ዓላማ ፦ የሰውነት ክፍሎችን ከተግባራቸዉ ጋር ማዛመድ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የሰውነት ክፍሎቻቸውን እየተጠቀሙ /እያንቀሳቀሱ/ መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ

  ለምሣሌ፦

  በእጆቼ አጨበጭባለሁ /ቾብ፣ ቾብ/

  በእግሮቼ  እዘላለሁ /ዝልል፣ ዝልል/

  በዓይኖቼ አያለሁ /በሩቅ ዓይንን ከልሎ ማየትን ማስመሰል/

  በአንገቴ እጅ እነሳለሁ /እጅ መንሳት/

  በአፍንጫዬ አሸታለሁ /እንደማሽተት አየር መሳብ/

- መዝሙሩን የአካል ክፍሎቻቸውን በትክክል እየተጠቀሙ/እያንቀሳቀሱ/እንዲዘምሩ ማድረግ

ምዘና ፦ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ከተግባራቸዉ ጋር ማዛመድ መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ የሰውነት ክፍሎችን መገኛ አቅጣጫ መናገር

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን መገኛ አቅጣጫ መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ ስዕል በሚታይ ቦታ በመስቀል ሕጻናት ስዕሉ ላይበመጠቆም የሰውነት ክፍሉንስያሜ እንዲናገሩ ማድረግ
- ሕጻናት የሰውነት ክፍሎቻቸውን እያሳዩ ስያሜቸውንና የሚገኙበትን አቅጣጫ እንዲናገሩ ማድረግ

  ለምሳሌ፡-ግራ፣ ቀኝ፣ፊት፣ ኋላ፣ ወዘተ...

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎች መገኛ አቅጣጫን መናገር መቻላቸዉን መገምገም።



ተግባር አራት ፡- የሰውነት ክፍሎችን መገኛ ቦታ መለየት


ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን መገኛ ቦታ መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጐደለ ክፍል ያለው የሰው ምስል፣ የሰውነት ክፍሎች ሎቶ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የጐደለ ክፍል ያለው የሰው ምስል ፊት ለፊታቸው በመስቀል ማሣየት
- የጐደለው ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ

- ከቀረቡት የጐደሉ ክፍሎች መሙያ መካከል የሚሞላውን አንስተው በቦታው እንዲያደርጉ ማድረግ



ማስታወሻ፡- ይህንን ተግባር ፐዝል በመጠቀም ማከናወን ይቻላል።

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎቻቸውን መገኛ ቦታ መለየታቸዉን ማረጋገጥ።



ተግባር አምስት ፡- የሰውነት ክፍሎችን ስዕል ነጠብጣብን በመገጣጠም መሳል

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን ስዕል ነጠብጣብን በመገጣጠም መሳል ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በነጠብጣብ የተሳለ የሰው ምስል፣ እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በነጠብጣብ የተሳለ የሰው የሰውነት ክፍሎችን የሚያሣይ ስዕል ለሕጻናቱ መስጠት
- ነጠብጣቡን አገናኝተው እንዲስሉ ማድረግ

  ለምሳሌ፡-



- ሲስሉ እየተዘዋወሩ ማየት

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎችን ስዕል ነጠብጣብን በመገጣጠም መሳላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- የሰውነት ክፍሎችን ቅርጽ /ሞዴል/መስራት

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን ቅርጽ /ሞዴል/መስራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቦካ ወረቀት /ጭቃ/፣ የሰውነት ክፍል ሥዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የሰው ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎችን በመጠየቅ እንዲያስታውሱ ማድረግ
- የተቦካ ወረቀት /ጭቃ/ በመጠቀም የሰው ምስል እንዴት መሥራት እንደሚቻል በቅደም ተከተል ማሣየት
- ባዩት መሠረት እንዲሠሩ ጭቃ ወይም የተቦካ ወረቀት ለእያንዳንዳቸው መጥኖ መስጠት
- ቅርጾቹን ሲሰሩ እየዞሩ አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ
- የሠሩት እንዲደርቅ የሚያስቀምጡበትን ቦታ ማመቻቸትና እንዲያስቀምጡ /እንዲደረድሩ/ ማድረግ
- የሠሩትን እየተዘዋወሩ በማየት ማድነቅ
- እነሱም በእጃቸው ሳይነኩ ከመምህር ጋር እንዲመለከቱ እና እንዲያደንቁ ማበረታታት

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎች ቅርጽ/ሞዴል/ መስራት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሰባት ፡- የሰውነት ክፍሎችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማዛመድ

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎቻቸውን ከእንቅስቃሴዎች ጋር ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎች ሎቶ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከአካል ከእንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ መዝሙሮችን ማዘመር
- ስለ ሰውነት ክፍሎች ግጥምን ከሎቶዎች ጋር በማዛመድ ማሰማትና እንዲያዳምጡ ማድረግ
- የሰሙትን ግጥም መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ

ለምሣሌ፡- ሙሉ ነኝንበእንቅስቃሴ ማለማመድ

እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ ትንሽ ልጅ ነኝ
ትንንሽ የአካል ክፍሎች አሉኝ
መሬመጃ ትንንሽ እግሮች አሉኝ
እኔ ትንሽ ልጅ ትንሽ ነኝ ትንሽ ልጅ ነኝ
መጫወቻ ትንንሽ እጆች አሉኝ
እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ ትንሽ ልጅ ነኝ
የማይባቸው ዓይኖች አሉኝ
እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ ትንሽ ልጅ ነኝ
የምሰማበት ትንንሽ ጆሮዎች አሉኝ
እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ ትንሽ ልጅ ነኝ

- ትልቁ ጐማ፣ ትንሹ ጐማ የሚባለውን እንቅስቃሴያዊ ጨዋታ ማጫወት

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎቻቸውን ከእንቅስቃሴዎች ጋር ማዛመድ መቻላቸዉን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. የሰውነት ክፍሎችን መለየትና | 2.2.የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚያከናውኗቸውን |

| | |
|---|---|
| ተግባራቸውን መናገር | የተለያዩ ተግባራት በትክክል መግለጽ ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ ፡- የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መናገር**

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎትን ተግባራት መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን ማዛመጃ /ሎቶ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናት በየተራ ከጓደኞቻቸው ፊት እየወጡ የአካል ክፍሎቻቸውን በማሣየት ተግባራቸውን እንዲናገሩ ማበረታታት

  ለምሣሌ ፡-ዓይን፡-ማየት፣ እንባ ማዉጣት፤ አፍንጫ፡- ማሽተት፣ ጉንፋን ሲይዘን ፈሳሽ ማዉጣት፤ ወዘተ...
- “እኔ ትንሽልጅ ነኝ” የሚባለውን ግጥም እንዲናገሩና በግጥሙ ያለውን እንቅስቃሴ ከግጥሙ ጋር እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ሁለት ፡- የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ጋር ማዛመድ**

ዓላማ ፡- የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ጋር ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን ማዛመጃ ሰሌዳ /ሎቶ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ማዛመጃ ሰሌዳ/ሎቶ/በመጠቀም ከሚሰጡት ተግባራት ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ
- ሰሌዳ ላይ የሰውነት ክፍሎችንና ተግባራቸውን በመጻፍ እንዲያዛምዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ጋር ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- በጨዋታ የሰውነት ክፍሎችን መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የእንቆቅልሽ መጽሀፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በአካል ክፍሎች እንቆቅልሽን ማጫወት

  ለምሳሌ፡- እንቆቅልህ/ሽ

## ተግባር ሶስት ፡- በጨዋታ የሰውነት ክፍሎችን መግለጽ

ዞሮ ዞሮ መግቢያው ጭራሮ

መልስ…ዓይን ወዘተ…

ምዘና ፡- በጨዋታ የሰውነት ክፍሎችን መግለጽ መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አራት ፦ በጨዋታ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መግለጽ

ዓላማ ፦ በጨዋታ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወንበር፣ ማራካሽ /ከበሮ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- አያ ጅቦ፣ አረንጓዴ አረንጓዴ፣ የወንበር ሽሚያ እና የመሳሰሉትን እንቅስቃሴአዊ ጨዋታዎች ማጫወት
- ከጨዋታዉ በኋላ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው ያከናወኗቸውን የተለያዩ ተግባራት እንዲናገሩ ማድረግ

ለምሳሌ፦ በእግር መሮጥ፣ በእጅ ማጨብጨብ ወዘተ...

ምዘና ፦ በጨዋታ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ተግባራት መግለጽ መቻላቸዉን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. ዓይኖችን መንከባከብ | 3.1. ዓይኖቻቸውን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ የአይንን ጥቅም መናገር`

ዓላማ ፡- የአይንን ጥቅም መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጎላ ብሎ የተሳለ የአይን ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ዓይናቸው ለምን እንደሚጠቅማቸው በመጠየቅ ማወያየት
- ጐላ ብለው የተሳሉ ሁለት ተመሣሣይ ስዕሎችን በማሣየት በስዕሎቹ መካከል ያለውን ልዩነት እንዲናገሩ ማድረግ
- ልዩነቱን እንዴት ሊያውቁ እንደቻሉ እና በየትኛው የአካል ክፍላቸው ተጠቅመው እንዳወቁ መጠየቅ
- በክፍላቸው ውስጥ የሚያዩትን ነገር እንዲናገሩ ማድረግ
- በመቀጠልም በሁለት እጃቸው አይናቸውን እንዲሸፍኑ ማድረግ እና የሚታያቸው ነገር ካለ እንዲናገሩ ማድረግ
- በዓይናችን ምን እናደርጋለን ብሎ በመጠየቅ በዓይን እናያለን፣ ለሰዎች መደነቃችንን እንገልፅበታለን፣ ስናዝን እናለቅስበታለን ወዘተ... እያሉ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የአይንን ጥቅም መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር ሁለት ፡- ለአይን ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄን መረዳት

ዓላማ ፦ ለአይን ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ይረዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ኀላ ብሎ የተሳለ የአይን ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ዓይናቸው ከታመመና በጣም ከተጐዳ ማየት እንደማይችሉ እንዲረዱ የተለያዩ ገጠመኞችን መንገር
- ዓይናቸውን በንጽህና መያዝ፣ በቆሻሻ እጃቸው አለመንካት፣ ምንም ነገር አይናቸው ውስጥ መክተት እንደሌለባቸውና ዝንቦችና ትንኞች እንዳያርፉባቸው መከላከል እንዳለባቸው ማስገንዘብ
- በተጨማሪም አረንጓዴ ተክሎች /ጐመን፣ ቆስጣ፣ ሰላጣ እንዲሁም ካሮት/ለአይን ጠቃሚ መሆናቸዉን እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፦ ለአይን ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ ማየት ስለተሳናቸው ሰዎች መገንዘብ

ዓላማ ፡- ማየት ስለተሳናቸው ሰዎች መገንዘብ ይችላሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጎላ ብሎ የተሳለ የአይን ስዕል፣ ብሬል/የብሬልስዕል/፣ ማየት የተሣናቸው ሰዎች ለመንቀሳቀስ የሚጠቀሙበት ከዘራ /ስዕል/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በአካባቢያቸው ማየት የተሳናቸው ሰዎችን አይተው ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- ማየት የተሣናቸው ሰዎች ለመንቀሳቀስ የሚጠቀሙበት የራሳቸው ከዘራ እንዳላቸው መንገር
- በተጨማሪም የሚጽፉበት እና የሚያነቡበት ብሬል የተባለ መሣሪያ እንደሆነ ማሳወቅ

ማስታወሻ ፡- ከተቻለ መሣሪያዎቹን አምጥቶ ማሣየት ጥሩ ይሆናል።

ምዘና ፡- ማየት ስለተሳናቸው ሰዎች መገንዘብ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4. ጆሮዎችን መንከባከብ | 4.1. ጆሮዎችን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የጆሮን ጥቅም መናገር

ዓላማ ፦ የጆሮን ጥቅም መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መጽሐፍ፣ የሰው ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ጆሮዎቻቸዉን እንዲያሳዩ እና በጣቶቻቸው ደፍነው ምን እንደሰሙ እንዲናገሩ ማድረግ
- የአካባቢውን ነፋስ ሽውታ፣ የመኪና ድምጽ፣ ሰዎች ሲነጋገሩ፣ መምህር ጥያቄ ሲጠይቁ፣ ሲያስረዱ፣ ተረት ሲተርቱ ወዘተ... የምናዳምጠው በጆሮአችን ነው በማለት የጆሮን ጥቅም ማስረዳት
- መስማት የተሳናቸው ሰዎች ከሌሎች ጋር እንዴት ሊግባቡ እንደሚችሉ መጠየቅና ማወያየት

ምዘና ፦ የጆሮን ጥቅም መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ ለጆሮ ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ መረዳት

ዓላማ ፡- ለጆሮ ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ዶቃ፣ ስንጥር፣ እንጨት፣ ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጆሮአቸውን አሟቸው ያውቅ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- ጆሮአቸዉን በጥንቃቄ ካለመያዝ የተነሳ ሊታመሙ እንደሚችሉ ማስረዳት
- ጆሮ ውስጥ እስኪሪብቶ፣ ዶቃ፣ እንጨት፣ ወዘተ… መጨመር እንደማይገባ ማስረዳት
- በአሸዋም ሆነ በውሃ ሲጫወቱ ጆሮአቸው ውስጥ እንዳይገባ መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ ማስገንዘብ
- አዋቂ ሰዎች ጆሮአቸውን ሲያፀዱ ቢመለከቱም እነርሱ ግን ወላጆቻቸው እንዲያፀዱላቸው መጠየቅ እንጂ በራሳቸው ጆሮአቸው ውስጥ ምንም መጨመር እንደማይገባቸው ማስረዳት

ምዘና ፡- ለጆሮ ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ መረዳታቸውን መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- የጆሮን ስዕል መሳል

ዓላማ ፡- የጆሮን ስዕል መሳል ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተሳለ የሰው ስዕል ከፊት ለፊታቸው በማስቀመጥ እንዴት እንደሚሳል በተግባር ማሳየት
- ሲስሉ ጆሮን አካተው እንዲስሉ ማስታወስ
- የሳሉትን ስዕል ቀለም /ከለር/ እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱ እያዩ በማድነቅ በቀጣዩ ጊዜ ሲሰሩ የተሻለ እንዲሠሩ ጥቂት ማረሚያዎችን መስጠት

ምዘና ፡- የጆሮ ስዕል መሳል መለማመዳቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 5. የማሽተት ስሜት ሕዋስን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ | 5.1. መጥፎና ጥሩ ሽታን መግለጽ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- መጥፎና ጥሩ ሽታን መለየት

ዓላማ ፡- መጥፎና ጥሩ ሽታን መለየት ይችላሉ::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የባህር ዛፍ ቅጠል፣ ጤናአዳም፣ ዳማከሴ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ሎሚ፣ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች፣ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በክፍል ውስጥ ለጋ ሽታ ያለዉ ነገር (ባህር ዛፍ፣ ዳማከሴ፣ወዘተ...) በማሽት በማይታይ አፉ ክፍት ዕቃ ውስጥ ማስቀመጥና የሕፃናቱን ሁኔታ መከታተል
- ሕፃናቱ ጥያቄ ካልጠየቁ መምህር ክፍላቸው ምን ምን እንደሚሸት መጠየቅ
- በየትኛው የአካል ክፍላቸው ተጠቅመው ሽታን መለየት እንደቻሉ መጠየቅ
- በአካባቢያቸው ካሉ ነገሮች ምን ምን ነገሮች ደስ የሚል ሽታ እንዳላቸውና የትኞቹ ደግሞ ደስ የማይል ሽታ እንዳላቸው በመጠየቅ ጥሩና መጥፎ ብለው ስለሚያስቡት ሽታ እንዲናገሩ መጠየቅና ማወያየት

  ለምሳሌ፡- የዶሮ ወጥ ሽታ፣ የመፀዳጃ ቤት ሽታ፣ የኬክ ሽታ ወዘተ...

ምዘና ፡- መጥፎና ጥሩ ሽታን መለየት መቻላቸውን መገምገም።



ተግባር ሁለት ፡- የተለያዩ ነገሮችን በሽታ መለየት

ዓላማ ፡- የተለያዩ ነገሮችን በሽታ መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጤና አዳም፣ ዳማከሴ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ሎሚ፣ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች፣ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያየ ሽታ ያላቸውን ቀደም ሲል የሚያውቋቸውን ተክሎችእንዲያሸቱ ማድረግ
  ለምሣሌ፡- ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ጤና አዳም፣ ዳማከሴ፣ ወዘተ…
- ምን እንደሆኑና ምን ዓይነት ሽታ እንዳላቸው ደስ ይላል ወይም ደስ አይልም ብለው እንዲናገሩ ማድረግ
- የተክሎችን ስዕል በማሣየት ስለሽታቸዉ እንዲናገሩ ማድረግ
- ሽታ መለያ ጆግን በመጠቀም የተለያየ ሽታ ያላቸውን እጽዋቶች በመጠቀም ሕፃናት በአይናቸው ሳያዩ ጆጉ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ምንነት በማሽተት ብቻ እንዲናገሩ ማድረግ
  ‹‹አሸተህ ዕወቅ›› ጨዋታን በማጫወት እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የተለያዩ ነገሮችን በሽታ መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- አፍንጫን ማጽዳት

ዓላማ ፡- አፍንጫን ማጽዳት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቀማ ፡- ሶፍት/መሃረብ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- አፍንጫቸውን ዘወትር እንዴት ማጽዳት እንዳለባቸው በመጠየቅ ማወያየት
- አፍንጫን በመፀዳጃ ቤት ወረቀት ወይም በመሀረብ ማጽዳት እንደሚገባ ማስረዳት
- ጉንፋን ሲይዛቸው አፍንጫቸው ላይ የሚታየውን ለውጥ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲረዱ ማድረግ
- ጉንፋን ሲይዛቸው እንዴት አፍንጫቸውን ማጽዳት እንዳለባቸው ማወያየት
- በመፀዳጃ ቤት ወረቀት ካፀዱ በኋላ በየቦታው መጣል እንደሌለባቸው የቆሻሻ ቅርጫት /ካርቶን/ ውስጥ ብቻ መጣል እንዳለባቸው ማስገንዘብ
- መሐረብንም በየዕለቱ ማጡብና ማድረቅ እንደሚያስፈልግ መንገር
- በተግባር እንዲያፀዱ ማለማመድ

ምዘና ፡- አፍንጫን ማጽዳት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- አፍንጫን መንከባከብ

**ዓላማ ፡-** አፍንጫን መንከባከብን ይለማመዳሉ።

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡-** የአፍንጫ ስዕል፣ የሹል ነገሮች ስዕል፣ጥራጥሬ፣ ዶቃዎች ወዘተ**…**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- አፍንጫችን በተለያዩ በሽታ አምጪ ሕዋሳት ሲበከል /ሲጐዳ/ ማሽተት እንደማይችል መንገር
- በአፍንጫ ውስጥ ሹል ነገሮችን፣ ዶቃ፣ እስክሪብቶ እና የመሣሠሉትን መክተት እንደማይገባ ማስገንዘብ

ምዘና ፡- አፍንጫቸውን መንከባከብ መለማመድ መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ ጉንፋን ሲይዝ ስለሚደረግ ጥንቃቄ ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የመፀዳጃ ቤት ወረቀት/ሶፍት/፣ መሀረብ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ሰዎች ጉንፋን ሲይዛቸው እንዴት እንደሚያስላቸው በመጠየቅ ማወያየት
- ሲያስላቸው ግን ከሰዎች ዞር ብለው አፋቸውን በእጃቸው ሸፍነው መሳል እንዳለባቸው መንገር
- አፋቸውን ሸፍነው ካልሳሉ ግን በትንፋሽ ውስጥያሉት በሽታ አምጪ ተህዋሲያን ወደሌላ ሰው እንደሚተላለፉ ማስረዳት
- ሕጻናት እንዴት መሣል እንዳለባቸው በተግባር ማሣየትና እንዲለማመዱ ማድረግ
- በተጨማሪም ሕፃናት ጉንፋን ሲይዛቸው አክታ ሊኖራቸው ስለሚችል አክታቸውን በሶፍት አድርገው ቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል እንዳለባቸውና በቤት ውስጥ፣ በክፍል ውስጥም ሆነ በመጫወቻ ቦታ ላይ ዝም ብለው መትፋት እንደሌለባቸው ማስገንዘብ

ምዘና ፦ ጉንፋን ሲይዝ ስለሚደረግ ጥንቃቄ መረዳታቸውን መገምገም::

ተግባር ስድስት ፡- የአፍንጫ ቅርጽ /ሞዴል/ መስራት

ዓላማ ፡- የአፍንጫ ቅርጽ /ሞዴል /ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቦካ ወረቀት ወይም ጭቃ፣ የተሰራ የአፍንጫ ቅርጽ/ሞዴል/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተሰራ የአፍንጫ ቅርጽን/ሞዴልን/ ፊት ለፊት ለሁሉም ሕጻናት በሚታይበት ቦታ ማስቀመጥ
- ከተቦካ ወረቀት ወይም ከጭቃ ያዩትን የአፍንጫ ቅርጽ/ሞዴል/ እንዴት እንደሚሠሩ ማሣየት
- ለእያንዳንዳቸው የተቦካ ወረቀት ወይም ጭቃ በማደል እንዲሠሩ ማድረግ እና መከታተል
- በመጨረሻም የሰሩትን የአፍንጫ ቅርጽ/ሞዴል/ማድነቅ

ምዘና ፡- የአፍንጫ ቅርጽ /ሞዴል/መስራት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ሰባት ፡- የሰውነት ክፍሎች ፐዝል ማጫወት

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎች ፐዝል መጫወት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎች ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የሰው ሰውነት ክፍሎች ፐዝልን ለህፃናቱ በየጠረጴዛቸው ማደል
- እየገጣጠሙ እንዲጫወቱ ማድረግ
- ፐዝል ሲገጣጥሙ የአፍንጫንቅርጽ በትክክለኛ መገኛ ቦታዉመግጠማቸዉን ማረጋገጥ

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎች ፐዝል መጫወት መቻላቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6. የመቅመስ ስሜት አካልን መጠቀምና አፍን መንከባከብ | 6.1 . የተለየዩ ጣዕም ያላቸውን የተለያዩ ምግቦች ማጣጣምና ማድነቅ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- በአፍ ውስጥ ያሉ የአካል ክፍሎችን መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎች ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጐላ ብሎ የተሳለ የአፍ ስዕል በማሣየት በውስጡ ምን ምን አካሎች እንዳሉት በመጠየቅ ማወየየት
- በአፍ ውስጥ ያሉትን አካሎች በተራ እንዲያሳዩ ማድረግ
- በአፋቸው ምን ምን ተግባራት እንደሚከናወኑ በመጠየቅ ማወያየት
- በመቀጠልም ሕጻናትን የሚከተለውን መዝሙር ማዘመር

ትንሿ አፌ የት ነው ያለሽው?
እዚህ ነኝ እዚህ ነኝ እንደምንናችሁ
ትናንሽ ጥርሶቼ የት ነው ያላችሁት
እዚህ ነን እዚህ ነን እንደምናችሁ
ቀዩ ምላሴ የት ነው ያለኸው?
እዚህ ነኝ እዚህ ነኝ እንደምናችሁ
ትናንሽ ከንፈሮቼ የት ነው ያላችሁት?
እዚህ ነን እዚህ ነን እንደምናችሁ

- በመጨረሻም በጨዋታ በአፍ ውስጥ የሚገኙ አካላትን እንዲገልጹ ማድረግ

እንቆቅልሽ/ሀ
ምን አውቅልህ /ሽ/
እኔ በማንኛውም ሰው አፍ ውስጥ እገኛለሁ ቀለሜ ቀይ ሲሆን ሁልጊዜ እርጥብ ነኝ
እኔ ማነኝ? በማለት በመጠየቅ ምላስ በአፍ ውስጥ መገኘቱን፣ ቀይ መሆኑንና ሁልጊዜ እርጥብ መሆኑን በማየትና በመንካት እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- በአፍ ውስጥ ስላሉ የአካል ክፍሎችመናገር/መግለጽ/ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡-ስለ ተለያዩ ጣዕሞች መናገር

ዓላማ ፡- ስለ ተለያዩ ጣዕሞች መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ ጣዕም ያላቸውና ሊበሉ የሚችሉ ምግቦች (ስኳር፣ ማር፣ ጨና አዳም፣ ዳማከሴ፣ ሎሚ፣ ኮሽም፣ ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ስለተለያዩ ምግቦች ጣዕም የሚገልጹ ተረቶችን፣ ታሪኮችን፣ ስንኞችን፣ ግጥሞችን በመንገር እና መዝሙሮችን በማዘመር ስለተለያዩ ጣዕሞች እንዲረዱና እንዲናገሩማድረግ

ለምሣሌ፡-ስኳር ይጣፍጣል ቃሙኝ ቃሙኝ ይላል

ማርም ይጣፍጣልላሱኝ ላሱኝ ይላል

ሎሚ ይኮመጥጣል አፍን ምራቅ ይሞላል

- "ቀምሰህ ዕወቅ" የሚለውን ጨዋታ በማጫወት ማጠናከር

ምዘና ፡- ስለ ተለያዩ ጣዕሞች መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሦስት ፡- የምግብ ጣዕሞችን በመቅመስ መለየት

ዓላማ ፡- የምግብ ጣዕሞችን በመቅመስ መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ ጣዕም ያላቸውና ሊበሉ የሚችሉ ምግቦች

ለምሳሌ፡-ስኳር፣ ማር፣ ሎሚ፣ ኮሽም፣ ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያየ ጣዕም ያላቸውን ምግቦች በማቅረብ ለሕፃናቱ ማሣየት
- በመቀጠል ምን እንደሆኑና ምን ዓይነት ጣዕም እንዳላቸው በመጠየቅ ማወያየት
- ከዚያም በተግባር ቀምሰው ጣዕሙን እንዲለዩና ምንእንደሆኑእንዲናገሩማድረግ
- በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚመገቧቸው ምግቦች የትኞቹ እንደሆኑና ምን ዓይነት ጣዕም እንዳላቸው እንዲናገሩ ዕድሉን መስጠት

ምዘና ፡- የምግብ ጣዕሞችን በመቅመስመለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6. የመቅመስ ስሜት አካልን መጠቀምና አፍን መንከባከብ | 6.2. አፋቸውንበጥንቃቄና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡-ጥርስን በጥንቃቄ መያዝ

ዓላማ ፦ ጥርስን በጥንቃቄ መያዝ ይለማመዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ መስታወት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ከመስታወት ፊት በመቆም የራሳቸውን ጥርስ እንዲመለከቱ ማድረግ
- ቀጥሎም የጓደኞቻቸውን ጥርስ እንዲመለከቱ እና ያስተዋሉትን ልዩነት እንዲናገሩ ማድረግ

ለምሳሌ፦ የተበላሸ ጥርስ፣ የወለቀ ጥርስ፣ አዲስ ሙብቀል የጀመረ ጥርስ

- ጣፋጭ ነገሮችን አዘውትሮ የሚበላ ሕፃን ጥርሶቹ እንደተበላሹና እንደታመመ የሚተርክ አጭር ገጠመኝ ወይም ትረካን በመፍጠርመንገር
- ታሪኩን መሰረት በማድረግየሕፃናት ትናንሽ ጥርሶች በቀላሉ በጣፋጭ ምግቦች እንደሚበላሹ በመንገር እነዚህን ምግቦች አዘውትረው ከመመገብ እንዲቆጠቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- በተጨማሪም ጥርስን ባለመፋቅ /ባለመቦረሽ/፣ ከምግብ በኋላ ባለመጉመጥመጥ ወዘተ ጥርሶቻቸው ሊበላሹ እንደሚችሉ ማሳወቅ
- "ጥርስን ማጽዳት እንደዚህ ነው" የሚለውን መዝሙር በማዘመር ማጠናከር

| |
|---|
| ማስታወሻ ፦ ከወላጆች ጋር በመወያየት ሕፃናቱን በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የጥርሳቸውን ንጽህና በጥንቃቄ መያዝ እንዲያለማምዷቸዉ ማድረግ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፦ ጥርሳቸውን በጥንቃቄ መያዝ መለማመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ ጥርስን መንከባከብ

ዓላማ ፡- ጥርሳቸውን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጥርስ ብሩሽ፣ የእንጨት መፋቂያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናት ጥርሳቸውን በየዕለቱ መፋቅ/መቦረሽ/ እንዳለባቸው፣ እንዲሁም ከምግብ በኋላ በደንብ መጉመጥመጥ እና መትፋት እንዳለባቸው ማስገንዘብ
- ያለበለዚያ ግን ጥርሳቸው ከመበላሸቱ በተጨማሪ አፋቸው ጥሩ ያልሆነ ጠረን /ሽታ/ ሊያመጣ እንደሚችል ማስረዳት

ምዘና ፡- ጥርሳቸውን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው መገንዘባቸውን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- ጥርስን ማጽዳት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጥርስ መፋቂያ ብሩሽ፣ የጥርስ ሣሙና፣ የጥርስ መፋቂያ እንጨት፣ ኩባያ፣ ውሃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የጥርስ መፋቂያ ብሩሽና ሳሙናን አሊያም በንጽህና የተዘጋጀ የጥርስ መፋቂያ እንጨትን በመጠቀም ከላይ ወደታች እጅን በማንቀሳቀስ እንዴት መፋቅ /መቦረሽ/ እንደሚችሉ ማሣየት
- ጥርስ ሲፋቅ /ሲቦረሽ/ ምራቅ መዋጥ እንደሌለበት እና ሲጉመጠመጡም የተጉመጠመጡበትን ውሃ መትፋት እንደሚገባ በማሣየት ማስረዳት
- ሕፃናቱም ባዩት መሠረት የራሳቸውን የጥርስ ብሩሽ ወይም የጥርስ መፋቂያ እንጨት በመጠቀም እንዲለማመዱ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ሕጻናት ለተግባራዊው ልምምድ የራሳቸውን የጥርስ ብሩሽ /መፋቂያ/ ከቤታቸው እንዲያመጡ በቅድሚያ ሊነገራቸው ይገባል። |

ምዘና ፡- ጥርስን ማጽዳት መለማመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- ጥርስን ማጽዳት መለማመድ

| | ብቃት |
|---|---|
| 7. በመዳሰስ [illegible] | 7.1. [illegible] መካከል ያለውን ባህሪ፣ የሙቀት መጠንና ቅርጽን መለየት ይችላሉ። |

ዓላማ ፡- በመዳሰስ የነገሮችን ባህሪ መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዳሰስ ሰሌዳዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሸካራ፣ በጣም ሸካራና ለስላሣ የሆኑ የመዳሰስ ሰሌዳዎችን መስጠት
- ጣቶቻቸውን በመጠቀም እንዲዳስሱና የተሰማቸውንም ስሜት ሸካራ ነው ለስላሣ ነው በጣም ሸካራ ነው ወዘተ... በማለት እንዲገልጹ ማበረታታት

ምዘና ፡- በመዳሰስ የነገሮችን ባህሪ መለየታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- በመንካት ሞቃትና ቀዝቃዛ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- በመንካት ሞቃትና ቀዝቃዛ ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቆራረጡ ብረቶች እና እንጨቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የብረትና የእንጨት ቁራጭን ለሕፃናት በመስጠት በእጃቸው ነክተው የትኛው ቀዝቃዛ የትኛው ሙቅ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- ብረት ነክ ነገሮች ቀዝቃዛ መሆናቸውን እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- በመንካት ሞቃትና እና ቀዝቃዛ ነገሮችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ በመዳሰስ የነገሮችን ምንነት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ከረጢት፣ የተለያየ ቅርጽ፣ መጠንና ባህሪ ያላቸው ቁሳቁሶች (ማበጠሪያ፣ እርሳስ፣ ላፒስ፣ መቅረጫ ወዘተ...)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ተአምረኛው ከረጢትን በማዘጋጀት ሕፃናት የሚያውቋቸውን ቁሳቁሶች በከረጢቱ ውስጥ መክተት
- ህጻናቱን በየተራ በማስነሳት እጃቸዉን ከረጢት ውስጥ በመክተት አንድ ዕቃ ይዘዉ ሳያወጡ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- ከዛም ዕቃውን አውጥተዉ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያሳዩና ትክክል መሆን አለመሆኑን እንዲያረጋግጡ ማድረግ
- በየተራ ሁሉንም ሕፃናት በማጫወት በእጃቸው ዳሰው ዕቃዎችን እንዲለዩ ማስቻል

ምዘና ፦ በመዳሰስ የነገሮችን ምንነት መለየታቸውን መገምገም።

ተግባር ሶስት ፦ በመዳሰስ የነገሮችን ምንነት መለየት



ተግባር አራት ፦ የተለያዩ ነገሮችን በባህሪያቸው መመደብ

ዓላማ ፡- የተለያዩ ነገሮችን በባህሪያቸው መመደብ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቀማ ፡- የተለያዩ ቅርጽ፣ መጠን፣ ባህሪ ያላቸው ቁሳቁሶች (እርሳስ፣ ላፒስ፣ መቅረጫ፣ ወዘተ...)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያየ ቅርጽና መጠን ያላቸውን ቁሳቁሶች በጠረጴዛቸው ላይ መስጠት
- በመቀጠል በቅርፃቸውና በመጠናቸው መሠረት እንዲመደቡ ማድረግ
- ለምን እንደዛ ሊመድቡ እንደቻሉ ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የተለያዩ ነገሮችን በባህሪያቸው መመደብ መቻላቸውን ማረጋገጥ።የተለያዩ ነገሮችን በባህሪያቸው መመደብ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- የእጅን ጥቅም በዜማ መናገር

ዓላማ ፡- የእጅን ጥቅም በዜማ መናገር ይችላሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕጻናት እጆቻቸውን እንዲመለከቱና በእጆቻቸው ምን ምን ተግባራት እንደሚያከናውኑበት እንዲናገሩ ማድረግ
- በመቀጠልም መምህር በእጅ ሊከናውኑ የሚችሉ ተግባራትን በማሣየት እጅ አለኝ ብለዉ በዜማ ሲናገሩ ሕፃናት ያዩትን ተግባር በዜማ በመግለጽ የእጆችን ጥቅም እንዲረዱ ማድረግ

  ለምሣሌ ፡- መምህር ‹‹እጅ አለኝ›› ብለዉ ምግብ እንደሚጎርሱ ሲያሳዩዋቸዉ ሕፃናቱ ‹‹በእጆቼም እመገባለሁ›› ብለው በዜማ ይመልሳሉ እንደሚጽፉ ሲያሳዩዋቸዉ ‹‹በእጆቼ እጽፋለሁ›› በማለት ይመልሳሉ

ምዘና ፡- የእጅን ጥቅም በዜማ መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር ስድስት ፡- እጆችን ለተለያየ ተግባር መጠቀም

ዓላማ ፡- እጆቻቸዉን ለተለያዩ ተግባራት ይጠቀማሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የውሃ ገንዳ፣ የአሸዋ ገንዳና የተለያየ መጠን ያላቸው መስፈሪያዎች፣ እርሳስ፣ ወረቀቶች፣ የውሃ ቀለሞች፣ የተረት መጽሀፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የውሃ ገንዳንና የአሸዋ ገንዳን በመጠቀም ውሃ፣ አፈር፣ አሸዋ በመስፈርና በመገንባት የተለያዩ ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ ዕድሉን መስጠት
- ሕፃናት በሁለት እጆቻቸው የተረት/የስዕል/መጽሐፍ በመያዝ ማንበብን እንዲለማመዱ ማድረግ
- እጃቸውን /የእጅ መዳፎቻቸውንና ጣቶቻቸውን/ በወረቀት ላይ እንዴት መሣል እንዳለባቸው መጀመሪያ መምህር በሕፃናቱ ፊት ለፊት በመቆም በመሣል ማሣየት
- በመቀጠልም ለእያንዳንዱ ልጅ ወረቀትና እርሳስ በመስጠት እጃቸውን እንዲስሉ ማድረግ
- የውሃ ቀለምን በመጠቀም እጃቸውን እንዲያትሙ ማድረግ
- ሲጨርሱም ስማቸውን ከግርጌ እንዲጽፉ ማበረታታት

> ማስታወሻ ፡-ከላይ የተዘረዘሩት ተግባራት ከአንድ ክፍለ ጊዜ በላይ የሚወስዱ በመሆናቸው ተግባራቱን በደንብ ማከናወን እስኪችሉ ጊዜ መስጠት አስፈላጊ ነው።

ምዘና ፡- እጆቻቸዉን ለተለያየ ተግባራት መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 8. ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ስርዓቶችን መለማመድ | 8.1. ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን ለይተው መናገር ይችላሉ። |

ዓላማ ፡- የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ስዕሎች/ፖስተሮች/፣ የእርሻ ቦታ፣ የገበያ ቦታ፣ የምግብ ግሮሰሪ፣ ወዘተ የሚያሳዩ ስዕሎች /ፖስተሮች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ስዕሎች/ፖስተሮች/ ለሕፃናት በማሣየት ምን እንደሆኑ ስማቸውን በመጠየቅ ማወያየት
- በተጨማሪም እነዚህ የምግብ ዓይነቶች የት እንደሚመረቱና ከየት እንደሚገዙ ሕጻናት በደረጃቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ/የእርሻ ቦታ፣ የገበያ ቦታ፣ የምግብ ግሮሰሪ፣ ወዘተ.../
- በአብዛኛው ምን ዓይነት ምግብ እንደሚመገቡና ቤተሰቦቻቸው በአብዛኛው ምግባቸውን ከየት እንደሚያገኙ/እንደሚገዙ/ማወያየት

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ይህ ይዘት በአንድ ክፍለ ጊዜ ሊጠናቀቅ ስለማይችል በተከታታይ ቀናት መተግበር ተገቢ ይሆናል። |

ምዘና ፡- የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን መተዋወቃቸውን መገምገም።

## ተግባር ሁለት ፡- የአመጋገብ ሥርዓትን መተግበር

ዓላማ ፡- የአመጋገብ ሥርዓትን መተግበር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ቅርጽ፣ መጠን፣ ባህሪ ያላቸው ቁሳቁሶች (እርሳስ፣ ላፒስ፣ መቅረጫ፣ ወዘተ...)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናት ምግብ በመመገቢያ ሰዓት ላይ ሊጠብቁ የሚገባቸውን ስርዓቶች በመጠየቅ ማወያየት
- ሕፃናትመጥነው መጉረስ እንዳለባቸው፣የጎረሱትን በደንብ አኝከው ሳይውጡ ሌላ መጉረስ እንደሌለባቸው፣ አፋቸውን ከፍተው ድምጽ እያሰሙ ማኘክ እንደሌለባቸው፣ በምግብ ሰዓት መነጋገር እንደሌለባቸው፣ ወዘተ... በመንገር የሚያስከትለው ጉዳት ላይ ማወያየት
- በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ተግባራዊ ማድረጋቸውን መከታተል

ምዘና ፡- የአመጋገብ ሥርዓትን መገንዘባቸውን መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- የአመጋገብ ሥርዓትን መተግበር

ዓላማ ፦ የአመጋገብ ሥርዓትን መተግበር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ማንኪያ፣ ሹካ፣ ኩባያ፣ ሳህን፣ ቁራጭ ፎጣ /ጨርቅ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ከምግብ በፊት "መልካም ምግብ ይሁንልን" በማለት ለራሳቸውና ለጓደኞቻቸው መልካም ምኞታቸውን እንዲገልፁ ማለማመድ
- በምግብ ሰዓት የማንኪያ፣ የሹካና የኩባያ አያያዝንና አጠቃቀምን በተግባር ማሣየት
- በሚበሉበት እጃቸው ኩባያ መያዝ ለምን እንደሌለባቸው በመጠየቅ ማወያየት
- ጣቶቻቸውን በመጠቀም እንጀራ እንዴት አድርገው በመጠን ቆርሰውና ጠቅልለው መጉረስ እንዳለባቸው ማሣየት
- ከተመገቡም በኋላ የዕለቱ የምግብ ተረኞችን፣ መምህርንና ያዘጋጁላቸውን ወላጆቻቸውን እናመሠግናለን ማለት እንዳለባቸው ማስገንዘብና በየዕለቱም መከታተል
- የምግብ ሰዓት ተረኞች በየዕለቱ ተራቸውን አውቀው ከምግብ በኋላ ህፃናቱ የተመገቡበትን ጠረጴዛ ቁራጭ ጨርቅ /ፎጣ/ በመጠቀም እንዲያፀዱ ማድረግ

ምዘና ፦ የአመጋገብ ሥርዓትን መተግበር መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አራት ፡ - በጨዋታ የምግብ አዘገጃጀትን እና አቀራረብን ማንጸባረቅ

ዓላማ ፡- በጨዋታ የምግብ አዘገጃጀትን እና አቀራረብን ማንጸባረቅ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለመስሎ መጫወት ጨዋታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች(ሳህን፣ ብረት ድስት፣ ሹካ፣ ማንኪያ፣ ትንንሽ ፎጣዎች ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ክፍሉን ለመስሎ መጫወት በሚመች ሁኔታ ማደራጀትና ሕፃናት የምግብ አዘገጃጀትን፣ የአበላል ሥርዓትን፣ ወዘተ… በጨዋታው እንዲያንፀባርቁ ማበረታታት
- ሕፃናት በቤታቸውም በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለውን የአመጋገብ ሥርዓት ተከትለው እንዲመገቡ ከወላጆች ጋር በመወያየት ልምዱን እንዲመሠርቱና እንዲያዳብሩ መርዳት

ማስታወሻ ፡- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ምግብ የሚዘጋጅበት ሁኔታ ካለሕፃናት በአዘገጃጀትና በአቀራረብ ላይ በደረጃቸው እና ለአደጋ በማያጋልጣቸው መልኩ የሚሣተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይቻላል።

ምዘና ፡- በጨዋታ የምግብ አዘገጃጀትን እና አቀራረብን ማንጸባረቅ መለማመዳቸዉን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 8. ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ስርዓቶችን መለማመድ | 8.2. የግል ንጽህናቸዉን መጠበቅ ይለማመዳሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የግል ንጽህናን መጠበቅ ጠቀሜታ

ዓላማ ፡- የግል ንጽህናን መጠበቅ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለመስሎ መጫወት ጨዋታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች(ሳህን፣ ብረት ድስት፣ ሹካ፣ ማንኪያ፣ ትንንሽ ፎጣዎች ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የግል ንጽህና መጠበቅ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ የሚያሳዩ ገጠመኞች /ታሪኮች/ መንገር
- የግል ንጽህናቸውን የሚጠብቁ ህጻናትን ዕውቅና መስጠት

ማስታወሻ ፡- በየሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ላይ ህጻናቱ ጸጉራቸውን መታጠባቸውን፣ ጥፍራቸው መቆረጡንና የታጠበ ልብስ መልበሳቸውን በማየት የግል ንጽህና የሚያስገኘውን ጠቀሜታ እንዲረዱ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲሁም መምህር የግል ንጽህናን በመጠበቅ ለህጻናቱ አርአያ መሆን ይገባል።

ምዘና ፡- የግል ንጽህናን መጠበቅ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ መገንዘባቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- የግል እና የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ

ዓላማ ፡- የግል እና የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተጠቀሙበትንና የማያስፈልጉትን ቁርጥራጭ ወረቀቶች፣ አፍንጫቸውን ካጸዱ በኋላ ያጸዱበትን የመጸዳጃ ቤት ወረቀት በየቦታው መጣል እንደሌለባቸው ማስገንዘብ
- መጣል ያለባቸው በቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ ብቻ እንደሆነ መንገር እንዲሁም ማድረጋቸውን መከታተል
- "ንጽህናዬን ጠብቄያለሁ" የሚለውን መዝሙር በህብረት ማዘመር
- በጥያቄና መልስ የመዝሙሩን መልዕክት እንዲረዱ ማድረግ
- መምህርም አርአያ በመሆን ልምዱን እንዲያዳብሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የግል እና የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር ሶስት ፡- ንጽህናን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት መረዳት

ዓላማ ፡- ንጽህናን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ይረዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ ገጠመኞችን መንገር
- ህጻናት እጃቸውን ሳይታጠቡ የሚመገቡ ከሆነ ሆዳቸውን ሊያማቸው እንደሚችል
- ቆሻሻ የሚከማችበት ቦታ ላይ የሚጫወቱ ከሆነ ጉንፋን ሊያዛቸው እንደሚችል
- ባልታጠበ እጃቸው ዓይናቸውን የሚነኩና የፊታቸው ንጽህና የማይጠብቁ ከሆነ ዓይናቸውን ሊታመሙ እንደሚችሉ እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ንጽህናን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- የግል ንጽህና አጠባበቅን በጨዋታ ያንጸባርቃሉ ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የግል ንጽህና አጠባበቅን የሚያስረዱ የአጫጭር ተረቶች መጽሀፍ፣ለድራማ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የግል ንጽህና አጠባበቅን የሚያስረዳ አጭር ተረት /ገጠመኝ/ መንገር
- የሰሙትን አጭር ተረት /ገጠመኝ/ ህጻናቱ ወደ ድራማ በመቀየር እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፡- የግል ንጽህና አጠባበቅን በጨዋታ ማንጸባረቅ መቻላቸውን መገምገም።

ተግ ተግባር አምስት ፡- የግል ንፅህና አጠባበቅን መተግበር

**ዓላማ ፦** የግል ንፅህና አጠባበቅን መተግበር ይለማመዳሉ።

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦** ጣሳ፣ ዉሃ፣ ሶፍት፣ ሳሙና፣ ፎጣ፣ ወዘተ…

**የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-**

- ሕፃናት የግል ንጽህና አጠባበቅን በተግባር እንዲለማመዱ አስፈላጊውን ቁሳቁሶች በማቅረብ ማለማመድ

**ለምሳሌ፡-** ፊትን መታጠብ፣ እጅና እግርን መታጠብ፣ አፍንጫ ማጽዳት ወዘተ…

| |
|---|
| **ማስታወሻ፡-** መምህር ራስዎ የግል ንጽህናን በመተግበር/እጅና ፊትን በመታጠብ/ ለሕፃናቱ ማሳየት ይኖርብዎታል። |

**ምዘና ፦** የግል ንፅሕና አጠባበቅን መተግበር መለማመዳቸዉን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 8. ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ስርዓቶችን መለማመድ | 8.3 .የራሳቸውን ንጽህና መጠበቅ ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ ፦** የግል ንፅሕናን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን መለየት

ዓላማ ፦ የግል ንፅሕናን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የግል ንጽህናን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ቁሳቁሶች (የውሃ ጣሳ፣ ፎጣ፣ እጅ ማስታጠቢያ፣ ሳሙና ወዘተ...)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ቁሳቁሶቹን በማቅረብ ምን እንደሆኑ፣ ለምን እንደሚያገለግሉ እና በቤታቸው ይጠቀሙበት እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- በመቀጠልም የግል ንጽህናን መጠበቅ ምን ማለት እንደሆነ፣ ለምን እንደሚያስፈልግናበእነዚህ ቁሳቁሶች እንዴት እንደሚጠቀሙ በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፦ የግል ንፅህናን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን መለየት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ በጨዋታ የግል ንጽህና አጠባበቅን ማንጸባረቅ

ዓላማ ፡- በጨዋታ የግል ንጽህና አጠባበቅን ማንጸባረቅ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ዉሃ፣ ትንሽ ፎጣ፣ ጣሳ፣ ማስታጠቢያ፣ የጥርስ ብሩሽ፣

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የፕላስቲክ አሻንጉሊት በመጠቀም የግል ንጽህናዋን እንዴት መጠበቅ እንዳለባትና ምን ምን ዓይነት ቁሳቁሶች እንደሚያስፈልግ እንደማታውቅ ለሕጻናቱ መንገር
- የእነሱን እርዳታ ለመጠየቅ እንደመጣች በማድረግ በውይይትና በተግባር እንዲረዷትማድረግ
- በመቀጠል እነሱ ጠዋት ከእንቅልፋቸው ተነስተው የግል ንጽህናቸውን ከመጠበቅ አኳያ ምን እንደሚያደርጉ በቅደም ተከተል እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በጨዋታ የግል ንጽህና አጠባበቅን ማንጸባረቅ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- እጅ፣ እግር እና ፊትን በንጽሕና መጠበቅ

ዓላማ ፦ እጅ፣ እግር እና ፊትን በንጽሕና መጠበቅ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የግል ንጽህና ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ቁሳቁሶች (የውሃ ጣሳ፣ ፎጣ፣ እጅ ማስታጠቢያ፣ ሳሙና፣ ወዘተ…)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- እጅን፣ እግርን እና ፊትን መታጠብ ለምን እንደሚጠቅም፣ መቼ መታጠብ እና እንዴት መታጠብ እንዳለባቸው በመጠየቅ ማወያየት
- በመቀጠልም እጃቸውን ከምግብ በፊትና በኋላ ከመፀዳጃ ቤት መልስ እንዴት መታጠብ እንዳለባቸው በተግባር እንዲያሣዩ ማድረግ
- ፊታቸውንና እግራቸውን በየዕለቱ መታጠብ እንዳለባቸውና ከታጠቡም በኋላ ፊታቸውንና እግራቸውን በንፁህ ፎጣ /ጨርቅ/ ማድረቅ እንዳለባቸው በማስረዳት በተግባር ማሣየት
- በተግባር እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፦ እጅ፣ እግር እና ፊትን በንጽሕና መጠበቅ መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፦ የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም

ዓላማ ፡- የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀምን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመፀዳጃ ቤት ወረቀት/ሶፍት/፣ ቁራጭ ሣሙና፣ ዉሃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናት የመፀዳጃ ቤትን እንዴት አድርገው በስርዓት መጠቀም እንዳለባቸው በመጠየቅ ማወያየት
- ሕፃናት መፀዳጃ ቤትን ሲጠቀሙ በትክክል ቀዳዳው ውስጥ መጠቀም እንዳለባቸው ማስገንዘብና ሲተገብሩም በመከታተል ልምዱን እንዲመሰርቱ መርዳት
- ሲጨርሱም እጃቸውን በውሃና በሣሙና መታጠብ እንዳለባቸው በመንገር በተግባር እንዲለማመዱ ማበረታታት

ምዘና ፡- የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም መለማመድ መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አምስት ፡- ልብስ ማጠብ

ዓላማ ፡- ልብስ ማጠብን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአሻንጉሊቶች ልብስ፣ ትንሽ የፕላስቲክ ሰሐን፣ ሣሙና፣ ዉሃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የአሻንጉሊቶች ልብስ፣ትንሽ የፕላስቲክ ሰሐን፣ ሣሙና እና ዉሃ ለሕፃናት በማቅረብ የአሻንጉሊቶቻቸውን ልብስ ማጠብ እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ልብስ ማጠብ መለማመዳቸዉን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|

| | |
|---|---|
| 9.አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ | 9.1 አካላቸውን መጠበቅና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- አካልን ከጉዳት መጠበቅ

ዓላማ ፡- አካላቸውን ከጉዳት እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሀፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ የአካል ክፍሎቻቸውን ተግባር በመጠየቅ ሕጻናትን ማወያየት
- የአካል ክፍሎቻቸው በምን አይነት መንገድ ሊጎዱ እንደሚችሉ ማስረዳት
- ከተጎዱ ደግሞ እንደልብ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን እንደማይችሉ ማስገንዘብ
- አካላቸውን እንዴት በጥንቃቄ መያዝ እንደሚችሉ በእድሜያቸው ደረጃ እንዲገነዘቡ ማድረግ
- በተለያየ ምክንያት የአካል ክፍሎቻቸው የተጎዱባቸውን ልጆች ታሪኮችን በመንገር አካላቸውን ከተለያዩ አደጋዎች መጠበቅ እንዳለባቸው ማሳወቅ

ማስታወሻ ፡- ይሄንን በተረት፣ በገጠመኝ፣ ወዘተ...ሕጻናትን በተደጋጋሚ ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- አካላቸውን ከጉዳት እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው መረዳታቸውን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- ንጽህናን አለመጠበቅ የሚያስከትለው ጉዳት

ዓላማ ፦ ንጽህናን አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ንጽህናቸውን የጠበቁ እና ያልጠበቁ ህጻናት ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ንጽህናቸውን የጠበቁ እና ያለጠበቁ ህጻናት ስዕል በማሳየትእነ ጥያቄዎች በመጠየቅ ማወያየት
- እጅን ሳይታጠቡ መመገብ፣ /ፊትን፣ እግርን፣ፀጉርን/ አለመታጡብ የሚያስከትለውን ጉዳት ማወያየት
- ንጽህና አለመጠበቅ ለበሽታ እንደሚያጋልጣቸውና ለሚመለከታቸውም ሰው ቆንጆ ሆነው እንደማይታዩ መንገር
- በመሆኑም እለት በእለት ንፅህናቸውን መጠበቅ እንደሚያስፈልጋቸው ማስገንዘብ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ንፅህናቸውን የማይጠብቁ ሕጻናት በክፍል ውስጥ ቢኖሩ ለምን እንዳልጠበቁ ለብቻቸውና ስሜታቸውን በማይጎዳ መልኩ መምከርና ከወላጆቻቸዉ ጋር ውይይት ማድረግ ተገቢ ነው። |

ምዘና ፦ ንጽህናን አለመጠበቅ የሚያስከትለዉን ጉዳት መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- ገላ አስተጣጠብን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አሻንጉሊት፣ ውሃ፣ ሳሙና፣ እጅ ማስታጠቢያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከፕላስቲክ የተሰራ አሻንጉሊትን በመጠቀም በጨዋታ ገላ አስተጣጠብን እንዲለማመዱ ማድረግ
- በተመሳሳይ እነሱን አሁን ወላጆቻቸው እንደሚያጥቡዋቸውና በሂደት እያደጉ ሲሄዱ አሻንጉሊቷን ባጠቡበት ሁኔታ እራሳቸው መታጠብ እንደሚችሉ መንገር

ማስታወሻ ፡- ከወላጆቻቸው ጋር በመወያየት ንፅህናን የመጠበቅ ልምድን እንዲያዳብሩ ማድረግ ተገቢ ነዉ።

ምዘና ፡- ገላ አስተጣጠብን መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር ሶስት ፡- ገላ መታጠብ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 10.ጉልህና ረቂት /ትላልቅና ትናንሽ /ጡንቻዎችን መጠቀም | 10.1.ትላልቅና ትናንሽ ጡንቻዎችን በመጠቀም የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ሚዛንን ጠብቆ መራመድ

ዓላማ ፡- ሚዛን ጠብቆ መራመድን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መጠነኛ ውፍረትና 3 ሜትር ርዝመት ያለው ግንድ፣ ጠመኔ/ቾክ/፣ ገመድ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መጠነኛ ውፍረትና 3 ሜትር ርዝመት ያለው ግንድ በተስተካከለ መሬት ላይ አደላድሎ መዘርጋት፣ መስመር ማስመር ወይም ገመድ በመሬት ላይ እንዲዘረጋ ማድረግ
- እጃቸውን ወደጐን በመዘርጋት አንድ በአንድ በግንዱ/በመስመሩ ወይም በገመዱ/ ላይ እንዲራመዱ ማድረግ
- በራስ መተማመን እንዲኖራቸው በቅርብ አካባቢ ተገኝቶ ማበረታታት እና መምራት

ምዘና ፡- ሚዛን ጠብቆ መራመድ መለማመዳቸውን መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- ሚዛንን ጠብቆ መሮጥ

ዓላማ ፡- ሚዛንን ጠብቆ መሮጥ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መሃረብ /ንጹህ ጨርቅ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- "መሐረቤን ያያችሁ" ጨዋታን በግቢ ውስጥ ሰፋ ያለ ክብ እንዲሠሩ በማድረግ እንደሚከተለው ማጫወት፡-
- ለጨዋታ ተራ የደረሰው /የደረሳት/ ሕፃን መሐረብ ደብቆ /ደብቃ/ ይይዝና /ትይዝና/ ከሕፃናት ጀርባ ክቡን እየዞረ /እየዞረች/

  መሐረቤን ያያችሁ? /ሲል/ስትል/

  አላየንም እባካችሁ /ሕፃናት ይላሉ/

  ይቺ ምንድናት ? /ሕፃኑ/ኗ/

  የውርዬ ኳስ ናት /ሕፃናት/

  ማየት የለም /ሕፃኑ/ኗ/

  መደባበስ የለም /ሕፃናት ይላሉ/

*የጨዋታ ሕግ፡- አንዱ/ዷ/ ሕፃን ጀርባ መሐረቡን ያስቀምጥና/ታስቀምጥና ይሮጣል/ትሮጣለች። መሐረቡ የተቀመጠለት /የተቀመጠላት/ ሳይነቃ /ሳትነቃ/ ከተደረሰበት /ከተደረሰባት/ አጫዋች ይሆንና/ትሆንና/ ወደ መካከል ይገባል/ትገባለች/። ሕፃናት አይጤ ቡና አፍይ /2/ በማለት ይናገራሉ። መሐረብ የተቀመጠለት/የተቀመጠላት/ ከነቃ/ከነቃች/ መሐረብ አስቀማጩን ያባርራል/ታባርራለች። ሕፃናት "ውርዬ ዞረሽ ግቢ ውርዬ ዞረሽ ግቢ" በማለት ያበረታታሉ። በዚህ ዓይነት ጨዋታው ይቀጥላል።*

ምዘና ፡- ሚዛን ጠብቆ መሮጥ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሦስት ፡- ቀላል የአካል እንቅስቃሴዎችን መስራት

ዓላማ ፦ ቀላል የአካል እንቅስቃሴዎችን መስራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ምንጣፍ/ንጹሕ ወለል/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በመማሪያ ክፍል ወይም በአዳራሽ ውስጥ ንፁህ ምንጣፍ መዘርጋት /ማንጠፍ/
- ‹‹ወፊቱን እሆናለሁ›› እና ‹‹አውሮፕላን እሆናለሁ›› የሚባሉትን መዝሙሮች በማዘመር ሕጻናት እጆቻቸውን በመዘርጋት እንደ ወፍ እና እንደ አውሮፕላን እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ
- ሕፃናት ተደራቢ ልብሶቻቸውን በማውለቅ ከግራ ወደቀኝ ከቀኝ ወደግራ እንዲንከባለሉ ማድረግ

ምዘና ፦ ቀላል የአካል እንቅስቃሴዎችን መስራት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አራት ፡- በተረከዝ እና በእግር ጣት መራመድ

ዓላማ ፡- በተረከዝና እና በእግር ጣት መራመድ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጸናፅል ወይም ማራካሽ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወንበር እና ጠረጴዛዎችን ወደ ዳር ማድረግ
- ሕፃናት ቢያንስ እስከ 3 ሜትር ሊራመዱ የሚችሉበትን ቦታ ማመቻቸት
- ሕፃናትን ክብ እንዲሠሩ ማድረግ
- የሙዚቃ መሣሪያ ጽናጽል /ማራክሽ/ ድምጽን ሲሰሙ እንቅስቃሴ እንዲጀምሩ መንገር
- እንቅስቃሴውን በእግር ጣቶቻቸው እንዲራመዱ በማድረግ ማስጀመር
- በመቀጠል በተረከዛቸው እንዲራመዱ ማድረግ
- በእያንዳንዱ የእርምጃ እንቅስቃሴ እጅ በወገብ፣ እጅ ወደታች እና ወደ ላይ በማድረግ እንዲንቀሳቀሱ /እንዲራመዱ/ በማድረግ እንቅስቃሴውን ማጠናከር
- አብሮ በመራመድ ማበረታታት

ምዘና ፡- በተረከዝና በእግር ጣት መራመድ መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አምስት ፡- በእጅ እና በእግር የሚተገበሩ ተግባራት

ዓላማ ፦ በተረከዝና እና በእግር ጣት መራመድ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጠመኔ/ቾክ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በእግሮቻቸው እና በእጆቻቸው ሊያከናውኑ ስለሚችሉአቸው እንቅስቃሴዎች መጠየቅ እና ማወያየት
- የተናገሩትን በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው በተግባር እንዲያሳዩ መጋበዝ
- የሰኞ ማክሰኞ መጫወቻ መስመሮችን በክፍል ውስጥ ወይም በግቢ ውስጥ በቾክ ለመሥራት አመቺ የሆነ ቦታ ማዘጋጀት
- መስመሮችን ከሰኞ እስከ ዕሁድ መሥራት
- መስመርን የረገጠ ከጨዋታ ውጪ እንደሚሆን ማስረዳት
- በሁለት ከዛም በአንድ እግር መዝለልን ማለማመድ
- በመቀጠል በየተራ እንዲዘሉ በማድረግ

| | |
|---|---|
| ሰኞ | |
| ማክሰኞ | |
| ረቡዕ | |
| ሐሙስ | |
| ዓርብ | |
| ቅዳሜ | |
| ዕሁድ | |

ማስታወሻ፦ በተቻለ መጠን ሁሉም ሕፃናት በየተራ እንዲሳተፉ በማድረግ እንቅስቀሴዎችን ማሠራት አስፈላጊ ነው።

ምዘና ፦ በእጅ እና በእግር የሚተገበሩ ተግባራትን መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር ስድስት ፦ ኳስ መወርወር

ዓላማ ፡- ኳስ መወርወር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክብ ፕላስቲክ፣ የጨርቅ ኳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከመነሻ ቦታ 2 ሜትር ርቀት ላይ ሁለት ክብ ፕላስቲኮች /የዘይት ፕላስቲክ ሊሆን ይችላል/ በመካከላቸው 1 ሜትር ርቀት ማስቀመጥ
- ከፕላስቲኮቹ ትይዩ 2 ሜትር ርቀት ላይ ሁለት ሕፃናት እንዲቆሙ ማድረግ
- ሁለት ሁለት ትናንሽ የጨርቅ ኳሶች መስጠት
- ሁለቱን ኳሶች በየተራ በመወርወር በፕላስቲኮች ውስጥ በመክተት ጨዋታውን እንዲጫወቱ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ፡- ጨዋታውን ከመጀመር በፊት የጨዋታውን ሕግ ማስረዳት ይገባል።<br>ለምሳሌ፡- ኳሶቹን ወርውሮ በፕላስቲኮች ውስጥ መክተት ያልቻለ ወይም በኳሱ መትቶ የጣለ ከጨዋታ ውጭ ይሆናል። |

ምዘና ፡- ኳስ መወርወር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- ኳስ የመቅለብና የመወርወር ክህሎት ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ኳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናትን በአንድ ረድፍ ማሰለፍ
- በፊት ለፊታቸው 2 ሜትር ርቀት ላይ መቆም
- ኳስ ለሕፃናቱ መወርወር እና ቀልበው መልሰው በመወርወር ሮጠው ከሰልፍ መጨረሻ እንዲቆሙ ማድረግ
- በረድፍ የተሰለፉ ሕጻናት በሙሉ በተመሳሳይ የተወረወረላቸውን ኳስ በመቅለብና መልሶ በመወርወር በሰልፉ መጨረሻ እንዲቆሙ በማድረግ የመቅለብና የመወርወር ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ኳስ የመቅለብና የመወርወር ክህሎት ማዳበራቸውን መከታተል።

ተግባር ስምንት ፡- ኳስ መቅለብና ማንጠር

ዓላማ ፡- ኳስ የመቅለብና የማንጠር ክህሎትን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ኳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መካከለኛ ሊነጥር የሚችል ኳስ ማዘጋጀትና ማቅረብ
- ኳስን እንዴት መቅለብ እና ማንጠር እንደሚቻል ማሣየት
- ሕጻናትን በሁለት ረድፍ ማሰለፍ እና በፊት ለፊታቸው 2 ሜትር ርቀት ላይ በመቆምበመጀመሪያው ረድፍ ላለው የመጀመሪያ ሕጻን ካስ መወርወር
- የመጀመሪያውን ኳስ የቀለበው/ችው/ ሕጻን 3 ጊዜ አንጥሮ/አንጥራ/ በጐን ረድፍ ላለው/ላለችው የመጀመሪያ ሕጻን በመወርወር እንዲቀመጥ/እንድትቀመጥ/ማድረግ
- በሁለቱ ረድፍ የተሰለፉ ሕጻናትበሙሉ በተመሳሳይ የተወረወረላቸውን ኳስ በመቅለብና በማንጠር መልሰም በረድፍ ላለውጓደኛው በመወርወር እንዲቀመጡ ማድረግ
- በዚህ ዓይነት ኳስ የማንጠር ክህሎት እንዲኖራቸው እና ኳስ በመጫወት እንዲደሰቱ ማድረግ

ምዘና ፡- ኳስ የመቅለብና የማንጠር ክህሎት ማዳበራቸውን መከታተል።

ተግባር ዘጠኝ ፡- ሚዛንን ጠብቆ መጫወት

ዓላማ ፡- ሚዛን ጠብቆ መጫወትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በሕፃናት እጅ ሊያዝ የሚችል ውፍረት ያላቸው መሠረታዊ ቀለማት የተቀቡ ዱላዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በሕፃናት እጅ ሊያዝ የሚችል ውፍረት ያላቸው መሠረታዊ ቀለማትን የተቀቡ ዱላዎችን በመጠቀም የዱላ ቅብብል ውድድርን ማካሄድ
- በውድድሩ የሚካፈሉት በየ10 ሜትር ርቀት የቆሙ ሶስት ሶስት ሕፃናት በሁለት ቡድን እንዲሆኑ ማድረግ
- የውድድሩ ጠቅላላ ርቀት 30 ሜትር እንዲሆን ማመቻቸትና ራሳቸው አሸናፊውን በመናገር እንዲሳተፉ ዕድል መስጠትና ማበረታታት

ምዘና ፡- ሚዛን ጠብቆ መጫወት መለማመድ መቻላቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- የልብስ አለባበስ ሥርዓትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የህፃናቱ ሹራብ የልብስ ፍሬሞች፣ የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/ ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በየዕለቱ የሚያከናውኗቸውን መሠረታዊ ተግባራት መጠየቅና ማወያየት
- የልብስ አለባበስ ስርዓትን ቅደም ተከተል፣ የልብስ አቆላለፍ፣ ወዘተ… ማሣየት
- የራሳቸውን ልብስ በመጠቀም እንዴት እንደሚለበስ እንዲያሳዩ በማድረግራሳቸውን ችለው የመልበስ ክህሎታቸውን ማጠናከር
- ድፍን ሹራብ ገልብጦ በመስጠት እንደገና አስተካክለው መልበስን ማለማመድ
- ቀን ተለብሶ የዋለ ልብስ ማታ ሲተኛ በሌሊት ልብስ እንደሚቀየር
- ያወለቁት ልብስ ታጥፎ መቀመጥ እንዳለበትናልብስ ሳይታጠፍ ከተቀመጠ እንደሚጨማደድ ማስረዳት
- ልብስ አስተጣጠፍን በተመለከተ የተለያዩ አልባሳትን በማጠፍ ማሣየት
- <<ጠዋት ተነስቼ>> የሚለውን መዝሙር ከእንቅስቃሴ ጋር በማገናኘት እንዲዘምሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የልብስ አለባበስ ሥርዓትን መለማመዳቸውን መገምገም።

ተግባር አስራ አንድ ፡- ጫማ ማሰር

ዓላማ ፡- ጫማ ማሰር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጫማ ማሠሪያ ፍሬም

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የጫማ ማሠሪያ ፍሬምን በመጠቀም ሁሉም ሕፃናት ጫማ ማሠርን እንዲተገብሩ ማድረግ
- ማሠሪያ ያለው ጫማ ያደረጉ ሕፃናትን በማሣተፍ የራሳቸውን ጫማ ማሠሪያ መፍታትና መልሶ በቀዳዳ ውስጥ የጫማ ክሩን በማስገባት ማሰርን እንዲያከናውኑ ማድረግ
- በሂደቱም ግራና ቀኝ ጫማ መለየታቸውን መከታተል

ምዘና ፡- ጫማ ማሰር መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አስራ ሁለት ፡- መሠረታዊ የእለት ተግባራት

ዓላማ ፡- መሠረታዊ የእለት ተግባራትን ማከናወን ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/፣ የጥርስ ብሩሽ፣ የጥርስ መፋቂያ እንጨት፣ የዉሃ ጆግ፣ ማስታጠቢያ፣ ዉሃ፣ ማበጠሪያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ፊት መታጠብ፣ ፀጉር ማበጠርና ጥርስ መፋቅ ቀደም ባለው ዕድሜ የተማሩት በመሆኑ እንዴት ማከናወን እንደሚቻል መጠየቅና ማወያየት
- ለየክንውኖቹ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችን ማቅረብ
- እያንዳንዳቸው እንዴት እንደሚከናወን በየግላቸው እንዲያሳዩ ማድረግ
- "ፊትን መታጠብ እንደዚህ ነው" የተባለውን መዝሙር በእንቅስቃሴ እንዲዘምሩት ማድረግ
- ትክክለኛውን እንቅስቃሴ መጠቀማቸውን መከታተል

ምዘና ፡- መሠረታዊ የእለት ተግባራትን ማከናወን መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አስራ ሦስት ፡- ትዕዛዝ ተከትሎ መጫወት

ዓላማ ፡- ትዕዛዝ ተከትለው መጫወት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት /በተንቀሳቃሽ ስልክ የተቀዳ/፣ የጥርስ ብሩሽ፣ የጥርስ መፋቂያ እንጨት፣ የዉሃ ጆግ፣ ማስታጠቢያ፣ ዉሃ፣ ማበጠሪያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የመምህርን ቃል እና እንቅስቃሴ በመከተል የመተግበር ጨዋታን እንደሚከተለው ማጫወት፡-
  - *መምህር ዱብ ዱብ በማለት ሲሮጡ ሕፃናትም በተለያየ አቅጣጫ ዱብ ዱብ ይላሉ*
  - *መምህር ግንባራቸውን ይዘው ሲቆሙ እነርሱም ግንባራቸውን ይዘው ይቆማሉ*
  - *ከግንባር ሌላ የሰውነት ክፍል የያዘ ከጨዋታ ውጭ ይሆናል*
  - *በዚህ ዓይነት አጫዋች /መሪ/ በመቀየር የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ጨዋታው እንዲቀጥል ማድረግ*

ምዘና ፡- ትዕዛዝ ተከትለው መጫወት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ አራት ፡- የኳስ ቅብብሎሽ

ዓላማ ፦ የኳስ ቅብብሎሽን ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ኳስ፣ ጽናጽል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በሁለት ረድፍ በእጃቸው ከንድተው ርቀታቸውን በማስተካከል እንዲቆሙ ማድረግ
- በሁለት እጃቸው ሊይዙት የሚችሉትን መካከለኛ ኳስ በመጠቀም ከፊት ወደኋላ በጭንቅላታቸው ላይ ኳስን በፍጥነት እንዲቀባበሉ በጽናጽል መምራት
- በመጨረሻ የቆመው ኳሱን ተቀብሎ በሩጫ ፊት ላለው ይሰጥና ቅብብሎሹን ይቀጥላል። በዚህ ዓይነት ሲጫወቱ በቅድሚያ ቅብብሎሹን የጨረሰ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

ምዘና ፦ የኳስ ቅብብሎሽ መጫወት መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አስራ አምስት ፦ ‹‹ መሪውን ዕወቅ ››ጨዋታ

**ዓላማ ፡-** ‹‹ *መሪውን ዕወቅ* ››ጨዋታን ይጫወታሉ፡፡

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- **"***መሪውን ዕወቅ* " የተባለውን ጨዋታ እንደሚከተለው ማጫወት፡-
  - *ሕፃናት በክብ እንዲቆሙ ማድረግ*
  - *መሪ ወይም ምልክት ሰጪ እና መሪውን ጠቋሚ ሰው መምረጥ*
  - *መሪ ጠቋሚውን ከክፍል ውጭ ማስወጣት*
  - *ሁሉም ሕፃናት መሪው የሚያሳየውን እንቅስቃሴ ተከትለው እንዲያከናውኑ ማድረግ*
  - *እንቅስቃሴው ሲቀየርም በመከታተል እንቅስቃሴያቸውን እየቀየሩ መጫወት*
  - *ከጥቂት ምልከታ በኋላ መሪ ጠቋሚው መሪውን እንዲጠቁም ማድረግ*
  - *የተሳሳተ ጠቋሚ ከጨዋታውውጪ ይሆናል፡፡*

**ምዘና ፡- "***መሪውን ዕወቅ*" ጨዋታን መጫወት መቻላቸዉን መከታተል፡፡

ተግባር አስራ ስድስት ፡-የተለያዩ እንቅስቃሴያዊ ጨዋታዎችን መጫወት

ዓላማ ፡- እንቅስቃሴያዊ ጨዋታዎችን መጫወት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝለያ ገመድ፣ በግቢ ውስጥ የሚገኙ መጫወቻዎች (ሸርተቴ፣ ዥዋዥዌ፣ሚዛን፣ ወዘተ...)፣ ቀላል መጽሐፍ፣ ቀላል ትንሽ ትሪ እና ተመሣሣይ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በግቢ ውስጥ የሚገኙትን መጫወቻዎች (ሸርተቴ፣ ዥዋዥዌ፣ ሚዛን፣ ወዘተ...) በመጠቀም እንዲጫወቱ ማድረግ
- ከጨዋታውበኋላ የተሰማቸውን እንዲናገሩ በማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴያዊ ጨዋታዎችን የመጫወት ክህሎታቸውን ማዳበር
- በተጨማሪም ሕፃናት ለየብቻቸው ሊዘሉ የሚችሉባቸውን መያዣ ያላቸውን ገመዶች በማዘጋጀት

  እንዴት በገመድ መዝለል እንደሚቻል በተግባር ማሣየት
- እያንዳንዳቸው ገመድ ይዘው እየተቆጠረላቸው እንዲዘሉ ማድረግ
- በጭንቅላታቸው ላይ ቀላል መጽሐፍ፣ ቀላል ትንሽ ትሪ እና ተመሣሣይ ነገሮች በማስቀመጥ በወለል ላይ በተሰመረ መስመር ላይ እንዲራመዱ ማድረግ

*የጨዋታው ሕግ፡-*

- *መስመሩን ተከትሎ በራሱ ላይ የያዘው ነገር ሳይወድቅበት መስመሩን ተራምዶ የጨረሰ/ጨዋታውን ላጠናቀቀ/ማጨብጨብ*
- *በጭንቅላቱ ላይ የያዘው ነገር የወደቀበት ጨዋታውን እንደገና ይጀምራል*
- *ጨዋታው በፍጥነት የሚከወን እንዲሆን በሁለት ወይንም ሦስት ጐን ለጐን በተሰመሩ መስመሮች ላይ ሁለት ወይንም ሦስት ሕፃናት እኩል ጀምረው እንዲራመዱ ማድረግ ይቻላል*

> *ማስታወሻ ፡- እነዚህን ጨዋታዎች በተለያዩ ቀናትና ክፍለ ጊዜያት በማጫወት የሕጻናቱ ትናንሽና ትላልቅ ጡንቻዎች እንዲዳብሩ ማድረግ ይቻላል።*

ምዘና ፡- የተለያዩ እንቅስቃሴያዊ ጨዋታዎችን መጫወት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

## ተግባር አስራ ሰባት ፡- የቦውሊንግ ጨዋታን መጫወት

*ዓላማ ፡- የቦውሊንግ ጨዋታን መጫወት ይችላሉ።*

*የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፕላስቲክ ትንሽ ኳስ፣ ባዶ የሃይላንድ ላስቲኮች /የታሸገ ውሃ መያዣዎች/*

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የፕላስቲክ ትንሽ ኳስ እና ባዶ የታሸገ ውሃ መያዣዎችን በመጠቀም የቦውሊንግ ጨዋታን እንደሚከተለው ማጫወት፡-
  - *ሃይላንድ የታሸገ ውሃ መያዣዎቹን በአስር እርምጃ ርቀት መደርደር*
  - *ኳስን እንዴት እንደሚወረውሩ ማሣየት /ኳሱየታሸገ ውሃ መያዣዎችን መትቶ መጣል አለበት/*
  - *በመቀጠል ሕጻናት ስንት የታሸገ ውሃ መያዣዎች እንደወቁና ስንት እንደቀሩ እንዲናገሩ ማድረግ*
  - *በመቀጠልም እያንዳንዱ ሕፃን እንዲያከናውን በማድረግ ማጫወት*

*ምዘና ፡- የቦውሊንግ ጨዋታን መጫወት መቻላቸውን ማረጋገጥ።*

ተግባር አስራ ስምንት ፡- በዶቃዎች ውስጥ ክር ማስገባት

ዓላማ ፡- በዶቃዎች ውስጥ ክር ማስገባት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ዶቃዎች፣ ክሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያየ መጠንና ቀለም ያላቸው ዶቃዎችንና ክሮችን መስጠት
- በዶቃዎቹ ቀዳዳ ውስጥ ክሩን በመክተት የተለያዩ የአንገትና የእጅ ጌጦችን በመሥራት እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፡- በዶቃዎች ውስጥ ክር ማስገባት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አስራ ዘጠኝ ፡-መስመር ጠብቆ መቁረጥ

ዓላማ ፡- መስመር ጠብቀዉ መቁረጥ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መቀስ፣ ክላሰሮች፣ ማጣበቂያ ኮላ፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያየ ቀለም ያላቸውን ክላሰሮች በመጠቀም በሕፃናቱ ፊት በመቆም የተለያዩ መስመሮችን ተከትሎ መቁረጥ ማሳየት
- በመቀጠልም ለሕፃናቱ ወፍራም ክላሰር ወይም ወረቀትና መቀስ መስጠት
- ባዩት መሠረት ተራ በተራ ቀጥታ፣ አግዳሚ፣ ዚግዛግ፣ ወዘተ...መስመሮችን እንዲቆርጡ ማድረግ
- በመጨረሻም የቆረጡት ቅርጽ ምን እንደሆነ በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው እንዲያሳዩ ማበረታታት

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ይህን ተግባር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲተገብሩት ስለሚከብዳቸው አንድ የጂኦሜትሪ ቅርጽ መምህር ሰርተው ለሕፃናቱ በማሣየት ሕፃናቱ ሊያዩት የሚችሉበት ቦታ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡ |

ምዘና ፡- መስመር ጠብቀው መቁረጥ መለማመዳቸዉን መከታተል።


ተግባር ሀያ ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጾችን መስመር ጠብቆ መቁረጥ

ዓላማ ፦ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን መስመር ጠብቆ መቁረጥ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች ወይም ክላሰሮች፣ መቀስ፣ ማጣበቂያ ኮላ፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የተለያዩ ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች ወይም ክላሰሮችን ለሕፃናቱ በመስጠትየተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን እንዲስሉ ማድረግ
- የተሳሉትን የጂኦሜትሪ ቅርፆች መስመራቸውን ጠብቀው በመቀስ ቆርጠው እንዲያወጡ ማድረግ
- በመቀጠልም የቆራረጧቸዉን የጂኦሜትሪ ቅርፆች በማጣበቂያ በማጣበቅ ልዩ ልዩ ምስሎችን እንዲሠሩ ማድረግ
- የሰሩትንም በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው እንዲያሳዩና ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ማድረግ



ምዘና ፦ ጂኦሜትሪ ቅርጾችን መስመር ጠብቀው መቁረጥ መለማመዳቸዉን መከታተል።

ተግባር ሀያ አንድ ፦ የስጦታ ካርድ ማዘጋጀት

ዓላማ ፡- የስጦታ ካርድ ማዘጋጀት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መቀስ፣ ወፍራም ክላሰር፣ ማጣበቂያ ኮላ፣ ባለቀለም እርሳሶች፣ አሮጌ መጽሔቶች፣ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከ 4-5 ዓመት በተማሩት መሠረት ፖስት ካርዶችን ከወፍራም ክላሰር እንዲያዘጋጁ ማድረግ
- የተለያዩ ምስሎችን ከአሮጌ መጽሔቶች ላይ ቆርጠው አውጥተው እንዲለጥፉና ከጓደኞቻቸው ጋር የመልካም ምኞት ስጦታን እንዲለዋወጡ ማድረግ

ምዘና ፡- የስጦታ ካርድ ማዘጋጀት መለማመዳቸዉን መከታተል።

ተግባር ሃያ ሁለት ፡- መጻሕፍትን ማደስ

ዓላማ ፦ መጻሕፍትን ማደስ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ መቀስ፣ ወረቀት፣ ማጣበቂያ ኮላ፣ ሽፋኑ የተቀደደ መጽሐፍ፣ የተቀደዱ መጽሐፍት፣ መጽሔቶችና ደብተሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- "የተገነጡ /የታመሙ/ መጽሐፎቻችንን እናክም" የሚል ፕሮግራም ማዘጋጀት
- ለሕፃናት ዕይታ አመቺ በታ ላይ በመቆም ሽፋኑ የተቀደደውን መጽሐፍ ማሣየት
- መቀስ፣ ወረቀትና ኮላን በመጠቀም እንዴት ማደስ እንደሚቻል ረጋ ብሎ በደረጃ ማሣየት
- ሕፃናቱን በትናንሽ ቡድን በመከፋፈል የተቀደዱ መጽሐፍት፣ መጽሔትና ደብተሮችን ኮላ፣ወረቀትና መቀስ በመስጠት ወረቀቱን በመስመር ቆርጠው ኮላ ቀብተው እንዲለጥፉና እንዲያደርቁ ማድረግ
- እየተዘዋወሩ ሥራቸውን በማየት ማበረታታት ሲጨርሱም በየቡድኑ ያደሷቸውን መጽሐፍት ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ማድረግ

ምዘና ፦ መጻሕፍትን ማደስ መለማመዳቸዉን መከታተል።

ተግባር ሃያ ሦስት ፦ በአዝዕርት ኮላዥ መስራት

ዓላማ ፦ በአዝዕርት ኮላዥ መሥራትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የእህል ዘሮች፣ወፍራም ክላሰር፣ ብሩሽ፣ ማጣበቂያ ኮላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በጠረጴዛቸው ላይ የተደባለቁ ነገር ግን ሊለዩና ሊለቀሙ የሚችሉ የእህል ዘሮችንና አራት ትናንሽ የተቆራረጡ የውሃ ኮዳ /ፕላስቲክ/ መስጠት

  ለምሳሌ፦ ሽምብራ፣ ባቄላ፣ አደንጓሬ ወዘተ...

- ሕፃናት እህሎችን በዓይነቱ እንዲመድቡ ማድረግ
- ለእያንዳንዱ ሕፃን በወፍራም ክላሰር ላይ የተሰራ የአበባ ምስል መስጠት
- በትንሽ [illegible] በተዘጋጀ ብሩሽና ኮላ በመጠቀም የተሰጣቸውን ስዕል እንዲቀቡ
-

ማስታወሻ ፦ በትልቅ ክላሰር ላይ ከተለያዩ የእህል ዘሮች የተዘጋጀ የአበባ ምስል ለሕፃናቱ ዕይታ አመቺ ቦታ ላይ ማስቀመጥ ሕፃናቱ እንዴት እንደሚሰራ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

ምዘና ፦ በአዝዕርት ኮላዥ መስራት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ሃያ አራት ፦ ጥልፍ መስራት

ዓላማ ፡- ጥልፍ መስራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወፍራም ደማቅ የሱፍ ክር፣ ዱልዱም መርፌ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለሕፃናቱ ዕይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም በወፍራም ክላሰር ላይ መሠረታዊ መስመሮችን መሥራት
- መስመሩን ጠብቆ አልፎ አልፎ ምልክት ማድረግ
- በመቀጠልም ወፍራም ደማቅ የሱፍ ክርንና ዱልዱም መርፌን በመጠቀም በተሰመረው መስመር ላይ የተደረጉ ምልክቶች ላይ መርፌና ክሩን በማሳለፍ የወረቀት ላይ ጥልፍ እንዴት መሥራት እንደሚቻል ረጋ ብሎ ማሣየት
- ከዚያም ሕፃናቱ ባዩት መሠረት እንዲጠልፉ ማድረግ
- ቀስ በቀስ የጂኦሜትሪ ቅርፆችንና ቀላል ምስሎችን በመስጠት የወረቀት ላይ ጥልፍን ማለማመድ

ምዘና ፡- ጥልፍ መስራት መለማመዳቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- የጣት እንቅስቃሴዎችን መሥራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወፍራም ደማቅ የሱፍ ክር፣ ዱልዱም መርፌ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለሕፃናት ዕይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም ሁለቱንም የእጅ ጣቶች መዘርጋት
- እያንዳንዱን ጣት በማሳየት የጣቱን መጠሪያ ስም መጠየቅ ከተሳሳቱ መንገር
- ከዚያም የአንድ ጣት ስም ሲጠራ የሁለቱም እጅ የተጠሩት ጣቶችን እንዲያሳዩ ማድረግ

  ለምሳሌ፡- አውራ ጣት ሲባል እኩል አውራ ጣትን በመንካት ማሣየት በዚህ መሠረት ሁለቱንም እጃቸውን ዘርግተው መምህር የሚጠሩትን ጣት አዳምጠው በፍጥነት በመንካት እንዲጫወቱ ማድረግ
- የሁለቱንም እጆቻቸውን ጣቶች እንዲጨብጡ ማድረግ
- ቀስ በቀስ ከተጨበጡት ጣቶች ውስጥ በየተራ /ከአውራ ጣት በመነሳት እስከ ትንሿ ጣት/ ቀና በማድረግ የእጅ ጡንቻዎቻቸውን እንዲያዳብሩ ማለማመድ

ምዘና ፡- የጣት እንቅስቃሴዎችን መሥራት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ሃያ አምስት ፡- የጣት እንቅስቃሴዎችን መሥራት

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 11. በነፃነት ፈጠራን መግለጽ | 11.1. በአካባቢ ሊገኙ ከሚችሉ ቁሳቁሶች ልዩ ልዩ መጫወቻዎችን መሥራት ይችላሉ። |

**ዓላማ ፡-** ፈጠራን በስዕል መግለጽ ይችላሉ።

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡-** የስዕል ደብተር /ነጭ ወረቀት/፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ /ከለር/

**የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-**

- ለሕፃናቱ የስዕል መሣያ ነጭ ወረቀት ወይም የስዕል ደብተርና እርሳስ መስጠት
- የፈለጉትን ነገር እንዲስሉና ባለቀለም እርሳስ/ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- በስዕሉ ግርጌ ስማቸውን እና የሳሉትን ስዕል መጠሪያ እንዲጽፉ ማድረግ
- በመጨረሻም በጓደኞቻቸው ፊት በመውጣት የሳሉትን ስዕል ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ እና ማበረታታት

**ምዘና ፡-** ፈጠራን በስዕል መግለጽ መቻላቸዉን መገምገም።

**ተግባር ሁለት ፡-** ከመስመር ሳይወጡ ቀለም መቀባት

ዓላማ ፡- ከመስመር ሳይወጡ ቀለም መቀባትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የስዕል ደብተር /ነጭ ወረቀት/፣ የውሃ ቀለም፣ ጎላ ብለው የተሳሉ የተለያዩ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጎላ ብለው የተሳሉ የተለያዩ ስዕሎች ማዘጋጀት
- በመጀመሪያ ከመስመር ሳይወጣ እንዴት እንደሚቀባ ማሣየት
- ለሕፃናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ ጎላ ብሎ የተሳለ ስዕል ለእያንዳንቸው መስጠት
- በጋራ ሊጠቀሙ የሚችሉበትን የውሃ ቀለም ማቅረብ
- እየተዟዟሩባዩት መሠረት መቀባታቸውን በማየት ለከበዳቸው ልጆች ፍንጭ በመስጠት ማበረታታት
- ሲጨርሱም እንዲደርቅ በማድረግ ለክፍል ማስዋቢያነት መጠቀም

ምዘና ፡- ከመስመር ሳይወጡቀለም መቀባት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ሶስት ፡- ስዕል መሳል እና መቀባት

**ዓላማ ፦** ስዕል መሳል እና መቀባት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የስዕል ደብተር/ነጭ ወረቀት/፣ ቀለም /ከለር/፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ለሕፃናት ጎላ ብሎ የተሳለ ስዕልን በማቅረብ ስዕሉ ምን እንደሆነ መጠየቅ
- ዋና ዋና ክፍሎቹ ላይና የተቀባው ቀለም ላይ ትኩረት በማድረግ ማወያየት
- በመቀጠልም ለእያንዳንዳቸዉ የስዕል ደብተር/ወረቀት/፣ እርሳስ፣ ቀለም /ከለር/ በመስጠት እንዲስሉ እና ቀለም /ከለር/ እንዲቀቡ ማድረግ

ምዘና ፦ ስዕል መሳል እና መቀባት መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር አራት ፦ ተረትን በስዕል መግለጽ

ዓላማ ፡- ተረትን በስዕል መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የስዕል ደብተር/ነጭ ወረቀት/፣ ቀለም /ከለር/፣ እርሳስ፣ የተረት መፅሐፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለሕፃናት ተረት መንገር
- ከተረቱ ውስጥ ያስደሰታቸውን ነገር በስዕል ስሜታቸውን እንዲያንፀባርቁ ማበረታታት
- ሲጨርሱም ወጥተው ለክፍል ጓደኞቻቸው የሰሩትን እንዲናገሩ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- በየጊዜው የሕፃናቱን የስዕል ሥራዎች በመሰብሰብ የስዕል ኤግዚቢሽን በማዘጋጀት ወላጆችና ሌሎች ሕፃናትም እንዲጐበኟቸው ማድረግ ተገቢ ነዉ።

ምዘና ፡- ተረትን በስዕል መግለጽ መለማመድ መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አምስት ፡- የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን አስመስለው መተግበር

ዓላማ ፦ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን አስመስለው ይተገብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ የሰዎችን እና እንሰሳትን እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በሕጻናቱ ፊት በመቆም የተለያዩ የሰዎችን እና የእንስሳትን እንቅስቃሴ ማሣየት
- ሕፃናቱ ያዩትን እንቅስቃሴ የማን እንደሆነ እና ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- በመቀጠልም እንቅስቃሴውን በተግባር እንዲያሳዩ ማድረግ

  ለምሣሌ፦ በምርኩዝ የሚሄዱ ሽማግሌ፣ ልጅ ያዘለች ሴት፣ የኤሊ እንቅስቃሴ፣የፈረስ እንቅስቃሴ ወዘተ…

ምዘና ፦ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን አስመስለው መተግበር መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር ስድስት ፦ በአካባቢ የሚታዩ ነገሮችን በጨዋታ ማንጸባረቅ

ዓላማ ፦ በአካባቢ የሚታዩ ነገሮችን በጨዋታ ማንጸባረቅ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ለግንባታ የሚያገለግሉ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የተለያዩ የግንባታ መጫወቻዎችን ለሕጻናቱ መስጠት
- የተለያዩ የግንባታ መጫወቻዎችን ተጠቅመው በአካባቢያቸው የሚያዩዋቸውን ነገሮች እንደ ድልድይ፣ቤት፣ መንገድ፣ መኪና፣ ወዘተ…በግንባታ ጨዋታ እንዲያንጸባርቁ ማበረታታት
- በጨዋታው ሂደት እየተዘዋወሩ ምን እየሰሩ እንደሆነ በመጠየቅ ማበረታታት

ምዘና ፦ በአካባቢ የሚታዩ ነገሮችን በጨዋታ ማንጸባረቅ መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሰባት ፦ አካባቢያዊ በሆኑ ቁሳቁሶች መጫወቻዎችን መሥራት

ዓላማ ፦ አካባቢያዊ በሆኑ ቁሳቁሶች መጫወቻዎችን መሥራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ነጭ ወረቀት፣ ከለር፣ እርሳስ፣ የኮባ ወይም የሙዝ ቅጠል፣ ንፁህ የሆነ አሮጌ ጨርቅ፣ ማጣበቂያ ኮላ፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ የባለሙያ የስራ ውጤቶች/ስዕሎች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- አካባቢያዊ በሆኑ ቁሳቁሶች መጫወቻዎችን መሥራት እንደሚቻል ለሕጻናቱ ማሳወቅ
- ወረቀቶች፣ የኮባ ወይም የሙዝ ቅጠል፣ ንጹህና አሮጌ ጨርቆች ወዘተ... በመተልተል የተለያዩ መጫወቻዎችን እንዴት መስራት እንደሚቻልማሳየት
- ሕጻናት አካባቢያዊ በሆኑ ቁሳቁሶች መጫወቻዎችን ራሳቸው እየሰሩ እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፦ አካባቢያዊ በሆኑ ቁሳቁሶች መጫወቻዎችን መሥራት መለማመዳቸዉን መከታተል።

ተግባር ስምንት ፦ አካባቢያዊ በሆኑ ቁሳቁሶች የተለያዩ ጌጣጌጦችን መሥራት

ዓላማ ፦ አካባቢያዊ በሆኑ ቁሳቁሶች የተለያዩ ጌጣጌጦችን መስራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የእስክሪብቶ ቀፎዎች፣ ማጣበቂያ ኮላ፣ ክር፣ ዱልዱም መርፌ፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ የባለሙያ የስራ ውጤቶች/ስዕሎች/፣ መቀስ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የተለያዩ ደማቅ ቀለም ያላቸው ሶስት ወረቀቶችን እያንዳንቸውን በተለያየ የእስክሪብቶ ቀፎ ላይ በመጠቅለል ጫፋቸውን በኮላ ማጣበቅ
- ቀስ ብሎ የእስክሪብቶውን ቀፎ ማውጣት
- የተጣበቀውን ወረቀት በተለያየ መጠን በመቀስ በመቆራረጥ ትናንሽና ትላልቅ ቀለበቶችን ማዘጋጀት
- በቀለበቶቹ ቀዳዳ ውስጥ ክር በማስገባት የእጅ አምባር፣ የአንገት ጌጥ፣ ወዘተ... በመሥራት ለሕፃናቱ ማሣየት
- የተለያየ ቀለም ያላቸው ወረቀቶችና የእስክሪብቶ ቀፎዎችን በመስጠት ባዩት መሠረት እንዲሠሩ ማድረግ
- በየጠረጴዛቸው እየተዘዋወሩ ሲሰሩ ማየትና እገዛ ለሚያስፈልጋቸው እገዛ ማድረግ

ምዘና ፦ አካባቢያዊ በሆኑ ቁሳቁሶች የተለያዩ ጌጣጌጦችን መሥራት መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር ዘጠኝ ፦ የሥዕል መጽሐፍ ማዘጋጀት

ዓላማ ፡- የሥዕል መጽሐፍ ማዘጋጀት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ነጭ ወረቀት፣ ከለር፣ እርሳስ፣ መጽሔቶች፣ መቀስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የራሳቸውን የስዕል መጽሐፍ ማዘጋጀት እንዳለባቸው በመንገር የሕፃናቱን የመሥራት ስሜት ማነሳሳት
- ለእያንዳንዳቸው ግማሽ ወረቀት በመስጠት በሚከተለው መንገድ እርስዎን ተከትለው እንዲሠሩ ማድረግ
    - በመጀመሪያ ነጭ ወረቀቱን ጫፍ እና ጫፉን በማገናኘት ሁለት እኩል ቦታ ማጠፍ
    - በታጠፈው በኩል መልሶ አሁንም ሁለት እኩል ቦታ ማጠፍ
    - ለሶስተኛ ጊዜ በሰፊው በታጣፊው በኩል ማጠፍ
    - ቀስ ብሎ ሁለት ጊዜ የተጣፈውን ወረቀት መዘርጋት
    - ከታጠፈው በኩል አራቱ የታጠፉ መስመሮች የሚገናኙበት መሃል ድረስ ቀስ ብሎ በመቀስ መቁረጥ
    - ወረቀቱን በቁመት መዘርጋት ከመሃል የታጠፈበት ላይ በመያዝ ወደጐን መሳብ
    - በዚህን ጊዜ የመስቀል ምልክት ሲሰራ እያንዳንዱን የታጠፈ ወረቀት ወደ አንድ አቅጣጫ በትክክል በማጠፍ 4 ገጽ ያለው መጽሐፍ ማዘጋጀት
    - ከከበዳቸው እገዛ ማድረግ
- በሰሩት መጽሐፍ ገፆች ላይ የፈለጉትን ስዕል ስለው ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- የተለያዩ ስዕሎችን ከመጽሔት ላይ ቆርጠው በመለጠፍ የራሳቸውን የሥዕል መጽሐፍ እንዲያዘጋጁ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ክህሎቱን እንዲያዳብሩ በተደጋጋሚ እንዲሠሩ ማድረግ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- የሥዕል መጽሐፍ ማዘጋጀት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አስር ፡- የወረቀት መጫወቻዎችን መሥራት

ዓላማ ፦ የወረቀት መጫወቻዎችን ይሠራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ነጭ /ባለቀለም ወረቀቶች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በአየር ላይ መብረር የሚችል ነገር ምን ምን እንደሆነ ሕፃናቱን በመጠየቅ ማነቃቃት
- በመቀጠልም በአየር ላይ መብረር ከሚችሉ ነገሮች ውስጥ ሰዎች ሊሰሯቸው የሚችሉትን ነገሮች በመጠየቅ ማወያየት

ለምሳሌ፦ ጀት፣አውሮፕላን፣ ወዘተ…

- ከወረቀት መጫወቻዎች ውስጥ ምን መሥራት እንደሚፈልጉ በመጠየቅጀት የመሥራት ፍላጐታቸውን ማነሳሳት
- ወረቀት ስምንት ቦታ እኩል በመቁረጥ አንድ አንድ መስጠት
- ረጋ ብሎ ማሣየት እና በመናገር ከሕፃናቱ ጋር እንደሚከተለዉ አብሮ መሥራት
    - በመጀመሪያ የወረቀቱን ጫፍ በማገናኘት ሁለት እኩል ቦታ እንዲያጥፉ ማድረግ
    - ወረቀቱን ዘርግተው የወረቀቱን ጫፍ መስመሩን በማስነካት በሁለቱም አቅጣጫ እንዲያጥፉ ማድረግ
    - ወረቀቱን መሃከሉን ይዘው መስመሩን ተከትለው ወደኋላ እንዲያጥፉና ያጠፉትን በደንብ እንዲጫኑት ማድረግ
    - የታጠፈውን ወረቀት መሃሉን በአንድ እጃቸው በመያዝ ከላይ ጀምረው የወረቀቱን ጫፍ በሁለቱም በኩል ወደመሃል በማጠፍ መጫን
    - መሃከሉን ይዘው የታጠፈው እንዲዘረጋ በማድረግ ትንሽ ጀት መስራት
    - ስማቸውንና ዕድሜያቸውን በሠሩት ጀት ላይ እንዲጽፉ በማድረግ ጀታቸውን በክፍል ውስጥ በመወርወር እንዲጫወቱ ማድረግ

> ማስታወሻ ፦ እያንዳንዱን ደረጃ ተረጋግቶ በማሣየት አሠራሩን እንዲረዱ ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ የወረቀት መጫወቻዎችን መሥራት መቻላቸውን ማረጋገጥ።


ተግባር አስራ አንድ ፦ የተለያዩ አሻንጉሊቶችን በወረቀት መሥራት

ዓላማ ፡- የተለያዩ አሻንጉሊቶችን በወረቀት መሥራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ነጭ ወረቀት፣ ከለር፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ትልቅ ወረቀት በመያዝና ለሕፃናቱም 10 X10 ሴ.ሜ የሆነ ወረቀት በመስጠት የሚከተለውን በማሣየትና በገለፃ አብሮ መሥራት
    - በመጀመሪያ ሁለቱን ትይዩ ጫፎች በማገናኘት ወረቀቱን ማጠፍ /የሶስት ማዕዘን ቅርጽ ይሰጣል/
    - በመቀጠል ከመካከል የተወሰኑ ሴንቲ ሜትሮችን በመተው የሶስት ማእዘኑን ጫፍ ወደታች ማጠፍ
    - ከታጠፈው ውጭ ያለውን መሃል ቦታ የውሻው የፊት ምስል ዓይን፣ አፍንጫናአፍ በመሳል ትንሽ የውሻ ቡችላን በወረቀት መሥራትን ማለማመድ
    - ሲጨርሱም ጠቋሚ ጣታቸው ላይ በማድረግ በማንቀሳቀስና እንደ ውሻ ው፣ው፣ው በማለት ድምጽ በማውጣት እንዲጫወቱ ማድረግ



ምዘና ፡- የተለያዩ አሻንጉሊቶችን በወረቀት መሥራት መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ ሁለት ፡- አልባሳት እና ጭምብል /ማስክ/ መሥራት

ዓላማ ፡- አልባሳት እና ጭምብል /ማስክ/ መስራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ነጭ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ /ከለር፣ እርሳስ፣ ማጣበቂያ ኮላ፣ ክር፣ ዱልዱም መርፌ፣ባለቀለም ወረቀቶች፣ የባለሙያ የስራ ውጤቶች/ስዕሎች/፣ መቀስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- አልባሳት እና ጭምብል /ማስክ/ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማሰባሰብ
- ለእያንዳንዱ ህጻን የሚሠራውን ተግባር በመንገር /ስዕሎችን ከለር እንዲቀቡ፣ እንዲለጥፉ ወዘተ…/ የሚያስፈልገውን አልባሳት እና ጭምብል /ማስክ/ ከመምህር ጋር እንዲያዘጋጁ ማበረታታት

ምዘና ፡- አልባሳት እና ጭምብል /ማስክ/ መስራት መለማመዳቸዉን መከታተል።

ተግባር አስራ ሶስት ፡- ከተለያዩ ባለሙያዎች እና የፈጠራ ውጤቶቻቸው ጋር መተዋወቅ

ዓላማ ፦ ከተለያዩ ባለሙያዎች እና የሥራ ውጤቶቻቸው ጋር ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቀማ ፦ የባለሙያ የስራ ውጤቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በአካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ባለሙያዎችንና የሥራ ውጤቶቻውን የሚገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት

  ለምሳሌ፦ ሸማኔዎች፣ ሸክላ ሠሪዎች፣ ወዘተ…
- ሕጻናት በጉብኝቱ ከተለያዩ ባለሙያዎችና የሥራ ውጤቶቻቸው ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ
- ከጉብኝት በኋላ ስላዩት ነገር በዜና መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ

ምዘና ፦ ከተለያዩ ባለሙያዎች እና የሥራ ውጤቶቻቸው ጋር መተዋወቃቸዉን መገምገም።

ተግባር አስራ አራት ፦ በተቦካ ጭቃ/ወረቀት/ የተለያዩ ቅርጸችን/ሞዴሎችን/መሥራት

ዓላማ ፡- በተቦካ ጭቃ /ወረቀት/ የተለያዩ ቅርጾችን /ሞዴሎችን/ ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቦካ ወረቀት ወይም ጭቃ፣ የባለሙያ የሥራ ውጤቶች/ስዕሎች/፣ የጠረጴዛ ላስቲክ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ተገቢውን የጭቃ አቦካክ ስርዓት በመከተል የተቦካ ጭቃወይምወረቀት ማዘጋጀት
- ጠረጴዛዎቹን በላስቲክ በመሸፈን ጭቃውን በየጠረጴዛው ላይ ማቅረብ
- የሚፈልጉትን ነገር እንዲሠሩ ማድረግ
- ሰርተው ሲጨርሱ በትንሽ ወረቀት ላይ ስማቸውን እና የሠሩት ምን እንደሆነ እንዲጽፉ ማድረግ
- በዚህ አይነት የተለያዩ ለጨዋታ የሚያስፈልጓቸውን ቅርጾች ራሳቸው እንዲያዘጋጁና ሲደርቁም ቀለም እንዲቀቡና እንዲጫወቱባቸው ማድረግ ይቻላል

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ከተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀት የተለያዩ ቅርጾችን /ሞዴሎችን/ እንዲሠሩ በማድረግ የሥራ ውጤቶቻቸው በሌሎች እንዲጎበኝ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ተገቢ ነዉ። |

ምዘና ፡- በተቦካ ጭቃ/ወረቀት/ የተለያዩ ቅርጾችን/ሞዴሎችን/መሥራት መቻላቸውን ማረጋገጥ።


ተግባር አስራ አምስት ፡- በወረቀት መሸመን

ዓላማ ፦ በወረቀት መሽመን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወፍራም ክላሰር፣ ባለቀለም ወረቀቶች፣ ማጣበቂያ ኮላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- 1០X1០ ሴ.ሜትር የሆነ ወፍራም ክላሰርና 10X10 ሴ.ሜትር የሆኑ ደማቅ ቀለማት ያላቸው የስዕል ወረቀቶች በሕፃናቱ ቁጥር መጠን ማዘጋጀት
- ክላሰሩን ከላይ ከታች እንዲሁም ከግራና ከቀኝ 2X2 ሴ.ሜትር ገባ ብሎ ማስመር



- የውስጡን 8X8 ሴ.ሜትር የሆነውን ቦታ ከላይ ወደታች 2 ሴ.ሜትር ስፋት እንዲኖረው አድርጎ ማስመር
- የተሰመረውን የውስጠኛውን 4ቱን መስመሮች ቀስ ብሎ የላይና የታቹን እንዲሁም የግራና የቀኝ መስመሩን ሳይነካ ቀስ ብሎ መሰንጠቅ
- የስዕል ወረቀቱንም 2 ሴ.ሜትር X 10 ሴ.ሜትር ወደታች በጥብጣብ መልክ በመቁረጥ ማዘጋጀት
- መምህር ኤ ፎር ሳይዝ ክላሰር በመጠቀም ከላይ በተሰራው መሠረት የተቆረጠውን አንዱን ጥብጣብ ስስ ወረቀት በመውሰድ በክላሰሩ ውስጥ አንዴ ከላይ አንዴ ከታች በማድረግ ወደጎን በማስተላለፍ መጨረሻ ጠርዝ ላይ ሲደርስ የመጀመሪያውን እና የመጨረሻዉን ጫፍ በኮላ በማጣበቅ መሽመን

ማስታወሻ ፦ መምህር እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በተግባር እያሳዩ ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ ( ... )ነም።

**2.1.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -----------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም ------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም --------------------------------------------- ዓመተ ምህረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ ----------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት ----------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት ----------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | የአመት መጀመሪያ | የአመት አጋማሽ | የአመት መጨረሻ |
| **1.** ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመንና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | | | |
| 1.1 . ራሳቸውን መግለጽ ይችላሉ | | | |
| 1.2 . ራሳቸውን ከሌሎች ጋር በማወዳደር መግለጽ ይችላሉ | | | |
| 1.3. በጨዋታ ሂደት የሚከሰቱትን አለመግባባቶችና ግጭቶች መፍታት ይችላሉ | | | |
| **2.** የሰውነት ክፍሎችን መለየትና ተግባራቸውን መናገር | | | |
| 2.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ | | | |
| 2.2.የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውን የሚያከናውኗቸውን የተለያዩ ተግባራት በትክክል መግለጽ ይችላሉ | | | |
| **3.** ዓይኖችን መንከባከብ | | | |
| 3.1. ዓይኖቻቸው በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ | | | |
| **4.** ጆሮዎችን መንከባከብ | | | |
| 4.1. ጆሮዎቻቸውን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ | | | |
| **5.** የማሽተት ስሜት ሕዋስን መጠቀም አፍንጫን መንከበካብ | | | |
| 5.1. መጥፎና ጥሩ ሽታን መግለጽ ይችላሉ | | | |
| **6.** የመቅመስ ስሜት ሕዋስን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ | | | |
| 6.1 . የተለያየ ጣዕም ያላቸውን የተለያዩ ምግቦች ማጣጣምና ማድነቅ ይችላሉ | | | |
| 6.2 .አፋቸውን በጥንቃቄና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ | | | |
| **7.** በመዳሰስ ነገሮችንና ሁኔታዎችን መግለጽ | | | |
| 7.1. በቁሶች መካከል ያለውን ባህሪ፣ የሙቀት መጠንና ቅርጽ መለየት ይችላሉ | | | |
| 8. ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ሥርዓቶችን መለማመድ | | | |
| 8.1. ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን ለይተው መናገር ይችላሉ | | | |
| 8.2. የግል ንጽህናን መጠበቅ ይለማመዳሉ | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8.3. የራሳቸውን ንጽህን መጠበቅ ይችላሉ | | | |
| 9. አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ | | | |
| 9.1. አካላቸውን መጠበቅና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ | | | |
| 10. ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎችን መጠቀም | | | |
| 10.1. ትላልቅና ትናንሽ ጡንቻዎቻቸውን በመጠቀም የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ይችላሉ | | | |
| 11. በነፃነት ፈጠራን መግለጽ | | | |
| 11.1. በአካባቢ ሊገኙ ከሚችሉ ቁሳቁሶች ልዩ ልዩ መጫወቻዎችን መሥራት ይችላሉ | | | |

## 2.2. ተቀባይነት ባለው መልኩ ከሌሎች ጋር ግንኙነት መፍጠር

### 2.2.1. መግቢያ

ማህበራዊና ስሜታዊ ክንዋኔ ማዳበር ከህጻናት የተሟላ ስብእና መዳበር አቅጣጫዎች አንዱ ነው። አንድ ህጻን ከወላጆቹ፣ ከመምህራን፣ ክትትል ከሚያደርጉለትና ከእድሜ እኩዮቹ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በመልካም ሁኔታ እንዲዳብር ሁኔታዎች ከተመቻቹለት ህጻኑ ለራሱ እና ለሌሎች ምቹ የሆነ ማህበራዊ ህይወት እንዲኖረውና የስሜት መረጋጋት እንዲያገኝ ይረዳዋል። በህጻንነታቸው ጥሩ የሆነ ማህበራዊ ትስስርና የስሜት መረጋጋት ያላቸው በወደፊት ህይወታቸው ስኬትና በትምህርት ቤትም ጥሩ ተሳትፎ ይኖራቸዋል።

የተረጋጋ ህይወት የሚመሰረተው ከህጻንነት ጀምሮ እርጋታ ባለው እንክብካቤና በጥሩ ማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ማደግ ሲቻል ነው።

ከህጻንነቱ ጀምሮ ጥሩ የማህበራዊ ህይወት መሰረት ያልተጣለለትና የተረጋጋ ስሜት ይዞ ያላደገ ህጻን ለድብርት፣ ለቁጣ፣ በፍርሃት የሚሸማቀቅ ለመሆንና ለአሉታዊ አመለካከት የተጋለጠ ይሆናል።

ስለዚህ የማህበራዊ ህይወት መዳበርና የስሜት መረጋጋት ገና ከጠዋቱ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። መምህራን ስለ እያንዳንዱ ህጻን ባህሪይ ከወላጆች ጋር በዝርዝር በመወያየት ስለግላዊና ማህበራዊ ክንዋኔ ጠቅለል ያለ ግንዛቤ መያዝ ይኖርባቸዋል።

መምህራንም ሆኑ ወላጆች በተቻለ መጠን ለልጆች አስፈሪ ነገሮችን ባለማውራት፤ የተለያየ የማስፈራሪያ ቃላቶችና ንግግሮችን ባለመናገር፤ የራስን ፍርሃት ለልጆች ባለማሳየት ወዘተ... የህጻናቱን የተፈጥሮ የልጅነት ፍርሃት ይበልጥ እንዳይጨምር /እንዳይባባስ/ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም በአጸደ ህጻናት እድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች ማህበራዊ ግንኙነትን መመስረትና በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት መረዳትና በሚጠብቃቸው የመደበኛ ት/ቤት የተማሪነት ህይወት ከእኩያ ጓደኞቻቸው ጋር ተግባብቶና ተባብሮ መስራትን መምህራንና የት/ቤት ማህበረሰብን ማክበር፣ መታዘዝ፣ ተቀባይነት ያላቸው የኑሮ ስርዓቶችንና ልምዶችን መቀበል፣ ወዘተ... በመልመድ ዝግጁ የሚሆኑበት ዕድሜ በመሆኑ ልዩ እገዛ ያስፈልጋቸዋል።

በዚህ የዕድሜ ክልል የተመሰረተ ጥሩ ማህበራዊ ህይወትና ስነ ምግባር በልጅነት ህይወት ሆነ በወጣትነት ብሎም በሙሉ ሰውነት ወዘተ...ቢያጋጥም ተቀባይነት ከሌለው ኢ-ስነምግባራዊ አካሄድ ከመጋለጥ ሊከላከል ይችላል፡፡ ስለዚህ ለዚህ የዕድሜ ክልል ልዩ ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡

**2.2.2..** አጠቃላይ ዓላማ

1. በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎችን መመልከትና ለማወቅ ፍላጎት ማሣደር እንዲሁም ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሣየት እንዲችሉ ለማድረግ
2. ሰዎች የሚያደርጉላቸውን ጥንቃቄ መረዳትና መግለጽ እንዲችሉ ለማድረግ
3. ከሌሎች ጋር በቡድን ሥራ መሣተፍ፣ የሌሎችን ስሜት መጋራትና በበጎ ተግባር ላይ መሣተፍ እንዲችሉ ለማድረግ

**2.2.3** የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት ለማወቅ ፍላጎት ማሣደርና መለየት
   - 1.1. በቅርብ ለሚያገኙአቸው ሰዎች ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሣየት ይችላሉ
   - 1.2. ስለ ጥሩና መጥፎ ስነምግባር መናገር ይችላሉ
2. ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ
   - 2.1. ሰዎች እንዴት እንደሚጠነቀቁላቸውና እንደሚንከባከቧቸው መግለጽ ይችላሉ
3. ሌሎችን መንከባከብና ያለን ነገር ማካፈል
   - 3.1. በቡድን ሥራ ውስጥ በተገቢው መንገድ መሣተፍና የሌሎችን ስሜት መጋራት ይችላሉ
   - 3.2. በአካባቢያቸው ለሰዎች በሚደረግ በጐ ተግባር ላይ መሣተፍ ይችላሉ

2.2.4 የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት ለማወቅ ፍላጎት ማሣደርና መለየት | 1.1.በቅርብ ለሚያገኙአቸው ሰዎች ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሣየት ይችላሉ፡፡ |

ተግባር አንድ ፡- ከሌሎች ጋር በመተባበር መስራት

ዓላማ ፡- ከሌሎች ጋር በመተባበር መስራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ /ከለር/፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ወረቀትና እርሳስ በየግላቸው ባለቀለም እርሳስ /ከለር/ ደግሞ ለሁለት፣ ለአራት እንዲጠቀሙ አድርጎ መስጠት
- በመቀጠል የፈለጉትን እንዲስሉ መንገር
- ከመጀመራቸው በፊት የቀረበላቸውን ባለቀለም እርሳስ/ከለር/ በጋራ መጠቀም እንዳለባቸው ማሳወቅ
- ሳያስፈቅዱ ከለር አንስተው እንዳይጠቀሙ ማሳሰብ
- ሲዋዋሱ በትህትና በአክብሮት ቃላት መሆኑን መንገር
- ሁለት ልጆችን እንደምሣሌ አድርጎ ማሣየት
- ሲስሉ እና ከለር ሲዋዋሱ በመመልከት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ
- ስለው ሲጨርሱ የሌሎች ጓደኞቻቸውን ስዕል አይተው እንዲያደንቁ ማበረታታት
- በመጨረሻም ሁሉም የሰሩትን መደርደርና አብሮ ማየት ማድነቅ

ምዘና ፡- ከሌሎች ጋር በመተባበር መስራት መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- ሥርዓት ጠብቆ መጫወት

ዓላማ ፡- ሥርዓት ጠብቀው መጫወት ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በግቢ ውስጥ በሚገኙ መጫወቻዎች ላይ የጨዋታ ክፍለ ጊዜን ማመቻቸት
- ሲጫወቱ ሥርዓት ጠብቆ መጫወት አስፈላጊ እንደሆነ፣ ድንገት ቢጋጩ ይቅርታ መጠየቅ እንዳለባቸዉ፣ የጨዋታ ሕግን ማክበር እንደሚገባ፣ ወዘተ… ማሳሰብና ሲጫወቱ መከታተል
- በመጫወቻዎቹ ላይ በሥርዓት መጫወታቸውን እየተዘዋወሩ መመልከት
- ‹‹ውሸታሙ እረኛ›› መዝሙርን በማዘመር ስለመዝሙሩ መልዕክት እና እውነትን ስለመናገር በማስረዳት ማወያየት

ምዘና ፡- ሥርዓት ጠብቀው መጫወት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ሦስት ፡- ይቅርታ መጠየቅ እና ይቅርታ ማድረግ

ዓላማ ፡- ይቅርታ መጠየቅ እና ይቅርታ ማድረግ ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ስለሁለት በጐማ መጫወቻ ላይ ስለተጋጩ ልጆች ገጠመኝ መናገር
- ሕጻናቱ ምን ማድረግ ነበረባቸው በማለት ማወያየት
- ሌሎችን ማሣዘን ተገቢ እንዳይደለና ሌሎችን በማስከፋት/በማስቀየም/ ጊዜ ይቅርታ መጠየቅ እንደሚገባ ማስረዳት
- በጨዋታ እና በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ጊዜ ሲጋጩ ይቅርታ መጠየቅን እንዲለማመዱ ማስገንዘብ

ምዘና ፡- ይቅርታ መጠየቅ እና ይቅርታ ማድረግ መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር አራት ፡- ተቀባይነት ያለው ባህሪን ማሣየት

ዓላማ ፡- ተቀባይነት ያለው ባህሪን ማሣየት ይችላሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከወላጆች ጋር በቤታቸው ሲውሉ ምን እንደሚሠሩ መጠየቅና ማወያየት
- በቤት ውስጥ ሲታዘዙ እምቢ ማለት እንደማይገባ
- ቢያጠፉ ያስቀየሙትን ሰው ይቅርታ መጠየቅ እንደሚያስፈልግ፤ መዋሸት፣ሰው ያስቀመጠውን ዕቃ ያለፈቃድ ማንሳት፣ ወዘተ… ተገቢ እንዳልሆነ ወዘተ… ማወያየት
- በቤታቸውም ሆነ በአፀደ ሕፃናት ዉስጥ ሊያሳዩ የሚገባቸውን ተቀባይነት ያለው ባህሪ እንዲረዱ እና እንዲተገብሩ በየጊዜው ክትትልና አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ

ምዘና ፡- ተቀባይነት ያለው ባህሪን ማሣየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አምስት ፡- የብሔር ብሔረሰቦች በዓልን ማክበር

ዓላማ ፡- የብሔር ብሔረሰቦች በዓልን ማክበር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ/ከለር/፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በብሔር ብሔረሰቦች በዓል የተለያዩ አልባሳትን ለብሰው እንዲመጡ ማድረግ
- ለብሰውት ስለመጡት ልብስ ብሔር እንዲናገሩ ማበረታታት
- አልባሳቱን ስሎ መስጠት እና በባለቀለም እርሳስ/ከለር/ እንዲቀቡ ማድረግ
- በቀቡት ላይ ማወያየት

ማስታወሻ፡- በዚህ ዕለት መምህርም ባህልን የሚያንጸባርቅ ልብስ መልበስ እንዳለብዎት ያስተውሉ።

ምዘና ፡- የብሔር ብሔረሰቦች በዓልን ማክበር መለማመዳቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት ለማወቅ ፍላጐት ማሣደርና መለየት | 1.2. ስለጥሩ እና መጥፎ ሥነምግባር መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የጥሩ ሥነ ምግባር መገለጫዎች

ዓላማ ፡- የጥሩ ሥነ ምግባር መገለጫዎችን ይረዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጥሩ ባህሪ ያለዉ ጎበዝ ልጅ የሚባለዉ ምን ዓይነት ልጅ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- የህጻናቱን መልስ ካዳመጡ በኋላ ጥሩና ጎበዝ ልጅ የሚባለዉ /የምትባለዉ/
  - የማይዋሽ /የማትዋሽ/
  - ያለፍቃድ የሌሎችን ንብረት የማይነካ /የማትነካ/
  - የማይሳደብ /የማትሳደብ/
  - ሌሎችን የማያስቀይም /የማታስቀይም/
  - እዉነተኛ /ሃቀኛ/
  - ደግ
  - ታዛዥ
  - ሰዉ አክባሪ ወዘተ... ናቸው በማለት መግለጽ

ምዘና ፡- የጥሩ ሥነ ምግባር መገለጫዎችን መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- ጥሩ እና መጥፎ ሥነ ምግባርን መለየት

ዓላማ ፦ ጥሩ እና መጥፎ ሥነ ምግባርን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ስለጥሩና መጥፎስነ ምግባር የሚያወሱ መዝሙሮች /የመዝሙር ካሴቶች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ‹‹ዉሸታሙ እረኛ›› እና ‹‹ተረት ተረት›› የሚባሉትን መዝሙሮች ማዘመር
- ጥያቄ በመጠየቅ የመዝሙሩን መልእክት እንዲረዱ ማድረግ
- መዋሸትና መስረቅ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌላቸዉ ማስገንዘብ
- መዋሸትና መስረቅ ለጊዜዉ ቢያስደስቱም ዞሮ ዞሮ ግን እንደሚጎዱ መንገር
- በተደጋጋሚ እንዲዘምሩ በማድረግ ስለጥሩ እና መጥፎ ስነ ምግባር እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፦ ጥሩ እና መጥፎ ሥነ ምግባርን መለየት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ በጨዋታ ጥሩ ሥነ ምግባርን ማንጸባረቅ

ዓላማ ፡- በጨዋታ ጥሩ ሥነ ምግባርን ማንጸባረቅ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለመስሎ ጨዋታ የሚያስፈልጉ ቁሰቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የመስሎ መጫወት ጨዋታ በሚጫወቱበት ወቅት ህጻናቱ እያንዳንዳቸዉ የሚናገሩትን ቃልና የሚያደርጉትን ድርጊት መከታተል
- በጨዋታዉ ተገቢ ያልሆነ ቃልና ድርጊትን ሲናገሩና ሲያሳዩ መምህር እንደ እንግዳ በመሆን ወደ ጨዋታዉ በመግባት ማስተካከልና ማረም
- ህጻናት ጥሩ ሥነ ምግባርን ሲያሳዩ በዕድሜ እኩዮቻቸዉ ፊት እዉቅና መስጠት
- በህብረተሰባችን ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸዉን የተለያዩ ባህሪያትን የሚገልጹ ገጠመኞችን በመንገር እንዲገነዘቡ ማድረግ

  ለምሳሌ ፡- ዉሸታምነት፣ ሌብነት፣ ጉቦኝነት፣ ተሳዳቢ መሆን፣ አለመታዘዝ፣ ሰዉ አለማክበር የመሳሰሉት

ምዘና ፡- በጨዋታ ወቅት ጥሩ ሥነ ምግባርን ማንጸባረቅ መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አራት ፡- ጥሩ ሥነ ምግባርን መተግበር

ዓላማ ፡- ጥሩ ሥነ ምግባርን ይተገብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጥሩ ሥነ ምግባርን የሚያሣዩ ተከታታይነት ያላቸው ስዕሎች ወይም ጽሁፎች

ለምሣሌ፡-

| | | |
|---|---|---|
| አንድ ሽማግሌ ኮፍያቸውን ንፋስ ጣለው | አንድ ትንሽ ልጅ አየና ሮጦ አንስቶ ሰጣቸው | ሽማግሌው ልጁን አቅፈው ሳሙት አመሰገኑት |

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በስዕሎቹ ላይ ስለሚታዩት ሁኔታዎች እንዲናገሩ ማድረግ እና ማወያየት
- በዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ ጥሩ ሥነ ምግባር እንዲያዳብሩ ድጋፍ ማድረግ

ምዘና ፡- ጥሩ ሥነ ምግባርን መተግበራቸዉን መገምገም።

ተግባር አምስት ፡- በአክብሮት ምላሽ መስጠት

ዓላማ ፦ በአክብሮት ምላሽ መስጠት ይችላሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ወላጆቻቸዉ፣ መምህራንና ጓደኞቻቸዉ ሲጠሯቸዉ ምን ብለዉ መመለስ እንዳለባቸዉ ማወያየት
- ሰዉ ሲጠራቸዉ ሁልጊዜ አቤት፣ እመት ብለዉ መልስ መስጠት እንዳለባቸዉ ማስገንዘብ
- አዋቂዎች፣ ወላጅ እና መምህራን የሚሰጧቸዉን ዕቃ ሲቀበሉ እንዴት መቀበል እንዳለባቸዉ መጠየቅ እና በተግባር እንዲያሳዩ ማድረግ
- በሁለት እጃቸዉ ከአንገታቸዉ ጎንበስ ብለዉ መቀበል እንዳለባቸዉ ማስገንዘብ

ምዘና ፦ በአክብሮት ምላሽ መስጠት መቻላቸውን መከታተል።

**ተግባር ስድስት ፦ ተራ ጠብቆ መጫወት**

ዓላማ ፦ ተራ ጠብቆ መጫወት ይችላሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- በክፍል ዉስጥ እና ከክፍል ውጪ እንዲሁም በትምህርት ክፍለ ጊዜ ሊጠብቁ ስለሚገባቸው ሥነምግባሮች በመጠየቅ ማወያየት
- በግቢያቸዉ ዉስጥ ምን ምን ዓይነት መጫወቻዎች እንዳሉ፣ ብዛታቸዉ ምን ያህል እንደሆነ እና በይበልጥ በየትኛዉ መጫወቻ መጫወት እንደሚወዱ መጠየቅ
- በግቢ ዉስጥ ያሉት መጫወቻዎች የማን እንደሆኑና እንዴት መጫወት እንዳለባቸዉ በመጠየቅ ማወያየት
- በግቢ ዉስጥ ያሉት መጫወቻዎች የሁሉም ህጻናት እንደሆኑና ተራ ጠብቀዉ በሥርዓት መጫወት እንዳለባቸዉ ማስገንዘብ
- በእረፍት ጊዜያቸዉና ነጻ ጨዋታን በሚጫወቱበት ጊዜ ተራን ጠብቀዉ መጫወት መቻላቸዉን መከታተል
- ተራ ጠብቀዉ በሥርዓት የተጫወቱትን ማሞገስና ማበረታታት፤ ያልተጫወቱትን ደግሞ እንዴት መጫወት እንዳለባቸዉ ማስረዳት

ምዘና ፦ ተራ ጠብቆ መጫወት መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር ሰባት ፦ የጨዋታ ሕግን ማክበር

ዓላማ ፡- የጨዋታ ሕግን ማክበር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለጨዋታዉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በህግ የሚመሩ ጨዋታዎችን ማጫወት
- የጨዋታዉን ሂደትና ህግን እንዲገነዘቡ ማድረግ
- የጨዋታዉን ህግ በማክበር አብረዉ እንዲጫወቱ ማድረግ

  ለምሳሌ፡- ንጉስ ንጉስ ሆይ፣ ያዕቆብ፣ አረንጓዴ አረንጓዴ፣ የጠፋዉን ፈልገህ አግኝ ወዘተ…
- የጨዋታዉን ህግ ካላከበሩ ከጨዋታ ዉጪ እንዲሆኑ ማድረግ
- ለህግ ተገዢነትን ከልጅነታቸዉ ጀምሮ በማለማመድ በዉስጣቸዉ እንዲሰርጽ ማድረግ

ምዘና ፡- የጨዋታ ሕግን ማክበር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስምንት ፡- ጥሩ እና መጥፎ ሥነ ምግባርን በድራማ ማሣየት

ዓላማ ፡- ጥሩ እና መጥፎ ሥነ ምግባርን በድራማ ማሣየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለድራማ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከህጻናቱ ጋር አልባሳትንና ጭንብል በማዘጋጀት ‹‹ጥንቸል ጉረኛ›› መዝሙርን ወደ ድራማ ቀይረዉ ለሌሎች ህጻናትና ለወላጆች እንዲያቀርቡ ማድረግ
- ‹‹ጥንቸል ጉረኛ›› መዝሙርን በማዘመር በጥያቄና መልስ የመዝሙሩን መልዕክት እንዲረዱ ማድረግ

- ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ፣ መኩራራትና ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማየት ተገቢ እንዳልሆነ ማስገንዘብ
- መዝሙሩን ለሌሎች ህጻናትና ለወላጆች በድራማ መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ጥሩ እና መጥፎ ሥነ ምግባርን በድራማ ማሣየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ዘጠኝ ፡- በቡድን ሥራ ላይ መሣተፍ

ዓላማ ፡- በቡድን ሥራ ላይ መሣተፍ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ገመድ፣ ዱላዎች፣ ኳስ ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከክፍል ዉጪ ህጻናቱን በሁለት ቡድን መመደብ
- የተለያዩ ስፖርታዊ ዉድድሮች ላይ ሁሉም ህጻናት እንዲሳተፉ ማድረግ
- ለቡድን ዉጤት በጋራ መስራት፣ መተባበር፣ መተሳሰብ፣ ለቡድን አባላት ድጋፍ /ሞራል/ መስጠት እና ማበረታታት አስፈላጊ እንደሆነ እንዲገነዘቡ ማድረግ
  ለምሳሌ፡- ‹‹ዱላ ቅብብል››፣ ‹‹ማን ቀድሞ ይገባል?››፣ ‹‹ጭራ ነቀላ››፣ ወዘተ…
- በመጨረሻም እያንዳንዱ ቡድን ራሱ የሚፈልገዉን መዝሙር በመምረጥ እንዲዘምር ማድረግ

ምዘና ፡- በቡድን ሥራ ላይ መሣተፍ መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አስር ፡- በሕብረት መስራት

ዓላማ ፦ በህብረት የመስራት ክህሎት ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጓንት/ስስ ፌስታል/፣ የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት፣ ዉሃ፣ ሳሙና

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ለግቢ ጽዳት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ማዘጋጀት
- ህጻናቱን በቡድን በመከፋፈል ለየቡድኑ የተለያየ የስራ ድርሻ መስጠት
- የእያንዳንዱን ቡድን ስራ በመገምገም ማበረታቻና ድጋፍ መስጠት
- በህብረት በመስራት ዉጤት ላይ የመድረስን ጥቅም እንዲረዱ ማድረግ
- ሲጨርሱ እጃቸዉን እንዲታጠቡ ማድረግ

ምዘና ፦ በህብረት የመስራት ክህሎት ማዳበራቸዉን መከታተል።

ተግባር አስራ አንድ ፦ ጥሩ እና መጥፎ ሥነ ምግባርን በድራማ ማሣየት

ዓላማ ፡- ጥሩ እና መጥፎ ሥነ ምግባርን በድራማ ማሣየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለድራማ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከህጻናቱ ጋር አልባሳትንና ጭንብል በማዘጋጀት ‹‹ጥንቸል ጉረኛ›› መዝሙርን ወደ ድራማ ቀይረዉ ለሌሎች ህጻናትና ለወላጆች እንዲያቀርቡ ማድረግ
- ‹‹ጥንቸል ጉረኛ›› መዝሙርን በማዘመር በጥያቄና መልስ የመዝሙሩን መልዕክት እንዲረዱ ማድረግ
- ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ፣ መኩራራትና ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማየት ተገቢ እንዳልሆነ ማስገንዘብ
- መዝሙሩን ለሌሎች ህጻናትና ለወላጆች በድራማ መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ጥሩ እና መጥፎ ሥነ ምግባርን በድራማ ማሣየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ ሁለት ፡- የወላጆች ቀንን ማክበር

**ዓላማ ፡- የወላጆች ቀንን ማክበር ይችላሉ።**

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለድራማ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የወላጆች ቀን ላይ ህጻናት በተለያዩ ፕሮገራሞች ስራ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ
- በህብረት በመስራት ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት

  ለምሳሌ፡- የመዝሙር፣ የስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ኤግዚቢሽን በማስጎብኘት የመሳሰሉት

ምዘና ፡- የወላጆች ቀንን ማክበር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ | 2.1 . ሰዎች እንዴት እንደሚጠነቀቁላቸውና እንደሚንከባከቧቸው መግለጽ ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ ፡- ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየት**

ዓላማ ፡- ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለድራማ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በክፍላቸው ውስጥ ለእነርሱ እንክብካቤ የሚያደርጉ ሰዎች እነማን እንደሆኑ መጠየቅ
- ማን ምን እንደሚያደርጉላቸው በመጠየቅ ማወያየት

  ለምሳሌ፡-መምህር፣ ሞግዚት፣ የጽዳት ባለሙያ፣ ወዘተ…
- ሁሉም ለሚያደርጉላቸው እንክብካቤ ማክበር እና ሥራቸውን መደገፍ እንዳለባቸው ማስረዳት
- በመጨረሻም የላሊቱ ሉሊት ተረት በመተረት አዳምጠው መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየታቸዉን ማረጋገጥ።

**ተግባር ሁለት ፡- ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች ስዕል መሳል**

ዓላማ ፡- ጥንቃቄ እና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች ስዕል መሳል ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ /ከለር/ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች እንዲስሉ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ/ከለር/መስጠት

- የሰሩትን ስእል እየዞሩ በመመልከት እየሳሉ ያሉት የማንን ምስል እንደሆነ መጠየቅ
- ለምን ይህን ሰው መሳል እንደመረጡ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች ስዕል መሳል መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ሶስት ፡- በጨዋታ ጥንቃቄ እና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች ማንጸባረቅ

ዓላማ ፡- በጨዋታ ጥንቃቄ እና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች ማንጸባረቅ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለመስሎ ጨዋታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች እንዲስሉ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ/ከለር/መስጠት
- የሰሩትን ስእል እየዞሩ በመመልከት እየሳሉ ያሉት የማንን ምስል እንደሆነ መጠየቅ
- ለምን ይህን ሰው መሳል እንደመረጡ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታሰዎች እንዴት እንደሚንከባከቧቸው በድርጊት እንዲያሣዩ በቅድሚያ ማሳየት

ለምሣሌ፡- ልብስ ያለብሱኛል ለማለት መልበስን ማሣየት ወዘተ....

- ለአስቸኳይ ጉዳይ እናለአደጋ ግዜ ስልክ መደወል እንደሚያስፈልግ ማስገንዘብ
- በመቀጠልም በመስሎ መጫወት ማዕዘን ይህንኑ እያንፀባረቁ እንዲጫወቱ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- በተለያየ ክፍለ ጊዜ ስለ መምህር፣ ፖሊስ፣ ዶክተር፣ ነርስ፣ ወዘተ... እንዲወያዩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- በጨዋታ ጥንቃቄ እና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች ማንጸባረቅ መቻላቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. ሌሎችን መንከባከብና ያለንን ነገር ማካፈል | 3.1. በቡድን ሥራ ውስጥ በተገቢው መንገድ መሳተፍና የሌሎችን ስሜት መጋራት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የመደሰት እና የመከፋት ስሜትን መለየት

ዓላማ ፡- የመደሰትን እና የመከፋት ስሜትን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመደሰት እና የመከፋት ስሜት የሚታይባቸው የህጻናት ፎቶግራፎች /ስዕሎች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ፎቶግራፎቹን /ስዕሎቹን/ ማሳየት
- በሚያዩዋቸዉ ምስሎች ላይ የሚታየዉን ስሜት የመከፋት ወይስ የመደሰት መሆኑን ለመናገር እንዲሞክሩ ማበረታታት
- በስእሉ ላይ ያለዉ/ያለችዉ/ ህጻን ምን እንዳስደሰተዉ /እንዳስደሰታት/፣ ምን እንዳስከፋዉ /እንዳስከፋት/ እንዲናገሩ ማድረግ
- እነርሱ ምን ሊያስከፋቸዉና ምን ሊያስደስታቸዉ እንደሚችል እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የመደሰት እና የመከፋት ስሜትን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር ሁለት ፡- የሌሎችን ስሜት መረዳት

**ዓላማ ፦ የሌሎችን ስሜት መረዳት ይችላሉ::**

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ተከታታይነት ያላቸው ሥዕሎች**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ተከታታይነት ያላቸውን ስዕሎች በማቅረብ አብረው እየሰሩ ያሉ ሰዎችን ስሜት በሚገባ እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፦ የሌሎችን ስሜት መረዳት መቻላቸውን መከታተል።

ዓላማ ፦ የሌሎችን ስሜት መገንዘብ ይለማመዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ለጽዳትና ለጥገና የሚጠቅሙ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተረኝነት ሰሌዳን በመጠቀም በሕብረት ሥራ፣ በትምህርታዊ ፕሮግራሞችና የቡድን ሥራዎች እንዲሳተፉ ማድረግ

  ለምሣሌ፦ በክፍል ውስጥ የጽዳት ሥራ፣ መርጃ መሣሪያዎችን ማጽዳት፣ አትክልትን መንከባከብ፣ ወዘተ...

- በተሳትፎ ሂደት ተባብሮ ሥራን በመጋራት መሥራት እንዳለባቸው ማስረዳት
- ሲሰሩ የሌሎችን አብረዋቸው የሚሠሩትን ጓደኞቻቸውን ስሜት ማስተዋል ይችሉ እንደሆነ መከታተል

ምዘና ፦ የሌሎችን ስሜት መገንዘብ መቻላቸዉን መገምገም፡፡

**ተግባር አራት ፦ የመዝሙርን መልዕክት መረዳት**

ዓላማ ፦ የመዝሙርን መልዕክት መረዳት ይችላሉ እንዲሁም የመዝሙርን መልዕክት በመረዳት ስሜታቸውን መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተለያዩ መዝሙሮችን አብረው እንዲዘምሩ ማድረግ
- የመዝሙሩን መልእክት እንዲናገሩ ማድረግ
- በመዝሙሩ የተሰማቸውን ስሜት እንዲናገሩ ማበረታታት

ማስታወሻ ፦ መምህር የሚመርጧቸው መዝሙሮች በተቻለ መጠን ስለሰዎች ስሜት የሚገልጹ ቢሆን ይመረጣል።

ምዘና ፦ የመዝሙርን መልዕክት መረዳት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፦ የሌሎችን ስሜት መግለጽ

ዓላማ ፡- የሌሎችን ስሜት መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለጽዳትና ለጥገና የሚጠቅሙ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሰዎች ሲደሰቱ፣ ሲያዝኑና ሲቆጡ እንዴት ዓይነት ስሜት እንደሚታይባቸዉ በተግባር እንዲያሳዩ ማበረታታትና ለማሳየት የሚያደርጉትን ጥረት ማድነቅ
- ሌሎች ጓደኞቻቸዉ የትኛዉ የስሜት አገላለጽ እንዳስደሰታቸዉና የትኛዉ እንዳላስደሰታቸዉ አስተያየት እንዲሰጡ ማበረታታት
- ስሜትን በአግባቡ የመግለጽን አስፈላጊነት ማስረዳትና ሰዎችን በማይጎዳ መልኩ ስሜትንመግለጽ ማለማመድ

ምዘና ፡- የሌሎችን ስሜት መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- የሌሎችን ስሜት መጠበቅ

ዓላማ ፡- የሌሎችን ስሜት መጠበቅ ይለማመዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለጽዳትና ለጥገና የሚጠቅሙ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሌሎችን ሳይረብሹና ሳያሳዝኑ እንዴት ስሜታቸዉን መግለጽ እንደሚችሉ እንዲናገሩ ፍንጭ በመስጠት መጠየቅ

ለምሳሌ፡- በመጫወቻ ቁሳቁስ፣ በቦታ፣ በጨዋታ ጊዜ መጣላት ወዘተ…

- በየዕለቱ የሚያጋጥማቸዉን የእርስ በእርስ ግጭት የሚያንጸባረቁ ገጠመኞችን መናገር

ምዘና ፡- የሌሎችን ስሜት መጠበቅ መለማመዳቸዉን መከታተል።

ተግባር ሰባት ፡- የተለያዩ ገጸባህሪያትን ማንጸባረቅ

ዓላማ ፦ የተለያዩ ገጸባህሪያትን ማንጻባረቅ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መጽሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- <<የትንሹ ዮናስ>> እና <<በድሉ በረኛዉ>> ተረቶችን መተረክና ስለዮናስ እና ስለ በድሉ የተሰማቸዉን ስሜት በመጠየቅ ማወያየት
- የዮናስንና የበድሉን ገጸ ባህሪያት ተላብሰዉ ስሜታቸዉን እንዲያንጸባርቁ ማበረታታት
- <<ማነዉ የሚበልጠዉ>> ተረት መተረትና ሶስቱ ባለታሪኮች በየደረጃቸዉ የሚገኙበትን ስሜት በመጠየቅ ማወያየት
- የ<<ዉርዬና ቦቢን>> ተረት ማንበብና የዉርዬና ቦቢን ስሜት እንዲያንጸባርቁ ማድረግ

> ማስታወሻ ፦ እነዚህን ተረቶች እንደሚወስዱት ጊዜ እና እንደ ህጻናቱ ብዛት በተከታታይ ክፍለ ጊዜያት መተግበር ይቻላል።

ምዘና ፦ የተለያዩ ገጸባህሪያትን ማንጸባረቅ መቻላቸውን መከታተል።

## ተግባር ስምንት ፦ ግጭትን መፍታት

ዓላማ ፡- ግጭትን መፍታት ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- እርስ በእርሳቸዉ ሲጫወቱ የሚያጋጥሟቸዉን ያለመግባባት ችግሮች እንዲናገሩ ማድረግ
- በጨዋታ ሲሸነፉ አለመቆጣት፣ ሌሎችን አለማስቀየም፣ ሲያስቀይሙ ይቅርታ መጠየቅና ይቅርታ ማድረግ እንዳለባቸዉ ማስረዳትና ማለማመድ

ምዘና ፡- ግጭትን መፍታት መለማመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. ሌሎችን መንከባከብ ያለንን ማካፈል | 3.2. በአካባቢያቸው ለሰዎች በሚደረግ በጎ ተግባር መሳተፍ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- በጨዋታ የሌሎችን ስሜት ማንጸባረቅ

ዓላማ ፡- በጨዋታ የሌሎችን ስሜት ማንጸባረቅ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ ዕድሜ ያላቸው ሰዎችን ሆነው ድራማ እንዲሰሩ የሚያስፈልጉ አልባሳት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በመስሎ መጫወት ጨዋታ ሌሎችን ሰዎች መስለው እንዲጫወቱ እና በጎ ምግባሮችን እንዲያንፀባርቁ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማጫወት

ምዘና ፡- በጨዋታ የሌሎችን ስሜት ማንጸባረቅ መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ሁለት ፡- በተለያየ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎችን መለየት

ዓላማ ፡- በተለያየ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎችን መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ ዕድሜ ያላቸው ሰዎች ፎቶግራፍ ወይም ስዕል /ሽማግሌ፣ ሕፃን፣ልጅ…/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያየ ዕድሜ ያላቸው ሰዎችን ፎቶግራፍ /ስዕል/ ማሣየት
- በፎቶግራፍ ወይም ስዕሉ ላይ የሚያዩዋቸውን ሰዎች የዕድሜ ክልል እንዲናገሩ ማወያየት /ሽማግሌ፣ ሕፃን፣ልጅ…/
- ከዚያም ፎቶግራፎቹን እያሳዩ መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በተለያየ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- ሌሎችን ማገዝ

ዓላማ ፡- ሌሎችን ማገዝ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መፅሃፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሌሎች ሰዎች አካባቢን በማጽዳት ተግባር ሲሳተፉ አብረው በመሆን ያቅማቸውን እንዲያደርጉ በተረት መልክ መንገር
- በቤታቸዉ አብረዋቸዉ የሚኖሩትን ሰዎች በስራ ያግዙ እንደሆነ መጠየቅ
- የሚያግዙ ከሆነ በምን ዓይነት ስራ ላይ ያግዟቸዉ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- በቤት ዉስጥ በአቅማቸዉ መላላክ፣ መታዘዝ፣ የተጫወቱበትን መጫወቻ መሰብሰብና ወላጆቻቸዉ ስራ ሲይዙ ታናናሾቻቸዉን መጫወት እንዳለባቸዉ እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ሌሎችን ማገዝ መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር አራት ፡- ከሌሎች ጋር በመተባበር መሥራት

ዓላማ ፡- ከሌሎች ጋር በመተባበር መሥራት ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የመማሪያ፣ የመመገቢያና የመኝታ ክፍልን በማሰናዳት ሂደት ላይ ህጻናት አብረዉ ከመምህራን ጋር በመተባበር ሌሎችን የመርዳት ክህሎትን እንዲያዳብሩ እገዛ ማድረግ
- በመጫወቻ ቦታ ላይ ከመምህራን ጋር አብረዉ በመሆን ትናንሽ ህጻናትን በማጫወት የሚሳተፉበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት መምህራንና ታናናሾቻቸዉን እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ከሌሎች ጋር በመተባበር መሥራት መለማመዳቸዉን መከታተል።

ተግባር አምስት ፡- ለሌሎች ማካፈል

ዓላማ ፡- ለሌሎች ማካፈል ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በቅድመ መደበኛ ት/ቤት የችሮታ ቀን ማዘጋጀት
- ህጻናት በቤታቸዉ የተቀመጡ የጠበቧቸዉና የማይለብሷቸዉን አልባሳት በማምጣት ለተቸገሩ ህጻናት /ሰዎች/ የሚረዱበት ሁኔታ በማመቻቸት ሌሎችን በተቻለ አቅም የመርዳት ፍላጎት በዉስጣቸዉ እንዲሰርጽ ማድረግ
- በአካባቢያቸው /በቤታቸው/ ሲውሉ ቤተሰቦቻቸው ምን እንደሚሠሩ መጠየቅ
- ሲናገሩም ሐሳባቸውን በማዳመጥ አቅጣጫ ማስያዝ
- ዘመድ፣ የታመመ ሰው መጠየቅ ጥሩ እንደሆነ ማስረዳት
- ለተቸገሩ ማየት ለማይችሉ፣ ለአካል ጉዳተኞች እገዛ ማድረግ እንደሚገባ ገጠመኝ በማውራት ማስረዳት

ማስታወሻ ፡- ወላጆች፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንና ሰራተኞችም ለህጻናቱም አርአያ መሆን ይኖርባቸዋል።

ምዘና ፡- ለሌሎች ማካፈል መለማመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- ከሌሎች ጋር መካፈል

ዓላማ ፡- ከሌሎች ጋር መካፈል ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለአሻንጉሊት መስሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለአሻንጉሊት መሥሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን በማቅረብ አብሮ ሁለት አሻንጉሌቶች መሥራት
- ከዚያም በአንዱ አብሮ መጫወት
- ሌላውን ደግሞ ለሌላ ክፍል /ለትንንሾች/ ስጦታ አብሮ በመሆን እንዲሰጡ ማድረግ

ምዘና ፡- ከሌሎች ጋር መካፈል መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

## **2.1.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ

**2.1.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም ------------------------------------------ ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም -------------------------------------------- ዓመተ ምህረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ ------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት --------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት --------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ^ | | |
|---|---|---|---|
| | የዓመት መጀመሪያ | የዓመት አጋማሽ | የዓመት መጨረሻ |
| **1.** በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት ለማወቅ ፍላጐት ማሣደርና መለየት | | | |
| 1.1 .በቅርብ ለሚያገኙአቸው ሰዎች ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሣየት ይችላሉ፡፡ | | | |
| 1.2. ስለ ጥሩና መጥፎ ስነምግባር መናገር ይችላሉ | | | |
| **2.** ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ | | | |
| 2.1. ሰዎች እንዴት እንደሚጠነቀቁላቸውና እንደሚንከባከቧቸው መግለጽ ይችላሉ፡፡ | | | |
| **3.** ሌሎችን መንከባከብና ያለንን ነገር ማካፈል | | | |
| 3.1 .በቡድን ሥራ ውስጥ በተገቢው መንገድ መሣተፍና የሌሎችን ስሜት መጋራት ይችላሉ | | | |
| 3.2. በአካባቢያቸው ለሰዎች በሚደረግ በጐ ተግባር ላይ መሣተፍ ይችላሉ | | | |

## 2.3. ቋንቋን በአግባቡ መጠቀም

### 2.3.1 ማብራሪያ

ቋንቋ መግባቢያና ሃሳብን፣ ፍላጐትን፣ ስሜትን ለሌላው ለመግለጽ የሚያስችል መሣሪያ ነው። ከ 5-6 ዓመት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ህጻናት ሰዎች የሚናገሩትን አስተውለው ማዳመጥና አድማጩ ሊረዳው እና ሊገባው በሚችል መልኩ ሃሳባቸውን፣ ፍላጐታቸውንና ስሜታቸውን ለመግለጽ ይሞክራሉ። ከዚህ በተጨማሪም በይበልጥ ለመደበኛ ት/ቤት የሚዘጋጁበት ዕድሜ እንደመሆኑ መጠን አብዛኛውን ፊደላት በድምጽና በቅርጽ መለየትና አስመስለው ለመፃፍ የመሞከር ዝንባሌ ይታይባቸዋል።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንም ከላይ የተጠቀሰውን የሕፃናቱን ችሎታና ዝንባሌ ከግምት ውስጥ በማስገባትና ዕድሜ ብቻውን ለውጥን እንደማያመጣ በመገንዘብ ለሕፃናቱ የቋንቋ ክህሎት መዳበር ምቹ አካባቢን በመፍጠር ተገቢውን እገዛ በማድረግ ሕፃናት ለመደበኛ ት/ቤት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

### 2.3.2 አጠቃላይ ዓላማዎች

1. በአካባቢያቸው የሚደመጡ ድምፆችን መለየትና ለትዕዛዞችና መመሪያዎች ምላሽ የመስጠት ችሎታንና ዝንባሌን እንዲያዳብሩ ማድረግ፤
2. በደረጃቸው የሚቀርቡ ተረቶችንና መዝሙሮችን አስተውለው በማዳመጥ ያለማንም እርዳታ መተረትና መዘመር እንዲችሉ ማድረግ፤
3. ራሳቸውን በተገቢው መንገድ በመግለጽ አስተውለው የማዳመጥና ሃሳብን በንግግር የመግለጽ ችሎታቸው እንዲዳብር ማድረግ፤
4. አብዛኛውን ፊደላት በድምጽና በቅርጽ በመለየት ቀላል ቃላቶችንና ዓረፍተ ነገሮችን ማንበብን እንዲለማመዱ ማድረግ፤
5. የተዋወቋቸውን ፊደላትንና ቃላትን አስመስለው መፃፍን እንዲለማመዱ ማድረግ፤

### 1.3.3 የሚጠበቅ ውጤትና ብቃት

1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት
    1.1. በአካባቢ የሚደመጡ ድምፆችን መለየት ይችላሉ
    1.2. በድምፆች መካከል ያለውን ልዩነት መለየት ይችላሉ
    1.3. ለትዕዛዞችና ለመመሪያዎች ምላሽ መስጠት ይችላሉ

2. ተረቶችን አዳምጠው የተረዱትን መግለጽና መልሰው መተረክ ይችላሉ
   2.1. በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግርና የምልክት ቋንቋ መግባባት
   2.2. ቋንቋን በእርግጠኝነት መጠቀም ይችላሉ
   2.3. በንግግር ቋንቋ ደስታን ማግኘት ይችላሉ
3. በማንበብ መደሰት ዕውቀት ማግኘትና መረዳት
   3.1. ቀላል ቃላቶችንና ዓረፍተ ነገሮችን ማንበብ ይችላሉ
4. የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት
   4.1. ፊደላትንና ቃላትን መፃፍ ይችላሉ

2.3.4 የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥ እና ለተለየዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.1. በአካባቢ የሚደመጡ ድምፆችን መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ ድምፆችን መለየት

ዓላማ፡- ድምፆችን መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- የተቀረፁ የእንሰሳት ድምፅ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተቀረጹ የበግ፣ የዉሻ፣ የድመት፣ የላም ድምጽን በየተራ ማስደመጥ
- ያዳመጡት ድምጽ የምን ድምጽ እንደሆነ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግ
- በተቻለ መጠን አንዱን ድምጽ አዳምጠዉ የምን እንደሆነ ሳይለዩ ወደሌላ ድምጽ አለመሄድ
- በተጨማሪም በአካባቢያቸው በአብዛኛው የምን ድምጾችን እንደሚሰሙ በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፡- ድምፆችን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- የድምጽ አቅጣጫን መለየት

ዓላማ፡- የድምጽ አቅጣጫን ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በክፍል ዉስጥ በተቀመጡበት ቦታ ዐይናቸዉን እንዲጨፍኑ በማድረግ አንድ ቦታ /ከጀርባ፣ ከጎን/ በመሆን አንድ አይነት ድምጽ ማሰማት

ለምሳሌ፡- ማጨብጨብ፣ በእግር መሬት መምታት፣ መጽሀፍ ማገላበጥ ወዘተ …

- ድምጹን ካዳመጡ በኋላ ዐይናቸዉን እንዲገልጡ ማድረግ
- ያዳመጡት ድምጽ ከየት አካባቢ እንደሆነ አቅጣጫዉን እንዲጠቁሙ ማድረግ
- በዚህ ዓይነት ሁሉንም በማሳተፍ የድምጽ አቅጣጫን የመለየት አቅማቸዉን ማዳበር

ምዘና ፡- የድምጽ አቅጣጫን መለየት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ሶስት ፡- ድምፅን አስመስሎ ማውጣት

ዓላማ፡- ድምፆችን አስመስለው ማውጣት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቤት እንሰሳት ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጎላ ብሎ የሚታይ የቤት እንስሳት ስዕሎችለሁሉም ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ መለጠፍ ወይም በእጅ መያዝና ማሳየት

  ለምሳሌ፡- የበግ፣ የፍየል፣ የድመት ወዘተ…
- መጠሪያ ስሙን፣ የት እንደሚኖር፣ ምን እንደሚመገብ በመጠየቅ ማወያየት
- ድምጹን አስመስለው በህብረት እንዲያሰሙ መጠየቅ

ምዘና ፡- ድምጽን አስመስለው ማዉጣት መቻላቸውን መገምገም::

ተግባር አራት ፡- ትዕዛዝ ተቀብሎ መተግበር

ዓላማ፡- ትዕዛዝ ተቀብለዉ መተግበር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክላሰር፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ/ከለር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከወረቀት የንጉስ ዘዉድ ማዘጋጀት
- <<ንጉስ ንጉስ ሆይ>> ጨዋታን ለመጫወት ስድስት ፈቃደኛ ህጻናትን መምረጥ
- ከተመረጡት አንዱን ንጉስ በማድረግ የንጉሱን ዘዉድ እንዲጭንና ከፍ ባለ ቦታ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ማድረግ
- የተቀሩት አምስቱ ህጻናት ከንጉሱ የተወሰነ ሜትር ያህል ራቅ ብለዉ በመደዳ እንዲቆሙ ማድረግ
- በየተራም እያንዳንዱ ህጻን በንጉሱ ፊት ጎንበስ በማለት <<ንጉስ ንጉስ ሆይ>> እንደምን ሆኜ ልምጣ? በማለት እንዲጠይቅ ማድረግ
- ንጉሱም ህጻናት ከሚያወቋቸዉ እንስሳቶች ወይም ሰዎች /ኤሊ፣ ወታደር፣ እንቁራሪት ወዘተ…/ አንዱን በመጥራት በየእርምጃ መጠን በመጥቀስ ማዘዝ

ለምሳሌ፡-እንደ እንቁራሪት ሁለት እርምጃ፣ እንደ ወታደር አንድ እርምጃ ወዘተ …

- ህጻኑ በንጉስ የታዘዘዉን በመፈጸም የደረሰበት ቦታ ላይሌላ ዙር እስኪደርሰዉ ቆሞ እንዲጠብቅ ማድረግ
- በዚህ ዓይነት የታዘዘዉን በአግባቡ ፈጽሞ ንጉሱ አጠገብ የደረሰ ንጉስ ይሆናል
- በዚህ መልኩ ህጻናት እየተቀያየሩ ጨዋታዉን እንዲጫወቱ ማድረግ ይቻላል
- ለመጀመሪያ ንጉስ የሚሆነዉ መምህር ቢሆን ይመረጣል

ምዘና ፡- የተለያዩ ትዕዛዞችን ተቀብለዉ መተግበር መቻላቸዉን መከታተል፡፡

ተግባር አምስት ፡- የጨዋታ ህግ ተከትሎ መጫወት

ዓላማ፡- የጨዋታን ህግ ተከትለዉ መጫወት ይችላሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህጻናቱን በቡድን መከፋፈል
- <<አረንጓዴ አረንጓዴ>> የተባለዉን ጨዋታ እንዴት እንደሚጫወቱ የጨዋታዉን ህግ ማስረዳት
- በመመሪያዉ ወይም በህጉ መሰረት መጫወት መቻላቸዉን መከታተል።

ምዘና ፡- የጨዋታ ህግ ተከትለው መጫወታቸዉን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.2 በድምፆች መካከል ያለውን ልዩነት መለየት ይችላሉ። |

## ተግባር አንድ ፡- ሰዎችን በድምጽ መለየት

ዓላማ፡ [illegible]

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክላሰር፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ/ከለር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የጠራህን እወቅ የሚባለዉን ጨዋታ ማጫወት
    - በቅድሚያ የጨዋታዉን አጨዋወትና ህግጋት ለህጻናቱ ማስገንዘብ
    - በመቀጠል 6 ህጻናትን ማስነሳትና በጓደኞቻቸዉ ፊት እንዲቆሙ ማድረግ
    - ከመካከላቸዉ አንዱን በፍቃደኝነት /በመጠቆም/ ተጠያቂ ተጫዋች ማድረግ
    - ተጠያቂ ተጫዋቹ/ቿ ህጻን ፊቱን ከህጻናቱ መልሶ እንዲቆም ማድረግ
    - ከአምስቱ አንዱ ፊቱን ከህጻናቱ መልሶ የቆመዉን ህጻን ድምጹን ከፍ አድርጎ በስም እንዲጠራዉ ማድረግ
    - ፊቱን/ፊቷን ከህጻናቱ መልሶ/መልሳ የቆመዉ ህጻን ስሙ ሲጠራ ማን እንደጠራዉ እንዲናገር ማድረግ
    - በመጨረሻም የህጻኑ መልስ ትክክል መሆን አለመሆኑን የክፍሉ ህጻናት ማረጋገጫ እንዲሰጡ ማድረግ
- በዚህ ዓይነት ቡድኑን በመቀያየር ሁሉም ህጻናት እንዲሳተፉ ማድረግ

ምዘና ፡- ሰዎችን በድምጽ መለየት መቻላቸውን መገምገም፡፡

## ተግባር ሁለት ፡- ድምጽን አስመስሎ ማውጣት

ዓላማ፡- ድምጽን አስመስሎ ማውጣት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ እንሰሳት ጭምብል/ማስኮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በቅድሚያ የተለያዩ እንስሳትን ጭምብል/ማስክ/ለሕፃናት ማዘጋጀት
- የተዘጋጀውን ማስክ በማቅረብ ለጨዋታው ፈቃደኛ የሆኑ ሕፃናትን መጋበዝ
- ለጨዋታው ፈቃደኛ ለሆኑ ሕጻናት የተዘጋጀውን ማስክ በመስጠትናየተሰጣቸውን ማሰክ አድርገው በቦታቸው ሄደው እንዲቀመጡ ማድረግ
- በመቀጠልም መምህር የአንዱን እንሰሳ ስም ሲጠሩ የዛን እንሰሳ ጭምብል/ማስክ ያደረጉ ልጆች የእንሰሳቱን ድምጽ በማውጣት ወደመምህር ጋ እንዲመጡ ማድረግ
- ሕፃናት ትክክል መሆን አለመሆናቸውን ጓደኞቻቸው በማየት እንዲያረጋግጡ ማድረግ
- በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሁሉም ሕፃናት በየተራ እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፡- ድምጽን አስመስሎ ማውጣት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሦስት ፡- ተመሳሳይ እና ልዩ ድምጽን መለየት

ዓላማ፡- ተመሳሳይ እና ልዩ ድምጽን መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- እርሳስ፣ ወረቀት/የስዕል ደብተር/፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መጀመሪያና መጨረሻዉ ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸዉን ቃላቶች ማቅረብ
- ቃላቶቹን ደጋግመዉ እንዲናገሩ ማድረግ
- ከተነገሩት ቃላቶች ዉስጥ መጀመሪያ ተመሳሳዮችን ቀጥሎም ልዩ የሆነዉን እንዲናገሩ በማድረግ ተመሳሳይና ልዩ ድምጾችን አዳምጦ የመለየት አቅማቸዉን ማዳበር

ለምሳሌ:- ጓሮ፣ ዶሮ፤ እጅ፣ ልጅ ወዘተ…

ምዘና ፡- ተመሳሳይና ልዩ ድምጽን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- ድምፆችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማቀናጀት

ዓላማ፡- ድምፆችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማቀናጀት ይችላሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናትን ወደ ሜዳ ይዞ መውጣት
- መምህር የተለያዩ እንሳትንና አእዋፍንድምፆችን ከእንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት እያወጡ ለሕጻናቱ ማሣየት
- ሕፃናቱም መምህርን ተከትለው ድምጽን ከእንቅስቃሴው ጋር እያቀናጁ በማውጣት እንዲጫወቱ ማድረግ

  ለምሣሌ፡- እንደላም እምቧ እያሉ መራመድ፣ እንደወፍ ፂውፂው እያሉ እጇን ዘርግቶ መብረር
- በተጨማሪም መምህር ከሕፃናቱ ፊት ለፊት በመቆም የተለያዩ ድምፆችን በየተራ ሲያወጡ ሕፃናቱ የሰሙት ድምጽ ከእንቅስቃሴ ጋር የምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ

  ለምሣሌ፡- መምህር ጲ ጲ ጲ ሲሉ ህጻናቱ መኪና፣ መምህር ፊርርር ሲሉ ህጻናት ፊሽካ በማለት ድምጽን ከእንቅስቃሴ ጋር እንዲያቀናጁ ማድረግ

ምዘና ፡- ድምፆችን ከእንቅስቃሴ ጋር ማቀናጀት መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አምስት ፡- የፊደላት ድምጾችን ከስዕሎችጋር ማዛመድ

ዓላማ ፡- የፊደላት ድምፆችን ከስዕሎችጋር ማዛመድ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ ስእሎችን ለሕፃናት መስጠት
- መምህር የስዕሉን መጠሪያ የመጀመሪያ ፊደል ድምጽ ሲናገሩ ያንን ዓይነት ስዕል የያዘው ልጅ ከፍ አድርጎ እንዲያሳይና ምን እንደሆነ እንዲናገር በማድረግ
- ድምፆችን ከስዕሎችጋር ማዛመድን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የፊደላት ድምፆችን ከስዕሎች ጋር ማዛመድ መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር ስድስት ፡- የፊደላትን ቅርጽ ከድምጽ ጋር ማዛመድ

ዓላማ ፡- የፊደላትን ቅርጽ ከድምጽ ጋር ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፊደላት ቅርጽ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተዋወቋቸውን የፊደላት ቤተሰቦች ለእያንዳንዱ ልጅ በነፍስ ወከፍ በትናንሽ ወረቀት ላይ ጽፎ መስጠት
- መምህሯ ፊደሉን ስትጠራ ያን ፊደል ቅርጽ የያዘ/ች ልጅ ወደ መምህር እንዲመጣ/እንድትመጣ ማድረግ
- የፊደላትን ቅርጽ ከድምጽ ጋር ማዛመድ እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የፊደላትን ቅርጽ ከድምጽ ጋር ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.3. ለትዕዛዞችና መመሪያዎች ምላሽ መሰጠት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ ለትዕዛዞችና መመሪያዎች ምላሽ መስጠት

ግብ ፦ ለትዕዛዞችና መመሪያዎች ምላሽ መስጠት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ‹‹ትዕዛዝን ፈጽም›› የሚል ጨዋታንን እንደሚከተለዉ ማጫወት:-
    - ሁለት ህጻናት በክፍል ጓደኞቻቸዉ ፊት ማቆም
    - አንዱ አዳማጭ /ትዕዛዝ ተቀባይ/ እንዲሆን ማድረግ
    - አቅጣጫ ጠቋሚ ትዕዛዝን መስጠት እና እንዲፈጸም በማበረታታት መከታተል

      ለምሳሌ ፦ የክፍሉ ህጻናት ከተቀመጡባቸዉ ወንበሮች ጀርባ ከሚገኘዉ ጠረጴዛ ስር በካርቶን ዉስጥ የሚገኘዉን ቾክ አምጣ
    - ትዕዛዙን በትክክል መፈጸሙን ከህጻናት ጋር መከታተልና ህጻናቱን በመጠየቅ ልክ መሆኑን እንዲያረጋግጡ ማድረግ
    - በተመሳሳይ በየተራ ሁለት ሁለት ህጻናትን በማስነሳት ትዕዛዝ በመስጠትና በመፈጸም በጨዋታዉ እንዲሳተፉ ማድረግ

ምዘና ፦ ለትዕዛዞች እና ለመመሪያዎች ምላሽ መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ የቡድን ስራን መመሪያ ተከትሎ መስራት

ዓላማ ፦ የቡድን ስራን መመሪያ ተከትሎ መስራት ይለማመዳሉ::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ሊታደሱ የሚገባቸዉ መርጃ መሳሪያዎች፣ ማደሻ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በክፍሉ ዉስጥ የቡድን ስራ ፕሮግራምን ማመቻቸት /ማቀድ/
- ለየቡድኑ ሊታደሱ የሚገባቸዉን መርጃ መሳሪያዎች ከማደሻ ቁሳቁሶች ጋር መስጠት ለምሳሌ ፦ ሽፋናቸው ያረጁና የተቀዳዱ የሥዕልና የተረት መጽሀፍት ወዘተ…
- ለየቡድኑ የአሰራር ቅደም ተከተልን መግለጽ /ማስረዳት/
- በተሰጣቸው ጊዜ የሚሰሩትን በየቡድኑ እየተዘዋወሩ መመልከት
- ክፍለ ጊዜዉ ሊያበቃ ሲቃረብ ምንና እንዴት እንደሰሩ ለክፍሉ ህጻናት እንዲያሳዩና እንዲናገሩ ማድረግ
- ከመመሪያ ዉጭ የሰሩ ቢኖሩ ለቀጣዩ ክፍለ ጊዜ በተሻለ መልኩ ሊሰሩ እንዲችሉ ማበረታታት

ምዘና ፦ የቡድን ስራን መመሪያ ተከትሎ መስራት መለማመዳቸዉን መከታተል።

**ተግባር ሦስት ፦ መልዕክት በትክክል ማድረስ**

ዓላማ ፡- መልዕክቶችን በትክክል ያደርሳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሊታደሱ የሚገባቸዉ መርጃ መሳሪያዎች፣ ማደሻ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለመምህራን፣ ለሞግዚቶቻቸው እና ለሌሎች ሠራተኞች እንዲሁም ለወላጆቻቸው አጫጭር መልዕክትን እንዲያደርሱ ማድረግ
- መልዕክቱን በትክክል ማድረሳቸውን በሚያመጡት ምላሽና ሠራተኞቹን በመጠየቅመረዳት
- መልዕክት በትክክል ያደረሱ ሕጻናትን በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት እውቅና መስጠት
- መልእክትን በትክክል ለማድረስ አስተውሎ ማዳመጥ አስፈላጊ መሆኑን ማስገንዘብ

ምዘና ፡- መልዕክቶችን በትክክል ማድረስ መቻላቸውን በመከታተል መገምገም።

ተግባር አራት ፡- መመሪያን ተከትሎ መጫወት

ዓላማ ፡- መመሪያን ተከትለው መጫወት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወንበር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- <<ወንበር ሽሚያ>>፣<<አረንጓዴ አረንጓዴ>>ወዘተ...ጨዋታ በክፍል ውስጥ ማጫወት
- በመመሪያው መሠረት ጨዋታዎቹን በየተራ መጫወታቸውን መከታተል

ምዘና ፡- መመሪያን ተከትለው መጫወት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.4. ተረቶችን አዳምጠው የተረዱትን መግለጽ እና መልሰው መተረክ ይችላሉ። |

ዓላማ

**ተግባር አንድ ፡- የተረትን መልዕክት መረዳት**

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሐፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህጻናትን ሊያስደስት እና ሊያዝናና የሚችል ተረት የባለታሪኮችን ስሜት ሊያንጸባርቅ በሚችል ድምጽ፣ እንቅስቃሴዎችና የፊት ገጽታ በተገቢዉ መልኩ በመጠቀም መተረክ
- ካዳመጡት ተረት ዉስጥ ስላሉት ባለታሪኮችና የተረቱን ይዘትበተመለከተ በቅደም ተከተል ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት
- የተረቱን መልእክት ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲረዱ ማድረግ
- ተረቱን ደግመዉ /ያለመምህር እርዳታ/ እንዲናገሩ ማድረግ
- የተረቱን ይዘት ደግመዉ /ያለመምህር እርዳታ/ ሲናገሩ ማበረታታት

ማስታወሻ ፡- በተረቶች ውስጥ ከበድ ያሉ ቃላት ቢኖሩ ተረቱ ከመነገሩ በፊት የቃላቱን ትርጓሜ መግለጽ ተገቢ ነው።

ምዘና ፡- የተረትን መልዕክት መረዳታቸውን መገምገም።

**ተግባር ሁለት ፡- ተረትን በስዕል መግለፅ**

ዓላማ ፦ የተረትን በስዕል መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መጽሐፍት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ፤ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- እርሳስና ወረቀት በመስጠት የሰሙትን ተረት መልእክት በስዕል እንዲያንፀባርቁ ማድረግ
- ሲጨርሱም የሳሉትን ስዕል ለጓደኞቻቸው በማሣየት መልእክቱን እንዲናገሩ ማበረታታት
- ከስአሉ ግርጌ ስማቸውን መፃፍ ከቻሉ እንዲፅፉ ካልቻሉ በመምህር እገዛ እንዲፅፉ በማድረግ ለእይታ አመቺ ቦታ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፦ ተረት በስዕል መግለፅ መለማመድ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሶስት ፦ ተረትን በድራማ መግለፅ

ዓላማ ፡- ተረትን በድራማ መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ አልባሳት፣ ጭምብል/ማስክ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በተደጋጋሚ በሰሟቸው ተረቶች ውስጥ ያሉትን ገፀባህሪያት ለሕፃናቱ ማከፋፈል
- በመጀመሪያ ፈቃደኛ ሕፃናት የሰሙትን ገፀባህሪ ተላብሰው እንዲጫወቱ ማበረታታት
- በመቀጠል እንደየገጸባህርያቸው ሕፃናቱ አልባሳትንና ማሰክን በመልበስ ተረቶቹን በድራማ መልክ ለክፍል ጓደኞቻቸውና ለሌሎችም እንዲያቀርቡ ማለማመድ
- [illegible]

ማስታወሻ ፡ ይህን ተግባር በአንድ ክፍለ ጊዜ ማጠናቀቅ ስለሚከብድ በተከታታይ ክፍለ ጊዜያት ሊተገበር ይገባል። ሕጻናትድራማውን በሚያቀርቡበት ወቅትምበተለይ ሥነምግባር ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ተረት በድራማ መግለጽ መለማመድ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- ተከታታይነት ያላቸው ስዕሎችን በመመልከት ተረት መፍጠርና መተረክ

ዓላማ ፡- ተከታታይነት ያላቸው ስዕሎችን ተመልክተው ተረት መፍጠርና መተረክ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተከታታይነት ያላቸው ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከ 5 ያልበለጡ ተከታታይነት ያላቸው ስዕሎችን ለሕፃናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ መስጠት
- ስዕሎቹን አይተውና የታሪኩን ይዘት ተረድተው በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- በመቀጠልም በእያንዳንዱ ስዕል ላይ የሚታየውን ታሪክ ተረት ፈጥረው እንዲተርኩ ዕድሉን በመስጠት ማበረታታት
- ተረት የመፍጠርና የመተረክ ክህሎታቸውን ማበረታታት

ምዘና ፡- ተከታታይነት ያላቸውን ስዕሎች ተመልክተውተረትን መፍጠርና መተረክ መለማመድ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አምስት ፡- የተጀመሩ ተረቶችን አዳምጦ መቀጠል

ዓላማ ፦ የተጀመሩ ተረቶችን አዳምጠዉ መቀጠል ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ አልባሳት፣ ጭምብል/ማስክ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ሕጻናትሌሎች የጀመሩትን ተረቶች አዳምጠው እንዴት ቀጥለው መናገር እንደሚችሉ ገለጻ ማድረግ /ማስረዳት/
- በደንብ አስተውሎ ያዳመጠ ልጅ ደግሞ ቀጥሎ እንደሚተርክ መንገር
- አንድ ተረት መንገር በመጀመር እንዲቀጥሉ ዕድሉን መስጠት

ለምሳሌ ፦ ተረት ተረት ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ትንሽ ድንክዬ ውሻ ከቤቷ ወጥታ ስትሄድ ስትሄድ በጣም ደከማትና ከአንድ ዛፍ ሥር ቁጭ አለች ብለው

- ማን ተረቱን መቀጠል እንደሚፈልግ መጠየቅ
- ፍላጎት ያለው ልጅ ወጥቶ ተረቱን መልሰው በመጀመር እንዲቀጥል ዕድሉን መስጠት
- ሶስትና አራት ዐረፍተ ነገር ከተናገረ በኋላ አበረታትቶ ሌላ ልጅ እንዲቀጥል በማድረግ ሌሎች የጀመሩትን ንግግር የመቀጠል ችሎታን ማለማመድ

ማስታወሻ ፦ ሁሉም ሕጻናት በየተራ እድል በመስጠት አስተውሎ የማዳመጥ ክህሎታቸውን እንዲዳብር ማበረታታት ተገቢ ነው።

ምዘና ፦ የተጀመሩትን ተረቶችን አዳምጠዉ መቀጠል መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ስድስት ፦ ገጠመኞችን በድራማ መልክ ማቅረብ

ዓላማ ፡- ገጠመኞችን በድራማ መልክ ማቅረብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ አልባሳት እና ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከዚህ በፊት ሰምተው የሚያውቁትን አስተማሪ የሆነ ገጠመኝን በጥያቄና መልስ እንዲያስታውሱ ማድረግ
- በመቀጠልም መምህር ገጠመኙን አጠር አድርገው መንገር
- ፈቃደኛ ሕፃናት የሰሙትን ገጠመኝ ገፀባህሪ ተላብሰው አስመስለው እንዲጫወቱ ማበረታታት
- ለሌሎች ክፍል ልጆችና ለወላጆች በተለያዩ የአፀደ ህፃናቱ ፕሮግራሞች ላይ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል

> ማስታወሻ ፡- በሚያቀርቡበት ወቅት በተለይ ሥነምግባር ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ገጠመኞችን አስመስለውበድራማ መልክ ማቅረብ መለማመድ መቻላቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. በተለየዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግርና የምልክት ቋንቋ መግባባት | 2.1.ቋንቋን በእርግጠኝነት መጠቀም ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የጠዋት ሪፖርት ማቅረብ

ዓላማ ፡- የጠዋት ሪፖርት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ አልባሳት እና ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን የጠዋት ሪፖርት ክፍለ ጊዜን ማዘጋጀት
- ቅዳሜና ዕሁድን ምን እየሰሩ እንዳሳለፉ በመጠየቅ ሁሉም ህጻናት እንዲናገሩ ማበረታታት
- አንድ ህጻን ሲናገር ሌሎች በጥሞና እንዲያዳምጡ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- ህጻናቱ መናገር ከከበዳቸዉ ጠቋሚ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማለማመድ ይቻላል፡፡

ምዘና ፡- የጠዋት ሪፖርት ማቅረብ መቻላቸውን መከታተል፡፡

ተግባር ሁለት ፡- በእለት ውስጥ ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት መናገር

ዓላማ ፡- በእለት ውስጥ ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት መናገር ይችላሉ::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ተግባራትን የሚያሳዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህጻናት ከመቀበያ ሰዓት እስከ መሸኛ ሰዓታቸዉ የሚያከዉኗቸዉን ተግባራት እንዲናገሩ ማበረታታት
- ቤታቸዉ ሲመለሱ ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናዉኑትርጉም በሚሰጥ ቋንቋ እንዲናገሩ ማድረግ
- በተለይ ምን ምን ተግባራትን እንደሚወዱ በመጠየቅ ማወያየት

ማስታወሻ ፡- በአጸደ ህጻናትና በቤት ዉስጥ ስለሚከናወኑ ተግባራት ለማስታወስ እንዲችሉ የተለያዩ ስዕሎችን በማሳየት ማነቃቃት ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- በእለት ውስጥ ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት መናገር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- በአካባቢያቸው ስለአዩት ነገር መናገር

ዓላማ ፡- በአካባቢያቸው ስለአዩት ነገር መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ተግባራትን የሚያሳዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህጻናት ወደ አጸደ ህጻናት ከመምጣታቸዉ በፊት በቤታቸዉ ሲከናወን ስላዩት ነገር በዝርዝር እንዲናገሩ በየተራ መጠየቅ
- ህጻናት ወደ አጸደ ህጻናት ሲመጡ በመንገድ ላይ ምን እንዳዩም በየተራ በመጠየቅ ስላዩት ነገር በዝርዝር እንዲናገሩ ማበረታታት
- ተረት የመፍጠርና የመተረክ ክህሎታቸውን ማበረታታት

ምዘና ፡- በአካባቢያቸው ስለአዩት ነገር መናገር መቻላቸዉን መገምገም::

ተግባር አራት ፡- ስለወደፊት ፍላጎት መናገር

ዓላማ ፡- ስለወደፊት ፍላጎታቸው መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ተግባራትን የሚያሳዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ወደፊት ሲያድግ ምን መሆን እንደሚፈልግ ስለተናገረ ህጻን አጭር ታሪክ ማንበብ
- እያንዳንዳቸዉ ወደፊት ሲያድጉ ምን መሆን እንደሚፈልጉ እንዲናገሩ እድል መስጠት
- ህጻናት ፍላጎታቸዉን ሲገልጹ አድናቆትና ድጋፍን ማሳየት

ምዘና ፡- ስለወደፊት ፍላጎታቸው መናገር መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አምስት ፡- ስለቤት እንስሳት መናገር

ዓላማ ፡- ስለቤት እንስሳት መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የቤት እንሰሳት ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የቤት እንስሳትን ስዕል በየተራ በማሳየት የት እንደሚኖሩና ለሰዉ ምን ጥቅም እንደሚሰጡ እንዲናገሩ ማድረግ

  ለምሳሌ፡- ድመት፣ ዉሻ፣ ዶሮ፣ ወዘተ…

ምዘና ፡- ስለቤት እንስሳት መናገር መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ስድስት ፡- በጨዋታ ሃሳብን መግለጽ

**ዓላማ ፡-** በጨዋታ ሃሳባቸዉን መግለጽ ይችላሉ::

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡-** የመስሎ መጫወት መጫወቻ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በየጨዋታ ማዕዘኖች የመስሎ መጫወት ጨዋታዎች ሚና ተከፋፍለዉ እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት
- ጨዋታዎቻቸዉን እየዞሩ በመመልከት በያዙት ሚና መሰረት የሚናገሩትን ማዳመጥ
- በጨዋታው ተገቢዉን ሃሳብ በተገቢዉ ቦታ አድማጭ ሊረዳዉ በሚችል መንገድ መግለጽ መቻላቸዉን መከታተል
- ሀሳባቸዉን በተገቢዉ መንገድ መግለጽ ያልቻሉትን በሂደት መግለጽ እንደሚችሉ በመንገር ማበረታታት
- በመጨረሻም ምን ምን አይነት ሚናዎችን ተከፋፍለዉ እንደተጫወቱ፣ ከማን ጋር እንደተጫወቱና በጨዋታዉ ምን እንደተሰማቸዉ በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፡- በጨዋታ ሃሳባቸዉን መግለጽ መቻላቸዉን መገምገም::

ተግባር ሰባት ፡- ተረት አዳምጦ መልሶ መናገር

ዓላማ ፡- ተረት አዳምጠዉ መልሰዉ መተረት ይችላሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መፅሃፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መምህር ተረት ሲተርቱ ህጻናትን ሊስብ በሚችል መልኩ የፊት ገጽታን፣ የእጅ እንቅስቃሴን በአጠቃላይ ተረቱን በተገቢዉ መልኩ ሊያንጸባርቁ የሚችሉ ሁኔታዎችን በመጠቀም ህጻናት እንዲያዳምጡ ማነቃቃት
- ተረቱን ካዳመጡ በኋላ ስለባለታሪኮቹ ማወያየት
- አንድ በአንድ በማስወጣት ያዳመጡትን ተረት ይዘቱን ሳያዛቡ እንዲናገሩ ማድረግ
- ተረት አዳምጠዉ መልሰዉ መናገር የሚከብዳቸዉን ህጻናት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተረቱን መልሰዉ እንዲናገሩ ማበረታታት

> ማስታወሻ ፡- በተረቱ ዉስጥ ከበድ ያሉ ቃላቶች ቢኖሩ በቅድሚያ ለህጻናቱ የቃላቱን ትርጓሜ መግለጽ ተገቢ ነዉ፡፡

ምዘና ፡- ያዳመጡትንተረት ይዘቱን ሳያዛቡ መልሰዉ መተረት መቻላቸዉን መከታተል፡፡

ተግባር ስምንት ፡- መዝሙር አዳምጦ መልሶ መዘመር

ዓላማ ፡- መዝሙር አዳምጠው መልሰዉ መዘመር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት/ሲዲ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ የህጻናት መዝሙሮችን በመዘመር የመዝሙሩን መልዕክት በጥያቄና መልስ እንዲረዱ ማድረግ
- በመቀጠልም ራሳቸዉን ችለዉ የመዝሙሩን ይዘት ሳያዛቡ እንዲዘምሩ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- አዲስ መዝሙር ከሆነ እያንዳንዱን የመዝሙሩን ስንኝ ረጋ ብሎ ከዜማዉ ጋር በማቀናጀት መዘመርና ከመምህር ቀጥለዉ የመዝሙሩን ስንኝ እንዲዘምሩ በማድረግ ማለማመድ አስፈላጊ ነው።

ምዘና ፡- መዝሙር አዳምጠዉ መልሰዉ መዘመር መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ዘጠኝ ፡- ገጠመኝን መናገር

ዓላማ ፡- ገጠመኝን መናገር ይችላሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መምህር የእርስዎን ገጠመኝ መናገር
- ህጻናት የየራሳቸዉን ገጠመኝ እንዲናገሩ ማበረታታት
- በሚናገሩበት ጊዜ በጥሞና በማዳመጥ ሲጨርሱ ማስጨብጨብ
- መጀመር የሚያቅታቸዉንና ጀምረዉ ለመቀጠል የሚቸገሩትን በጥያቄዎች በማገዝ ማበረታታት

ምዘና ፡- ገጠመኝን መናገር መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አስር ፡- ስዕልን ተመልክቶ መግለጽ

ዓላማ ፡- ስእልን ተመልክተው መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ስዕልን መመልከት በሚል ርዕስ ፕሮግራም ማዘጋጀት
- የተለያዩ ታሪኮችን /ክስተቶችን/ የሚያንጸባረቁ ባለቀለም ስዕሎችን በየተራ ማሳየት
- በስዕሉ ላይ ምን እንደሚያዩ፣ የሚያዩዋቸዉ ባለታሪኮች ምን እያደረጉ እንደሆነ እና የሚታየዉን የሚያደርጉበት ምክንያት ምን እንደሆነ እንዲገምቱ ወዘተ... ቀስ በቀስ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ስእል ተመልክተው መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ አንድ ፡- ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች ታሪክ መረዳት

ዓላማ ፡- ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች ታሪክ መረዳት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተከታታይነት ያላቸው ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከ 5 ያልበለጡ ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች ለህጻናቱ በየጠረጴዛቸዉ ላይ መስጠት
- ስዕሎቹን አይተዉና የታሪኩን ይዘት ተረድተዉ በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- በመቀጠልም በእያንዳንዱ ስዕል ላይ የሚታየዉን ታሪክ እንዲናገሩ እድሉን መስጠት እና ማበረታታት

ምዘና ፡- ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች ታሪክ መረዳት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አስራ ሁለት ፡- ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች ወደ ትረካ መቀየር

ዓላማ ፡- ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች ወደ ትረካ መቀየር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተከታታይነት ያላቸው ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለህጻናት እይታ አመቺ በታ ላይ በመቆም ሶስት ተከታታይነት ያላቸዉንና ጎላ ብለዉ የተሳሉ ሥዕሎችን በየተራ ማሳየት
- በእያንዳንዱ ስዕል ላይ ምን እንዳዩ እንዲናገሩ ማድረግ
- በመቀጠልም በፍላጎት ሶስት ህጻናትን በማስነሳት አንዳንድ ስዕል መስጠትና ስዕሎቹን በቅደም ተከተል እንዲይዙ ማድረግ
- ከዚያም አንዱ በጀመረዉ ታሪክ ላይ ሌላዉ ቀጥሎ እንዲናገር ማድረግ

ምዘና ፡- ተከታታይነት ያላቸዉን ስዕሎች ወደ ትረካ መቀየር መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አስራ ሶስት ፡- የተረት ስዕሎችን ብቻ በማየት መተረት

ዓላማ ፡- የተረት ስዕሎችን ብቻ በማየት መተረት ይችላሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሀፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከተረት መጽሀፍት ላይ ስዕሎቹን ብቻ በየተራ በማሳየት ተረቱን እንዲናገሩ ማበረታት
- በተጻፈው መሠረት የተረቱ ሕጻናትን ማሞገስ

ምዘና ፡- የተረት ስዕሎችን ብቻ በማየት መተረት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አስራ አራት ፡- ስሜትን በንግግር መግለፅ

ዓላማ ፡- ስሜትን በንግግር መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሀፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በተለያየ ክፍለ ጊዜ ሕፃናት ከቤተሰባቸው፣ ከሚመገቧቸው ምግቦች፣ ከአዕዋፍ፣ ከእንስሳት፣ ከዕጽዋቶች እና ከነፍሳቶች መካከል በጣም የሚወዱትን ወይም የሚጠሉት ነገር ምን እንደሆነ እና ለምን ሊወዱ ወይም ሊጠሉ እንደቻሉ ምክንያታቸውን እንዲናገሩ ማበረታታት
- ከሕፃናቱ ምላሽ በመነሳት የሕፃናቱን ስሜት /መውደዳቸውን፣ መጥላታቸውንና እና ፍራቻቸውን/ በመረዳት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ

ምዘና ፡- ስሜትን በንግግር መግለፅ መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ አምስት ፡- አካባቢን በድራማ ማንጸባረቅ

ዓላማ ፡- አካባቢን በድራማ ማንጸባረቅ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሀፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ስለቤታቸው፣ ስለትምህርት ቤታቸውና ስለሚኖሩበት ማህበረሰብ አንዳንድ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት
- ለድራማአስፈላጊውን አልባሳት ማዘጋጀት
- በመቀጠልም ሕፃናት የተለያዩ ገፀባህርያትን ተላብሰው በድራማ መልክ እንዲተውኑት ማበረታታት

ምዘና ፡- አካባቢን በድራማ ማንጸባረቅ መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር አስራ ስድስት ፡- ከበድ ያሉ ቃላትን ማውጣት

ዓላማ ፡- ከበድ ያሉ ቃላት ማዉጣት ይለማመዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሀፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከሕፃናቱ ፊት በመቆም ድምጽን ከፍ አድርጎ ለምላስ አስቸጋሪ የሆነ ቃልን ማውጣት
- ሕፃናትም የሰሙትን ቃል መልሰው እንዲያወጡ ማድረግ
- በመቀጠልም ቃሉን በፍጥነትና በተደጋጋሚ እንዲያወጡ በማድረግ ማጫወት
- በተደጋጋሚ ሳይሳሳቱ ቃሉን እንዲያወጡ ማበረታታት

ለምሣሌ፡- ጨለቅላቃ፣ ማንቆለጳጰስ

ምዘና ፡- ከበድ ያሉ ቃላትን ማውጣት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ ሰባት ፡- ስሜትን በፊት ገጽታ እና በአካላዊ እንቅስቃሴ መግለፅ

ዓላማ ፡- ስሜትን በፊት ገጽታ እና በአካላዊ እንቅስቃሴ መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሀፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ቀላልና አጫጭር ስሜትን የሚገልፁ ተረቶችን/ገጠመኞችን/ ለሕፃናቱ መንገር
- የሰሙትን ታሪክ /ገጠመኝ/ ገፀባህርያትስሜት በፊት ገጽታና በአካላዊ እንቅስቃሴ እንዲገልፁ ማበረታታት

  ለምሣሌ፡-

  - ልጁ እናቱ ያስቀመጠችውን ዕቃ ሳያስፈቅድ በመውሰዱእናቱ ማን እንደወሰደ ስትጠይቀው እንዴት አለች? ያስቀመጥኩትን ዕቃ የነካው ማን ነው አለች? በንዴት ጠቋሚ ጣታቸውን እያወዛወዙና ፊታቸውን አኮሳትረው እንዲናገሩ ማድረግ
  - ልጁ ምን አለ? ይቅርታ አድርጊልኝ ሁለተኛ ሳላስፈቅድ አልወስድም አለ በፍርሃት ሁለት እጃቸውን በመዘርጋትና ፊታቸው ላይ የፍርሃት ስሜት በማሣየት እንዲገልጹ ማድረግ
  - ልጁ እናቱ ከአፀደ ህፃናት ልትወስደው ስትመጣ ምን አለ? ምን አደረገ? እጁን ዘርግቶ እማማመጣሽ? ብሎ እቅፍ አደረጋት በማለት እንዲያሣዩ ማድረግ

ምዘና ፡- ስሜትን በፊት ገጽታ እና በአካላዊ እንቅስቃሴ መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ ጊዜንና ድርጊትን መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መጽሀፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ሕፃናት የጊዜን ጽንሰ ሐሳብ /የቅርብ፣ ያለፈንና የወደፊትን/ እንዲረዱ የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ተገቢውን ግዜንና ድርጊትን ገላጭ ቃላትን በመጠቀም ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት

ለምሣሌ፦

ተረት ተረት የሚለውንመዝሙር መቼ ዘመርን?

ትናንት /ቅድም/ አሁንምን እያደረግን ነው?

አሁን እየተማርን ነው

በኋላ ሰዓት ሲደርስ ወላጆቻችሁ ሲመጡ

ምን ታደርጋላችሁ?

በኋላ ወላጆቻችን ሲመጡ ወደቤታችን እንሄዳለን

- በመቀጠልም ትላንት፣ዛሬ፣ ነገ  የሚሉትን ጊዜ ገላጭ ቃላቶችን በመጠቀም የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን በመሥራት ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ዕድሉን መስጠት

ምዘና ፦  ጊዜንና ድርጊትን መግለጽ መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ ዘጠኝ ፦ አዳዲስ ቃላትን ማስተዋወቅ

ዓላማ ፡- አዳዲስ ቃላትን መተዋወቅ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሀፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ የሕፃናቱን ዕድሜ የሚመጥኑ ተረቶችንና ግጥሞችን መንገር
- በተረቱና በግጥሙ ውስጥ የነበሩትን አዳዲስ ቃላት ትርጓሜ እንዲረዱና መልሰው ቃላቱን እንዲናገሩ ማድረግ
- ሕፃናት በሰሚቸው ተረቶችና ግጥሞች የተሰማቸውን ስሜት በቃላት እንዲገልፁ ማድረግ

  ለምሣሌ፡- በድሮ ጊዜ አለቃ ገ/ሃና የሚባሉ ቀልድና ጨዋታ አዋቂ ሰው ነበሩ። ከዕለታት አንድ ቀን አለቃ ገ/ሃና ድግስ ተጠሩና ቡቱቱ የተቀዳደደ ልብሳቸውን ለብሰው ወደተጠሩበት ድግስ ቤት ሄዱ። በር ላይ ያለው አሳላፊ የለበሱትን ልብስ አይቶ አላስገባ አላቸው። ከዚያም አለቃ ገ/ሃና ወደቤታቸው ተመልሰው ሄደው የክት ልብሳቸውን ለብሰው ሲመጡ አሳላፊው እጅ ነስቶ አስገባቸው። ጥሩ የእንግዳ ቦታም ሰጣቸው ከዚያም ምግብ ሲቀርብላቸው ምግቡን እያነሱ ልብሳቸውን ወጥ መለቅለቅ ጀመሩ። ከዚያም አሳላፊው አለቃ ገ/ሃና የሚያደርጉትን አይቶ መጣና አለቃ ገ/ሃና ለምንድነው ልብሶትን ወጥ የሚለቀልቁት? ሲላቸው ‹‹የተጠራሁት እኔ ሳልሆን ልብሱ ስለሆነ ይብላ ብዬ ነው። ›› አሉ ይባላል።

- በታሪኩ ውስጥ ለምን? እንዴት? መቼ ? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ

ምዘና ፡- አዳዲስ ቃላትን መተዋወቃቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ አበላላጭ ቃላትን ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያየ መጠን ያላቸው እርሳሶች ወይም ማስመሪያዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ለሕጻናቱ የተለያየ መጠን ያላቸውን እርሳሶች /ማስመሪያዎች/ በመስጠት ትልቅ፣ በጣም ትልቅ፣ እጅግ በጣም ትልቅ የሚባሉትን አበላላጭ ቃላት ማስተዋወቅ
- በእጃቸው ከያዟቸው እርሳሶች /ማስመሪያዎች/ የትኛው ትልቅ፣ የትኛው በጣም ትልቅ፣ የትኛው እጅግ በጣም ትልቅ እንደሆነ አበላላጭ ቃላትን በመጠቀም እንዲናገሩ ማድረግ
- በመቀጠልም እጃቸውን በፍጥነት እንደመኪና እንዲያሽከረክሩ ማድረግ
- ቀጥለውም በጣም በፍጥነት እንዲያሽከረክሩ ማድረግ እንደገና እጅግ በጣም በፍጥነት እንዲያሽከረክሩ ማድረግ
- ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት በፍጥነት፣ በጣም በፍጥነት፣ እጅግ በጣም በፍጥነት የሚለውን ትርጉም እንዲያውቁና እነዚህን አበላላጭ ቃላቶችን በንግግር ሂደታቸው እንዲጠቀሙበት ማድረግ

ምዘና ፦ አበላላጭ ቃላትን መረዳት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሀያ አንድ ፦ ሁኔታዎችን በምናብ መሳል

ዓላማ ፡- ሁኔታዎችን በምናብ መሳል ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ መጠን ያላቸው እርሳሶች ወይም ማስመሪያዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መፍትሔ የሚሹ የተለያዩ ገጠመኞችን በመንገርእናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር? በማለት የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- በወቀቱ በአካባቢያቸው ስለሌሉ ነገሮችና ሁኔታዎች በምናባቸው /በዓይነህሊናቸው/ በማየት እንዲናገሩ ዕድሉን መስጠት

ምዘና ፡- ሁኔታዎችን በምናብ መሳል መለማመዳቸውን መገምገም።

ተግባር ሀያ ሁለት ፡ - በዐረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ስህተቶችን መለየት

ዓላማ ፡- በዓረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ስህተቶችን መለየት ይችላሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ስህተት ያለበትንዓረፍተ ነገርበመንገር ሕፃናት አስተውለው በማዳመጥ ስህተቱ ምን እንደሆነ በመለየት እንዲናገሩ ዕድሉን መስጠት

  ለምሣሌ፡-

  - <<ዛሬ እኔ ሆዴን ስላመመኝ ለመታከም ጋራዥ እሄዳለሁ>>
  - <<ዛሬ ምሣዬን የምበላው በጣም ጣፋጭ የሆነውን መጽሐፍ ነው>> ወዘተ…

- በመቀጠልም ህጻናቱ እንደዚህ ትርጉም የማይሰጡ ዐረፍተ ነገሮችን በመናገር ጓደኞቻቸው ስህተቱን እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በዐረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ስህተቶችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ መተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግርና የምልክት ቋንቋ መግባባት | 2.2 . በንግግር ቋንቋ ደስታን ማግኘት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- በግጥም መደሰት

ዓላማ ፡- በግጥም መደሰት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የግጥም መጽሀፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለሕፃናት የሚመጥኑ ግጥሞችን እና ስንኞችን ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ/መንገር/
- የግጥሙን ይዘት በድርጊት በማሣየት እንዲረዱ ማድረግ

ለምሣሌ፡-

ተረት ተረት

የላም በረት

ማስታወሻ ፡- መምህሩን የሕጻናቱን ትኩረት የሚስቡ አጫጭር ግጥሞችን በመግጠምና ለሕጻናቱ በማቅረብ የሕጻናቱን በግጥም የመደሰት ክህሎት ማዳበር ይቻላል።

ምዘና ፡- በግጥም መደሰት መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- ለጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠት

ዓላማ ፡- ለጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠት ይችላሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ስለራሳቸውና ስለቤተሰባቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ጥያቄዎችን አስተውሎ በማዳመጥ ለጥያቄዎቹ ተገቢና የተሟላ መልስ መስጠትን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ለጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. በማንበብ መደሰት ዕውቀት ማግኘት እና መረዳት | 3.1 . ቀላል ቃላቶችንና ዐ/ነገሮችን ማንበብ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ፡- የስዕሎችን ተመሳሳይነት እና ልዩነትን መናገር

ዓላማ ፡- የስዕሎችን ተመሳሳይነት እና ልዩነትን መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የስእል ካርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ የስዕል ካርዶችን በመስጠት ተመሣሣዮቹን እንዲመርጡ ማድረግ
- ስዕሎቹን የሚያመሳስላቸውንና የሚለያያቸውን እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የስዕሎችን ተመሳሳይነት እና ልዩነትን መናገር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- የስዕሎችን ተመሳሳይነት እና ልዩነትን መረዳት

ዓላማ ፡- የስዕሎችን ተመሳሳይነት እና ልዩነትን ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የስዕል ዶሚኖና የስዕል ማዛመጃ ሰሌዳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የስዕል ዶሚኖና የስዕል ማዛመጃ ሰሌዳ መጫወቻዎችን በመስጠት እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፡- የስዕሎችን ተመሳሳይነት እና ልዩነትን መረዳት መቻላቸዉን መገምገም።

**ተግባር ሶስት ፡- የመሪ ፊደላትን ስያሜ መናገር**

ዓላማ፡- የመሪ ፊደላትን ስያሜ መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- የመሪ ፊደላት ሠሌዳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ቀደም ሲል የተዋወቋቸውን መሪ ፊደላት ማሣየት
- በመቀጠል መጠሪያ ስማቸውን እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የመሪ ፊደላት ስያሜ መናገር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ዓላማ፡- የፊደላት ቤተሰቦችን መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- የፊደል ሠሌዳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የፊደል ሠሌዳን በመጠቀም ሶስት በቅርፃቸው ተመሣሣይ የሆኑ መሪ ፊደላቶችን መውሰድ
- ቀጥሎ የሚገኙትን የፊደላት ቤተሰቦች /ካዕብን/ በየተራ በማሣየት መጠሪያ ስማቸውን መንገር

  ለምሳሌ፡- ቡ ሱ ሹ

- ሕፃናቱም መልሰው እንደናገሩ ማድረግ
- ከመሪ ፊደላቶች /ግዕዝ/ ጋር /በ ሰ ሸ/ ያላቸውን መመሳሰልና ልዩነት በየተራ አስተውለው በመመልከት እንዲናገሩ እድሉን መስጠት
- መምህር ፊደላቱን የሚያመሣስላቸውንና ልዩነታቸውን በመንገር እንዲገነዘቡ ማድረግ
- ‹‹ማነኝ ማነኝ›› የሚለውን መዝሙር በማዘመር ማጠናከር

ምዘና ፡- የፊደላት ቤተሰቦችን መለየት መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አምስት ፡- በጨዋታ የፊደላት ቤተሰብን ድምጽና ቅርጽ መለየት

ተግባር አራት ፡- የፊደላት ቤተሰቦችን መለየት

ዓላማ፡- በጨዋታ የፊደላት ቤተሰብን ድምጽና ቅርጽ መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- የፊደላት ሠሌዳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- <<እንቆቅልሽ>> እና <<የጐደለውን ዕወቅ>> ጨዋታ በሚከተለው መንገድ በማጫወት የፊደላቱን ድምጽና ቅርጽ እንዲለዩ ማድረግ

  እንቆቅልሽ /ህ/**?**
  ምን አውቅልሽ /ህ/**?**
  እኔ የ "በ " ፊደል ቤተሰብ ነኝ
  በቀኝ እግሬ ጐን ላይ ቅጥያ አለኝ
  እኔ ማነኝ **?** ቡ

- የተዋወቋቸውን ሶስት የመሪ ፊደል ቤተሰቦችን በማሣየት መጠሪያ ስማቸውንና ቅርፃቸውን እንዲናገሩ ማድረግ
- ዓይናቸውን እንዲጨፍኑ ማድረግ
- ዓይናቸውን ሲጨፍኑ ከመካከላቸው አንዷን ፊደል መደበቅ
- ከዛም ዓይናቸውን እንዲገልጡና የጠፋቸው ፊደል ማን እንደሆነችና አብራቸው ከነበሩት ፊደላት በምን እንደምትለይ በመጠየቅ በተደጋጋሚ ማጫወት

ምዘና ፡- በጨዋታ የፊደላት ቤተሰብን ድምጽና ቅርጽ መለየት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ስድስት ፡- የተዋወቋቸውን ፊደላት ማንበብ

ዓላማ፡- የተዋወቋቸውን ፊደላት ማንበብ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- የፊደላት ሠሌዳ፣ የፊደላት ካርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በጥቁር ሠሌዳ ላይ የተዋወቋቸውን ፊደላት ቁልቁል ወደታች እና አግድም መፃፍ
- ከላይ ወደታች ከግራ ወደቀኝ ዓይናቸውን በማንቀሳቀስ እንዲያነቡ ማድረግ
- የተዋወቋቸውን ፊደላት በትናንሽ ወፍራም ወረቀቶች ላይ ጽፎ መስጠት
- መምህር "ልትወጣ ነው! ልትወጣ ነው!" በማለት በእጃቸው ላይ ያለውን የፊደል ሰሌዳ ሲያሳዩ መምህር የያዙትን ፊደል አይነት የፊደል ካርድ የያዘ ልጅ እንዲያሳይ በማድረግ በማጫወት ማጠናከር

ምዘና ፡- የተዋወቋቸውን ፊደላት ማንበብ መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር ሰባት ፡- የፊደላትን ድምጽ እና ቅርጽ መለየት

ዓላማ፡- የፊደላትን ድምጽ እና ቅርጽ ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የፊደላት ሎቶ እና ዶሚኖ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የፊደላት ሎቶና ዶሚኖ መስጠት
- እንዲጫወቱ በማድረግ ፊደላቱን በድምጽ እና በቅርጽ እንዲለዩ ማድረግ

ለምሳሌ፡- <u>የፊደላት ማዛመጃ ሰሌዳ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ቡ | ኩ | ዙ |
| ጕ | ሉ | ሹ |
| ሱ | ኹ | ኡ |

| | | |
|---|---|---|
| ቡ | ኹ | ኩ |
| ሱ | ኡ | ሹ |
| ሉ | ዙ | ጕ |

<u>የፊደላት ዶሚኖ</u>

| | |
|---|---|
| ቡ | ሱ |

| | |
|---|---|
| ኩ | ሉ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሱ | ኩ | ሉ | ኡ |

ማሳሰቢያ ፡- ሕፃናቱ በአንድ ጊዜ መተዋወቅ ያለባቸው ፊደላት ከሶስት መብለጥ የለባቸውም እንዲሁም ፊደላቶቹ በቅርፃቸው ተመሣሣይ መሆን ይኖርባቸዋል።

- አስቀድመው በተዋወቋቸውና በሚያውቋቸው ፊደላት የተመሠረቱ ቃላቶችን ማንበብ መለማመድ ይኖርባቸዋል
- ካዕብን ሲጨርሱ በዚሁ ዓይነት የማስተማር ዘዴ የመሪ ፊደላቱን ቤተሰቦች /ሳልስን፣ ራብዕን፣ ሃምስን፣ ሳድስንና ካብዕን ማስተዋወቅ ያስፈልጋል/ ቢ ሲ ሺ፣ ባ ሳ ሻ፣ ቤ ሴ ሼ፣ብ ስ ሽ፣ቦ ሶ ሾ/

በተለይ ሳድስ /ስድስተኛው ቤተሰብ/ ለሕፃናቱ ከሌሎቹ የፊደላቱ ቤተሰቦች ስለሚከበድ /የፊደላቱ ቅርጽ ተመሣሣይነት ስለሌለው/ ሕፃናቱ ሸምድደው እንዲይዙ ማስጨነቅ አያስፈልግም

ምዘና ፡- የፊደላትን ድምጽ እና ቅርጽ መለየት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ስምንት ፡- የቃላት ትርጉምን መረዳት

ዓላማ፡- የቃላት ትርጉምን መረዳት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቅማ ፡- በትልቅ ወረቀት ላይ በመሪ ፊደላት እና በተዋወቋቸው ፊደላት ቅንጅት የተጻፉ ትርጉም የሚሰጡ ቃላት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በትልቅ ወረቀት ላይ በተዋወቋቸው ፊደላት የተጻፉ ቃላትን ይዞ ለሕፃናት እይታ አመቺ ቦታ ላይ መቆም
- ከትልቁ ወረቀት ላይ እያንዳንዱን ፊደል ሕፃናት ከመምህሩ ጋር አብረው ከግራ ወደቀኝ በመቁጠር ደጋግመው እንዲያነቡ ማድረግ
- ሕፃናቱን የቃላቱን ትርጉም በመጠየቅ ካላወቁ መንገር
- ማን ማንቡብ እንደሚፈልግ በመጠየቅ የሕፃናቱን የማንቡብ ፍላጐት ማነሳሳት

ምዘና ፡- የቃላት ትርጉምን መረዳታቸዉን መገምገም።

ተግባር ዘጠኝ ፡- ስዕሎችንና ቃላትን ማዛመድ

ዓላማ፡- ስዕሎችንና ቃላትን ማዛመድ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ስዕሎች፣ የስዕሎቹ ስያሜ የተጻፈበት ትልቅ ወረቀት/ሠሌዳ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ስዕሎቹን ለሕፃናቱ ማደል
- ለሕፃናቱ ከተሰጡት ስዕሎች ውስጥ የአንዳንዱን ስዕል መጠሪያ ስም ቃላት ማሣየት
- ሕፃናቱ ድምጽ ሳያሰሙ አንብበው የተነበበውን ቃል የሚገልጽ ስዕል የያዘ ሕፃን መምህሩ ጋር ወጥቶ በመቆም ከቃሉ ጋር እንዲያዛምድ ማድረግ

ምዘና ፡- ስዕሎችንና ቃላትን ማዛመድ መቻላቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፡- ቃላትና ስዕሎችን ማዛመድ ይችላሉ።


የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የስዕል ሎቶዎች፣ ቃላት የተፃፋባቸዉ ካርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በየቡድናቸው /በየጠረጴዛቸው/ የስዕል ሎቶዎቹን እና ቃላት የተፃፋባቸዉን ካርዶችን መስጠት
- ሕፃናቱ እነዚህን እንዲያዛምዱ ማድረግ

ለምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| መፅሐፍ | ፀሐይ |
| መነፅር | ብስክሌት |



ምዘና ፡- ስዕሎችንና ቃላትን ማዛመድ መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አስር ፡- ቃላትና ስዕሎችን ማዛመድ



ተግባር አስራ አንድ ፡- የተለያዩ ቃላትን ማንበብ እና ትርጉማቸዉን መናገር

ዓላማ፡- የተለያዩ ቃላትን ማንቡብ እና ትርጉማቸዉን መናገር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በወፍራም ወረቀት/ክላሰር/ ላይ የተፃፉ ቃላት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለእያንዳንዱ ህጻናት አንድ አንድ ቃል መስጠት
- በመቀጠል ማንቡብ የሚፈልጉ ህጻናት እጃቸውን በሥርዐት በማውጣት ከክፍል ጓደኞቻቸው ፊት ቆመው እንዲያነቡ ማድረግ
- የቃሉን ትርጓሜ በመጠየቅ ለሕፃናቱ እንዲናገሩ ማድረግ
- ያነበቡትን ቃል የተፃፈበትን ወረቀት ለሕጻናቱ በሽልማት መልክ መስጠት

ማስታወሻ ፡- ቃላቱ አዲስ በተዋወቁትና ቀደም ሲል በሚያውቁት ፊደል የተመሠረተ መሆን አለበት።

ምዘና ፡- የተለያዩ ቃላትን ማንቡብና ትርጉማቸዉን መናገር መለማመዳቸዉን መገምገም።

ተግባር አስራ ሁለት ፡- ድምጽ ሳያሰሙ ማንቡብ

ዓላማ፡- ድምጽ ሳያሰሙ ማንበብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቃላት ሠሌዳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በጥቁር ሠሌዳ ላይ በተዋወቋቸው ፊደላት የተመሠረቱ ቃላትን መፃፍ
- እያንዳንዱን ፊደል በመቁጠርና ቀጥሎም ፊደላቶቹን በመገጣጠም እንዲያነቡ ማድረግ
- በተጨማሪም ከላይ ወደታች እና ከግራ ወደቀኝ በተዋወቋቸውናቀደም ሲል በሚያውቋቸው ፊደላት የተመሰረቱ የተለያዩ ቃላቶችን መፃፍ
- ሕፃናቱ ድምጽ ሳያሰሙ ፊደላቱን በመገጣጠም አንብበው ምን እንደሚል እጅ በማውጣት እንዲመልሱ ማድረግ

ምዘና ፡- ድምጽ ሳያሰሙ ማንበብ መለማመዳቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶች መጠሪያ ቃላትን ማንበብ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶች፣ የቁሳቁሶቹ መጠሪያ የተጻፈባቸዉ ካርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ቁሳቁሶቹን በሕፃናቱ ፊት ማስቀመጥ
- የቁሳቁሶቹን መጠሪያ ስም የያዘውን ፍላሽ ካርድ ለእያንዳንዱ ልጅ በመስጠት እንዲያነቡማድረግ
- ከዛም በየተራ እየተነሱ የያዙትን መጠርያ ስም አንብበው ቁሱ የትኛው እንደሆነ ለመምህር ማሳየት

ምዘና ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶች መጠሪያ ቃላትን ማንበብ መቻላቸዉን ማረጋጥ።

ተግባር አስራ ሦስት ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶች መጠሪያ ቃላትን ማንበብ

ዓላማ ፡- ተመሳሳይነት እና ልዩነት ያላቸዉን ቃላት መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቃላት ሠሌዳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በትልቅ ወረቀት ላይ በተራ ቁጥር 3 ቃላቶችን መፃፍ /ሁለቱ ተመሣሣይ አንዱ የተለየ ቃል/
- በየትኛው ተራ ቁጥር ላይ የተፃፈዉ ቃል ከሌሎቹ የተለየ እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ተመሳሳይነት እና ልዩነት ያላቸዉን ቃላት መለየት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ አምስት ፡- የተፃፈ ቃላትን ፊልጎ ማግኘት

ዓላማ ፡- የተፃፈ ቃላትን ፈልገው ማግኘት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በወረቀት ላይ የተጻፉ በሚያውቋቸው ፊደላት የተመሰረቱና ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ ቃላቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ወረቀቶቹን በክፍል ውስጥ በተለያየ ቦታ መለጠፍ
- ‹‹የሰማኸውን ቃል ፈልግና አግኝ›› የሚለውን ጨዋታ እንደሚከተለዉ ማጫወት፡-
    - ሁለት ሕፃናት ማስነሳት
    - ቃሉን መምህር ሲናገሩ በክፍል ውስጥ ተጽፈው ከተለጠፉት ቃላት ውስጥ አንብበው እንዲያሣዩ ማድረግ

ምዘና ፡- የተፃፈ ቃላትን ፈልገው ማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር አስራ ስድስት ፡- እየተጫወቱ ቃላት ማንበብ**

ዓላማ ፡- እየተጫወቱ ቃላት ማንበብን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቃላት ሎቶ፣ የቃላት ዶሚኖ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የቃላት ሎቶና ዶሚኖ ለእያንዳንዳቸዉ መሥጠት
    - ሕፃናት እየተጫወቱ ቃላትን በማዛመድና በማገጣጠም ማንበብ እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- እየተጫወቱ ቃላት ማንበብን መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር አስራ ሰባት ፡- ቀላል ሀረጎችን ማንበብ**

ዓላማ ፡- ቀላል ሀረጐችን ማንበብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሀረጐች ሠሌዳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጥቁር ሰሌዳ ላይ ቀለል ያሉ ሀረጐችን በመፃፍ ማንበብ ማለማመድ

ለምሳሌ፡- አበበ ጫማ

ምዘና ፡- ቀላል ሀረጐችን ማንበብ መለማመዳቸውን መገምገም።

**ተግባር አስራ ስምንት ፡- ዐረፍተ ነገር ማንበብ**

ዓላማ ፡- ዐረፍተ ነገሮችን ማንበብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዐረፍተ ነገሮች ሠሌዳ፣ ቀለል ያሉ ዐረፍተ ነገር የተፃፈባቸዉ ወረቀቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተሟላ ዐረፍተ ነገር በመፃፍ ሕፃናቱ እነዲያነቡ ማድረግ
- ለእያንዳንዳቸው ዐረፍተነገር የተፃፈባቸዉን ወረቀቶች መስጠት
- ድምጽ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ማድረግ
- እንብበው ሲጨርሱ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ዐረፍተ ነገሮችን ማንበብ መለማመዳቸዉን መገምገም።

**ተግባር አስራ ዘጠኝ ፡- ቃላትን አንብበው በድርጊት መግለጽ**

ዓላማ ፡- ቃላትን አንብበው በድርጊት መግለጽ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ትዕዛዞችን የሚገልፁ ቃላቶች እና ዐረፍተ ነገሮች የተፃፈባቸዉ ወረቀቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ካርዶቹን በማሣየት ሕፃናቱ ቃላቱን አንብበው በድርጊት እንዲገልፁ በማድረግ ማጫወት ለምሳሌ፡- ተነሱ፣ ተራመዱ፣ ዝለሉ ወዘተ...
- በሂደት ዐረፍተነገሮችን በመጠቀም በደስታ ማንበብን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ቃላትን አንብበው በድርጊት መግለጽ መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ሀያ ፡- መጻሕፍትንና ደብተርን በንጽህና እና በሥርዐት መያዝ

ዓላማ ፡- መጻሕፍትንና እና ደብተሮቻቸዉን በንጽህና እና በሥርዐት መያዝ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ደብተር፣ መጽሐፍት፣ መጽሔት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናቱ በሚቀጥለው ዓመት የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች እንደሚሆኑ መንገር /ማስታወስ/
- አንደኛ ክፍል ሲገቡ ከእነሱ ምን እንደሚጠበቅባቸው ማወቅ ይፈልጉ እንደሆነ በመጠየቅ ትኩረታቸውን መሣብ
- የተለያዩ መሐፍቶች እንደሚኖራቸው፣ ደብተሮቻቸውም በርካታ እንደሚሆኑ ማስረዳት
- የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች መጽሐፍትና ደብተሮችን በስርዐት መያዝ እንደሚጠበቅባቸው ማስረዳት
- መጽሀፍ እና ደብተራቸዉን በንጽህና ለመያዝ፡-
  - በእርጥብ እጅ አለመያዝ
  - ንፁህ ባልሆነ እጅ አለመያዝ
  - ምግብ አለማስነካት
  - አለመቅደድ ወዘተ…
- ደብተርንና መጽሔትን በመጠቀም እንዴት በቀላሉ ሊበላሹ እንደሚችሉ በተግባር ማሣየት
- የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች መጽሐፎቻቸውን ሳያጥፉ በሥርዐት ወደቦርሣቸው መክተትን ማወቅ አለባቸው፣ እናንተስ ይህንን ታውቃላችሁ? በማለት ማወያየት
- በሥርዐት ወደ ቦርሳ መክተትን በራሳቸው መጻህፍትና ደብተሮች እንዲለማመዱ ማድረግ
- የሥዕል መጽሐፍትንና ደብተርን ተጠቅመው ሲጨርሱ በሥርዐት ዝግ ብለው ሳያጥፉ ወደቦርሳቸው መክተት እንዳለባቸው በተግባር ማሣየት
- ሕፃናቱ በሂደት እራሳቸው ደብተሮቻቸውን በሥርዐት እቦርሳቸው ውስጥ መክተትንና ማውጣትን እንዲለማመዱ ማድረግ
- መጻህፍት ላይ ያለመምህር ፈቃድ መፃፍ እንደሌለባቸው ማሳወቅ
- መምህር ፃፉ ወይም ቀለም ቀቢቸው ሲሉ ብቻ የታዘዙትን ማድረግ እንደሚገባቸው ማስገንዘብ

ምዘና ፡- መጻሕፍት እና ደብተሮቻቸዉን በንጽህና እና በሥርዐት መያዝ መቻላቸዉን መከታተል።

ዓላማ ፡- ተረት መተረት እና ማዳመጥ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ደብተር፣ መጽሐፍት፣ መጽሔት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናት ራሳቸው የሚያውቁትን ተረት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ
- መምህር ተረቱ ይዘቱን ሳይለቅ አጠር አድርገው በወረቀት ላይ መጻፍ
- በሌላ ክፍለ ጊዜ የማን ተረት እንደሆነ ልጆቹን በመጠየቅና በመንገር ተረቱን መልሰው መተረክ
- ሕፃናት አስተውለው የራሳቸውንና የጓደኞቻቸውን ተረት እንዲያዳምጡ ማድረግ

ምዘና ፡- ተረት መተረት እና ማዳመጥ መቻላቸውን መገመገም።

ተግባር ሀያ አንድ ፡- ተረት መተረት እና ማዳመጥ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4.የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ ማዘጋጀት | 4.1. ፊደላትን እና ቃላትን መፃፍ ይችላሉ። |


## ተግባር አንድ ፦ መሠረታዊ መስመሮችን መስራት

ዓላማ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ለሕጻናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ ወረቀትና እርሳስ በማደል መሠረታዊ መስመሮችን እንዲሰሩ ማድረግ
- የሠሯቸውን መሠረታዊ መስመሮችን በመጠቀም የተለያዩ ቅርጾችን እንዲሠሩ ማለማመድ



- ዜብራ፣ ዝናብ ሲዘንብ፣መስቀል፣ የሣሙና አረፋ፣ የውሃ ትል፣መሰላል ወዘተ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፦ ይህ ተግባር ልጆቹ ደጋግመው በተለያዩ ክፍለ ጊዜያት እንዲሰሩት ማድረግ ተገቢ ነው። |

ምዘና ፦ መሠረታዊ መስመሮችን መሥራት መቻላቸውን መገምገም።

## ተግባር ሁለት ፦ ስዕል መሳል

ዓላማ ፡- ስዕል  ይስላሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የስእል ደብተር፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለ ቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለሕፃናቱ የስዕል ደብተር ወይም ወረቀት አዘጋጅቶ መስጠት
- የተሰጣቸውን የስዕል ደብተር/ወረቀት/ በመጠቀም የፈለጉትን ነገር እንዲስሉ እና የሳሉትን ከመስመር ሳይወጡ ቀለም እንዲቀቡ መርዳት
- የሳሉትን እና ቀለም የቀቡትን ስዕል ለጓደኞቻቸው በማሳየት ምን እንደሣሉ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ስዕል መሳል መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሦስት ፡- ነጠብጣቦችን ማገናኘት

ዓላማ ፦ ነጠብጣቦችን ማገናኘት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የስእል ደብተር፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ቀለም፣ በነጠብጣብ የተሰሩ ስዕሎች፣ በወረቀት ላይ የተሳሉ የጂኦሜትሪ ቅርፆች ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ለእያንዳንዱ ልጅ ነጠብጣብ ያለባቸውን ወረቀቶች መስጠት
- ነጠብጣቦችን በማገናኘት የሚገኙትን ምስሎች የተለያየ ክፍል ከመስመር ሳይወጡ ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- የሳሉትንና ቀለም የቀቡትን ምስል መጠሪያ ስም በመፃፍ በክፍል ውስጥ እንዲለጠፉ ማድረግ

ምዘና ፦ ነጠብጣቦችን በማገናኘት ለጽሁፍ መዘጋጀት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ፦ ድርብ ፊደላትን ቀለም መቀባት

ዓላማ ፦ ድርብ ፊደላትን ቀለም መቀባት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ባለ እርሳስ ቀለም

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የተዋወቋቸውን ፊደላት በትንሽ ወረቀት ላይ በድርብ ጽፎ መስጠት
- በታዘዙት መሠረት ከመስመር ሳይወጡ ቀለም እንዲቀቡ ማስቻል
- የቀቡትን ፊደል መጠሪያ ስም እንዲናገሩ በማድረግ ለእይታ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፦ ድርብ የተጻፉ ፊደላትን ቀለም መቀባት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አምስት ፦ ስእልን አስመስሎ መሳል

ዓላማ ፡- ስእል አስመስሎ መሳል ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጐላ ብለው የተሳሉ የተለያዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለሕፃናት ዕይታ አመቺ ቦታ ላይ ጐላ ብሎ የተሳሉ የተለያዩ ስእሎችን መለጠፍ
- ያዩትን ስዕል አስመስለው መሳል እንዲለማመዱ ማድረግ
- ሲጨርሱም ከጓደኞቻቸው እና ከመምህራን ጋር በጋራ ስራቸውን መገምገም
- የተሻለ የተሳሉትንና እና እንዲሁም ከትዕዛዝ ውጪ የሆኑትን ለሕጻናቱ በማሳየት ማወያየት

ምዘና ፡- ስዕልን አስመስሎ መሳል መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ስድስት ፡- ፊደላትን መጻፍ

ዓላማ ፡- ፊደላትን መጻፍ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናቱ ከግራ ወደቀኝ በትክክል በደብተራቸው ላይ ፊደላትን እንዲጽፉ ይርዱአቸው
- የተዋወቋቸውን የመሪ ፊደላት ቤተሰቦች ከመሪ ፊደላቱ በምን እንደሚለዩ ይጠይቁአቸው
- ትናንሽ ቁርጥራጭ ወረቀቶችን በመስጠት በወረቀቱ ላይ ፊደሉን እንዲፅፉ ማለማመድ
- አጠገባቸው ካሉ ሕፃናት  ጋር የፃፉትን ፊደላት እንዲያስተያዩ ማድረግ
- በወፍራም ክላሠር ላይ ከተፃፈው ፊደልጋር በማስተያየት ሕፃናት ራሳቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ

ምዘና ፡- ፊደላትን መጻፍ መለማመዳቸውን መገምገም።

ተግባር ሰባት ፡-መስመር ጠብቆ ቃላትን መፃፍ

ዓላማ ፡- መስመር ጠብቀው ቃላትን መፃፍ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወፍራም ክላሠር፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ከለር፣ ቾክ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በተዋወቋቸው ፊደላት የተመሠረቱ ቃላቶችን በትልቅ ወረቀት ላይ ከላይ ወደታች እና ከግራ ወደ ቀኝ መፃፍ
- ከመስመር ሳይወጡ እና ፊደላቱን ሳያበላልጡ እንዴት መፃፍ እንደሚቻል መስመር ባለው በትልቅ ወረቀት ላይ ጽፎ ማሣየት
- ሕፃናቱ በደብተራቸው ላይ መስመርን ጠብቀው ፊደላቱን ሳያበላልጡ እንዲጽፉ ማለማመድ

ማስታወሻ ፡- ሕፃናቱ ሲጽፉ ሁሉንም ሕፃናት እየተዘዋወሩ መመልከትና ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

ምዘና ፡- መስመር ጠብቀው ቃላትን መፃፍ መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስምንት ፡- ያነበቡትን ቃል አስታውሶ መጻፍ

ዓላማ ፦ ያነበቡትን ቃል አስታውሰው መጻፍ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በተዋወቋቸው እና አዲስ በሚተዋወቋቸው ፊደላት የተመሠረቱ ቃላትን እንዲያነቡ ማድረግ
- የተፃፈውን ቃል አንድ ጊዜ ብቻ አይተው በትክክል እንዲያነቡ ማለማመድ
- ቃሉን አስታውሰው እንዲጽፉ እና በመጨረሻም የፃፉትን በትክክል እንዲያነቡ ማለማማድ
- በወረቀት ላይ የተፃፈውን ቃል ማሣየትና ሥራቸውን ራሳቸው እንዲገመግሙ ማድረግ

ምዘና ፦ ያነበቡትን ቃል አስታውሰው መጻፍ መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፦ ከጥቁር ሰሌዳ ላይ ቃላትን መገልበጥ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች እንዴት እንደሚማሩ ትንሽ ገለፃ ማድረግ
- ከጥቁር ሰሌዳ ላይ በትክክል መገልበጥ እንዳለባቸው ማስገንዘብ
- ቃላቶቹ ሲፃፉ ፊደላቶቹ ተራርቀው ወይም ተነጣጥለው መፃፍ እንደሌለባቸው ማስገንዘብ

ምዘና ፦ ከጥቁር ሰሌዳ ላይ ቃላትን መገልበጥ መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አስር ፦ የተለየውን ቃል መክበብ

ተግባር ዘጠኝ ፦ ከጥቁር ሰሌዳ ላይ ቃላትን መገልበጥ

ዓላማ ፦ የተለየውን ቃል መክበብ ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በጥቁር ሠሌዳ ላይ በአንድ መስመር ላይ ሶስት አንድ ዓይነት እና አንድ የተለየ ቃል መፃፍ
- በየተራ /በፍቃደኝነት/ ሕፃናቱን እያስነሱ እንዲያነቡ ማድረግ
- ከአራቱ ቃላቶች የትኛው የተለየ እንደሆነ እና ለምን እንደተለየ በመጠየቅ ማወያየት
- ተመሣሣይ ጥያቄዎችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ መፃፍ
- ሕፃናቱ በደብተራቸው ላይ ገልብጠው ትክክለኛውን መልስ እንዲያከቡ ማድረግ

ምዘና ፦ የተለየውን ቃል መክበብ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

## ተግባር አስራ አንድ ፦ አጫጭር ዐረፍተ ነገሮችን ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ አጫጭር ዐረፍተ ነገሮችን ከወረቀት ላይ መገልበጥ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- አጫጭር ዐረፍተ ነገሮችን ወረቀት ላይ በመፃፍ በየጠረጴዛቸው ላይ ማስቀመጥ
- የተሰጣቸውን ዐረፍ ተነገር ከወረቀቱ ላይ እንዲጽፉ እና ሲጨርሱም ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ማለማመድ

ምዘና ፦ አጫጭር ዐረፍተ ነገሮችን ከወረቀት ላይ መገልበጥ መለማመዳቸውን መከታተል።

## ተግባር አስራ ሁለት ፦ ዐረፍተ ነገሮችን ከጥቁር ሰሌዳ ላይ በመገልበጥ ማንበብ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ዐረፍተ ነገሮችን ከጥቁር ሰሌዳ በመገልበጥ ያነባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በጥቁር ሠሌዳ ላይ የተፃፉ ዐረፍተነገሮችን በደብተራቸው ላይ በመገልበጥ እንዲጽፉ ማድረግ
- ሕፃናቱ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ አሟልተው መፃፍ እስኪችሉ ማለማመድ
- የፃፉትን መልሰው ማንበብ መቻላቸውን ማረጋገጥ

ምዘና ፡- ዐረፍተ ነገሮችን ከጥቁር ሰሌዳ ላይ በመገልበጥ ማንበብ መለማመዳቸውን መገምገም።

**ተግባር አስራ ሶስት ፡-ጥያቄዎችን ከጥቁር ሰሌዳ ላይ በመገልበጥ መልስ መስጠት**

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ጥያቄዎችን ከጥቁር ሰሌዳ ላይ በመገልበጥ መልስ መስጠት ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በጥቁር ሠሌዳ ላይ ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን በመጻፍመልስእንዲመልሱ ማድረግ
- አጫጭር ጥያቄዎችን በደብተር ላይ በመገልበጥ መልሱን እንዲጽፉ ማለማመድ

ለምሳሌ፡- ስምህ ማነው?

ስንት ዓመትህ ነው?

ዛሬ ዕለቱ ምንድ ነው? ወዘተ…

ምዘና ፡- ጥያቄዎችን ከጥቁር ሰሌዳ ላይ በመገልበጥ መልስ መስጠት መቻላቸውን መገምገም።

**ተግባር አስራ አራት ፡- በተዋወቋቸው ፊደላት ቃላት መመስረትና መጻፍ**

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- በተዋወቋቸው ፊደላት ቃላት መመስረትና መጻፍ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተዋወቋቸውን ፊደላት መጠሪያ ስም በቃል ይንገሩአቸው እና ሕፃናቱ እንዲጽፉ ያድርጉ
- በተዋወቋቸው እና በሚያውቋቸው ፊደላት የተመሠረቱ ቃላትን መንገር
- ሕፃናት የፊደላቱን ቅርፅ በማስታወስ በደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ማለማመድ

ምዘና ፡- በተዋወቋቸው ፊደላት ቃላት መመስረትና መፃፍ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አስራ አምስት ፡- ስለ ራሳቸው መፃፍ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ስለ ራሳቸው መፃፍ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለሕፃናት ወረቀት እና እርሳስ በመስጠት የሚከተሉትን መፃፍ፡-
    - ስማቸውን
    - የሚኖሩበትን ሰፈር
    - የወላጆቻቸውን እና የሚቀርቧቸውን ሰዎች ስም መፃፍን እንዲለማመዱ ያድርጉ

ምዘና ፡- ስለ ራሳቸው መፃፍ መለማመዳቸውን መገምገም።

ተግባር አስራ ስድስት ፡- ዶቃ ውስጥ ክር ማስገባት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ዶቃ ውስጥ ክር ማስገባት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ዶቃ፣ ክር ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ዶቃዎችን በመስጠት ዶቃዎቹን በክር ውሰጥ እንዲከቱ ማለማመድ
- ዶቃዎችን በውድድር መልክ ልጆቹ በክር ውሰጥ መከተት ማለማመድ
- ቀድሞ የጨረሰን ቢንጐ በማለት መጨረሱን/ሷን ማሳውቅ በዚህ ዓይነት ሁሉንም ሕፃናት በጨዋታው ማሳተፍ

ማስታወሻ ፡- ይህ ተግባር ተደጋግሞ ሊሰራ የሚችል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ዶቃ ውስጥ ክር ማስገባት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ ሰባት ፡-በመቀስ ወረቀቶችን መቆራረጥ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- በመቀስ ወረቀቶችን መቆራረጥ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ባለቀለም ወረቀቶች፣ጫፉ ዱልዱም የሆነ መቀስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ ባለቀለም ወረቀቶችን እና ጫፉ ዱልዱም የሆነ መቀስን መስጠት
- በተለያየ መጠን እና ቅርጽ ወረቀቶችን ሕፃናቱ እንዲቆራረጡ ማድረግ
- ስዕል በመስጠት በስዕሉ ላይ የተቆራረጡትን ወረቀት ኮላ በመለቅለቅ እንዲለጥፉ ማድረግ

ምዘና ፡- በመቀስ ወረቀቶችን መቆራረጥ መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- የተለያዩ ሞዴሎችን መስራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቦካ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ ሞዴሎችን እንዲሠሩ ማድረግ
- ሲጨርሱም ስማቸውን ከግርጌ እንዲጽፉ በማድረግ በግርግዳ ላይ መለጠፍ

ማስታወሻ ፡- ይህ ተደጋግሞ ሊሰራ የሚችል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ማስታወሻ፡- ይህ ተደጋግሞ ሊሰራ የሚችል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የተለያዩ ሞዴሎችን መስራት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አስራ ስምንት ፡- የተለያዩ ሞዴሎችን መስራት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

## 2.3.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም ----------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም -------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም ---------------------------------------------- ዓመተ ምህረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ ----------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት ----------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት ----------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል፡፡

| | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመት መጀመሪያ | በዓመት አጋማሽ | በዓመት መጨረሻ |
| **1.** መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽመስጠት | | | |
| 1.1 በአካባቢ የሚደመጡ ድምፆችን መለየት ይችላሉ | | | |
| 1.2 በድምፆች መካከል ያለውን ልዩነት መለየት ይችላሉ | | | |
| 1.3ለትዕዛዞችና ለመመሪያዎች ምላሽ መሰጠት ይችላሉ | | | |
| 1.4 ተረቶችን አዳምጠው የተረዱትን መግለጽና መልሰው መተረክ ይችላሉ | | | |
| **2.** በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግርና የምልክት ቋንቋ መግባባት | | | |
| 2.1 ቋንቋን በእርግጠኝነት መጠቀም ይችላሉ | | | |
| 2.2 በንግግር ቋንቋ ደስታን ማግኘት ይችላሉ | | | |
| **3.** በማንበብ መደሰት ዕውቀት ማግኘትና መረዳት | | | |
| 3.1 ቀላል ቃላቶችንና ዓረፍተ ነገሮችን ማንበብ ይችላሉ | | | |
| **4.** የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት | | | |
| 4.1 ፊደላትንና ቃላትን መፃፍ ይችላሉ | | | |

## 2.4. በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ የሂሣብ ስሌትንና ጽንሰ ሐሳብን መጠቀም

### 2.4.1 ማብራሪያ

የሂሳብ ክንዋኔ /ትምህርት/ በባህሪዉ በአእምሮአዊ ስራ ላይ ያተኮረ ነዉ። ሂደቱን በተገቢዉ ደረጃ ለመምራት ህጻናት ተፈላጊዉ ብቃት ላይ ለማድረስ የህጻናቱን የአእምሮ /የማሰብ/ መዳበር ደረጃ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ይህ ከሆነ ህጻናት ራሳቸዉን ችለዉ ማሰብ የሚችሉ፣ ችግር የመፍታት ዝንባሌ ያላቸዉና የሂሳብ ትምህርትን በመዝናናትና በደስታ የሚማሩ ሊሆኑ ይችላሉ።

> የሂሳብ ትምህርት በቀጥታ በህጻናት በዕለት ተዕለት ተሞክሮ ላይ ተመስርቶ በነገሮች መካከል ያለ ግንኙነትን ለመረዳት ይጠቅማል። ህጻናት ከሚገኙበት የዕድሜና ግንዛቤ ደረጃ የተነሳ ግንኙነቶችን ለማስተዋል ይቸገራሉ።
>
> ስለዚህ ህጻናት በበለጸገ አካባቢ ቁሳቁሶችን እየተጠቀሙ በራሳቸዉ አቅም እንዲንቀሳቀሱና አካባቢያቸዉን እየፈተሹ እንዲማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል።

ህጻናት መደበኛ ትምህርት ቤት ሲገቡ ከሚጠብቋቸዉ ከፍተኛ ተግባራት አንዱ የአእምሮ ስራ ነዉ። ከ 5-6 ዓመት ያለዉ እድሜ ክልል የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የሚጠቃለልበትና ለመደበኛ ትምህርት ቤት የሚዘጋጅበት በመሆኑ በዚህ ጊዜ ከሂሳብ ጽንሰ ሃሳብ ጋራ የተያያዙ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ እገዛ የሚያደርጉ ተግባራት ናቸዉ። ስለዚህ የሂሳብ ትምህርት የህጻናት አእምሮ የሚያዳብርና በደስታ የሚሳተፉበት እንዲሆን እንቅስቃሴያቸዉ ተግባራዊና ከዕለት ተዕለት ክንዉኖች ጋር የተያያዘ ሆኖ ታቅዶ ከዕድሜና ከችሎታቸዉ ጋር ተመጥኖ መከናወን ይኖርበታል።

### 2.4.2 አጠቃላይ ዓላማዎች

1. ነገሮችን በዓይነት መመደብ፣ በነገሮች መካከል ያለ ዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ የማሳየት ችሎታቸውን ማዳበር
2. በነገሮችና በቁጥሮች መካከል ያለ አንድነትና ልዩነት መናገር እንዲችሉ ማድረግ
3. 1-20 አሃዞችን መለየት፣ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስን እንዲለማመዱና ገንዘብን እንዲለዩ ማድረግ
4. ቦታን፣ ርቀትንና አቅጣጫን መግለፅ፣ ነገሮችን መደርደርና ማወዳደር እና ቦታን መግለፅ እንዲችሉ ማድረግ

### **2.4.3** የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. የቁሳቁሶችን ባህሪ መፈተሽ መረዳትና መለየት
    1.1. ነገሮችን በዓይነት መመደብ ይችላሉ
2. ነገሮችን በባህርያቸው መሠረት ማወዳደር
    2.1. በነገሮች መካከል ያለ ዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሣየት ይችላሉ
3. ቁጥሮችን መተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መሥራት
    3.1. በነገሮችና በቁጥሮች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት መናገር ይችላሉ
    3.2. እኩል ናቸው፣ ይበልጣል፣ያንሳል በማለት መናገር ይችላሉ
    3.3. ከ 1-20 አሃዞችን መለየት ይችላሉ
    3.4. ከ 1-20 መቁጠር መደመርና መቀነስ ይችላሉ
4. በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችንና መሣሪያዎችን መጠቀም
    4.1. ቦታን፣ ርቀትንና አቅጣጫን መግለጽ ይችላሉ
    4.2. ነገሮችን በሥርዓት መደርደርና ማወዳደር ይችላሉ
5. የጊዜን ጽንሰ ሐሳብ መረዳት መገለጫዎችን መጠቀም
    5.1. በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየትና መከተል ይችላሉ
6. የቦታን ጽንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም
    6.1. የቁሳቁሶችን መገኛ ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር መናገር ይችላሉ
7. ገንዘብን መተዋወቅ፣ መለየት፣ መግለጽና መጠቀም
    7.1. የገንዘብን ዋጋ መናገር ይችላሉ

2.5.4 የሚጠበቁ ውጤቶች ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎች፣ የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. የቁሳቁሶችን ባህሪ መፈተሽ መረዳትና መለየት | 1.1. ነገሮችን በዓይነት መመደብ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- አንድ አይነት ነገሮችን ማዛመድ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በአካባቢ ሊገኙ የሚችሉ ጥንድ ነገሮች፣ ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች፣ ጠጠሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጥንድ የሆኑ ነገሮችን መደባለቅ

ለምሳሌ፡- ፍሬዎች በያይነቱ /የባህር ዛፍ፣ የጥድ ወዘተ.../፣ ቆርኪዎች፣ ጠጠሮች፣ ትልልቅ የአደንጓሬ ዘሮች ወዘተ...

- ከተደባለቁት በመቆንጠር ለእያንዳንዱ ህጻን ማደል
- በፊት ለፊታቸዉ በጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ
- ጥንድ የሚባሉት ሁለት አንድ አይነት ነገሮች መሆናቸዉን በየጠረጴዛቸዉ አቅርቦ በማሳየት ማስረዳት
- በመቀጠል ጥንድ የሆኑትን እየለቀሙ በቅደም ተከተል በየጠረጴዛቸዉ እንዲያስቀምጡ መንገር
- በትክክል ማስቀመጣቸዉንና ማዛመዳቸዉን መመልከት
- ምን ምን ጥንድ ነገሮች በፊታቸዉ እንዳስቀመጡ እንዲናገሩ ማድረግ
- አንድ አይነት ነገሮችን በጥንድ ማስቀመጥ ያቃታቸዉ ቢኖሩ አስፈላጊዉን ድጋፍ ማድረግ

ምዘና ፡- አንድ ዓይነት ነገሮችን ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

## ተግባር ሁለት ፡- በጥንድ በመያያዝ መጫወት

ዓላማ ፡- በጥንድ በመያያዝ ይጫወታሉ።
ከወረቀት ላይ መገልበጥ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ማራካሽ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጓደኛህን ፈልግ ጨዋታን እንደሚከተለዉ ማጫወት
    - ህጻናት በክፍል ዉስጥ ተበታትነዉ እንዲሮጡ በማራካሽ መምራት
    - ሁለት ሲባል ሁለት ሁለት /በጥንድ/ እንዲያያዙ መንገር
    - ሁለት ሁለት ሳይሆን ከዛ በላይ ከተያያዙ ከጨዋታ ዉጭ እንደሚሆኑ ማስገንዘብ

ማስታወሻ:- የሚጫወቱት ሕጻናት ቁጥር ሁልጊዜ ጎዶሎ ቁጥር መሆን ይኖርበታል።

ምዘና ፡- በጥንድ በመያያዝ መጫወት መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ከባለ ቀለም ክላሰር የተዘጋጁት /ተቆርጠው የወጡ/ ቅርፃ ቅርፆች፣ ነጭ ወረቀት፣ ባላቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የጂኦሜተሪ ቅርጻ ቅርጾች ካሬ፣ ጎነ ሶስት፣ ጎነ አራት የተሳሉበት ወረቀት ማደል
- ቅርጾቹን የተለያዩ ቀለሞች እንዲቀቡ ማድረግ
- የቅርጾቹን አይነትና የቀቧቸዉን ቀለም አይነት እንዲናገሩ ማድረግ
- ቀደም ሲል በቡድን 4-5 ስለ ጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾች የተማሩትን ማጠናከር

ምዘና ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን መለየት መቻላቸዉን ማረጋገጥ::

ተግባር ሦስት ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን መለየት

ተግባር አራት ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን በስም መጥራት


ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን በስም መጥራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ከባለ ቀለም ክላሰር የተዘጋጁ /ተቆርጠው የወጡ/ የጂኦሜትሪ ቅርፃ ቅርፆች ፐዝል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለህጻናቱ ጎነ አራት፣ ካሬ /እኩል ጎኖች/፣ ጎነ አምስትና ጎነ ስድስትን ማቅረብ
- ጎነ አራትን በማንሳት ማሳየት፣ ስሙን መጥራትና ጎኖቹን አብሮ መቁጠር
- ካሬንም እንደዚሁ እኩል ጎኖች እንዳሉት ማሳየትና ስሙን በመጥራት ማስቆጠር
- በተመሳሳይ ጎነ አምስት እና ጎነ ስድስት ለይተዉ እንዲያሳዩ በመጠየቅ የሚያሳየዉ ልጅ የያዘዉን ቅርጽ ጎኖች በመቁጠር እንዲያረጋግጥ ማድረግ
- በመቀጠል በየጠረጴዛቸው ላይ የተቆራረጡ የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾች ፐዝል መስጠት
- ፐዝሉን ገጣጥመዉ ያገኙትን ቅርጽ መጠሪያ ስም እንዲናገሩ ማበረታታት



ምዘና ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን በስም መጥራት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አምስት ፡- የጂኦሜትሪ  ቅርጻ ቅርጾችን ማመሳሰል

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን ማመሳሰል ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ከባለ ቀለም ክላሰር የተዘጋጁ /ተቆርጠው የወጡ / ቅርፃ ቅርፆች፣ ነጭ ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጎነ አምስት፣ ጎነ ስድስት፣ ነጭ ወረቀቶችና እርሳስ ለእያንዳንዳቸዉ ማደል
- ተዘጋጅተው የቀረቡላቸዉን ቅርጻ ቅርጾች በወረቀት ላይ በማስደገፍ እንዴት ምስሉን ማስቀረት እንደሚቻል ሰርቶ ማሳየት
- በተመሳሳይ እያንዳንዳቸዉ እንዲሰሩ በማድረግ ቅርጹን እና ኮፒ ያደረጉትን እንዲያመሳስሉ ማድረግ


ምዘና ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን ማመሳሰል□መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጾች በቦታቸው ይሞላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቅርጽ ቦርድ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የቅርጽ ቦርድን በመጠቀም የተለያዩ የጂኦሜትሪቅርጾችን ቅርጹን ከቦርዱ አዉጥተዉ /በትነዉ/ መልሰዉ እንዲገጥሙ ማድረግ
- ሁለት ሁለት ህጻናት በመመደብ በዉድድር መልክ በማጫወት ስለቅርጾች ያላቸዉን ግንዛቤ ማጠናከር



ግ ተግባር ስድስት ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጽ ቦርድን መሙላት ት።

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ተግባር ሰባት ፡- የቅርጻ ቅርጾችን ተመሳሳይነትና ልዩነትን መረዳት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ የቅርጻ ቅርጾችን ተመሳሳይነትና ልዩነትን ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ከባለ ቀለም ክላሰር የተዘጋጁት /ተቆርጠው የወጡ / ቅርፃ ቅርፆች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ኩብንና ሞላላን በመስጠት በጠረጴዛቸዉ ላይ በማንከባለል ተመሳሳይነታቸዉንና ልዩነታቸዉን እንዲናገሩ ማድረግ
- በክላሰር ላይ ወይም ወፈር ባሉ ባለቀለም ወረቀቶች ላይ ትናንሽ ክቦች፣ ሶስት ማዕዘኖችና ሲሊንደሮች መሳልና አደባልቆ መስጠት
- ኩብን አንስቶ በማሳይነት በፊታቸዉ ከሚገኙት ቅርጾች መካከል የሚመስለዉን አንስተዉ ከፊታቸዉ እንዲያስቀምጡ መጠየቅ
- ሌሎችንም ቅርጻ ቅርጾች እንደዚሁ ለይተዉ እንዲያወጡ ማድረግ
- የደረደሯቸዉ ቅርጻ ቅርጾች በምን እንደሚመሳሉና እንደሚለያዩ በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፦ የቅርጻ ቅርጾችን ተመሳሳይነትና ልዩነት መረዳት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስምንት ፡- ስብስብ መስራት እና ማወዳደር

ዓላማ ፡-

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- 3 ዐ ሴ.ሜ የሚያክል ክር ወይም ሲባጐ በሕፃናት ቁጥር ልክ፣ የስዕል ሎቶዎች፣ የእስክሪፕቶ ቀፎዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያየ ቀለም ያላቸዉ የእስክሪፕቶ ቀፎዎች በአንዳንድ ሴ.ሜ. ርዝመት መቆራረጥና ከቀጭን ሲባጎ ጋር መስጠት
- አንድ ዓይነት ቀለሞችን ጥንድ ጥንድ እያደረጉ በሲባጎዉ እንዲከቡ በማድረግ ስለጥንድ ያላቸዉ እዉቀት ማጠናከር
- የተለያዩ ቁሳቁሶች ክር /ሲባጎ/ 30 ሴ.ሜ. የሚያህል /ለእያንዳንዳቸዉ ማደልና በተሰጣቸዉ ክር /ሲባጎ/ ጫፍና ጫፉን በማገናኘት ጠረጴዛቸዉ ላይ ክብ /አጥር/ እንዲሰሩ ማድረግ
- እየዞሩ በማየት የቸገራቸዉ ህጻናት ቢኖሩ ማገዝ
- ከተሰጣቸዉ ቁሳቁስ መካከል አንዱን በመምህር እጅ ላይ የሚያዩትን ዓይነት እንዲያነሱና አጥራቸዉ ዉስጥ እንዲከቱ ማድረግ
- እያንዳንዳቸዉ የታዘዙትን በአጥሩ ዉስጥ መክተታቸዉን ማረጋገጥ
- በተመሳሳይ የቀሩትን ቁሳቁሶች አንድ በአንድ አጥራቸዉ ዉስጥ እንዲከቱ ማድረግ
- በአጥር ዉስጥ የተሰበሰቡት ‹‹ስብስብ›› እንደሚባሉ ማስረዳት
- ቀጥሎም እያንዳንዳቸዉ የየራሳቸዉን ስብስብ እያዩ በአጥራቸዉ ዉስጥ ያሉትን የስብስብ አባላት እንዲናገሩ ማድረግ
- ከላይ በተጠቀሰዉ መሰረት ስብስብ ማሰራትና በምን በምን ስብስብ እንደሰሩ ማወያየት
- ሁለተኛ አጥር ማሰራትና ሌሎች ቁሳቁሶች በመጀመሪያዉ ስብስብ ዉስጥ የሌሉትን ማስገባት
- ሁለቱንም ስብስቦች እንዲመለከቱ ጊዜ መስጠት እና ከሁለቱ ስብስብ አንድ ዓይነት የሆኑትን እየመረጡ እንዲያወጡና እንዲደረድሩ በማድረግ ሁለቱን ስብስቦች እንዲያወዳድሩ ማድረግ
- ‹‹አንድ ሁለት ሶስት ትንሽ ትንሽ ወፎችን›› በማዘመር ማጠቃለል

ምዘና ፡- ስብስብ መስራት እና ማወዳደር መቻላቸዉን ማረጋገጥ::

ዓላማ ፦ ተመሳሳይ ነገሮችን ማዛመድ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ሎቶዎች፣ የተለያዩ ቁሳቁስ ስእሎች፣ የቀለም ሰሌዳ፣ የቤት እንስሳት ቅርጽ፣ የቤት ቁሳቁስ፣ የትራንስፖርት መንገዶች እና የእጽዋት ሎቶ

የአተገባበር

ተግባር ዘጠኝ ፦ ተመሳሳይ ነገሮችን ማዛመድ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

- የቤት እንስሳት ቅርጽ፣ የቤት ቁሳቁስ፣ የትራንስፖርት መንገዶች እና የእጽዋት ሎቶን ከተቻለ ለሁለት ካልተቻለ በጠረጴዛ አራት አራት በማስቀመጥ ማደል
- እየተነጋገሩ የደረሳቸዉን ሎቶ በዓይነት በዓይነት እንዲያዛምዱ ማድረግ

ምዘና ፦ ተመሳሳይ ነገሮችን ማዛመድ መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አስር ፦ የጎደለን መሙላት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ


ዓላማ ፡- የጎደለን መሙላት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የስዕል ሎቶዎች፣ የተለያዩ ቁሳቁስ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የጎደለዉን ሙላ ጨዋታን ማጫወት
- የእንስሳት፣ የቤት ቁሳቁስ ወዘተ... ስዕል መሳል እና የተለያዩ የአካል ክፍሎቻቸዉን /አንድ ወይም ሁለት/ ቆርጦ ማዉጣትና ቁርጥራጮቹን በአንድ ላይ ማስቀመጥ
- ሙሉ የሆኑ ተመሳሳይ ስዕሎችን በአንድ ላይ መደርደር እና የጎደለ አካል ያላቸዉን ከተቀመጡት ቁርጥራጮች መካከል ፈልገዉ እንዲሞሉ ማድረግ

ለምሳሌ፡-



ምዘና ፡- የጎደለን መሙላት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።



ተግባር አስራ አንድ ፡- ስዕል መሣል

ዓላማ ፦ ስዕል መሣል ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በሥዕል ክፍለ ጊዜ ወረቀት እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ  ማደል
- ምን መሣል እንደሚፈልጉ መጠየቅ
- የፈለጉትን እንዲስሉ እና ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ

ምዘና ፦ ስዕል መሣል መቻላቸውን መከታተል።

**ተግባር አስራ ሁለት ፡- ተመሣሣይ ነገሮችን በአይነት መለየት**

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ውጤት፡- ተመሣሣይ ነገሮችን በአይነት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች፣ ጠጠሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያየ ቀለም ያላቸውን ቆርኪዎች፣ ፍሬዎች፣ ጠጠሮች ማደል
- ተመሣሣዮቹን አውጥተው እንዲደረድሩ ማድረግ
- ለምን እንደዛ እንደደረድሩአቸው እንዲናገሩ ማድረግ
- ተመሣሣዮቹን ለይተው እንዳወጧቸው እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ተመሣሣይ ነገሮችን በአይነት መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር አስራ ሶስት ፡- የሚመሳሰሉ እና የማይመሳሰሉ ነገሮችን መለየት**

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የሚመሳሰሉ እና የማይመሳሰሉ ነገሮችን መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቀለም ሰሌዳ፣ አሻንጉሊት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- አሻንጉሊት እንግዳ ሆና መጥታ <<ቤት ስሩልኝ>> ስትል የቀለም ሰሌዳን በመጠቀም በተለያየ ቀለም ቤት እንዲሠሩ ማድረግ
- በሰሩት ቤት ምን የሚመሳሰል ምን የማይመሳሰል ነገር እንዳለ እንዲናገሩ ማድረግ
- የሚመሳሰለው ቤቱ የተሠራው በቀለም ሰሌዳ መሆኑ፣የማይመሳሰለው ደግሞ ቀለማቱ የተለያዩ መሆናቸው እንደሆነ በመረዳት በየተራ እንዲገልጹ ማድረግ
- <<ቤቴ ቤቴ>> የሚለውን መዝሙር ማዘመር

ምዘና ፡- የሚመሳሰሉ እና የማይመሳሰሉ ነገሮችን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. ነገሮችን በባህርያቸው መሠረት ማወዳደር | 2.1.በነገሮች መካከል ያለ ዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሣየት ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ ፡- በነገሮች መሀከል ያለ ዝምድናን መግለፅ**

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ቅርጽናቀለም ያላቸው ነገሮች ኳሶች፣ ቆርኪዎች፣ የሀይላንድ ክዳኖች፣

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ ቁሳቁሶችን በየጠረጴዛቸዉ ላይ አደባልቆ ማስቀመጥ
- ተመሳሳይ የሆኑትን አዉጥተዉ በአንድ ላይ እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- ተመሳሳዮቹን አዉጥተዉ በጠረጴዛ ላይ ካስቀመጡ በኋላ በምን እንደሚመሳሰሉ እና ዝምድናቸዉን እንዲያስተዉሉ ማድረግ

  ለምሳሌ፡- ኳስ፣ ቆርኪ ወዘተ…
- ያወጧቸዉን ተመሳሳይ ነገሮች በቅደም ተከተል መግለጽ እንዲችሉ ማድረግ

  ለምሳሌ፡- ትንሽ፣ ትልቅ፤ ቀላል፣ ከባድ ወዘተ…

ምዘና ፡- በነገሮች መካከል ያለ ዝምድናን መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ።


## ተግባር ሁለት ፡- አበላላጭ ቃላትን መጠቀም

ዓላማ ፡- አበላላጭ ቃላትን መጠቀም ማስቻል።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትንሽ፣ ትልቅ፣ በጣም ትልቅ፣ በጣም ትንሽ ወዘተ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- እርከን ለህጻናቱ ጠረጴዛቸው ላይ ማቅረብ
- ከትልቅ ወደ ትንሽ፣ ከትንሽ ወደ ትልቅ እንዲደረድሩ ማድረግ
- በመቀጠል ትንሽ፣ ትልቅ፣ በጣም ትልቅ፣ በጣም ትንሽ ወዘተ... በማለት ለመግለጽ እንደሚመች እንዲደረድሩና አበላላጭ ቃላትን በመጠቀም እንዲናገሩ ማበረታታት



ምዘና ፡- አበላላጭ ቃላትን መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥ።



## ተግባር ሶስት ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን በቅደም ተከተል መደርደር

ዓላማ ፡- የጂኦሜትሪ  ቅርጻ ቅርጾችን በቅደም ተከተል መደርደር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በወረቀት ላይ የተሳለ ጎነ ሶስት፣ ጎነ አራት፣ ጎነ አምስት፣ ኪዩብ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በወረቀት ላይ የተሳሉትንሽና ትልቅ የሆኑ የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን/ጎነ ሶስት፣ ጎነ አራት፣ ጎነ አምስት፣ ኪዩብ መስጠት
- ትንንሾችን ቀይ፣ ትልልቆቹን ቢጫ እንዲቀቡ ማድረግ
- በመቀስ ቆርጠዉ እንዲያወጡና ትንሽ እና ትልቁን ለይተዉ እንዲደረድሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን በቅደም ተከተል መደርደር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- ቁሶችን ከትንሽ ወደ ትልቅ በመደርደር ማወዳደር


ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ቁሶችን ከትንሽ ወደ ትልቅ በመደርደር ያወዳድራሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ከትልቅ ወደ ትንሽ የተቆረጡና ቀለም የተቀቡ ሸምበቆዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከትንሽ ወደ ትልቅ /ከአጭር ወደ ረጅም/ ተቆራርጠው ቀለም የተቀቡ ሸምበቆዎች /ሽመሎችን/ በደረጃቸው መደርደር
- በጨዋታ መልክ ትንሽ፣ በጣም ትልቅ፣ እጅግ በጣም ትልቅ ብለው በመደርደር እንዲያወዳድሩ ማድረግ



ምዘና ፡- ቁሶችን ከትንሽ ወደ ትልቅ በመደርደር ማወዳደር መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. ቁጥሮችን መተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መሥራት | 1.1. በነገሮችና በቁጥሮች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት መናገር ይችላሉ፡፡ |

ተግባር አንድ ፡- ተቆጣሪዎችን መቁጠር

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ተቆጣሪዎችን መቁጠር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሽመሎች፣ ቆርኪዎች፣ ጠጠሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከ 10 ያልበለጡ የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮችን ማደልና በዓይነት እንዲለዩ ማድረግ
  ለምሳሌ፡- ሽመሎች፣ ቆርኪዎች፣ ጠጠሮች
- በዓይነት የለዩአቸዉን እንዲደረድሩ እና እንዲቆጥሩ ማድረግ
- በወረቀት ላይ የተሳሉ ትንንሽ ተቆጣሪ ነገሮች ስዕሎች ማደልና እንዲቆጥሩ ማድረግ
- ቁሳቁሶች የተለያዩ ቢሆኑም ሲቆጠሩ መጠናቸዉ እንደማይለያዩ እንዲያስተዉሉ ማድረግ

ምዘና ፡- ተቆጣሪዎችን መቁጠር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- <<ጭብጨባን በቁጥር አዛምድ>> የሚለዉን ጨዋታ መጫወት ይችላሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ተቆጣሪ ነገሮችን ከቁጥር አሃዞች ጋር ማዛመድ እንዲችሉ ቀድመዉ ከ4-5 ዓመት የተዋወቋቸዉን የቁጥር አሃዞች በመጠቀም የቁጥር አሃዝ ማሳየት
- በእርጋታ ማጨብጨብና ጭብጨባዉን እንዲቆጥሩ ማድረግ
- ያዩትን የቁጥር አሃዝ መጠን በጭብጨባ እንዲገልጹ በማድረግ ማጫወት
- እያንዳንዱ ህጻን በተመሳሳይ እንዲተገብር እድል መስጠት

ምዘና ፡- <<ጭብጨባን በቁጥር አዛምድ>> የሚለዉን ጨዋታ መጫወት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሦስት፡- ተቆጣሪዎችን ከአሀዝ ጋር ማዛመድ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ



ተግባር ሁለት ፡- <<ጭብጨባን በቁጥር አዛምድ>> የሚለዉን ጨዋታ ማጫወት

ዓላማ ፡- ተቆጣሪዎችን ከአህዝ ጋር ማዛመድ ይችላሉ::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሽመሎች፣ ቆርኪዎች፣ ጠጠሮች፣ ተንቀሳቃሽ የቁጥር አህዞች፣ እርሳሶች፣ ከለሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ተቆጣሪ ነገሮችን ለሕጻናቱ ማደል

  ለምሳሌ፡- ሽመሎች፣ ቆርኪዎች፣ ጠጠሮች፣ ተንቀሳቃሽ የቁጥር አህዞች
- የተሰጧቸውን ተቆጣሪ ነገሮች በዓይነት እንዲለዩ ማድረግ
- በዓይነት የተለዩትን ተቆጣሪ ነገሮች ከተንቀሳቃሽ የቁጥር አህዝ ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ
- እየተዘዋወሩ ሕጻናት በትክክል ማዛመዳቸውን በማየት ማበረታታት
- በትክክል ያላዛመዱ ቢኖሩ ድጋፍ ማድረግ

ምዘና ፡- ተቆጣሪዎችን ከአህዝ ጋር ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- የአሃዝን መጠን በተቆጣሪ ነገሮች ማሳየት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የአሃዝን መጠን በተቆጣሪ ነገሮች ማሳየት ይችላሉ::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከ 1-20 በቃል እንዲቆጥሩ ማድረግ
- ተቆጣሪ ነገሮች መስጠት
- መምህር የሚጠሩትን ቁጥር ተቆጣሪ ነገሮች በመደርደር እንዲያሳዩ ማድረግ

  ለምሳሌ፡- መምህር አራት ሲሉ ሕጻናት አራት ተቆጣሪ ነገሮችን በመደርደር እንዲያሳዩ ማድረግ።

ምዘና ፡- የአሃዝን መጠን በተቆጣሪ ነገሮች ማሳየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- የቁጥር አሃዞችን ከተቆጣሪዎች ጋር ማዛመድ



ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ የቁጥር አሃዞችን ከተቆጣሪዎች ጋር ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የአሃዝ ካርዶች፣ ሽመል፣ የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የሽመል ቆጠራ ሳጥንን ማቅረብ
- ከ 1-10 ድረስ አሃዝ እና ተቆጣሪ /ሽመልን/ እንዲያዛምዱ ለእያንዳንዱ ህጻን እድል መስጠት
- የቁጥር አሃዝን ከላይ ተቆጣሪዎችን ከታች እንዴት ማስቀመጥ እንዳለባቸዉ በአንድ የቁጥር አሃዝ ማሳየት
- በመቀጠል ሕጻናቱ በተመሳሳይ እንዲተገብሩ በማድረግ የቁጥር አሃዝና መጠንን የማዛመድ ችሎታቸዉን ማጠናከር
- ቀድሞ ከ 1-10 አሃዝና ተቆጣሪን አዛምዶ የጨረሰ ቡድን መዝሙር በመዘመር ሌሎችን እንዲያበረታታ ማድረግ

ምዘና ፦ የቁጥር አሃዞችን ከተቆጣሪዎች ጋር ማዛመድ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ስድስት ፦ በጭብጨባ ቁጥር ልክ ተቆጣሪ ነገሮችን መደርደር

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- በጭብጨባ ቁጥር ልክ ተቆጣሪ ነገሮችን ይደረድራሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮችን ለህጻናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ ማደል
- ጭብጨባን ቆጥረዉ ተቆጣሪ ነገሮችን እንዲደረድሩ ማድረግ
- ሕጻናት በጥንድ እየሆኑ እርስ በርሳቸው እንዲተገብሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በጭብጨባ ቁጥር ልክ ተቆጣሪ ነገሮችን መደርደር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- ስዕል በመሳል ቁጥርን ይቆጥራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ፣ ከለር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ወረቀት፣ እርሳስና ከለር ለሕጻናቱ በየጠረጴዛቸው ማደል
- ስዕል እንዲስሉና ከሳሏቸው ሥዕሎች ውስጥ አንድ ስዕል ከለር እንዲቀቡ ቀጥሎ ሁለት እያሉ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት እንዲቀቡ ማድረግ
- የሳሏቸውን ሥዕል ብዛትና ከሳሏቸው ውስጥ ምን ያህሉን ከለር እንደቀቡ እንዲናገሩ ማድረግ
- 

[illegible]

ተግባር ሰባት ፡- ስዕል በመሳል ቁጥርን መቁጠር

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3.ቁጥሮችን መተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መሥራት | 3.2. እኩል ናቸው ይበልጣል፣ ያንሳል በማለት መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የይበልጣል እና ያንሳል ጽንሰ ሀሳቦችን መገንዘብ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ


ዓላማ ፡- የይበልጣልና ያንሳል ጽንሰ ሀሳቦችን ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ቆርኪ፣ ጠጠር፣ ፍሬዎች፣ የእስክሪፕቶ ክዳን፣ የሃይላንድ ክዳኖች፣ ሲባጎ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሁለት ስብስብ አጥር ለመስራት የሚያገለግሉ 30 ሴ.ሜ. ያህል ርዝመት ያላቸዉ ሲባጎዎች እና ለስብስብ መስሪያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ማደል

  ለምሳሌ፡-ቆርኪ፣ ጠጠር፣ ፍሬዎች፣ የእስክሪፕቶ ክዳን፣ የሃይላንድ ክዳኖች፣ ሲባጎ
- ህጻናት የስብስብ አጥሮች እንዲሰሩ ማድረግ
- ስለአጥራቸዉ እንዲናገሩ ማድረግ
- በአንደኛዉ እና በሁለተኛዉ ስብስብ ዉስጥ ምን እንደተሰበሰበና በመሃከላቸዉ ያለዉን ልዩነት እንዲናገሩ ማድረግ
- የሁለቱም ስብስብ አባላት አንድ አንድ በማገናኘት ማስቀጠር
- የየትኛዉ ስብስብ አባላት ይበልጣል የየትኛዉስ ያንሳል ብሎ በመጠየቅና እንዲያሳዩ በማድረግ የይበልጣልና የያንሳል ጽንሰ ሀሳቦችን እንዲረዱ ማበረታታት



☑ **ምዘና ፡- የይበልጣል እና ያንሳል ጽንሰ ሀሳቦችን መገንዘብ መቻላቸውን ማረጋገጥ።**



**ተግባርሁለት ፡- የማዛመድ ጨዋታ ማጫወት**


**ከወረቀት ላይ መገልበጥ**


ዓላማ ፡- የማዛመድ ጨዋታ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሎቶ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ ቁሳቁሶች ሎቶን በማዛመድ እንዲጫወቱ ማድረግ





ምዘና ፡- የማዛመድ ጨዋታ መጫወት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. ቁጥሮችን መተዋወቅ፣ መግለጽ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መሥራት | 3.3. 1-20 አሃዞችን መለየት ይችላሉ። |

### ተግባር አንድ ፡- በተለያየ አቅጣጫ ቁጥር መቁጠር

ዓላ[illegible]
ከወረቀት ላይ መገልበጥ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቀማ ፡- የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከ **1-20** በቃል እንዲቆጥሩ በማነቃቃት ማስቆጠር
  - የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች /ቁሳቁስ/ መስጠት
  - **1-20** በመደርደር እንዲቆጥሩ ማድረግ
  - ሲቆጥሩ በተለያየ አቅጣጫ ወደጎን፣ ወደታች እንዲደረድሩ ማድረግ
  - የተደረደሩትን ከቀኝ ወደግራ እና ከግራ ወደቀኝ፣ ከላይ ወደታች እና ከታች ወደ ላይ ማስቆጠር
  - በተለያየ አቅጣጫ ቢቆጥሩና የተለያዩ ተቆጣሪ ነገሮች በሆኑም መጠናቸዉ እንደማይለወጥ እንዲያስተዉሉ መርዳት
  - ሲቆጥሩ የመጨረሻዉን የተጠራ ቁጥር አሃዝን በማሳየት እንዲቆጥሩ ማድረግ

  ለምሳሌ**:-** 4 ተቆጣሪ ነገሮች ቢቆጥሩ አራት የመጨረሻዉ ተቆጣሪ ሳይሆን በሙሉ አራት ነገሮች እንደሆኑ መረዳትን ማዳበር።
- <<ትንሽ ትንሽ ወፎች>> እና <<**10** አዳዲስ ልብሶችን>> ማዘመር

ምዘና ፡- በተለያየ አቅጣጫ ቁጥር መቁጠር መቻላቸውን ማረጋገጥ።



### ተግባር ሁለት ፡- አዲስ የቁጥር አሃዝ መተዋወቅ

ዓላማ ፡- አዲስ የቁጥር አሃዝ ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የብርጭቆ ወረቀት፣ የቁጥር ሰሌዳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የቁጥር አሃዞች 1-20 ለማስተዋወቅ ቀደም ሲል የሚያዉቁትን በክለሳ መልክ መጠየቅ እነ ማስታወስ
- አዲስ የቁጥር አሃዞችን /ከ11-20/የብርጭቆ ወረቀት የቁጥር ሰሌዳ በመጠቀም ማሳየት

አሃዞቹን በስም በመጥራት በየጠረጴዛቸዉ ላይ ማድረግና በሁለት ጣቶቻቸዉን እንዲዳስሱ ማድረግ

- የዳሰሱትን ቁጥር በአየር ላይ እንዲጽፉ ማሳየት እና ማለማመድ
- አዲስ የቁጥር አሃዞችን በቅደም ተከተል የሦስት ክፍለ ጊዜ የማስተማሪያ ዘዴ በመጠቀም ማስተዋወቅ
- አዲስ ከተዋወቋቸዉ ዉጭ የሆኑትን የቁጥር አሃዞች አደባልቆ በማስቀመጥ የተዋወቁትን ቁጥር በየተራ መጥራት
- የተጠራዉን ቁጥር ለይተዉ እንዲያወጡ ማድረግ።

ምዘና ፡- አዲስ የቁጥር አሃዝ መተዋወቃቸዉን መገምገም።

ተግባር ሦስት ፡- የቁጥሮችን አመሰራረት መገንዘብ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የቁጥሮችን አመሰራረት ይገነዘባሉ::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጠጠሮች፣ ፍሬዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የቁጥሮችን አመሰራረት እንዲገነዘቡ 1-10 ቁጥሮችን በጠጠሮች /በፍሬዎች/ ማስቆጠርና በቀደመዉ ቁጥር ላይ ጠጠር /ፍሬ/ ሲጨመርበት ቀጣዩ ቁጥር እንደሚገኝ ማስረዳት
- ቀጣዩን ቁጥር በመጥራትና በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ሁሉም ህጻናት እንዲያዩትና እንዲጠሩት ማድረግ
- ጠጠሮች /ፍሬዎች/ በመጠቀም ያዩትን አሃዝ እንዲገነቡ ማድረግ
- ከ 11-20 ያሉ ቁጥሮችን አመሰራረት እንዲገነዘቡ ከአንድ ጎን ሌላ አንድ ስንጽፍ 11 እንደሚሆን፤ ከአንድ ጎን 2 መጥታ ስትቆም 12 እንደሚሆን ወዘተ... ማሳየት

ማስታወሻ ፡- ይህንን በተረት /በጨዋታ/ መልክ እንዲናገሩ በማድረግ በተነቃቃ ሁኔታ ሊከናወን ይችላል።

ለምሳሌ ፡-አንድ ቁጥር መጥታ ቆመችና ብቻዬን መሆን አልፈልግም እኔን የምትመስል ሌላ ቁጥር ጓደኛ እንደትሆነኝ ጎኔ አቁሙልኝ አለች። ጎኗ አቆምንላት ግን የቁጥሯ መጠሪያ ተቀየረ አስራ አንድ ሆነች በማለት የሌሎቹንም ቁጥሮች አመሰራረት ቀስ በቀስ ማሳየት።

ምዘና ፡- የቁጥሮችን አመሰራረት መገንዘባቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- ቁጥርን መጻፍ እና ማንበብ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ ቁጥርን መጻፍና ማንበብ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ባለቀለም እርሳስ□

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ከ 1-20 በድርብ የተጻፉ የቁጥር አሃዞችን መስጠትና ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
    - ከ 1-20 በነጠብጣብ የተጻፉ የቁጥር አሃዞችን በወረቀት ላይ ጽፎ መስጠት
    - እንዴት ማድመቅ /ማያያዝ/ እንደሚቻል በማሳየት እንዲያደምቁ ማድረግ
    - ያደመቁትን የቁጥር አሃዝ መጠሪያ እንዲናገሩ በመጠየቅ ማበረታታት
    - የተጻፉ ቁጥሮችን በማየት አስመስሎ መጻፍን እንዲለማመዱ ማድረግ
    - ከ 1-20 የቁጥር አሃዞችን ደባልቆ መስጠትና ቁጥሩ ሲጠራ ከተደባለቁት ዉስጥ አሀዙን መርጦ ወደ ላይ አንስቶ የማሳየት ጨዋታን እንዲጫወቱ በማድረግ ማጠናከር
    - ከ 1-20 ቁጥር የያዙ የቁጥር ፐዝሎችን በመገጣመም እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፦ ቁጥርን መጻፍና ማንበብ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አምስት ፦ የቁጥር ስንኞችን መናገር

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የቁጥር ስንኞችን መናገር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ፒዝሎች፣ የቁጥር ዶሚኖ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የቁጥር ስንኞችን እንዲናገሩ ማለማመድ

ለምሣሌ ፡- አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት የልጅ ምሣና እራት

አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠኝን ምን ላድርጋት

አስር ከአንድ ጋር ዜሮን ቆማ አየሁዋት

- በመቀጠል የቁጥር እንቆቅልሽንማጫወት

ለምሣሌ፡- ‹‹እኔ ከ **5** በኋላ ከ **3** በፊት እገኛለሁ እኔ ማነኝ**?**››

- የቁጥር ዶሚኖ እንዲጫወቱ ማለማመድና ጊዜ መስጠት

ምዘና ፡- የቁጥር ስንኞችን መናገር መለማመዳቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3.ቁጥሮችን መተዋወቅ | 3.4 . ከ 1-20 መቁጠር መደመርና መቀነስ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የመደመር ጽንሰ ሀሳብን ማስተዋወቅ


ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የመደመር ጽንሰ ሃሳብን ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመቁጠሪያ ክላሰሮች፣ ተቆጣሪ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ተቆጣሪ ነገሮችን እና የመደመር ምልክትን እንዲሁም የመቁጠሪያ ክላሰሮችን ለህጻናቱ ማደል
- የመደመር /የመጨመር/ ምልክትን በማሳየት እንደሚከተለዉ ማስረዳት፡-
    - ○ አንድ ህጻን ወደ መምህር ጠረጴዛ መጥራት
    - ○ በመቁጠሪያ ክላሰር ላይ ሁለት ክቦችን እንዲያስቀምጥ ማድረግ
    - ○ ሌላ ልጅ ደግሞ በዛው መስመር ላይ ትንሽ ራቅ ብሎ አንድ ክብ እንዲያስቀምጥ ማድረግ
    - ○ መጀመሪያ ያስቀመጠው ስንትክብ እንዳስቀመጠ፤ ሁለተኛው ደግሞ ስንት ክብ እንደጨመረ መጠየቅ
    - ○ የሁለቱ አንድ ላይ ስንት እንደሆነ መጠየቅ
    - ○ በሁለቱ መካከል የመደመር ምልክት ማስቀመጥ እና መልሱን ይሆናል (=) የሚለውን ቃል እና ምልክት በመጠቀም መንገር
    - ○ ይህን በየግላቸው ወይም በቡድን እንዲለማመዱ ማድረግ



▯ ▯ + ▯ = ▯ ▯ ▯

- ○ <<አንድ ላይ አንድን ጨምሬ>> የሚለውን መዝሙር ማዘመር

ምዘና ፡- የመደመር ጽንሰ ሃሳብን መረዳታቸውን መከታተል።

ተግባር ሁለት ፡- የመደመር እና የመቀነስ ጽንሰ ሀሳብን መተዋወቅ


ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የመደመር እና የመቀነስ ጽንሰ ሃሳብን ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተቆጣሪ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ተቆጣሪ ነገሮችን ለህፃናት ማደል
- አንድ ላይ ተከማችተው ከተቀመጡ ቁሳቁሶች መካከል ህፃናት ሊመለከቱ በሚችሉበት ቦታ የመቁጠሪያ ካርዶችን በመጠቀም መቁጠር እና መደርደር
- በመምህር የተቆጠሩትን ያህል በፊታቸው ባሉ ካርዶች ላይ ቆጥረው እንዲያስቀምጡ/እንዲደረድሩ ማድረግ
- በካርዶቹ ላይ ያስቀመጡትን ቆጥረው መደርደራቸውን መከታተል
- ሌላ አንድ ተቆጣሪ በማንሳት ህፃናቱም የራሳቸውን እንዲያነሱ ማድረግ
- ቀደም ሲል ተደርድረረው በተቆጠሩት አቅጣጫ ትንሽ ራቅ አድርጎ ተጨማሪውን አንድ ማስቀመጥ
- በነበሩት ላይ አንድ ሲጨመር ለማሳየት የመደመር ምልክት እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- ስንት እንደሆነ መጠየቅ፤ አብሮ በመቁጠር ውጤቱን ይሆናል (=)የሚለውን ቃል እና ምልክት በመጠቀም መናገር



ማስታወሻ ፡- ይህንን ለመቀነስም መጠቀም ይቻላል።

- አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ የሚለውን መዝሙር ማስዘመር

ማስታወሻ፡- መደመር እና መቀነስን ለማለማመድ ለመጀመሪያ የምንጠቀመው ተቆጣሪ ነገሮችን ብቻ ሊሆን ይገባል።

ቦርድ ላይ ቁጥሮችን ከማስደመር ይልቅ የተሻለ ተነቃቅተው እንዲሳተፉ የሚያደርገው ቁሳቁሶችን እና ስእሎችን መጠቀም ነው። የመደመር (+)፣ የመቀነስ (-)፣ የእኩል ይሆናል (=) ምልክቶችም ከክላሰር ተቆርጠው በሚስብ መልኩ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

☑ ምዘና ፡- የመደመር እና የመቀነስ ጽንሰ ሃሳብን መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- በተለያየ አቅጫጫ ቁጥር መቁጠር

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- በተለያየ አቅጫጫ ቁጥር መቁጠር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተቆጣሪ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ተቆጣሪ ነገሮችን ከ 1-20 እንዲደረድሩ ማድረግ
- ወደፊትና ወደኋላ በመደጋገም እንዲቆጥሩ ማድረግ
- የቁጥር አሃዝን በማሣየት ካዩት አሃዝ በፊት ቀድማ ያለችው ስንት ቁጥር እንደሆነች ከኋላ ያለችውስ በማለት በተለያዩ አሃዞች መጠየቅና እንዲናገሩ ማበረታታት፤ ካቃታቸው ፍንጭ መስጠት
- አንድ የቁጥር አሃዝ በማሣየት እስካዩት አሃዝ ድረስ እንዲቆጥሩ ማድረግ
- ከደረሱበት የቁጥር አሃዝ ቀጥሎ ያለችውን ቁጥር እንዲናገሩ በማድረግ በተለያዩ ቁጥሮች /አሃዞች/ መደመርንና መቀነስን ማለማመድ

ለምሣሌ ፡- በ 5 ላይ 1 አረንጓዴ ጠርሙስ ሲጨመር ስንት ይሆናል? ከ 5 ላይ 1 አረንጓዴ ጠርሙስ ሲነሳ /ሲቀነስ/ ስንት እንደቀረ ማነው የሚቆጥርልኝ? ወዘተ...

> ማስታወሻ፡- መቁጠር በሽምደዳ ብቻ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።
>
> - አንድ ላይ አንድን ጨምሬ የሚለውንና አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ መዝሙርን በማዘመር ማጠናከር

ምዘና ፡- በተለያየ አቅጫጫ ቁጥር መቁጠር መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4.በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችንና መሣሪያዎችን መጠቀም | 4.1 . ቦታን፣ርቀትንና አቅጣጫን መግለጽ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የአቅጣጫ እና የርቀት ጽንስ ሀሳብን መገንዘብ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ የአቅጣጫ እና የርቀት ጽንሰ ሀሳብን ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወንበር፣ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ሁለት ህፃናት እርስ በርሳቸው በተለያየ ርቀት ላይ ከግራ እና ከቀኝ በመካከላቸው ወንበር በማድረግ እንዲቆሙ ማድረግ
- አንዱን ከወንበሩ ራቅ፤ አንዱን ቀረብ አድርጎ ማቆም
- መሃከላቸው ካለው ወንበር አንፃር የቆሙበት ቦታ ማን ቅርብ እንዳለ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት
- በመቀጠል ማን በግራ፤ ማን በቀኝ እንደቆመ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት
- ህፃናት የሚኖሩበትን አካባቢ (የቤታቸውን) አድራሻ ያውቁ እንደሆነ መጠየቅ
- ወደ አፀደ ህፃናት በምን እንደመጡና በምን ትራንስፖርት/መጓጓዣ/ እንዳስፈለጋቸው በመጠየቅ ሲመልሱ ቅርብ፣ ሩቅና በጣም ሩቅ ብለው መግለፅ እንዲችሉ በጥያቄዎች ማገዝ

ማስታወሻ ፦ ይህን ተግባር እንደ አስፈላጊነቱ ለሁለት ክፍሎ በተከታታይ ክፍለ ጊዜያት ማስተግበር የተሻለ ይሆናል ምክንያቱም ግራ እና ቀኝን ማወቅ እና ርቀትን መገንዘብ በተወሰነ መልኩ ልዩነት ስላላቸው ነዉ።

ምዘና ፦ የአቅጣጫ እና የርቀት ጽንሰ ሀሳብን መገንዘብ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ ቦታ እና አቅጣጫ መለየት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ቦታ እና አቅጣጫን መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወንበር፣ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህፃናት በሚማሩበት አፀደህፃናት ውስጥ የመማሪያ ክፍሎቻቸው የሚገኙበትን ቦታ እና አቅጣጫ መግለፅ እንዲችሉ ማለማመድ

  ለምሳሌ፡- የመማሪያ ክፍላቸው፣ቢሮው፣ የመጫወቻ ቦታቸው፣ የመመገቢያ እና የመፀዳጃ ቤት የት እንደሚገኝ እና ከየትኛው ክፍል አጠገብ እንደሆነ ወዘተ… እንዲናገሩ ማድረግ
- ቦታን ጠቋሚ መዝሙሮችንና ግጥሞችን እንዲናገሩ /እንዲዘምሩ/ ማለማመድ
- “የት ይገኛል?” ጨዋታን እና ‹‹ምን እንደተቀየረ ዕወቅ›› ጨዋታን እንዲጫወቱ በማድረግ ማጠናከር።

ምዘና ፡- ቦታ እና አቅጣጫን መለየት መቻላቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4.በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችንና መሳሪያዎችን መጠቀም | 4.2 .ነገሮችን በሥርዓት መደርደርና ማወዳደር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ትንሽና ትልቅ ቁሶችን ማወዳደር

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ትንሽና ትልቅ ቁሶችን ማወዳደር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትንሽና ትልቅ የፕላስቲክ ኩባያዎች፤በአሸዋ የተሞላ ሳጥን

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕጻናቱን ወደ ሜዳ በማውጣት ‹‹የመስፈር››ጨዋታን እንዲጫወቱ ማድረግ
- ትንሽና ትልቅ የፕላስቲክ ኩባያዎችን ለሕጻናቱ ማደል
- አሸዋ ከትልቅ ኩባያ ወደ ትንሹ ከትንሹ ወደ ትልቁ በመስፈር እንዲያወዳድሩ ማድረግ
- እየሰፈሩ በማገለባበጥ ትንሹ ኩባያ ጥቂት ትልቁ ኩባያ ብዙ እንደሚይዝ እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ትንሽና ትልቅ ቁሶችን ማወዳደር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- አጭርና ረጅም ቁሶችን በመለካት ማወዳደር

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ አጭርና ረጅም ቁሶችን በመለካት ማወዳደር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣እርሳስ፣ከለር፣ቀጫጭን ጥብጣቦች /ከክላሰር ወረቀት የተሰሩ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ወረቀት፣ እርሳስ፣ከለርና ቀጫጭን ጥብጣቦች ለሕጻናቱ ማደል
- በተሰጣቸው ወረቀት ላይ እርሳስ በመጠቀም ሁለት መንገዶች አንዱ አጭር አንዱ ረጅም ከላይና ከታች አድርገው እንዲስሉ ማድረግ
- ስለው ሲጨርሱ በቀጫጭኖቹ ጥብጣቦች እንዲለኩና የቱ አጭር የቱ ረጅም እንደሆነ በማወዳደር እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፦ አጭርና ረጅም ቁሶችን በመለካት ማወዳደር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሦስት ፦ ቀላል እና ከባድ ነገሮችን ማወዳደር

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ቀላል እና ከባድ ነገሮችን ማወዳደር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ ክብደት ያላቸው በመጠን እኩል የሆኑ በቅርፅ የሚመሳሰሉ እንጨቶችን በአሸዋ እና በጥጥ የተሞሉ በአይን ሲታዩ እኩል መጠን ያላቸው ከረጢቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- እንጨቶች በማቅረብ በሁለት እጆቻቸው መዳፍ ላይ አስቀምጠው የትኛው ቀላል የትኛው ከባድ እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- ደጋግመው በእጆቻቸው በመመዘን እንዲናገሩ ማበረታታት

| kLM | ŸvÉ |
|---|---|

- በዚሁ አይነት ከረጢቶቹን በእጆቻቸው በመለካት ከባድ እና ቀላል ቁሶችን እንዲያወዳድሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ቀላል እና ከባድ ነገሮችን ማወዳደር መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- ርቀትን መለካት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ርቀትን መለካት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ማስመሪያ፤ የመለኪያ ሲባጎ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በመምህር መቀመጫ እና በህፃናት መቀመጫ መካከል ያለውን ርቀት በእርምጃ እንዲለኩ በማድረግ ስንት እርምጃ እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- በመቀጠልም በማስመሪያ እንዲለኩ እና ስንት ማስመሪያ እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- የነሱ ጠረጴዛ ከመምህር ጠረጴዛ በመጠን መለየቱን እና አለመለየቱን መጠየቅ
- በመለኪያ ሲባጎ ተጠቅመው እንዴት መለካት እንደሚችሉ ማሳየት
- በየተራ ሲባጎውን በመጠቀም ሁለቱን ጠረጴዛዎች በመለካት እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ርቀትን መለካት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡

ተግባር አምስት ፡- ስፋትን መለካት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ ስፋትን መለካት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጎነ አራት ካሬ እና የመለኪያ ጥብጣብ (ከክላሴር ወረቀት የተቆረጠ)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በየጠረጴዛቸው ላይ ጎነ አራት ካሬ እና የመለኪያ ጥብጣብ በመስጠት የቅርፆችን ጎኖች ስፋት እንዴት እንደሚለኩ ማሳየት
- በጥብጣቡ በመለካት የትኛው ጎን ከየትኛው እንደሚጠብ/ እንደሚሰፋ ወይም እኩል እንደሆኑ እንዲናገሩ ማበረታታት


ምዘና ፦ ስፋትን መለካት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፦ የሙሉ እና የክፍልፋይ ፅንሰ ሀሳብን ማስገንዘብ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

**ዓላማ ፡-** የሙሉ እና የክፍልፋይ ፅንሰ ሀሳብን ይገነዘባሉ።

**የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡-** ቁመታቸው 12 ሳ.ሜ.፤ የጎን ስፋታቸው 3 ሳ.ሜ. የሆኑ ሁለት ሲሊንደሮች፤



**የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-**

- ከተዘጋጁ ሲሊንደሮች ውስጥ አንዱን አራት እኩል ቦታ መቆራረጥ
- የተቆራረጡትን በመደራረብ እና ከትልቁ ሲሊንደር ጋር ጎን ለጎን በማቆም እንዲያለካኩ ማድረግ
- ትልቁ/ሙሉው ሲሊንደር ከተቆራረጡት ጋር እኩል መሆኑን ማስረዳት
- ስንት እኩል ቦታ የተከፋፈለ አንድ ሙሉ እንደሚሆን እንዲያስተውሉ መርዳት

**ምዘና ፡-** የሙሉ እና የክፍልፋይ ፅንሰ ሃሳብን መገንዘባቸውን ማረጋገጥ::

**ተግባር ሰባት ፡- መለኪያ መሣሪያዎችን መጠቀም**

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- መለኪያ መሣሪያዎችን መጠቀም ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ማስመሪያ፣ መለኪያ ሲባጎ፣ገመድ፣ ጨርቅ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ስለመለኪያ መሳሪያዎች እንደሚከተለው መጠነኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ
  - ወረቀትን በማስመሪያ መለካት
  - ገመድ ወይም ጨርቅን በክንድ መለካት
  - የክፍላቸውን መጠን ከበሩ እስከ ፊት ለፊቱ ግድግዳ በእርምጃ በመለካት ማሳየት
- እያንዳንዳቸው ባዩት መሰረት ለክተው ያገኙትን መጠን ለመናገር እንዲሞክሩ ማበረታታት

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- መለኪያ መሳሪያዎችን በመጠቀም በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ነገሮችን እንዲለኩ ማበረታታት |

ምዘና ፡- መለኪያ መሣሪያዎችን መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 5. የጊዜን ጽንሰ ሐሳብ መረዳት መገለጫዎቹን መጠቀም | 5.1. በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየትና መከተል ይችላሉ። |

**ተግባር አንድ ፡- በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት**

ዓላ[illegible]
ከወረቀት ላይ መገልበጥ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጻሕፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በየጊዜው የሚከበሩ የተለያዩ የበዓል ቀናትን በማንሳት ለምን እንደሚከበሩ ማወያየት
- በየቤታቸው በአል ሲከበር ምን እንደሚደረግ እንዲናገሩ እድል መስጠት
- መቼ ነው ይህ የተከናወነው? የሚከናወነው? /መቼ ነበር ልደት ያከበርነው? /በማለት መጠየቅና ያለፉና የወደፊት ጊዜ ሁኔታን የሚገልፁ ቃላትን በመጠቀም መልስ እንዲሰጡ ማድረግ
- የበዓላት አከባበር በማንጸባረቅ የሚጫወቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት

ምዘና ፡- በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ሁለት ፡- የሰዓትን ጥቅም መረዳት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የሰዓትን ጥቅም ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በወፍራም ወረቀት ወይም ካርቶን ላይ የተሰራ ሰዓት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ለማስተማሪያ የተሠራ ትልቅ ሰዓት ማቅረብ
- ከዚያም ሰዓት ለምን እንደሚጠቅምና እንዴት ሰዎች እንደሚጠቀሙበት በመጠየቅ ማወያየት
- የተሰራውን ሰዓት ፊት ለፊታቸው መስቀል እና እርሳስ ወረቀትና ከለር በመስጠት እንዲስሉ ማድረግ
- የሳሉትን በማየት ማድነቅ

ምዘና ፡- የሰዓትን ጥቅም መረዳታቸውን ማረጋገጥ፡

ተግባር ሶስት ፡- የቀን መቁጠሪያን ማስተዋወቅ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ ስለቀን መቁጠሪያ ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የቀን መቁጠሪያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ጎላ ብሎ የሚታይ የቀን መቁጠሪያ ማቅረብና ማሣየት
- በመቁጠሪያው ላይ ወራት፣ የሳምንቱ ቀናት፣ እንዲሁም በዓል የሆኑ ቀናትን የሚያመለክቱ በልዩ ቀለም የተቀመጡ መግለጫዎች ወዘተ እንዳሉበት በማሣየት ማወያየት

ምዘና ፦ ስለቀን መቁጠሪያ መገንዘባቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፦ ቀንና ማታ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ቀንና ማታ የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ቀንና ማታ ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራትን የሚያሳዩ ስእሎችን በሎቶ መልክ ማዘጋጀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-


- "ጠዋት ተነስቼ›› የሚለውን ስንኝ በመደጋገም እንዲናገሩ ማድረግ

  ጠዋትተነስቼ

  ቁርሴንም በልቼ

  ልሂድ ት/ቤት ቦርሳዬን አንግቼ

- ቀን እና ማታ የሚከናወኑ ተግባራትን በስእል ማሳየት እና ማወያየት
- ስእሎቹ ላይ የሚታዩትን ተግባራት በመመልከት እንዲያዛምዱ ማድረግ
- ቀንን በነጭ ወረቀት ላይ ቢጫ ትንሽ ክብ (የፀሀይ ምልክት)፤ ማታን ጥቁር በተቀባ ወረቀት ላይ የጨረቃ እና ትንንሽ ከዋክብት ቀርፀው የቱን ጊዜ እንደሚወክል ማስረዳት



ምዘና ፡- ቀንና ማታ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት መቻላቸውን ሲናገሩ በማዳመጥ መገምገም።

ዓላ ተግባር አምስት ፡- የሳምንቱን ቀናት መለየት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በወፍራም ወረቀት ወይም ካርቶኒ ላይ የተሰራ የቀን መቁጠርያ፣ክላሰር፤ ሻሽ ቦርድ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህፃናቱ ስለጊዜ ያላቸውን ግንዛቤ ማጠናከር
- ጠዋት ክፍል ገብተው ለእለቱ የታቀደውን ፕሮግራም ከመጀመር በፊት እለቱን፤ወሩን አመተምህረቱን እንዲናገሩ ማድረግ
- በጥቁር ሰሌዳው ላይ እለቱን፣ወሩን፣ዓመተ ምሕረቱን በሻሽ ቦርድ ላይ በመጻፍ መለጠፍ
- ‹‹የሳምንቱ ቀናት›› መዝሙርን ማስዘመር
- የሳምንቱን ቀናት የተለያየ ቀለም ባላቸው ወፍራም ወረቀቶች ላይ መፃፍ
- ከጀርባው የብርጭቆ ወረቀት በመለጠፍ ሻሽ ቦርድ ላይ ማጣበቅ
- ስለሳምንቱ ቀናት (የእረፍት እና የትምህርት ቀናት) ያላቸውን ግንዛቤ ማዳበር

ምዘና ፡- የሳምንቱን ቀናት ለይተው መናገር መቻላቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- በቀን ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረኝነት ሰሌዳ፣ የተረት መጻሕፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተረኝነት ሰሌዳዎችን ማሳየት

  ለምሳሌ፡-የአትክልት ቦታ ተረኝነት፣ የትምህርት ክፍለጊዜ ተረኝነት፣ የምግብ ሰዓት ተረኝነት

- መቼ ምን እንደሚከናወን በመጠየቅ ማወያየት
- ጊዜን ሊገልፁ የሚችሉ ተረቶች እና አጫጭር ታሪኮችን አዳምጠው ምን? መቼ? እንደተካሄደ እንዲናገሩ ማወያየት

ምዘና ፡- በቀን ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ሰባት- ‹‹ምን መቼ ይደረጋል?" የሚለውን ጨዋታ ማጫወት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ተግባር ስድስት ፡- በቀን ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ ‹‹ምን መቼ ይደረጋል?” ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረኝነት ሰሌዳ፣ የተረት መጻሕፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ገላችንን እንታጠባለን**!** መቼ? ቅዳሜና እሁድ
- እጃችንን እንታጠባለን**!** መቼ? ከምግብ በፊት እና ከምግብ በኋላ
- ቁርሳችንን እንበላለን”**!** መቼ? በቁርስ ሰአት
- ት/ቤት **(**አፀደህፃናት**)** እንመጣም**!** መቼ? ቅዳሜ እና እሁድ እና በእረፍት ቀናት ወዘተ... እያሉ እንዲጫወቱ መርዳት

ምዘና ፦ ‹‹ምን መቼ ይደረጋል?” የሚለውን ጨዋታ መጫወታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስምንት ፦ የወቅቶችን ምንነትና ዓይነቶችን ማስተዋወቅ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ የወቅቶችን ምንነትና ዓይነቶች ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ ወቅቶችን አለባበስ የሚያሳዩ ስእሎች፣

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ሕጻናት የወቅቶችን ትርጓሜ እንዲናገሩ ማበረታታት
- በክረምት እንዲሁም በበጋ የሰዎችን አለባበስ የሚያሳዩ ስዕሎችን ማሳየት
- በበጋና በክረምት ሰዎች የሚለብሱት ልብስ ለምን እንደሚለያይና የወቅቶች ዓይነቶች በሰዎች አኗኗር ላይ ምን ተጽዕኖ እንዳላቸው ማወያየት
- ወቅቶችን ከሚያስከትሉት ለውጥ ጋር የማዛመድ ጨዋታን ማጫወት
- በአራቱ ወቅቶች (ከተቻለ) በተለይ በክረምት እና በበጋ በሰዎች እና በአካባቢ ላይ የሚታዩ የሚያሳዩ ስእሎችን በሎቶ መልክ በማዘጋጀት ማጫወት

ምዘና ፦ የወቅቶችን ምንነትና ዓይነቶችን መገንዘባቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6. የቦታን ጽንሰ ሐሳብ መረዳት እና መገለጫዎቹን መጠቀም | 6.1.የቁሳቁሶችን መገኛ ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ፦ የቁሶችን አቀማመጥ መናገር

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የቁሶችን አቀማመጥ መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሶችን በጠረጴዛ ላይ ጎን ለጎን፤ ከኋላ፣ ከፊት፤ ከታች ማስቀመጥ
- ህፃናትን በየተራ ወደ ጠረጴዛው እንዲመጡ መጥራት እና የተቀመጡት ቁሶች አንዱ ከሌላው አቀማመጥ አንፃር በየት በኩል እንደተቀመጡ እንዲያስተውሉ ማድረግ
- ምን የት ቦታ እንደተቀመጠ እንዲናገሩ ማድረግ
- ፊታቸውን አዙረው እንዲቆሙ በማድረግ የቁሶቹን አቀማመጥ መቀየር
- እንደገና እንዲያስተውሉ እና የተለወጠውን አቅጣጫ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የቁሶችን አቀማመጥ መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- አቅጣጫን መለየት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- አቅጣጫ መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ነገሮችን በተለያየ ቦታ እና አቅጣጫ የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ ነገሮችን የሚሳይ ስእል ለህፃናት በግልፅ ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ  መስቀል
- ህፃናት ስእሉን በማስተዋል ምን ምን ስእሉ ላይ እንዳለ እንዲናገሩ ማድረግ
- ቀጥሎም ምን ከምን በየት በኩል / ግራ፣ ቀኝ /እንዳለ እንዲናገሩ መጠየቅ

ለምሳሌ:- ‹ትንሹ ልጅ የት ጋ ነው የቆመው**?**›፤ ‹አጠገቡ ምን አለ?›፤ ብስክሌቱ ላይ ማን አለ?›፤ ልጁ ከብስክሌት በየት በኩል ይገኛል**?**›፤ ወዘተ።





ምዘና ፡- አቅጣጫን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሦስት ፡- በጨዋታ ሩቅና ቅርብን መለየት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- በጨዋታ ሩቅና ቅርብን መለየትይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወንበር፣ ማራካሽ/ ፀናጽል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በክፍሉ ውስጥ 4 ወንበሮች በተለያየ አቅጣጫ ማስቀመጥ
- በማራከሽ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ
- የህጻናት ቁጥር ከወንበሮች ቁጥር በአንድ መብለጥ አለበት
- የማራከሽ ድምፅ ሲቆም እና ‹ሩቅ!› ሲባል ሩቅ ያለው ወንበር ላይ፣ ቅርብ!› ሲባል ቅርብ ያለው ወንበር ላይ መቀመጥ እንዳለባቸው ማስረዳት
  - ተጫውቶ ማሳየት እና በየተራ ማጫወት

ምዘና ፡- በጨዋታ ሩቅና ቅርብን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 7. ገንዘብን መተዋወቅ፣መለየት፣ መግለጽና መጠቀም | 7.1 . የገንዘብን ዋጋ መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የገንዘብ መጠንን መገንዘብ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የገንዘብን መጠን ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የብር ወረቀት፣ሳንቲሞች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህፃናቱን ገንዘብ ይዘው ያውቁ እንደሆን መጠየቅ
- ገንዘብ ነበረን ብለው መልስ የሰጡትን ስንት እንደነበራቸው እና ምን እንዳደረጉበት በመጠየቅ ማወያየት
- የገንዘብ ወረቀቶችን፣ ሳንቲሞችን በጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ
- ምረጡ እና ውሰዱ ቢባሉ የቱን እንደሚመርጡ መጠየቅ
- የመረጡት ገንዘብ ከሌላው በምን እንደሚለይ መጠየቅ
- በመጨረሻም የተለያየ የገንዘብ መጠን(ብዙ ነገር ሊገዛ የሚችል እና ጥቂት ነገር ሊገዛ የሚችል) የገንዘብ መጠን እንዳለ እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- የገንዘብን መጠን መገንዘባቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ሁለት ፡- የተለያዩ ሳንቲሞችን መለየት**

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ የተለያዩ ሳንቲሞችን መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ ሳንቲሞች፣ስስ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ለሱቅ ሱቅ ጨዋታ የሚያስፈልጉ መጫወቻዎች /የሱቅ ጨዋታ ማዕዘን/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ስስ ወረቀት፤ እርሳስ፤ የተለያየ መጠን ያላቸው ሳንቲሞች በቡድን፤ ከተቻለም ለሁሉም ሕጻናት ማደል
- ሳንቲምን በስስ ወረቀት ጠቅልሎ/ሸፍኖ፤ የተሸፈነበትን ወረቀት በእርሳስ በማሸት እንዴት የሳንቲም ምስልን ማውጣት እንደሚቻል ማሳየት
- ህጻናቱ በተመለከቱት መሰረት በእርሳስ አሽተው ምስሉን እንዲያወጡ ማድረግ
- የሰሩትን መሰብሰብ እና ምስሉን በመቀስ ቆርጦ ማውጣት
- ከዚያም በ ‹ሱቅ ሱቅ› እና በቤተሰብ ጨዋታ እንዲጠቀሙበት ማበረታታት

ምዘና ፦ የተለያዩ ሳንቲሞችን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሦስት ፦ የገንዘብ ተቋም ጠቀሜታን መተዋወቅ

ዓላማ ፡- የገንዘብ ተቋምን ጠቀሜታ ያውቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ሳንቲሞች፣ስስ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ለሱቅ ሱቅ ጨዋታ የሚያስፈልጉ መጫወቻዎች /የሱቅ ጨዋታ ማዕዘን/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ወላጆቻቸው ገንዘብ የት እንደሚያስቀምጡ መጠየቅ
- ከወላጆቻቸው ጋር ወደባንክ ሄደው ያውቁ እንደሆነ መጠየቅ
- ባንክ ምን እንደሆነ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማበረታታት
- ባንክ ገንዘብ ማስቀመጫ ቦታ መሆኑን እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የገንዘብ ተቋምን ጠቀሜታ መገንዘባቸውን መገምገም።

**ተግባር አራት ፡- የግብይት ሥርዓትን መለማመድ**

ዓላማ ፡- የግብይት ሥርዓትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የብር እና የሣንቲም ምስሎች፣ ለሱቅ ሱቅ ጨዋታ የሚያስፈልጉ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሱቅ ሄደው ዕቃ ሲገዙ ምን ተብሎ እንደሚጠየቅ ማወያየት
- በሱቅ ጨዋታ ማዕዘን በተለያየ ጊዜ እንዲጫወቱ ማድረግ
- በመገበያየት ጊዜ ሊጠቀሙ የሚገባቸውን ቃላት ገዥ ሆኖ በጨዋታው በመግባት ማገዝ

ምዘና ፡- የግብይት ሥርዓትን መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

## **2.1.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -----------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም -------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም ---------------------------------------------- ዓመተ ምሕረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ ---------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት ---------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት ---------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ^ | | |
|---|---|---|---|
| | የዓመት መጀመሪያ | የዓመት አጋማሽ | የዓመት መጨረሻ |
| **1.** የቁሳቁሶችን ባህሪ መፈተሽ መረዳትና መለየት | | | |
| 1.1. ነገሮችን በዓይነት መመደብ ይችላሉ | | | |
| 1.2. አንድ ዓይነት ነገሮችን ማዛመድ መቻል | | | |
| 1.3. በጥንድ በመያያዝ መጫወት መቻል | | | |
| 1.4. የጂኦሜትሪ ቅርጻ ቅርጾችን መለየት መቻል | | | |
| **2.** ነገሮችን በባህሪያቸው መሠረት ማወዳደር | | | |
| 2.1. በነገሮች መካከል ያለዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሣየት ይችላሉ | | | |
| **3.** ቁጥሮችን ማስተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መሥራት | | | |
| 3.1. በነገሮችና በቁጥሮች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት መናገር ይችላሉ | | | |
| 3.2 እኩል ናቸው፣ ይበልጣል፣ያንሳል በማለት መናገር ይችላሉ | | | |
| 3.3 ከ1-20 አሃዞችን መለየት ይችላሉ | | | |
| 3.4 ከ1-20 መቁጠር መደመርና መቀነስ ይችላሉ | | | |
| **4.** በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችንና መሣሪያዎችን መጠቀም | | | |
| 4.1 ቦታን፣ ርቀትንና አቅጣጫን መግለጽ ይችላሉ | | | |
| 4.2 ነገሮችን በሥርዓት መደርደርና ማወዳደር ይችላሉ | | | |
| **5.** የጊዜ ፅንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም | | | |
| 5.1. በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየትና መከተል ይችላሉ | | | |
| **6.** የቦታ ጽንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም | | | |
| 6.1. የቁሳቁሶችን መገኛ ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር መናገር ይችላሉ | | | |

| **7.** ገንዘብን መተዋወቅ፣ መለየት፣መግለጽና መጠቀም | | | |
|---|---|---|---|
| 7.1 የገንዘብን ዋጋ መናገር ይችላሉ | | | |

## 2.5. ከአካባቢ ጋር በሚፈጠር መስተጋብር አካባቢን ማጥናትና በአግባቡ ማጣጣም

### 2.5.1 ማብራሪያ

በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች /ከ5-6 አመት/ ቋንቋን እና የስሜት ህዋሳታቸውን በመጠቀም አካባቢቸውን በይበልጥ የሚፈትሹበት እና ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎትና መነቃቃት የሚታይባቸው ከመሆኑም በተጨማሪአዳዲስ ፅንሰሀሳቦችን የሚማሩበት እና የነገሮችን መንስኤ እና ውጤት ማወቅ የሚፈልጉበት እድሜ ነው። በመሆኑም፡-

- የስሜት ህዋሳቶቻቸውን በመጠቀም የነገሮችን ባህርይ እንዲረዱ እገዛ በማድረግ አካባቢያቸውን አስተውለው እንዲመለከቱ እና እንዲፈትሹ እድሉን መስጠት እና በደረጃቸው የተለያዩ ሙከራዎችን በማድረግ የሚከተለውን ለውጥ እንዲረዱ ማድረግ
- ለሚጠይቁት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ በመስጠት ድጋፍ ማድረግ

ህፃናት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ህፃናቱ ካሉበት የእድገት ደረጃ ጋር ተስማሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ተግባራቱን ደጋግመው ደጋግመው እንዲለማመዱ በማድረግ ለህፃናቱ ጥረት እውቅና መስጠት ያስፈልጋል።

### 2.5.2 አጠቃላይ ዓላማዎች

1. በቤታቸውና በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤታቸው የሚያገኙአቸውን ሰዎችና ሌሎች ተፈጥሮአዊ ነገሮችን መለየትና በደረጃቸው ሙከራ ማካሄድ እንዲችሉ ማድረግ
2. የጠቃሚ ቦታዎችንና ሰዎችን የሥራ ድርሻ መናገርና ሀገርን የመውደድ ስሜት እንዲያዳብሩ ማድረግ
3. በአካባቢ ፅዳት ላይ መሳተፍና ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች ራሳቸውን መጠበቅ እንዲችሉ ማድረግ
4. የእንቅስቃሴን ፅንሰ ሐሳብን መረዳት፣ የመጓጓዣ ዓይነቶችን መለየትና የተለያዩ ነገሮችን በመሥራት ፈጠራቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ

### 2.5.3 የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ
   1.1. በቤታቸውና በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤታቸው የሚገኙትን ሰዎች፣ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት ይችላሉ
   1.2. በአካባቢቸው በሚያገኛቸው ነገሮች ላይ ሙከራ ማካሄድ ይችላሉ

2.በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማድነቅ

2.1. የጠቃሚ በታዎችንና ሰዎች የስራ ድርሻ መናገር ይችላሉ

2.2. ሀገርን የመውደድ ስሜት ያድርባቸዋል

3. አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅና መንከባከብ

3.1. በአካባቢ ጽዳት ላይ መሳተፍ ይችላሉ

4. በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ

4.1. ራስን ከአደገኛ ነገሮች መጠበቅና አካባቢን ማፅዳት ይችላሉ

4.2. በደረጃቸው የህፃናት መብትን ተረድተው ራሳቸውን ከህፃናት ጥቃት ለመከላከል ይሞክራሉ

5. የእንቅስቃሴን ፅንሰ ሀሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ

5.1. በአካባቢያቸው የሚገኙትን የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶች አንድነትና ልዩነት ማወዳደር ይችላሉ

6. በስነስዕልና ቅርፃቅርፅ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅና ራስን መግለፅ

6.1. የተለያዩ ነገሮችን በመስራት የፈጠራ ችሎታን ያዳብራሉ

### **2.5.4** የሚጠበቁ ውጤቶች ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎች፣ የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | 1.1. በቤታቸውና በቅ/መ/ት/ቤታቸው የሚገኙትን ሰዎች ሰዎች ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮች ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰው ስዕል፣ የእንስሳቶች እና የነፍሳቶች ስዕል፣ ጠጠር፣ ድንጋይ፣ አፈር ፣የመኪና ስዕል፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮች የትኞቹ እንደሆኑ በደረጃቸው ምሣሌ በመስጠት እንዲገነዘቡ ማድረግ
- ተፈጥሮአዊ ነገሮች በተፈጥሮ የሚገኙ እንደሆኑ መግለጽ
  ለምሣሌ፡- ሰው፣ እንስሳቶች፣ ነፍሳቶች፣ ጠጠር፣ ድንጋይ፣ አፈር
- ሰው ሰራሽ የሚባሉት ደግሞ ሰዎች የሚሰሯቸው የተለያዩ ነገሮች እንደሆኑ ማስረዳት
  ለምሳሌ፡- መኪና፣ ቤት፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ ወዘተ...
- የተለያዩ ስዕሎችን በመስጠት ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮችን ለያይተው እንዲመድቧቸው ማድረግ

ምዘና ፡- ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር ሁለት ፡- ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮችን በባህርይ መመደብ

ዓላማ ፡- ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮችን በባህሪያቸው ይመድባሉ።


የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ጥንድ ስዕሎች፣

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሕፃናት በጥንድ ያሉ የተለያዩ ስዕሎችን መስጠት
- ስዕሎቹን በባህሪያቸው እንዲመደቡ ማድረግ
- ሲጨርሱም ለምን እንደዛ እንደመደቡ እና የጋራ መጠሪያቸው ምን እንደሆነ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት

ለምሳሌ፡- ፍራፍሬ፣የዱር እንስሳት፣ተሽከርካሪዎች፣የጓሮ አትክልት--- ወዘተ

- ከተሳሳቱ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስህተታቸውን እንዲያርሙ መርዳት፤








ምዘና ፡- ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮችን በባህሪያቸው መመደብ መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር ሶስት ፡- እንስሳትን፣ ነፍሳትን እና አዕዋፍን መለየት

ዓላማ ፦ እንስሳትን፣ ነፍሳትን እና አዕዋፍን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የእንስሳት ሎቶ እና ፐዝል፣ የስዕል ዶሚኖ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የእንስሳት የነፍሳት እና የአእዋፍ ፐዝል እንዲሁም የስዕል ዶሚኖን ማዘጋጀት
- የጐደለውን ዕወቅ ጨዋታን ማጫወት
- ሕፃናት እየተጫወቱ የተማሩትን እንዲያጠናክሩ ማድረግ

ምዘና ፦ እንስሳትን፣ነፍሳትን እና አዕዋፍን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፦ እንስሳቶችን፣ ነፍሳቶችንና አዕዋፍን መሳል

ዓላማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የእንስሳት ሎቶ እና ፒዝል፣ የስዕል ዶሚኖ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ወረቀት እና እርሳስ መስጠት
- እንሰሳቶችን፣ ነፍሳቶችንና አዕዋፍን እንዲስሉ እና ባለቀለም እርሳስ/ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱ ቀደው እንዲያወጡት ማገዝ
- በትልቅ ወረቀት ላይ በመለጠፍ በክፍል ውስጥ ግርግዳ ላይ መስቀል

| |
|---|
| ማስታወሻ፡- በአንድ ክፍለ ጊዜ መጠናቀቅ ስለማይችል በተከታተይ ክፍለ ጊዜያት እንዲተገብሩ ማድረግ |

ምዘና ፡- እንስሳቶችን፣ ነፍሳቶችንና አዕዋፍን መሳል መለማመዳቸዉን መከታተል።



ተግባር አምስት ፡- የእንስሳትን አኗኗር መረዳት

ዓላማ ፡- የእንስሳትን አኗኗር ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የእንስሳት ሎቶ እና ፐዝል፣ የስዕል ዶሚኖ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በግቢ ውስጥ የሚገኙ እንስሳትን አኗኗር እንዲመለከቱ ማድረግ
- አካባቢያቸው እንስሳት ተከልለው የሚኖሩበት ባታ ካለ ሕፃናትን ይዞ በመሄድ አኗኗራቸውን እንዲያዩ ማድረግ

  ለምሳሌ፡- ስድስት ኪሎ የሚገኘው አንበሳ ግቢ
- ስላዩት ነገር በክፍል ውስጥ በማወያየት ግንዛቤያቸውን ማጠናከር

ምዘና ፡- የእንስሳትን አኗኗር መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- የቤት እንስሳትን እና አትክልቶችን መንከባከብ

ዓላማ ፡- የቤት እንስሳትን እና አትክልቶችን መንከባከብ ይለማመዳሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በፕላስቲክ እቃ የተተከሉ አትክልቶች፣ የአትክልት ዉሃ ማጠጫ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በቤታቸው ያሉትን እንስሳት፣ ዶሮ፣ ድመት፣ ውሻ ወዘተ.... ወላጆቻቸው ምግብ በመስጠት ሲንከባከቧቸው እነሱም ከወላጆቻቸው ጋር አብረው መንከባከብ እንዳለባቸው ማስረዳት

  ለምሳሌ፡- የውሻ ምግብን መንጠቅ፣ መድፋት ወዘተ.... እንደሌለባቸው ማስረዳት፡፡
- በክፍላቸው ውስጥ በፕላስቲክ እቃ እና በአትክልት ቦታ ላይ የተተከሉ አትክልቶችን በተራቸው መሠረት በየዕለቱ እንዲንከባከቡና ለውጣቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- እንስሳትን እና አትክልቶችን መንከባከብ መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. የቅርብ አካባቢን መፈተሽ እና ማወቅ | 1.2. በአካባቢያቸው በሚያገኟቸው ነገሮች ላይ ሙከራ ማካሄድ ይችላሉ። |

ዓላማ ፡- በአካባቢያቸዉ የሚገኙ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትንንሽ ጠጠሮች፣ ትንንሽ ድንጋዮች፣ የተለያዩ የባህር ዛፍ ፍሬዎች፣ የተለያየ መጠን ያላቸው ቅጠሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ በአካባቢ የሚገኙ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ወደ ክፍል ይዞ መምጣት
  ለምሳሌ፡- ትንንሽ ጠጠሮች፣ትንንሽ ድንጋዮች፣ የተለያዩ የባህር ዛፍ ፍሬዎች፣ የተለያየ መጠን ያላቸው ቅጠሎች
- ለሕፃናት በየጠረጴዛቸው ላይ በመስጠት ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ማድረግ
- ተመሳሳዮችን አንድላይ እንዲያደርጉ ማድረግ
- ሁሉም በአንድነት ተፈጥሮአዊ ነገሮች ተብለው እንደሚጠሩ መግለጽ::

ምዘና ፡- በአካባቢያቸዉ የሚገኙ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን መለየታቸውን መገምገም።

ተግባር አንድ፡- በአካባቢ የሚገኙ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን መለየት



ተግባር ሁለት ፡- የእንቁራሪት እና ነፍሳትን አኗኗር መገንዘብ

ዓላማ ፡- የእንቁራሪት እና ነፍሳትን አኗኗር ግንዛቤ ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የእንቁራሪት ስዕል፣ የትላትል ምስል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በአካባቢያቸው ክረምት ሲሆን እና መሬቱ ውሃ ሲያቁር ምን አይተው እንደሚያውቁ መጠየቅ
- የእንቁራሪትን እና የትላትልን ምስል ማሣየት
- በተጠራቀመ ውሃ ውስጥ እንደሚኖሩ መንገር
- እንቁራሪት ቋርቋር የሚል ድምጽ እንደምታወጣ እና መዝለል እንጂ መራመድ እንደማትችል መግለጽ
- እንቁራሪት ሰውን እንደማትነካ እንዳንዴም ክረምት ሲሆን ወደ ቤት አካባቢ እንደምትመጣ መንገር
- ትላትሎችም እየተሳቡ እንደሚጓዙና ውሃ ሲኖር እንደሚፈጠሩ እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- የእንቁራሪት እና ነፍሳትን አኗኗር ግንዛቤ ማዳበር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሦስት ፡- ስለ ዓሣ አኗኗርና ጠቀሜታ መረዳት

ዓላማ ፡- ስለ ዓሣ አኗኗርና ጠቀሜታ ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዓሳ ምስል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በትላልቅ ውሃ ያለበት ቦታ/ወንዞች፣ሃይቆች/ ላይ አሳዎች እንደሚኖሩ መግለጽ
- አሳ ከውሃ ውጪ መኖር እንደማይችል እንዲገነዘቡ ማድረግ
- አሳ ለምግብነት እንደሚያገለግል እና ለሰውነታችን ጠቃሚ መሆኑን መግለጽ

ምዘና ፡- ስለ ዓሣ አኗኗርእና ጠቀሜታ መረዳታቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- የበጋ እና ክረምትን ልዩነት መረዳት

ዓላማ ፡- የበጋ እና የክረምትን ልዩነት ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ስለበጋ እና ክረምት የሚያሣዩ ስዕሎች ወይም ፎቶግራፎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በጋ እና ክረምትን የሚያሣዩ ስዕሎችን መጠቀም
- በጋ ሲሆን ባብዛኛው የሚከተሉትን ባህሪ እንደሚያዩ ማስገንዘብ
  - ፀሐይ ሁሌ እንደምትታይ
  - አየሩ ሞቃት እንደሆነ
  - ዝናብ እንደማይዘንብ
  - መሬቱም ደረቅ እንደሆነ
  - ልብስ ታጥቦም ቶሎ እንደሚደረቅ መግለጽ
- ክረምት ሲሆን ደግሞ ባብዛኛው የሚከተሉትን ባህሪ እንደሚያዩ ማስገንዘብ
  - ሁልቀን ፀሐይ እንደማትታይ
  - አየሩ እንደሚቀዘቅዝ
  - ዝናብ እንደሚዘንብ
  - መሬቱም ርጥብ እንደሚሆን
  - ልብስም ታጥቦ ቶሉ እንደማይደርቅ እንዲረዱ ማድረግ፡፡
- በበጋ እና በክረምት ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ የሚከሰተውን ለውጥ (በሰው፣ በእንስሳት እና በእፀዋት) በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፡- የበጋ እና የክረምት ልዩነቶችን መረዳት መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር አምስት ፡- የውሃን ጥቅም መረዳት

ዓላማ ፡- የውሃ ጥቅምን ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዓሳ ምስል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የውሃን ጥቅም በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት
- ውሃ ለምግብ ማብሰያነት፣ ንጽህናን ለመጠበቂያ፣ ለመጓጓዣ ወዘተ እንደሚያስፈልግ እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- የውሃ ጥቅምን መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- ስለንፋስ መረዳት

ዓላማ ፦ ስለንፋስ  ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣ ክላሰር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕጻናቱን ወደ ሜዳ ይዞ በመውጣት ንፋስ ምን እንደሆነና በአካባቢያቸው ንፋስ መኖሩን እንዴት እንደሚያውቁ በመጠየቅ ማወያየት
- ንፋስ ብዙ ነገሮችን እንደሚያንቀሳቅስና ድምጽ እንዳለው ማስገንዘብ
- የወረቀት ሽክርክሪት አሰራር ማሳየት
- የወረቀት ሽክርክሪት በመስራት እንዲጫወቱ ማበረታታት
- ንፋሱ ወደሚመጣበት አቅጣጫ በፍጥነት በመራመድ ወይም በመሮጥ ሽክርክሪት በንፋስ ሀይል በመታገዝ እንደሚሽከረከር እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፦ ስለንፋስ መረዳታቸውን መገምገም።



ተግባር ሰባት ፦ የንፋስ ጥቅምን መረዳት

ዓላማ ፡- የንፋስ ጥቅምን ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ ሁለት ስስ ጨርቆች ፣ ውሃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሕፃናት ወረቀትን በማጠፍ እንደማራገቢያ በማራገብ የተሰማቸውን ስሜት እንዲናገሩ በማድረግ የንፋስን ጥቅም እንዲረዱ
- ሁለት ስስ ጨርቆችን ውሃ ውስጥ በመንከር እና በመጠምዘዝ አንዱን ንፋስ የሚያገኝበት ቦታ ላይ ማንጠልጠል
- ሌላውን ንፋስ በማያገኝበት ቦታ ላይ በማንጠልጠል የትኛው ቀድሞ እንደሚደረቅ እንዲያዩ ማድረግ
- ንፋስ ሞቃት አየርን እንደሚያቀዘቅዝ እና ልብስን ቶሎ እንደሚያደርቅ ጥቅሙን እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የንፋስ ጥቅምን መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- በአካባቢ በሚገኙ ነገሮች በመጠቀም መጫወቻዎችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ ባህር ዛፍ ቅጠል፣ ስስ ጨርቅ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ወረቀትን በማጣጠፍ ጀት እና መርከብ እንዴት እንደሚሠራ ማሣየት
- ለሕፃናት ወረቀት በመስጠት ባዩት መሠረት እያጣጠፉ እንዲሠሩ ማነቃቃት እና መርዳት
- ከባህር ዛፍ ቅጠል እንዲሁም ከሞባይል ካርድ ሽክርክሪትን በመሥራት ለሕፃናት ማሣየት
- ሕፃናቱ ባዩት መሠረት ሠርተው እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፡- በአካባቢያቸው በሚያገኙ ነገሮች መጫወቻዎች መስራት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር ዘጠኝ ፡- የሚሰምጡ እና የሚንሳፈፉ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- የሚሰምጡና የሚንሳፈፉ ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ብርሃን የሚያስተላልፍ ጐርጓዳ ፕላስቲክ ሣህን፣ትናንሽ ዕቃዎች (ትንሽ የልብስ ቁልፍ ላፒስ፣ ቅጠል፣ውሃ ወዘተ...)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ብርሃን የሚያስተላልፍ ጐርጓዳ ፕላስቲክ ሣህን ውስጥ ውሃ ማድረግ
- ሣህኑን ለሕፃናቱ ዕይታ አመቺ ቦታ/ጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ
- ጠረጴዛ ላይ የተለያዩ ሕፃናት የሚያውቋቸውን ትናንሽ ዕቃዎችን ማስቀመጥ

  ለምሳሌ፡- ትንሽ የልብስ ቁልፍ፣ላጲስ፣ ቅጠል ወዘተ...
- ሁለት ሕፃናትን በማስነሳት ጠረጴዛ ላይ ከተቀመጡት ዕቃዎች ውስጥ የሚፈልጉትን አንድ ዕቃ ብቻ እንዲያነሱ ማድረግ
- ምን እንደሆነ ለጓደኞቻቸው በማሣየት እንዲናገሩ መጠየቅ
- የያዙትን ዕቃ በሰሀን ውስጥ ባለው ውሃ ላይ እንዲጨምሩ ማድረግ
- ዕቃው ተንሳፈፈ ወይም ሰመጠ ብለው እንዲናገሩ ማገዝ
- በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሁሉም ሕፃናት በጨዋታው እንዲሳተፉ ማበረታታት

ምዘና ፡- የሚሰምጡና የሚንሳፈፉ ነገሮችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር አስር ፡- የሚሰምጡ እና የሚንሳፈፉ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- በእስክሪብቶ ቀፎ የአረፋ እንክብሎችን ማውጣት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የእስክሪብቶ ቀፎ፣ በጎድጓዳ ሳህን ውሃ፣ ኦሞ /ሣሙና/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ንፁህ የእስክሪብቶ ቀፎዎችን በሕፃናቱ ቁጥር ማዘጋጀት
- በዕቃ ላይ ውሃ እና ኦሞ /ሣሙና/ በመበጥበጥ አረፋ ማውጣት
- እያንዳንዱ ሕፃን ቀፎውን አረፋ ውስጥ ነክሮ በማውጣት በአፋቸው አየርን ቀስ ብለው ኡፍ ብለው እንዲያወጡ ማድረግ
- በዚህ ዓይነት የተለያየ መጠን ያላቸውን የአረፋ እንክብሎች በመሥራት እንዲጫወቱ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- እያንዳንዱ ሕፃን በራሱ ቀፎ ብቻ መጫወት እንዳለበት እና የሳሙናውን አረፋ ወደ አፉ ውስጥ መሳብ እንደማይገባ መንገር ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- በእስክሪብቶ ቀፎ የአረፋ እንክብሎችን ማውጣት መቻላቸውን መከታተል።



ተግባር አስራ አንድ ፡- የሚሟሙና የማይሟሙ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- የሚሟሙና የማይሟሙ ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ብርሀን የሚያስተላልፉ የፕላስቲክ ኩባያዎች፣ ጨው፣ ስኳር፣ ዱቄት፣ ደቃቅ አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ዘይት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ ብርሀን የሚያስተላልፉ የፕላስቲክ ኩባያዎች ማዘጋጀት
- በትናንሽ እቃዎች ጨው፣ስኳር፣ ዱቄት፣ ደቃቅ አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ዘይት ማቅረብ
- በፍቃደኝነት ህፃናቱን አንድ በአንድ በማስነሳት አንዱን ነገር አንስተው በውሀ ውስጥ ጨምረው በማማሰያ እንጨት እንዲያማስሉ ማድረግ
- ሁሉም ህፃናት ለውጡን እንዲመለከቱ ማድረግ
- በውሀ የሚሟሙ እና የማይሟሙ ነገሮችን ሙከራ በማድረግ እንዲለዩ ማድረግ

ምዘና ፡- የሚሟሙ እና የማይሟሙ ነገሮችን በሙከራ መለየት መቻላቸውን መከታተል።


ተግባር አስራ ሁለት ፡- የጠባብ እና ሰፊ ዕቃዎች ልዩነትን መረዳት

ዓላማ ፡- የጠባብ እና ሰፊ ዕቃዎች ልዩነትን መረዳት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ብርሀን የሚያስተላልፉ  ሁለት እኩል ቁመት እና የተለያየ ስፋት ያላቸው የፕላስቲክ ኩባያዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ብርሀን የሚያስተላልፉ ሁለት እኩል ቁመት እና የተለያየ ስፋት ያላቸውን የፕላስቲክ ኩባያዎች ማዘጋጀት
- ሁለቱም ውስጥ እኩል በአነስተኛ ኩባያ አንድ ኩባያ ውሀ መጨመር
- የትኛው የፕላስቲክ ኩባያ ብዙ ውሀ እንደያዘ ህፃናቱን መጠየቅ
- የህፃናቱን መልስ ካዳመጡ በኋላ ውሀውን ከፕላስቲክ ኩባያዎቹ ተራ በተራ ወደ አነስተኛ ኩባያው መመለስ
- ይህን ካሳዩ በኋላ ከሰፊውና ከጠባቡ የፕላስቲክ ኩባያ የትኛው ብዙ ውሀ ይዞ እንደነበር መጠየቅ
- በአይን ሲታይ ጠባብ እቃ ከሰፊ እቃ ብዙ ውሀ የያዘ እንደሚመስል በመንገር እንዲገነዘቡ ማድረግ



ምዘና ፡- የጠባብ እና ሰፊ  ዕቃዎችን ልዩነት መረዳት መቻላቸውን ማረጋገጥ::

ተግባር አስራ ሶስት ፡- የተለያዩ የአፈር ዓይነቶች

ዓላማ ፡- የተለያዩ የአፈር ዓይነቶች መኖራቸውን ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የአፈር ዓይነቶች፣ ውሀ፣ ብርሀን የሚያስተላልፉ የፕላስቲክ ኩባያዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ የአፈር ዓይነቶችን ብርሀን በሚያስተላልፍ የፕላስቲክ ኩባያ ውስጥ ለሕጻናቱ መስጠት
- ትንሽ ውሀ በመጨመር እንዲበጡብጡት ማድረግ
- ውጤቱ ምን እንደሆነና ምን ዓይነት ቀለም እንዳገኙ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የተለያዩ የአፈር ዓይነቶች መኖራቸውን መገንዘባቸውን መከታተል።

ተግባር አስራ አራት ፡- ቁሶችን በክብደት ማወዳደር

ዓላማ ፦ ቁሶችን በክብደት ማወዳደር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የአፈር ዓይነቶች፣ ውሀ፣ ብርሀን የሚያስተላልፉ የፕላስቲክ ኩባያዎች፣ የፍሊት ቆርቆሮ ክዳኖች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሁለት የፍሊት ቆርቆሮ ክዳኖችን በመጠቀም ሚዛን መስራት
- የሚመዘኑ እቃዎች እኩል ክብደት ካላቸው ሚዛኑ እኩል ቦታ ላይ እንደሚቆም ማስገንዘብ
- በአንድ ትንሽ እቃ አሸዋ በመስፈር  አንድ ስፍር አንደኛው ሚዛን ላይ አንድ ስፍር ሌላኛው ሚዛን ላይ በማድረግ እኩል መሆናቸውን ህፃናቱ እንዲያረጋግጡ ማድረግ
- አንደኛው ሚዛን ላይ በዚያው መስፈሪያ በውሀ የራሰ አሸዋ ማድረግ፤ ሌላኛው ሚዛን ላይ ውሃ ያልነካው አሸዋ ማድረግ እና ልዩነቱን እንዲመለከቱ ማድረግ
- ለምን እኩል እንዳልሆኑ በመጠየቅ ማወያየት እና የሚበልጠው (በውሀ የራሰው) ወደታች እንደሚመዝን በማሳየት ማስረዳት
- ውሀ የነካውን (የሚከብደውን) እና ውሀ ያልነካው (የማይከብደውን) በእጃቸው እየነኩ ሕጻናት እንዲያወዳድሩ ማድረግ

ምዘና ፦ ቁሶችን በክብደት ማወዳደር መቻላቸውን መገምገም::



ተግባር አስራ አምስት ፦ መጠን እና ቅርጽን ማወዳደር

ዓላማ ፡- መጠን እና ቅርጽ ማወዳደር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተቦካ ጭቃ ወይም የተቦካ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለእያንዳንዱ ልጅ እኩል መጠን ያለው ጭቃ ወይም የተቦካ ወረቀት መስጠት
- ሁለት ድቡልቡል ኳሶች እንዲሰሩ ማድረግ
- አንዱን ያድቦለቦሉትን በእጃቻቸው ወደፊትና ወደኋላ በመስበቅ ሞላላ ቅርፅ እንዲኖረው ማድረግ
- የሰሩትን ኳስ እና ሞላላ ቅርፅ ከፊት ለፊታቸው እንዲያስቀምጡ በማድረግ የትኛው እንደሚበልጥ መጠየቅ
- መልሰው ሞላላውን ክብ አድርገው እንዲያድቦለቡሉት እና ከኳሱ አጠገብ በማስቀመጥ እኩል መሆናቸውን እንዲረዱ ማድረግ
- የተለያየ ቅርፅ ያላቸው ነገሮች በመጠን እኩል ሊሆኑ እንደሚችሉ ማስረዳት



ምዘና ፡- መጠንና ቅርጽ ማወዳደር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | 2.1 የጠቃሚ ቦታዎችንና ሰዎች የሥራ ድርሻ መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ስለአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና በውስጡ ስለሚሰሩ ባለሙያዎች መናገር

ዓላማ ፡- ስለ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና በውስጡ ስለሚሰሩ ባለሙያዎች መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በአካባቢ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ስእሎች፣ ባለሙያዎችን የሚያሳዩ ስእሎች/ፎቶግራፎች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በስም እንዲጠሩ ማድረግ
- በስእል በማሳየት ሄደው ያውቁ እንደሆነ፤ ከማን ጋር እንደሄዱ እና ለምን እንደሄዱ በመጠየቅ ማወያየት

ለምሳሌ፡- ወፍጮ ቤት፣ ሱቅ፣ መድሀኒት ቤት፣ ገበያ ወዘተ…

- በመቀጠልም በእነዚህ አገልግሎት ሰጪ ቦተዎች የሚሰሩ ባለሙያዎች ማን ተብለው እንደሚጠሩ እና ምን እንደሚሰሩ በመጠየቅ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- በመጨረሻምበጨዋታ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን እና ባለሙያዎችን እንዲገልፁ ማድረግ

ለምሳሌ፡- እንቆቅልሽ/ህ"

ምን አዉቅልህ/ሽ

ከአገልግሎት ሰጪ ቦታዎች አንዱ ነኝ

ሰዎች ሲታመሙ ሀኪም ቤት እንደሚሄዱ ሁሉ

መኪናዎች ሲታመሙ ወደኔ ይመጣሉ

እኔ ማን ነኝ? <u>ጋራዥ</u>

ምዘና ፡- ስለአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና በውስጡ ስለሚሰሩ ባለሙያዎች መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ፡

ተግባር ሁለት ፡- የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን መጎብኘት

ዓላማ ፦ የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን ይጎበኛሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ባለሙያዎችን የሚያሳዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ህፃናትን ወደ ተለያዩቦታዎች ይዞ በመሄድ እንዲጎበኙ ማድረግ

  ለምሳሌ፡- ፋብሪካ፣ አንበሳ ግቢ፣ የህፃናት ትያትር፣ሙዚየም፣ ወዘተ…
- በጉብኝት ወቅት በጉብኝቱ ቦታ የሚሰሩ ባለሙያዎችን እና የስራ ድርሻቸውን ለህፃናቱ እንዲያስተዋውቁ ማድረግ
- ከጉብኝት በኋላ ስላዩት እና ስለሰሙት ነገር የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፦ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ዓላማ ፦ ስለ ባለሙያዎች እና ስራዎቻቸዉ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በአካባቢ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትንና ባለሙያዎቸን የሚያሳዩ ሰእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የወላጆቻቸውን እና የቅርብ ዘመዶቻቸውን ሙያ እና የሚሰሩበትን ቦታ ጠይቀው እንዲመጡ ማድረግ
- ያገኙትን መልስ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፦ ስለ ባለሙያዎች እና ስለሥራቸው መናገር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሦስት ፦ ስለ ባለሙያዎች እና ስራዎቻቸዉ መናገር



ተግባር አራት ፦ የአገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎችንና የሥራ ድርሻ አስመስሎ መጫወት

ዓላማ ፡- የአገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎችንና የሥራ ድርሻ አስመስለዉ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በአካባቢ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትንና ባለሙያዎችን የሚያሳዩ ስእሎች፣ የመስሎ መጫወት ጨዋታ ማዕዘን

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ክፍሉን ለመስሎ መጫወት ጨዋታ በሚያመች መልኩ ማደራጀት
- ህፃናት አካባቢያቸው ያሉትን ባለሙያዎች የስራ ድርሻ በማንፀባረቅ እንዲጫወቱ እድሉን መስጠት እና መደገፍ

ምዘና ፡- የአገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች እና የስራ ድርሻቸውን አስመስለው መጫወታቸውን መከታተል።

ዓላማ ፡- የአገልግሎት ሰጪ ቦታዎችንና የባለሙያዎችን የሥራ ድርሻ መናገር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በአካባቢ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትንና ባለሙያዎችን የሚያሳዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ ትርጉም የማይሰጡ ታሪኮችን በመንገር የተለያዩ የአገልግሎት ሰጪ ቦታዎችንና የባለሙያዎችን ተግባርና የስራ ድርሻ እንዲረዱ ማድረግ

  ለምሳሌ፡-

  - ‹ከእለታት አንድ ቀን ቤታችን ውስጥ መብራት ጠፋ እና ሻማ ለመግዛት መድሀኒት ቤት ሄድኩኝ እና መድሀኒት ቤት ውስጥ ሻማ ለሚሸጠው ሹፌር ሻማ ለመግዛት እንደመጣሁ ነገርኩት። እሱም ሻማውን ሰጠኝ እና ይዤ ወደቤቴ መጣሁ› በማለት መንገር
  - በመቀጠል የተነገረው ታሪክ ስህተት እንዳለው እና እንደሌለው በመጠየቅ ስህተቱ ምን ላይ እንደሆነ እና ምን መሆን እንዳለበት በመጠየቅ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን እና የሚሰጡትን አገልግሎት እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- የአገልግሎት ሰጪ ቦታዎችንና የባለሙያዎችን የሥራ ድርሻ መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- የአገልግሎት ሰጪ ቦታዎችንና የባለሙያዎችን የሥራ ድርሻ መናገር



ተግባር ስድስት ፡- መደበኛ ትምህርት ቤትን መጎብኘት

ዓላማ ፡- መደበኛ ትምህርት ቤትን በመጎብኘት ለአንደኛ ክፍል ይዘጋጃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በአካባቢ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ባለሙያዎችን የሚያሳዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህፃናቱ ለመደበኛ ትምህርት ቤት የሚዘጋጁበት እድሜ ላይ ያሉ እንደመሆናቸው መጠን በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ መደበኛ ትምህርት ቤት በመውሰድ ጉብኝት እንዲያደርጉ ማድረግ
- በጉብኝት ወቅት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትኩረት እንዲያደርጉ ማነቃቃት
- ከጉብኝቱ በኋላም አንደኛ ክፍል የሚማሩ ልጆችን ማን እንደሚያስተምራቸው፤ አስተማሪያቸውን ማን ብለው እንደሚጠሩ፤ የተማሪዎቹ አቀማመጥ፤ ክፍሉ እና የግቢው አደረጃጀት ላይ በማወያየት ህፃናት ለመደበኛ ትምህርት ቤት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ይህን መሳይ ጉብኝት ስለ መደበኛ ትምህርት ቤት ያላቸውን ግንዛቤ ስለሚጨምር በተደጋጋሚ ቢያደርጉ ህፃናቱ የበለጠ ይጠቀማሉ። |

ምዘና ፡- መደበኛ ትምህርት ቤትን በመጎብኘት ለአንደኛ ክፍል መዘጋጀታቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2.በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | 2.2.ሃገርን የመውደድ ስሜት ያድርባቸዋል። |

ተግባር አንድ ፡- የኢትዮጵያን ካርታ ቅርፅ መተዋወቅ።


ዓላማ ፡- የኢትዮጵያን ካርታ ቅርፅ ይተዋወቃሉ::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የኢትዮጵያ ካርታ ፐዝል፣ ክላሰር፣ ዱልዱም መርፌ፣ የሱፍ ክር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የኢትዮጵ ካርታን
- የኢትዮጵያ ካርታ ፐዝልን በመስጠት እንዲገጣጠሙ ማድረግ
- በመቀጠል የኢትዮጵያን ካርታ በወፍራም ክላሰር ላይ በመሥራት አልፎ አልፎ ቀዳዳ ማበጀት
- ከዚያም የተሰራውን ካርታ እና ዱልዱም መርፌ የሱፍ ክር አስገብቶ መስጠት
- ቀዳዳውን ተከትለው ክሩን በማስገባት እንዲሰሩ ማድረግ
- በመጨረሻም የሁሉንም ስራ በክፍል ውስጥ መለጠፍ

ምዘና ፡- የኢትዮጵያን ካርታ ቅርፅ ማወቃቸውን መከታተል::





ተግባር ሁለት ፡- የኢትዮጵያን ካርታ መለየት

ዓላማ ፡- የኢትዮጵያን ካርታ መለየት ይችላሉ::::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የኢትዮጵያ ካርታ፣ የሌሎች አገሮች ካርታ፣ ነጭ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ/ከለር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በትናንሽ ወፍራም ካርቶን ላይ የተሰሩ የኢትዮጵያን እና የሌሎች አገሮችን ካርታ በመስጠት የትኛው የሀገራችን ካርታ እንደሆነ እንዲመርጡ ማድረግ
- የመረጡትን የኢትዮጵያ ካርታ እንዲያደምቁና ባለቀለም እርሳስ/ከለር እንዲቀቡ ማድረግ

ምዘና ፡- የኢትዮጵያን ካርታን ቅርጽ መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ::

ዓላማ ፡- የሙያ ጠቀሜታን ይረዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ባለሙያዎችን የሚያሳዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በሀገራችን ያሉ የተለያዩ ባለሙያዎች እንዳሉና ሥራቸው ምን እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት

  ለምሳሌ ፡- ሃኪም፣ ፖሊስ፣ አስተማሪ፣ ወታደር፣ ሸማኔ፣ ሸክላ ሰሪ፣ አናፂ፣ ግንበኛ ወዘተ

- ሁሉም ባለሙያዎች ለሃገራችን ጠቃሚ እንደሆኑ እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የሙያ ጠቀሜታን መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ የሙያ ጠቀሜታን መረዳት



ተግባር አራት ፡- ለሀገራችን ጠቃሚ ስራ የሰሩ ሰዎችን መተዋወቅ

ዓላማ ፡- ለሀገራችን ጠቃሚ ስራ የሰሩ ሰዎችን ይተዋወቃሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ለሀገራችን ጠቃሚ ስራ የሰሩ ሰዎች ፎቶግራፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሀገራችን ጠቃሚ ስራ የሰሩ ሰዎችን በስእል/ፎቶ በማሳየት እና ስማቸውን በማስተዋወቅ ምን እንዳደረጉ ግንዛቤ ማስጨበጥ

ለምሳሌ፡- ሀይሌ ገብረስላሴ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ አበበች ጎበና፣ ዶ/ር በላይ አበጋዝ

- ስለታዋቂ ሰዎች የተፃፉ ፅሁፎችን በደረጃቸው አሳጥሮ በማዘጋጀት ለህፃናቱ ማንበብ
- እነርሱም ሲያድጉ ለሀገራቸው እና ለወገናቸው ጠቃሚ ነገር ማድረግ እንደሚችሉ ማሳወቅ
- ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፡- ለሀገራችን ጠቃሚ ስራ የሰሩ ሰዎችን መተዋወቃቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- የኢትዮጵያ ባንዲራ መስራት

ዓላማ ፦ የኢትዮጵያ ባንዲራ መስራትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ቀጭን እንጨት፣ ነጭ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ/ ከለር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መምህር አንድ ነጭ ወረቀት ላይ ሶስት እኩል መስመሮችን አግድም ማስመር እና አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማትን ከመስመር ሳይወጡ በመቀባት ለህፃናት ማሳየት
- በመቀጠልም ቀጭን እንጨት ላይ ማጣበቂያ በመቀባት ወረቀቱን ሁለት ዙር መጠቅለል
- ከዛም ምን እንደሆነ ህፃናቱ እንዲገምቱ ማድረግ ካላወቁት ፍንጭ መስጠት
- በመቀጠልም አንድ ሉክ ወረቀት አራት ቦታ በመቁረጥ በህፃናት ቁጥር ማዘጋጀት
- እያንዳንዱን ቁርጥራጭ ሶስት ቦታ ከፍሎ ማስመር
- ለእያንዳንዱ ህፃን ወረቀቱን እና ከለሮች በመስጠት የኢትዮጵያን ባንዲራ እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱም ለእያንዳንዳቸው ቀጫጭን እንጨቶችን በመስጠት እንጨቱ ላይ ሁለት ዙር እንዲጠቀልሉ እና ማጣበቂያ በመቀባት እንዲያጣብቁ ማድረግ
- በመጨረሻም ህፃናቱ ባሉበት በመቆም የሰሩትን ባንዲራ በማውለብለብ ‹ባንዲራችን› የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ

> ማስታወሻ ፦ ይህንን ተግባር የተለያዩ ብሄራዊ በዐላት (የባንዲራ ቀን) በሚከበርበት ቀን ማከናወን ይቻላል።

ምዘና ፦ የኢትዮጵያ ባንዲራ መስራት መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።



ተግባር ስድስት ፦ የሀገራችንን ብሄር ብሄረሰቦች መተዋወቅ

ዓላማ ፡- የሀገራችንን የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሀገራችንን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የሚያሳዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን የሚያሳዩ ስእሎችን በመጠቀም በሀገራችን የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች እንደሚኖሩ ማስገንዘብ
- እነዚህ ብሄር ብሄረሰቦች የተለያየ ቋንቋ እንደሚናገሩ ማስገንዘብ
- ሀገራችን የሁላችንም እንደሆነች እና በሰላም በፍቅር በመተሳሰብ መኖር እንዳለብን መግለ

ማስታወሻ ፡- ይህ ተግባር የብሄር ብሄረሰቦች በዐል በሚከበርበት ወቅት ቢከናወን ህፃናቱ የበለጠ እንዲገነዘቡ ያደርጋል።

ምዘና ፡- የሀገራችንን ብሔር ብሔረሰቦችን መተዋወቃቸውን ማረጋገጥ::

ዓላማ ፡- የሀገራችንን ታሪካዊ ቦታዎች በስም ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የታሪካዊ ቦታዎች ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሀገራችን የምትታወቅባቸውን ታሪካዊ ቦታዎችን በስእል በማሳየት እና በስማቸው በመጥራት ማወያየት

ለምሳሌ፡- አክሱም፣ላሊበላ፣ የፋሲል ግንብ፣ የሀረር ግንብ፣ ወዘተ....

- ውብት እንዳላቸውና ለቱሪስት መስህብነት እንደሚያገለግሉ ማስረዳት

ምዘና ፡- የሀገራችንን ታሪካዊ ቦታዎች መተዋወቃቸውን መከታተል::

ተግባር ሰባት ፡- የሀገራችንን ታሪካዊ ቦታዎች መተዋወቅ

ተግባር ስምንት ፡- የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙርን መዘመር

ዓላማ ፡- የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙርን መዘመር ይችላሉ::

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር የተቀረጸበት ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በተለያየ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙርን በህብረት እንዲዘምሩ ማድረግ
- ሲዘምሩ ሊከተሉ የሚገባቸውን ስርአቶች ማሳወቅ እና ማለማመድ

  ለምሳሌ፡- በተጠንቀቅ መቆም፣ ሌላ ወሬ አለማውራት፣ አለመሳቅ፣ ወዘተ…
- የተለያዩ የህዝብ በአላት በአፀደ ሕፃናት ውስጥ ሲከበሩ የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙርን መዘመር ማለማመድ እና በደረጃቸው ሀገርን የመውደድ ስሜትን እንዲያንፀባርቁ ማድረግ

ምዘና ፡- የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙርን መዘመር መቻላቸውን ማረጋገጥ::

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅ እና መንከባከብ | 3.1.በአካባቢ ጽዳት ላይ መሣተፍ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የጽዳት መሣሪያዎችን አገልግሎት መለየት

ዓላማ ፦ የጽዳት መሣሪያዎችን አገልግሎት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጐላ ብለው የተሳሉ የጽዳት መሣሪያዎች ስዕል፣ ወረቀቶች፣ እርሳሶች፣ ባለቀለም እርሳሶች፣ ትልቅ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ጐላ ብለው የተሳሉ የጽዳት መሣሪያዎችን ስዕል ከፊት መስቀል
- ለሕፃናቱ ወረቀት፣ እርሳስ እና ባለቀለም እርሳስ መስጠት
- የጽዳት መሣሪያዎችን ስዕል በማየት አስመስለው እንዲስሉ እና ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱም የምን ስዕል እንደሆኑ እና ለምን እንደሚያገለግሉ በመጠየቅ ማወያየት
- በቤታቸውና በአጸደ ሕጻናት በጽዳት ሥራ ላይ መሳተፋቸው ያስደስታቸው እንደሆነ እንዲናገሩ ማበረታታት
- ስዕሉን ቆርጠው እንዲያወጡ ማድረግ
- በትልቅ ወረቀት ላይ የሁሉንም ሕፃናት ስዕል በመለጠፍ ክፍሉ ውስጥ መስቀል

ምዘና ፦ የጽዳት መሣሪያዎችን አገልግሎት መረዳት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ በአካባቢ ጽዳት ላይ መሣተፍ

ዓላማ ፦ በአካባቢ ጽዳት ላይ ይሳተፋሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረኝነት ሰሌዳ /ማስታወቂያ/፣የቆሻሻ ማፈሻ፣ የቆሻሻ መሰብሰቢያ ቅርጫቶች፣ የውሃ ማጠጫዎች ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መምህር ከሕፃናቱ ጋር ለጽዳት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት
- ሕፃናቱን በቡድን በመመደብ ለእያንዳንዱ ቡድን የሥራ ድርሻ እና የጽዳት መሣሪያን መስጠት
- ሕፃናቱ በየዕለቱ ያለማንም አስታዋሽነት የተረኝነት ሰሌዳውን በመመልከት ከዕድሜ እኩዮቻቸው ጋር በጽዳት ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ
- ግጥሞችን በመንገር አካባቢን የማጽዳት ባህልን እንዲያዳብሩ እና ጠቀሜታውን እንዲረዱ ማድረግ

ለምሣሌ፦

ልጆች ልጆች እባካችሁ
ስሙኝ ልንገራችሁ
ቆሻሻዎችን በየቦታው አትጣሉ
ቆሻሻዎች በሽታን ያመጣሉ
እኛ ከተያዝን በበሽታ
እንቀራለን ከትምህርት ገበታ
አይኖርም ያ ጣፋጭ ጨዋታ

ምዘና ፦ በአባባቢ ጽዳት ላይ መሣተፍ መቻላቸውን መከታተል።

ዓላማ ፡- መጫወቻዎችንና የመጫወቻ አካባቢያቸውን በአግባብ መያዝን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የግንባታ ብሎኮች፣ መጫወቻዎች፣ የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የግንባታ እና የመስሎ መጫወት ጨዋታን ማጫወት
- ከተጫወቱ በኋላ የተጠቀሙባቸዉን መጫወቻዎች እና መሳርያዎች በቦታዉ እንዲመልሱ በማድረግ ዕቃዎችን በስርዐት የማስቀመጥ ልምድን እንዲለማመዱ ማድረግ
- የሚቀመጡበትን ወንበር ከጨዋታ በኋላ ወደቦታው መመለስ እንዳለባቸው ማሳሰብ
- የማያስፈልጉትን ቁርጥራጭ ወረቀቶች እና አፍንጫቸዉን ካጸዱ በኋላ ያጸዱበትን ሶፍት በየቦታዉ መጣል እንደሌለባቸዉና በቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ዉስጥ ብቻ መጣል እንዳለባቸው መንገር
- በተጨማሪም አርአያ በመሆን ልምዱን እንዲመሰርቱ ማስቻል

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- እነዚህን ስነሥርዐቶች በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ክትትል በማድረግ ባህል እንዲሆን ማለማመድ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- መጫወቻወችንና የመጫወቻ አካባቢያቸውን በአግባብ መያዝ መለማመዳቸውን መከታተል::

ተግባር ሦስት ፡- መጫወቻዎችንና የመጫወቻ አካባቢን በአግባቡ መያዝ



ተግባር አራት ፡- የመመገቢያ አካባቢን ማጽዳት

ዓላማ ፦ የመመገቢያ አካባቢያቸውን ማጽዳት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ትናንሽ ቁርጥራጭ ጨርቅ፣ ውሀ፣ ቆሻሻ መጣያ ቅርጫት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ትንሽ ቁራጭ ጨርቅ ውሃ በመንከር ጠረጴዛን በመጥረግ/ በመወልወል/ ማሳየት
- በምግብ ተረኝነት ጊዜ እንዴት ጠረጴዛን መጥረግ እና መወልወል እንዳለባቸው መንገር
- የጠረጉትንም መሬት መጣል እንደሌለባቸውና በዕቃ መሰብሰብ እንዳለበት በተግባር በማሣየት እንዲለማመዱ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፦ የመወልወያ ጓንት በሕፃናቱ እጅ ልክ ቢዘጋጅ ይመረጣል። |

ምዘና ፦ የመመገቢያ አካባቢያቸውን ማጽዳት መለማመዳቸዉን መገምገም።

ዓላማ ፦ አካባቢን መንከባከብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጐላ ብሎ የሚታይ ሰዎች ቆሻሻ በየቦታው ሲጥሉ፣ ሣር ሲረግጡ፣ አበባ ሲቀነጥሱ የሚያሣይ ስዕል ላይ በቀይ ቀለም X የተደረገበት ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሰዎች ቆሻሻን በየቦታው ሲጥሉ የሚያሳይ ስዕልን ማሣየት
- ስዕሉ ምን መልእክት እንዳለው ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት
- የስዕሉን መልእክት እንዲረዱና እነሱም እንደዚህ ዓይነት ድርጊቶችን መፈፀም እንደሌለባቸው ሊገባቸው በሚችል መልኩ መግለጽ
- አካባቢያቸውን በተመለከተ ስላዩት እና ስለሰሙት ነገር እንዲናገሩ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማበረታታት
- አካባቢያቸውን የሚጎዱ ድርጊቶችን እንዳይፈጽሙ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸዉን መከታተል
- ከፈጸሙም ጉዳቱን በማስረዳት ማስተካከያ እንዲያደርጉ ማድረግ

ምዘና ፦ አካባቢን መንከባከብ መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፦ አትክልቶችን መንከባከብ

ዓላማ ፡- አትክልቶችን መንከባከብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቀለም ቆርቆሮ/ ጣሳ፣ የአትክልት ዘሮች/ ችግኞች/፣ ዉሃ፣ የዉሃ ማጠጫ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህጻናት በቤትም ሆነ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ዉስጥ አትክልቶችን መቅጠፍ /መቁረጥ/ እንደሌለባቸዉና አትክልቶች ለአከባቢ ዉበትን እንደሚሰጡና አየር መዛባትንም እንደሚከላከሉ በመንገር ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ሕፃናት እያንዳንዳቸው በፕላስቲክ እቃዎች ላይ የተለያዩ አትክልቶችን እንዲተክሉ ማድረግ
- ዕለት በዕለት አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያደርጉላቸው ማድረግ
- አትክልቶችን ከራሳቸው ሕይወት ጋር በማዛመድ እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸዉ ማስገንዘብ

  ለምሳሌ፡- ሕፃናት ምግብ ካልተመገቡ እንደማያድጉ ሁሉ አትክልትም ውሃ ማግኘት እንዳለባቸው

  ሕፃናት ሰዎች ሲቆነጥጧቸው እንደሚያማቸው ሁሉ አትክልቶችም ሲቀነጠሱ እንደሚያማቸው ወዘተ…

ማስታወሻ ፡- ሕጻናት በፕላስቲክ ዕቃዎች ላይ እንጂ ሊቆርጧቸውና ሊዝጉ ስለሚችሉ በቆርቆሮ እቃዎች ላይ አትክልት እንዳይተክሉ ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- አትክልቶችን መንከባከብ መለማመዳቸዉን መገምገም።

ተግባር ሰባት ፡- የቤት እንስሳትን መንከባከብ

ዓላማ ፡- የቤት እንስሳትን መንከባከብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቤት እንስሳት ስዕሎች( ዶሮ፣ ድመት፣ ውሻ ወዘተ...)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት በቤታቸው ያሉትን እንሰሳት/ዶሮ፣ ድመት፣ ውሻ ወዘተ...ወላጆቻቸው ምግብ፣ዉሃ እንዲሁም መጠለያ በመስጠት እንደሚንከባከቧቸው ማስታወስ
- እነሱም የእንሰሳቱን ምግብ መንጠቅ፣ መድፋት ወዘተ...እንደሌለባቸው እና ከወላጆቻቸው ጋር አብረው መንከባከብ እንዳለባቸው ማስረዳት

ምዘና ፡- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቤት እንስሳትን መንከባከብ መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስምንት ፡- ሌሎችን መንከባከብ

ዓላማ ፡- ሌሎችን መንከባከብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አሻንጉሊት፣ የአሻንጉሊት ልብሶች፣ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ወላጆቻቸው ስራ ሲይዙ በቤት ዉስጥ ያሉ ሕፃናት ወንድም እና እህቶቻቸውን በማጫወት መንከባከብ እንዳለባቸው ማስረዳት
- መስሎ መጫወትን በማዘጋጀት እንዴት መጫወት እና መንከባከብ እንዳለባቸዉ ማለማመድ

> ማስታወሻ ፡- ታናናሾቻቸውን ከአልጋ ላይ ማንሳት፣ መጐተት፣ ማቀፍ እንደሌለባቸው ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ሌሎችን መንከባከብ መለማመዳቸዉን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4. በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየት እና ጥንቃቄ መውሰድ | 4.1. ራስን ከአደገኛ ነገሮች እና አካባቢን ማጽዳት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ፡- ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን መለየት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክብሪት፣ ምላጭ፣ጠርሙስ፣ሹል ነገር ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን የሚገልፁ አጫጭር ግጥሞችን በቃል መንገር
- አደገኛነታቸውን ለማጠናከር የሚከተለውን ምሳሌ መጠቀም፡-
    - ክብሪትና ምላጭ መጫወቻ አይደሉም
      ከአጠገባችን ይጥፉ ለእኛ አይጠቅሙም
      ተወዳጆች ለእኛ ጠቃሚዎቻችንን
      ኳሶቻችን እና አሻንጉሊቶቻችንን
      አምጡአቸው ወደ እኛ እንወዳቸዋለን
- በአካባቢያቸው ሹል ነገር የወጋችው፣ ጠርሙስ ወይም ምላጭ የቆረጣቸው፣ እሳት ያቃጠላቸው እና መኪና የገጫቸው ሰዎችን ታሪክ ሰምተው እንደሆኑ መጠየቅ
- ስላዩትና ስለሰሙት ነገር እንዲናገሩ እድሉን መስጠት እና እንዲወያዩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ዓላማ ፡- ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መኪና መንገድ ላይ ኳስ የሚጫወቱ ህፃናት ስዕል

የአ [illegible]

ተግባር ሁለት ፡- ራስን ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች መጠበቅ

- [illegible] ጊያሣዩ ታሪኮችን መንገር
- ህጻናት በቤት አካባቢ በክብሪት መጫወት፣ የኤሌክትሪክ ሶኬቶችን መነካካትና ጋዝ መለኮስ እንደሌለባቸዉ መንገር
- ሹል ነገሮችና ስለታማ ነገሮች መጫወቻ እንዳልሆኑ ማስገንዘብ
- ትንንሽ ነገሮችን ወደ አፋቸዉ እና አፍንጫቸዉ መክተት ዉስጥ መክተት እንደሌለባቸዉ ማስረዳት
- ትንንሽ ነገሮችን ወደ አፋቸዉ እና አፍንጫቸዉ ቢከቱ የሚያስከትለዉን ጉዳት ማስረዳት
- የምግብ ትርፍራፊዎችን፣ የፍራፍሬ ልጣጭን መሬት ላይ መጣል አደጋ እንደሚያስከትል መግለፅ
- ይህንን ሲያደርጉ የተጎዱ ህጻናትን ገጠመኞች በመንገር ግንዛቤ ማስጨበጥ

ምዘና ፡- ራስን ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች መጠበቅ መለማመዳቸዉን መከታተል፡፡

ተግባር ሶስት ፡- በመጓጓዣ ላይ ሊደረግ ስለሚገባ ጥንቃቄ መገንዘብ

ዓላማ ፡- በመጓጓዣ ላይ ሊደረግ ስለሚገባ ጥንቃቄ ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ህፃናት በትራንስፖርት ሲጓዙ የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህጻናት ከወላጆቻቸዉ ጋር በህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ሄደዉ ያዉቁ እንደሆነ፣ ወዴት እንደሄዱ፣ ቆመዉ ወይም ተቀምጠዉ እንደሄዱ መጠየቅ
- መዉረጃቸዉ ሲደርስ አብረዋቸዉ የሄዱ ሰዎች ምን ብለዉ ለሹፌሩ /ረዳቱ/ እንደተናገሩ መጠየቅ
- በትራንስፖርት ዉስጥ ቢቻል ተቀምጠዉ መሄድ እንዳለባቸዉ ማስረዳት
- መቀመጫ ካላገኙም ወንበሩን ወይም ቋሚ ብረቱን በሁለት እጃቸዉ እንዴት መያዝ እንዳለባቸዉ ማሳየት
- መዉረጃቸው ሳይደርስ መነሳትም ሆነ መቆም እንደሌለባቸዉና ቢንቀሳቀሱ ሊወድቁና ጉዳት ሊደርስባቸዉ እንደሚችል ማስረዳት
- በትራንስፖርት ሲጓዙ ሊጠብቁ የሚገቧቸዉን ስርዓቶች እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- በመጓጓዣ ላይ ሊደረግ ስለሚገባ ጥንቃቄ መገንዘብ መቻላቸውን ማረጋገጥ፤

ዓላማ ፡- ራሳቸውን ከመኪና አደጋ ይጠብቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መኪና መንገድ ላይ ኳስ የሚጫወቱ ህፃናት ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መኪና መንገድ ላይ ኳስ የሚጫወቱ ህፃናት ስእልን ለሁሉም ህጻናት ማሳየት
- ስዕሉ ላይ ስላዩት ነገር እንዲናገሩ ዕድል መስጠት
- መንገድ ላይ መጫወት ለመኪና አደጋ ሊያጋልጥ እንደሚችል ማስገንዘብ
- የትንሹ ዮናስ ተረትን አሳጥሮ በመተረክ ትምህርቱን ማጠናከር

ምዘና ፡- ራሳቸውን ከመኪና አደጋ መጠበቅ መቻላቸውን መገምገም፡፡

ተግባር አራት ፡- ራስን ከመኪና  አደጋ መጠበቅ

ዓላማ ፡- የትራፊክ ህግጋትን መጠበቅ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መኪና መንገድን ብቻቸውን የሚያቋርጡ ህፃናት ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መኪና መንገድን ብቻቸውን ማቋረጥ እንደሌለባቸዉ ማስገንዘብ
- ቻ መሆኑን ማስገንዘብ

ተግባር አምስት ፡- የትራፊክ ህግጋትን መጠበቅ

- ሲጓዙም የመንገዱን የግራ ጠርዝ ይዘዉ በእግረኛ መንገድ ላይ መጓዝ እንዳለባቸዉ መንገር
- በክፍል ዉስጥና ከክፍል ዉጭ መስመር በማስመር በተግባር ማሳየትና ማለማመድ
- የመንገድ ትራፊክ መብራት የሚለዉን ጨዋታ ማጫወት

ማስታወሻ ፡- ከ 4-5 ዓመት ላለዉ ዕድሜ በተዘጋጀዉ አጋዥ መጽሃፍ ላይ ጨዋታዉ ተጽፏል። ጎበዙ ተማሪ በጣም ጠንቃቃ ነው። የሚለዉን መዝሙር በህብረት በመዘመር የመዝሙሩን መልእክት እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የትራፊክ ህግጋትን መጠበቅ መቻላቸውን መገምገም::

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4. በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ | 4.2. በደረጃቸው የሕፃናት መብትን ተረድተው ራሳቸውን ከሕፃናት ጥቃት ለመከላከል ይሞክራሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ራስን ከጥቃት መከላከል

ዓላማ ፡- ራሳቸውን ከጥቃት መከላከልን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መኪና መንገድን ብቻቸውን የሚያቋርጡ ህፃናት ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህጻናት ወላጆቻቸዉን እና መምህራኖቻቸዉን ማክበርና መታዘዝ እንዳለባቸዉ መንገር
- የራሳቸዉ ያልሆነን ዕቃ ሳያስፈቅዱ ማንሳት እንደሌለባቸዉ ገጠመኞችን መንገር
- ህጻናት ከቤታቸዉ ወጭ በመንገድ ላይ የማያዉቋቸዉ ሰዎች ልዉሰዳችሁ ቢሏቸዉ ተከትለዉ መሄድ እንደሌለባቸዉ ማሳወቅ
- እንደዚህ ያለ ሁኔታ ቢያጋጥማቸዉ በአካባቢዉ ለሚገኙ ሰዎች እንዲደርሱላቸዉ መንገር /መጮህ/ እንዳለባቸዉ ማስገንዘብ
- የማያዉቋቸዉ ሰዎች አታለዉ ወስደዋቸዉ የተለያዩ ጥቃቶች ሊያደርሱባቸዉ እንደሚችሉ ማስረዳት

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ጭንቀት በማያሳድር መልኩና በደረጃቸዉ ሊገባቸዉ በሚችል መልኩ ገጠመኞችን መንገር። |

ምዘና ፡- ራሳቸውን ከጥቃት መከላከል እንዳለባቸው መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- ሙብትን ማክበር

ዓላማ ፦ መብታቸውን ተረድተው ራሳቸውን ከጥቃት ይከላከላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የሕፃናትን ጥቃት የሚያሳዩ ስእሎች፤ገጠመኞች፡ መዝሙሮች ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ህጻናት የተለያየ ጉዳት የደረሰባቸዉን ህጻናት የሚያሳይ ስዕል ማሳየት
- በቤታቸዉ እና በየአካባቢያቸዉ በቤት ዉስጥ ያለ ሰዉ የሚደበድባቸዉ፣ የሚያስፈራራቸዉ፣ ሁልጊዜ የሚሰድባቸዉና የሚቆጣቸዉ ካለ ለአስተማሪያቸዉ መጥተዉ መንገር እንዳለባቸዉ ማስረዳት
- ህጻናት ልብሳቸዉ እንዲታጠብ ሲያስፈልግ ከወላጆቻቸዉ ዉጭ ማንም ሰዉ ፊት ልብሳቸዉን ማዉለቅ እንደሌለባቸዉ ማስገንዘብ
- ከወላጆቻቸዉ ዉጭ ሌላ ሰዉ ልብሳቸዉን እንዲያወልቁ ቢያስገድዳቸዉ እንኳን መጮህ እንዳለባቸዉ ማስገንዘብ
- ማንም ሰው ከእጃቸው፣ ከግንባራቸውና ከጉንጫቸው በስተቀር ሌላ የሰውነት ክፍሎቻቸውን መሳምም ሆነ መነካካት እንደሌለበት እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፦ መብታቸውን ተረድተው ራሳቸውን ከጥቃት መከላከል እንዳለባቸው መገንዘባቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሦስት ፡- የሌሎችን መብት ማክበር

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የሌሎችን መብት ማክበር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ገጠመኞች፣ መዝሙሮች ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ገጠመኞች እና መዝሙሮችን በመጠቀም ለክፍል ጓደኞቻቸዉ ተገቢዉን ፍቅር እና አክብሮት መሥጠት እንዳለባቸዉ ማስገንዘብ
- መሳደብ፣ መማታት እና ማሾፍ እንደሌለባቸዉ መንገር
- ራሳቸዉን ከተጎጂዉ ቦታ ላይ አድርገዉ እንዲመለከቱና ምን አይነት ስሜት እንደሚሰማቸዉ በመጠየቅ ማጠናከር

ምዘና ፡- የሌሎችን መብት ማክበር መለማመዳቸውን መከታተል።

ዓላማ ፦ በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የሕፃናትን ጥቃት የሚያሳዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተለያዩ ደረጃቸውን የሚመጥኑ በሕፃናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን የሚዘግብ ገጠመኝን ለሕፃናት መተረክ
- የተለያዩ በህጻናት ላይ የደረሱ ጥቃቶችን በማንሳት በማወያየት እንዲረዱ ማድረግ
- ገጠመኞችን በደረጃቸው ወደ ድራማ በመቀየር ወላጆች በሚገኙበት በዓል ላይ በማሳየት የሕፃናት ጥቃቶችን ወላጆችና አሳዳጊዎች እንዲገነዘቡ ብሎም እንዲከላከሉ ማስገንዘብ

ምዘና ፦ በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን መገንዘባቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፦ በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን መገንዘብ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ስለ ህጻናት መብት ወላጆችን ማስገንዘብ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሕፃናትን ጥቃት የሚያሳዩ ስእሎች፣ የመዝሙር ካሴቶች ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሚከተለው ግጥም ዜማ በማዘጋጀት ሕፃናት ለወላጆች ቀን እንዲያቀርቡ ማለማመድ

ተግባር አምስት ፡- ስለ ህጻናት መብት ወላጆችን ማስገንዘብ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

መብታችንን አስከብሩልን እናንተም አክብራችሁ
ስናጠፋ ከመምታት ይልቅ ምከሩን
ከመሳደብ ከመጮህ ይልቅ አስተምሩን
ይገባናል እኮ ምንም ትንሽ ብንሆን
ደግሞም አትከልክሉን እባካችሁ እንጫወት
እንዝለል እንቦርቅ እንደሰት
ጊዜያችን ነው መፈንደቁ መቦረቁ
ትፈቅዱልን ነበር እኮ መብታችን መሆኑን ብታወቁ

- ሕጻናቱ በተገኙበት ከወላጆቻቸው ጋር በሕፃናት ላይ ስለሚደርሱ ጥቃቶች መወያየት
- ሕፃናትን ከጥቃቱ እንዲከላከሉ እና የሕፃናት መብትን ተረድተው እንዲያከቡብሩላቸው ግንዛቤ ማስጨበጥ

ምዘና ፡- ስለ ህፃናት መብት ወላጆችን ማስገንዘብ  መቻላቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 5. የእንቅስቃሴ ጽንሰ ሐሳብ መረዳት እና ሙከራ ማካሄድ | 5.1.በአካባቢያቸው የሚገኙትን የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶች አንድነትና ልዩነት ማወዳደር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- መጓጓዣ አይነቶችን መለየት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የመጓጓዣ አይነቶችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመጓጓዣ ዓይነቶች ስዕል፣ የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶች አሻንጉሊቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጎላ ብለዉ የተሳሉና ባለቀለም የሆኑ የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶችን በየተራ ማሳየት
- የመጓጓዣ አይነቶችን መጠሪያ ስም፣ በምን ላይ እንደሚጓዙ፣ ጥቅሙን በመጠየቅ ማወያየት
- የመጓጓዣ አይነቶች የተለያዩ እንደሆኑ እና የሚጓዙበትም መንገድ የተለያየ መሆኑን ማስረዳት

  ለምሳሌ፡- በአየር ላይ ፡- አዉሮፕላን፣ ጀት፣ ሂሊኮፕተር ወዘተ...

  በየብስ ላይ ፡- መኪና፣ አዉቶብስ፣ ባቡር ጋሪ ወዘተ...

  በዉሃ ላይ ፡- መርከብ፣ ጀልባ፣ ታንኳ ወዘተ...

- መጓጓዣዎች ሰዎችን እና ዕቃዎችን በፍጥነት ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንደሚያጓጉዙ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ከሁሉም በጣም ፈጣኖች የአየርመጓጓዣዎች እንደሆኑ መግለጽ
- ብዙ ዕቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚያጓጉዘዉ የዉሃ ላይ መጓጓዣ እንደሆነ ማሳወቅ
- በከተማ ብዙ ሰዎች በዕለት ተዕለት ህይወታቸዉ የሚጠቀሙት የየብስ መጓጓዣዎችን እንደሆነ መግለጽ
- በገጠር አካባቢ ደግሞ እንደ አህያ፣ ፈረስ፣ በቅሎ የመሳሰሉት እንስሳት ለሰዉና ለዕቃ መጓጓዣነት እንደሚያገለግሉ በመግለጽ እነሱ በየትኛዉ ቢሄዱ እንደሚደሰቱ በመጠየቅ ማወያየት

ምዘና ፡- የመጓጓዣ አይነቶችን መለየታቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- የመጓጓዣ አይነቶችን መመደብ

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የመጓጓዣ አይነቶችን መመደብ ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ፍላሽ ካርድ፣ ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችን የያዘ ፍላሽ ካርድ መስጠት
- ህጻናቱ በዓይነታቸዉ እንዲመድቧቸዉ በማድረግ ለምን እነደዛ እንደመደቧቸው በመጠየቅ ማወያየት
- በተጨማሪም ወረቀትን በማጣጠፍ ጀት፣ መርከብ፣ የመሳሰሉትን በመስራት እንዲጫወቱ ማበረታታት

ምዘና ፡- የመጓጓዣ አይነቶችን መመደብ መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ዓላማ ፡- የመጓጓዣ አይነቶችን ይስላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሕፃናት ወረቀት፣ እርሳስ እና ባለቀለም እርሳስ መስጠት
- ከመጓጓዣ ዓይነቶች አንዱን የፈለጉትን እንዲስሉ እና ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ምን እንደሳሉ እና ቀለም እንደቀቡ እንዲናገሩ እና ለጓደኞቻቸው እንዲያሣዩ ማድረግ
- ከመጓጓዣ ዓይነቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መዝሙሮች እንዲዘምሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በሥዕል የመጓጓዣ ዓይነቶችን መግለጽ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሦስት፡- የመጓጓዣ አይነቶችን መሳል

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ተግባር አራት ፡- በጨዋታ የመጓጓዣ አይነቶችን መግለጽ



ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- በጨዋታ የመጓጓዣ አይነቶችን መግለጽ ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የተለያዩ እንቆቅልሾችን በመጠየቅ የመጓጓዣ ዓይነቶችን በባህሪያቸው እንዲያውቋቸው ማድረግ

  ለምሣሌ ፡- እንቆቅልሽ

  ምን አውቅልሽ
  እኔ ሰዎችን ከሚያጓጉዙ
  መጓጓዣዎቹ አንዱ ነኝ
  በአየር ላይ እበራለሁ
  እኔ ማነኝ**?**

- የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችን የያዙ ሎቶዎችን ዶሚኖዎችን በማዘጋጀት እንዲጫወቱበት ማድረግ

ምዘና ፡- በጨዋታ የመጓጓዣ አይነቶችን ማንጸባረቅ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- የመጓጓዣ አይነቶችን መሳል



ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የመጓጓዣ አይነቶችን መሳል ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሕፃናት ወረቀት፣ እርሳስ እና ባለቀለም እርሳስ መስጠት
- ከመጓጓዣ ዓይነቶች አንዱን የፈለጉትን እንዲስሉ እና ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ምን እንደሳሉ እና ቀለም እንደቀቡ እንዲናገሩ እና ለጓደኞቻቸው እንዲያሣዩ ማድረግ
- ከመጓጓዣ ዓይነቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መዝሙሮች እንዲዘምሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የመጓጓዣ ዓይነቶችን መሳል መቻላቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6. በሥነ ስዕልና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅ እና ራስን መግለጽ | 6.1. የተለያዩ ነገሮችን በመስራት የፈጠራ ችሎታቸውን ያዳብራሉ። |

ተግባር አንድ ፡- አስመስሎ መሳል

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ አስመስለው መሳል ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ስዕል፣ እርሳስ፣ ወረቀት እና ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእይታ አመቺ ቦታ ላይ ጐላ ብሎ የተሳለ ስዕልን ማስቀመጥ
- ለሕፃናቱ በየጠረጴዛቸው እርሳስ፣ ወረቀት እና ከለር መስጠት
- ከፊት ለፊታቸው ያለውን ስዕል በማየት እንዲስሉ እና ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱ ስማቸውን ከስዕሉ ግርጌ እንዲጽፉ ማድረግ
- በጠረጴዛ ላይ የሳሉትን ስዕል ማስቀመጥ እና ማድነቅ

ምዘና ፦ አስመስሎ መሳል መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ በአካባቢያቸው ያዩትን ነገር መሳል

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- በአካባቢያቸው ያዩትን ነገር መሳል ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- እርሳስ፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናት ከቤታቸው ወደ አጸደ ሕጻናት ሲመጡ በመንገድ ላይ ምን እንዳዩ በመጠየቅ ማወያየት
- ቀጥሎም ለእያንዳንዱ ልጅ እርሳስ እና ወረቀት መስጠት
- ከዚያም ሲመጡ በመንገድ ላይ የዩትን አስታውሰው እንዲስሉ ማድረግ
- በአካባቢያቸው የሚያዩትን ነገር አስተውለው እና አስታውሰው በስዕል የማንፀባረቅ ችሎታን እንዲያዳብሩ ማድረግ
- ሲጨርሱም የሳሉትን ለክፍል ጓደኞቻቸው በማሣየት ምን እንደሳሉ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- በአካባቢያቸው ያዩትን ነገር መሳል መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር ሦስት ፡- ብሩሽ በመጠቀም መሳልን ማለማመድ

ዓላማ ፡- ብሩሽ በመጠቀም መሳልን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የስዕል ብሩሽ፣የውሃ ቀለም፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ከሕፃናቱ ፊት ለፊት መቆም
- የስዕል ብሩሽን የውሃ ቀለም ውስጥ በመንከር ወረቀት ላይ ፀሐይ፣ ብርቱካን፣ ቤት የመሣሠሉትን ቀላል ስዕሎች በመሣል ማሳየት
- በየጠረጴዛቸው ላይ የውሃ ቀለምንና /በትንሽ የፕላስቲክ ዕቃ ላይ/ ወረቀትን መስጠት
- ሕፃናት ባዩት መሠረት ብሩሽን በመጠቀም እንዲስሉ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- የስዕል ብሩሽ ማግኘት ካልተቻለ የመፋቂያ እንጨትን ጫፉን በማኘክ እንደብሩሽ መጠቀም ይቻላል እንደዚሁም የውሃ ቀለም ማግኘት ካልተቻለ በአካባቢ ከሚገኙ መርዛማነት ከሌላቸው የተለያዩ ዕጽዋቶች እና አፈሮች ማዘጋጀት ይቻላል።

ምዘና ፡- ብሩሽ በመጠቀም መሳልን ማለማመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- ጣትን በመጠቀም ስዕል መሳል

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ጣትን በመጠቀም ስዕል የመሳል ክህሎትን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የውሃ ቀለም፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የውሃ ቀለምንና ወረቀትን ማዘጋጀት
- ጠቋሚ ጣትን በመጠቀም ስዕል እንዴት መሣል እንደሚቻል ማሣየት
- ለሕፃናቱም የውሃ ቀለምንና ወረቀትን መስጠት
- ባዩት መሠረት እንዲስሉ ማድረግ

ምዘና ፡- ጣትን በመጠቀም ሥዕል መሳል መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- ሕትመት ማተም

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- ሕትመት ማተምን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የውሃ ቀለም፣ ብሩሽ፣ ቅጠል፣ ነጭ ወረቀት፣ ድንች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በብሩሽ ቀስ ብሎ ቅጠሉን ውስጡን የውሃ ቀለም መቀባት
- በነጭ ወረቀት ላይ ማንሳት እና ማተም
- ከዚያም የታተመውን የቅጠል ሕትመት ለሕፃናት ማሣየት
- ሕፃናት ሕትመትን ማተም እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ስሜታቸውን ማነሳሳት
- ለእያንዳንዱ ልጅ ወረቀትና ቅጠል መስጠት
- መምህር ጋ በየተራ እየመጡ ቅጠሉን ቀለም እንዲቀቡና እንዲያትሙ ማድረግ
- ሲደርቅ ከሕትመቱ ግርጌ ስማቸውን እንዲጽፉ ማድረግና ክፍሉ ውስጥ መለጠፍ
- በዚህ ዓይነት ሁኔታ ድንች በክቡ ቆርጦ በላዩ ላይ የተለያዩ ቅርፆችን በመሥራት ማተምን ማለማመድ

ምዘና ፡- ሕትመት ማተምን መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር ስድስት ፡- የወረቀት ጥልፍ

ዓላማ ፡- የወረቀት ጥልፍ መሥራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክላሰር፣ መቀስ/ከተር፣ ክር፣ መርፌ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በወፍራም ክላሰር ላይ መሠረታዊ መስመሮችን መሥራት
- መስመሩን ጠብቆ አልፎ አልፎ ምልክት ማድረግ
- ወፍራም ደማቅ የሱፍ ክርንና ዱልዱም መርፌን በመጠቀም የወረቀት ላይ ጥልፍ እንዴት መሥራት እንደሚቻል ረጋ ብሎ በማስረዳት ማሣየት
- ሕፃናቱ ባዩት መሠረት እንዲጠልፉ ማድረግ
- ቀስ በቀስ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን እና ቀላል ምስሎችን በመስጠት የወረቀት ላይ ጥልፍን ማለማመድ

ምዘና ፡- የወረቀት ጥልፍ መሥራት መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር ሰባት ፡- የወረቀት ሽመና


ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የወረቀት ሽመና መሥራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክላሰር፣ መቀስ/ከተር፣ክር፣ መርፌ፣ኮላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የወረቀት ሽመናን ለማሰራት የሚከተሉትን ቅድመ ዝግጅት ማከናወን
  - 1០X1០ ሴ.ሜትር የሆነ ወፍራም ክላሰር እና 10X10 ሴ.ሜትር የሆኑ ደማቅ ቀለም ያላቸውን የስዕል ወረቀቶች በሕፃናቱ ቁጥር መጠን ማዘጋጀት
  - ክላሰሩን ከላይ ከታች እንዲሁም ከግራና ከቀኝ 2X2 ሴ.ሜትር ገባ ብሎ ማስመር
  - የውስጡን 8X8 ሴ.ሜትር የሆነውን ቦታ ከላይ ወደታች 2 ሴ.ሜትር ስፋት እንዲኖረው አድርጎ ማስመር
  - የተሰመረውን የውስጠኛውን 4 ቱን መስመሮች ቀስ ብሎ የላይና የታቹን እንዲሁም የግራና የቀኝ መስመሩን ሳይነካ በከተር/መቀስ / መሰንጠቅ
  - የስዕል ወረቀቱንም 2 ሴ.ሜትር X 10 ሴ.ሜትር ወደታች በጥብጣብ መልክ በመቁረጥ ማዘጋጀት፣
  - A4 ሳይዝ/ ሙሉ የታይፕ ወረቀት መጠን ያለው ክላሰርን መጠቀም



- ከላይ በተሰራው መሠረት የተቆረጠውን አንዱን ጥብጣብ ሰስ ወረቀት መውሰድ
- በክላሰሩ ውስጥ አንዴ ከላይ አንዴ ከታች በማድረግ ወደጎን ማስተላለፍ
- መጨረሻ ጠርዝ ላይ ሲደርስ መጀመሪያውን ጫፉን ጣትን ኮላ በማስነካት ኮላ መለቅለቅ እና ማጣበቅ
- 
- 
-  ረግ

ማስታወሻ ፡-መምህር እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በተግባር እያሳዩ ማስረዳት ያስፈልጋል። መጨረሻ ጠርዝ ላይ ሲደርሱ የጀመሩበትን እና የጨረሱበትን በኮላ ማጣበቅ እንደሚኖርባቸው ካልተጣበቀ ተመዞ ሊወጣ እንደሚችል መግለጽ።

ምዘና ፡- የወረቀት ሽመና መሥራት መለማመዳቸውን መከታተል።

ተግባር ስምንት ፡- በጂኦሜትሪ ቅርጾች ልዩ ልዩ ምስሎችን መሥራት


ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ በጂኦሜትሪ ቅርጾች ልዩ ልዩ ምስሎችን መሥራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀት፣ እርሳስ፣ መቀስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተለያዩ ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች ወይም ክላሰሮችን ለሕፃናቱ መስጠት
- የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን እንዲስሉ ማድረግ
- የተሳሉትን የጂኦሜትሪ ቅርፆች በመቀስ ቆርጠው እንዲያወጡ ማድረግ
- ቆራርጠው የጂኦሜትሪ ቅርፆችን ሰርተው የተረፉቸውን ወረቀቶች እንዲሰበስቡ ማድረግ
- ከዚያም በማጣበቂያ በማጣበቅ ልዩ ልዩ ስዕሎችን እንዲሠሩ ማድረግ
- የሰሩትንም በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው እንዲያሳዩ እና ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ



ማስታወሻ ፦ በመጀመሪያ ሰርተው ለሕፃናቱ በማሣየት ሕፃናቱ ሊያዩት የሚችሉበት ቦታ ማስቀመጥ

ምዘና ፦ በጂኦሜትሪ ቅርፆች ልዩ ልዩ ምስሎችን መሥራት መለማመዳቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ዘጠኝ ፦ የስጦታ ካርድ መስራት

ተግባር ዘጠኝ ፦ የስጦታ ካርድ መስራት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ የስጦታ ካርድ መስራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወፍራም ክላሰር፣ ምስሎች፣ መቀስ፣ ኮላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ከ 4-5 ዓመት በተማሩት መሠረት ፖስት ካርዶችን ከወፍራም ክላሰር እንዲያዘጋጁ ማድረግ
- የተለያዩ ምስሎችን ከአሮጌ መጽሔቶች ላይ ቆርጠው አውጥተው እንዲለጥፉ እና እንዲያስውቡ ማድረግ
- ከዚያም ከጓደኞቻቸው ጋር የመልካም ምኞት ስጦታን እንዲለዋወጡ ማድረግ

ምዘና ፦ የስጦታ ካርድ መስራት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አስር ፦ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ምስል በጭቃ መስራት

ተግባር ዘጠኝ ፦ የስጦታ ካርድ መስራት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶችን ምስል በጭቃ መስራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጭቃ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ተገቢውን የጭቃ አቦካክ ስርዓትን በመከተል የተቦካ ጭቃን ማዘጋጀት
- የሕፃናቱን ጠረጴዛ በላስቲክ በመሸፈን ጭቃውን በየጠረጴዛው ላይ ማቅረብ
- የተለያዩ የሚፈልጉትን ነገር እንዲሠሩ ማድረግ
- ሰርተው ሲጨርሱ በትንሽ ወረቀት ላይ ስማቸውን እና የሠሩት ምን እንደሆነ እንዲጽፉ በማድረግ ከሰሩት ምስል ሥር እንዲያስቀምጡ ማድረግ
- ሲደርቁም ቀለም እንዲቀቡዋቸው ማድረግ
- የሥራ ውጤቶቻቸው በሌሎች እንዲጐበኝ ሁኔታዎችን ማመቻቸት

ማስታወሻ ፡- የተለያዩ ለጨዋታ የሚያስፈልጓቸውን መጫወቻዎች ራሳቸው እንዲያዘጋጁ ማበረታታት ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶችን በጭቃ መስራት መቻላቸውን መከታተል።



ተግባር አስራ አንድ ፡- በወረቀት የጣት አሻንጉሊት መስራት

ተግባር ዘጠኝ ፡- የስጦታ ካርድ መስራት


ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፡- በወረቀት የጣት አሻንጉሊትን መስራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ትልቅ ወረቀት በመያዝ እና ሕፃናቱም 1 o X1 o ሴ.ሜ የሆነ ወረቀት መስጠት
- የሚከተለውን በገለፃ በማሣየት ማሰራት
    - *በመጀመሪያ ሁለቱን ትይዩ ጫፎች በማገናኘት ወረቀቱን ማጠፍ /የሶስት ማዕዘን ቅርጽ ይሰጣል/*
    - *ከመካከል የተወሰኑ ሴንቲ ሜትሮችን በመተው የሶስት ማእዘኑን ጫፍ ወደታች ማጠፍ*
    - *ከታጠፈው ውጭ ያለውን መሃል በታ የውሻውን የፊት ምስል ዓይን፣ አፍንጫ፣ አፍ መሳል*
    - *ትንሽ የውሻ ቡችላን በወረቀት መሥራትን ማለማመድ*
- *ሲጨርሱም ጠቋሚ ጣታቸው ላይ በማድረግ በማንቀሳቀስና እንደ ውሻ ው፣ው፣ው በማለት ድምጽ በማውጣት እንዲጫወቱ ማድረግ*



ምዘና ፡- በወረቀት የጣት አሻንጉሊትን መስራት መቻላቸውን ማረጋገጥ።



ተግባር አስራ ሁለት ፡- የተለያዩ ፓኮዎችን በመጠቀም መጫዎቻዎችን መስራት

ከወረቀት ላይ መገልበጥ

ዓላማ ፦ የተለያዩ ፓኮዎችን በመጠቀም መጫዎቻዎችን መስራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የክብሪት ፓኮ/ የሣሙና /የሻይቅጠል/፣ክር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእያንዳንዱ ሕፃን  የክብሪት፣የሣሙናና  የሻይቅጠል ሦስት ፓኮዎችን መስጠት
- በእየአንዳንዱን የውስጠኛውን ክፍል ጫፍ ላይ በዱልዱም መርፌ ሰፋ ያለ ቀዳዳ ማበጀት
- በቀዳዳ ውስጥ ክርን በማስገባት እርስ በእርስ እንደ ባቡር ፉርጐዎች እንዲሠሩ ማድረግ
- ሲጨርሱም በረዥም ክር እየጐተቱ በክብሪት ፓኮ ላይ ቀለል ያሉ ጠጠሮችን በመጫን ከቦታ ቦታ እያጓጓዙ እንዲጫወቱ ማድረግ

| |
|---|
| ማስታወሻ ፦ የተለያዩ ፓኮዎችን ሕፃናቱ ከቤታቸው እንዲያመጡ ማድረግ ይቻላል። |

ምዘና ፦ የተለያዩ ፓኮዎችን በመጠቀም መጫዎቻዎችን መስራት መቻላቸውን ማረጋገጥ።




ተግባር አስራ ሦስት ፦ በሶፍት ካርቶን አሻንጉሊት መስራት

ዓላማ ፡- በሶፍት ካርቶን አሻንጉሊት መስራት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሶፍት መጠቅለያ ካርቶን፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ጭራሮ፣ንፁህ ላስቲክ /ጨርቅ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- የሶፍት መጠቅለያ ካርቶንን ለሕፃናት መስጠት
- በቀለም የተለያዩ መስመሮችን ቅርፆችን በመሥራት እንዲያሸበርቁት ማድረግ
- በመቀጠልም ከወደላይ ካርቶኒውን መብሳት
- በጭራሮ ላይ ወረቀት በመጠቅለል በቀዳዳ ውስጥ እንዲያስገቡ እጅ እንዲሰሩለት ማድረግ
- ቀጥሎም ንፁህ ላስቲክ ወይም ጨርቅ በመጠቅለል በካርቶኒው በላይኛው በኩል ትንሽ ገባ አድርጎ በመከተት ጭንቅላት እንዲሠሩ ማድረግ
- በመጨረሻም በባለቀለም እርሳስ ዓይን፣ አፍንጫ፣ አፍ እንዲሠሩ በማድረግ በመፀዳጃ ቤት ወረቀት መጠቅለያ አሻንጉሊት በመሥራት እንዲጫወቱ ማድረግ



ምዘና ፡- በሶፍት ካርቶን አሻንጉሊት መስራት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

## 2.1.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም ----------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም ------------------------------------------ ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም -------------------------------------------- ዓመተ ምሕረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ --------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት --------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት-------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | የዓመቱ መጀመሪያ | የዓመቱ አጋማሽ | የዓመቱ መጨረሻ |
| 1. የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | | | |
| 1.1 በቤታቸውና በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤታቸው የሚገኙትን ሰዎች፣ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት ይችላሉ | | | |
| 1.2 በአካባቢቸው በሚያገኛቸው ነገሮች ላይ ሙከራ ማካሄድ ይችላሉ | | | |
| **2.** በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | | | |
| 2.1 የጠቃሚ ቦታዎችንና ሰዎች የስራ ድርሻ መናገር ይችላሉ | | | |
| 2.2 ሀገርን የመውደድ ስሜት ያድርባቸዋል | | | |
| **3.** አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅና መንከባከብ | | | |
| 3.1 በአካባቢ ጽዳት ላይ መሳተፍ ይችላሉ | | | |
| **4.** በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ | | | |
| 4.1 ራስን ከአደገኛ ነገሮች መጠበቅና አካባቢን ማፅዳት ይችላሉ | | | |
| 4.2 በደረጃቸው የህፃናት መብትን ተረድተው ራሳቸውን ከህፃናት ጥቃት ለመከላከል ይሞክራሉ | | | |
| **5.** የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሃሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ | | | |
| **5.1** መኪና ጐማዎችን መጠን ብዛትና ጥቅም መናገር ይችላሉ | | | |
| **6.** በስነ ሥዕልና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅና ራስን መግለጽ | | | |
| 6.1 የተለያዩ ነገሮችን በመስራት የፈጠራ ችሎታን ያዳብራሉ | | | |

# አባሪ

| መዝሙር/ግጥም/ | ጨዋታ | ተረት |
|---|---|---|
| 1. እኔ ልጅ ነኝ | 1. ዱላ ቅብብል | 1. ትንሹ ዮናስ |
| 2. የሰውነት ክፍሎች”” | 2. ማን ቀድሞ ይበጥሳል | 2. የላሊቱ ሉሊት |
| 3. ሙሉነኝ (እኔ ትንሽ ነኝ)”” | 3. ጭራ ነቀላ | 3. በድሉ በረኛው |
| 4. ስለመቅመስ”” | 4. ትንሹ ጎማ | 4. ማ ነው የሚበልጠው |
| 5. ትንሿ አፌ”” | 5. ወፊቷን እሆናለሁ | 5. ውርዬና ቦቢ |
| 6. ጥርስን መፋቅ እንደዚህ ነው | 6. አያ ጅቦ | 6. በራሪው አበባ |
| 7. ንጽህናዬን ጠብቄአለሁ | 7. አረንጓዴ | 7. ጃምቦና ኩባያው |
| 8. ወፊቷን እሆናለሁ | 8. የወንበር ሽሚያ | |
| 9. ጠዋት ተነስቼ | 9. የጠራህን ዕወቅ | |
| 10. ፊትን መታጠብ እንደዚህ ነው | 10. ቀምሰህ ዕወቅ | |
| 11. ውሽታሙ እረ | 11. ተአምረኛው ከረጢት | |
| 12. ጥንቸል ጉረኛው | 12. መሃረቤን ያያቹ | |
| 13. ተረት ተረት | 13. ማነው ቀድሞ የሚለብሰው | |
| 14. ማን ነኝ ማን ነኝ | 14. መሪውን ዕወቅ | |
| 15. ትንሽትንሽ ወፎች | 15. ትዕዛዝን ፈጽም | |
| 16. ቤቴ ቤቴ | 16. ልትወጣ ነው ልትወጣ ነው | |
| 17. አንድ ላይ አንድን ጨምሬ | 17. ጓደኛህን ፈልግ | |
| 18. የቁጥር ስንኝ | 18. የጎደለውን ሙላ | |
| 19. አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች | 19. ጭብጨባውን በቁጥር አዛምድ | |
| 20. ጠዋት ተነስቼ | 20. የመስፈር ጨዋታ | |
| 21. የሳንቱ ቀናት እነማን ናቸው | 21. ምን መቼ ይደረጋል | |
| 22. ባንዲራችን | 22. ምን የት እንዳለ ዕወቅ | |
| 23. ልጆች ልጆች እናካችሁ | 23. የመንድ ትራፊክ ሙብራት | |
| 24. አደገኛ ነገሮች | | |
| 25. ጎበዙ ተማሪ | | |
| 26. ለወላጆች ቀን | | |

# መዝሙር

1. <u>እጅ ለእጅ ተያይዘን</u>

እጅ ለእጅ ተያይዘን

እጅ ለእጅ ተያይዘን

እንሽከረከራለን

መዘመር እንችላለን

መደነስ እንችላለን

2. <u>ዓይን አለኝ አያለሁ</u>

ዓይን አለኝ አያለሁ

ዓይን አለኝ አያለሁ

አካባቢዬን አስተውላለሁ

ከምንም ጋር አልጋጭም በመንገድ

አስተውዬ እያየሁ ሰለምሄድ

3. <u>ሽታን የሚገልፁ ስንኞች</u>

ሽተተን ሽተተን ሎሚው

ሽተተን ሽተተን ማንጎው

ብሉት ብሉት አለን ሽታው

የቆሻሻ ገንዳ ሽታ

ልጆች ያስይዛል በሽታ

እንራቅ እንራቅ ከቆሻሻ ሽታ

እንዳንያዝ በጉንፋን በሽታ

4. <u>የላሊቱ ሉሊት</u>

የላሊቱ ሉሊት በለጠች

ከቲቲ ቡችሊት

ቲቲ ቡችሊት እንዴት ሆነች

ትምህርት ጠልታ በየቆሻሻው ተልከሰከሰች

ባልታጠበ እጅ እየጎረሰች

ታመመች ፣ አስቀመጣት፣ አስታወካት
ደከመች፣ ተዝለፈለፈች፣ ወደቀች
የላሊቱ ሉሊት
በለጠች ከቲቲ ቡችሊት
የላሊቱ ሉሊት
በለጠች ከቲቲ ቡችሊት
ላሊትስ እንዴት ሆነች ?
ከእንቅልፏ ተነሳች
ልብሷን ለባበሰች
በሣሙና ተጣጠበች
ምግቧን ተመገበች
ቦርሳዋን አነገበች
ጉዞዋን ቀጠለች

**5.** ሃሎ ሃሎ

ሀሎ ሀሎ ጓዴ እንደምንድነህ?
ሀሎ ሀሎ እኔ በጣም ደህና ነኝ
አንተስ እንደምንድነህ ?

**6.** ትንሽ ትንሽ ወፎች

አንድ ሁለት ሶስት ትንሽ ትንሽ ወፎች
አራት አምስት ስድስት ትንሽ ትንሽ ወፎች
ሰባት ስምንት ዘጠኝ ትንሽ ትንሽ ወፎች
አሥር ትናንሽ ወፎች

**7.** በአካባቢያቸው የሚገኙ ግልጋሎት ሰጪ ቦታዎች

እማማ ስንዴ ለማስፈጨት
ሄደች ወፍጮ ቤት
አስፈጭታ ስትመጣ
አባባ ከሥራ መጣ
ከዕለታት አንድ ቀን
ስላመመኝ ሆዴን

ሃኪም ቤት ሄደኩኝ

ሐኪሙም እንዲህ አለኝ

እጅህን ሳትታጠብ

እንዳትበላ ምግብ

እሺ ብዬ ቃል ገባሁኝ እኔም

ሁለተኛ እጄን ሳልታጠብ አልበላም

**8.** <u>የሕብረት ጽዳትን በተመለከተ ግጥምና ስንኝ</u>

ትናንሽ ልጆች በህብረት

ግቢያቸውን ያፀዳሉ በአንድነት

ሲጨርሱም አጽድተው ግቢያቸውን

በሳሙና ይታጠባሉ እጃቸውን

**9.** <u>በምን ምን እናደርጋለን</u>**?**

መምህር እናያለን ሲሉ /በዜማ/

ሕፃናት በዓይናችን ይላሉ /በዜማ/

መምህር እንሮጣለን /በሩጫ መልክ በዜማ/

ሕፃናት በእግራችን

መምህር እንሰማለን

ሕፃናት በጆሮአችን

መምህር እንቀምሳለን

ሕፃናት በምላሳችን

እናሽታለን

በአፍንጫችን ወዘተ.....

**10.** <u>ቀስ በቀስ ሽረሪቷ</u>

ቀስ በቀስ ሽረሪቷ ወደ ላይ ወደ ላይ ወጣች

ንፋሱ ነፍሶ ሲያወዛውዛት

ዝናቡ ዘንቦ ወደታች ወደታች ጣላት

**11.** <u>እንደ ዛፍ እወዛወዛለሁ</u>

እንደ ዛፍ እወዛወዛለሁ

እንደ ወፍ እበራለሁ

እንደ ፊንጣ እዘላለሁ ወዘተ.....

**12.** <u>ወፊቷን እሆናለሁ</u>

ወፊቷን እሆናለሁ

በአየር ላይ እበራለሁ

ከዛፎቹም በላይ

ወደ ላይ ወደ ላይ

ቢራቢሮን እሆናለሁ

በአየር ላይ እበራለሁ

ከአበቦቹም በላይ

ወደ ላይ ወደ ላይ

**13.** <u>ጥንቸል ጉረኛው</u>

ጥንቸል ጉረኛው አፈረ

ኤሊ ትጉህ ተከበረ

ጥንቸል ጉረኛው ሲነዛ ጉራ

ኤሊ አሸነፈ ሮጠ በተስፋ

አጨበጨቡ ዳኞች እንስሳት

በኤሊ ኮሩ ቀሰሙ ትምህርት

**14.** የቤት እንስሳት መዘመር ይችላሉ

| | |
|---|---|
| የቤት እንስሳት መዘመር ይችላሉ /2/ | ሆሆ ምን ምን እያሉ? |
| ድመት ትዘምራለች ትደንሳለች | ሚያው ሚያው ሚያው ትላለች |
| የቤት እንስሳት መዘመር ይችላሉ /2/ | ሆሆ ምን ምን እያሉ? |
| ውሻስ ምን አለ ምን ምን አለ? | ው ው አለ አጥንት ቆረጠመ |
| የቤት እንስሳት መዘመር ይችላሉ /2/ | ሆሆ ምን ምን እያሉ? |
| ዶሮስ ምን አለ ምን ምን አለ? | ኩኩሉ አለ ከአጥር ላይ ዘለለ |

**15.** <u>ደስተኛ የሆነ</u>

ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ

ደስተኛ የሆነ ይዘላል

ደስተኛ የሆነ ደስታውን

ዱብ ዱብ በማለት ይግለፅ

**16.** <u>እጅን መታጠብ እንደዚህ ነው</u>

እጅን መታጠብ እንደዚህ ነው እንደዚህ ነው

ፊትን መታጠብ እንደዚህ ነው እንደዚህ ነው

ፀጉርን ማበጠር እንደዚህ ነው እንደዚህ ነው ወዘተ.....

**17.** <u>አምስት ሙዞች አሉኝ</u>

አምስት ሙዞች አሉኝ

ለማን ልስጣቸው?

ለሃና ሰጠሁ 4 ቀረኝ

ለሄኖክ ሰጠሁ 3 ቀረኝ

ለአስቴር ሰጠሁ 2 ቀረኝ

ለአሹ ሰጠሁ 1 ቀረኝ

ለራሴ አንድ ወሰድኩ ስንት ቀረኝ?

**18.** <u>ትንሽ ትንሽ ወፎች</u>

አንድ ሁለት ሶስት ትንሽ ትንሽ ወፎች

አራት አምስት ስድስት ትንሽ ትንሽ ወፎች

ሰባት ስምንት ዘጠኝ ትንሽ ትንሽ ወፎች

አሥር ትናንሽ ወፎች

**19.** <u>አምስቱ የስሜት ሕዋሳት</u>

አምስቱ አምስቱ

የስሜት ህዋሳት

የስሜት የስሜት

አዝማች ህዋሳት ህዋሳት

×2 ዓይን አፍንጫ (×2)

ምላስ ጆሮና (×2)

እጃችን ናቸው (×2)

ዓይን አለኝ አያለሁ

ጆሮ አለኝ እሰማለሁ

በአፍንጫዬም አሸታለሁ (×2)

በምላሴም እቀምሳለሁ (×2)

መዳሰሻ እጅም አለኝ (×2)

የስሜት ህዋሴን እወቁልኝ

**20.** ሁልጊዜ ይህን እናደርጋለን

ሁልጊዜ ጠዋት ስንነሳ

ፊታችንን እንታጠባለን

ቁርሳችን እንበላለን

ሁልጊዜ ይህን እናደርጋለን

**21.** ወደ ሱቅ እሄዳለሁ(የአገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን ማስተዋወቅ)

| | |
|---|---|
| እኔ ወደ ሱቅ ከእናቴ ጋር እሄዳለሁ | እሄዳለሁ |
| እኔ ወደ ሱቅ ከአባቴ ጋር እሄዳለሁ | እሄዳለሁ |
| ሂጄም ብስኩት እገዛለሁ | እገዛለሁ |
| ሂጄም ደብተር እገዛለሁ | እገዛለሁ |
| ተመልሼም ወደ ቤቴ እመጣለሁ | እመጣለሁ |

| | |
|---|---|
| እኔ ወደ ሃኪም ቤት ከእናቴ ጋር እሄዳለሁ | እሄዳለሁ |
| ሄጀም ያመመኝን እታከማለሁ | እታከማለሁ |
| ተመልሼ ድኜም ወደ ቤቴ እመጣለሁ | እመጣለሁ |

**22.** . ትናንሽ ወረቀቶች

ትናንሽ ወረቀቶች

ትናንሽ ወረቀቶች

መሬት ላይ ወድቀዋል

ወለሉ /ግቢውን /አቆሸሹት

አንሷቸው አንሷቸው

**23.** ጉበዙ ተማሪ

ጉበዙ ተማሪ በጣም ጠንቃቃ ነው

በመንገድ ላይ ሲሄድ እያስተዋለ ነው

መኪና ሲመጣ ከሩቅ እንዲታየው

የመንገዱን ግራ ይዞ ነው የሚጓዘው

**24.** ወፊቷ

ወፊቷ ከየት ይሆን ቤትሽ?

የምትገቢውን ዞረሽ

በሰማይ ስትበሪ

አጥሩን ስትሰብሪ

ቤትሽን ስትሰሪ

መሆኑን አወቅሁኝ

ወፊቱ ልታርፊ ልተኚ

**25.** እኔ ልጅ ነኝ

| | |
|---|---|
| እኔ ልጅ ነኝ | ሰው |
| ሁሉ የሚወደኝ | እኔ |
| የምወደው ጨዋታ ነው | |
| በሸርተቴ በመሰላል በሽክርክሮሽ | |
| መውጣት መውረድ ደስታዬ ነው | |

**26.** <u>የሰውነት ክፍሎች</u>

በእጆቼ አጨበጭባለሁ /ቾብ ፣ ቾብ/

በእግሮቼ እዘላለሁ /ዝልል፣ ዝልል/

በዓይኖቼ አያለሁ /በሩቅ ዓይንን ከልሎ ማየትን ማስመሰል/

በአንገቴ እጅ እነሳለሁ /እጅ መንሳት/

በአፍንጫዬ አሸታለሁ /እንደማሽተት አየር መሳብ/

**27.** <u>ሙሉነኝ</u>

እኔ ትንሽ ነኝ ትንሽ ነኝ
ትንንሽ የአካል ክፍሎች አሉኝ
መረመጃ ትንንሽ እግሮች አሉኝ
እኔ ትንሽ ነኝ ትንሽ ነኝ
መጫወቻ ትንንሽ እጆች አሉኝ
እኔ ትንሽ ነኝ ትንሽ ነኝ
የማይባቸው ዓይኖች አሉኝ
እኔ ትንሽ ነኝ ትንሽ ነኝ
የምሰማበት ትንንሽ ጆሮዎች አሉኝ
እኔ ትንሽ ነኝ ትንሽ ነኝ

**28.** <u>ትንሹ አፊ</u>

ትንሹ አፊ የት ነው ያለሽው ?
እዚህ ነኝ እዚህ ነኝ እንደምንናችሁ
ትናንሽ ጥርሶቼ የት ነው ያላችሁት
እዚህ ነን እዚህ ነን እንደምናችሁ
ቀዩ ምላሴ የት ነው ያለኸው?
እዚህ ነን እዚህ ነን እንደምናችሁ
ትናንሽ ከንፈሮቼ የት ነው ያላችሁት?
እዚህ ነን እዚህ ነን እንደምናችሁ

**29.** <u>የመቅመስ መዝሙር</u>

ስኳር ይጣፍጣል ቃሙኝ ቃሙኝ ይላል

ማርም ይጣፍጣል ላሱኝ ላሱኝ ይላል

ሎሚ ይኮመጥጣል አፍን ምራቅ ይሞላል

**30.** <u>መሃረቤን ያያችሁ</u>

መሐረቤን ያያችሁ? /ሲል/

አላየንም እባካችሁ /ሕፃናት ይላሉ/

ይቺ ምንድናት ? /ሕፃኑ/

የውርዬ ኳስ ናት /ሕፃናት/

ማየት የለም፣ /ሕፃኑ/

መዳበስ የለም /ሕፃናት ይላሉ/

**31.** <u>ጠዋት ተነስቼ</u>

ጠዋት ተነስቼ

ፊቴንም ታጥቤ

ቁርሴንም በልቼ

ልሂድ ትምህርት ቤት

ቦርሳዬን አንግቼ

**32.** <u>ውሽታሙ እረኛ</u>

ውሽጻሙ እረኛ

ዘውትር ልማደኛ

ቀበሮ መጣብኝ

በጎቼን በላብኝ
እያለ ዘወትር
ሲቀልድ ሲያስቸግር
በዚህ አድራጎቱ
ደግሞም በውሸቱ
ሁሉም ሰው ተማሮ
አንድ ቀን ቀበሮ
መጣና በድንገት
በጎቹን በላበት *2
ውሽታሙ እረኛ
ዘውትር ልማደኛ

ኡኡ እያለ ወጣ
የሚረዳው አጣ*2

## 33. ተረት ተረት

ተረት ተረት የላም በረት
ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ጦጣ
በስልቻ ያለ ማር ሰርቃ እጇን ከታ
እያላሰች ምንም ምንም አላስቀረች
ሆዷ ተነፍቶ መሄድ አቅቷት የማሩ ጌታ
ድንገት አገኛት እጇን አስሮ ወደኋላ
ገርፎ ገርፎ በያዘው ዱላ ጦጢትም
ታውቃት ያ ጥፋቷ የሰውየውን ማር በመስረቋ
አይለመደኝም ብላ ጮኸች በመስረቋም
ተፀፀተች ተረቴን ተረቴን መልሱ
አፌን በዳቦ አብሱ አብሱ

## 34. ቤቴ ቤቴ

ቤቴ ቤቴ በምን ያጌጠ ነው ? /አሻንጉሊት/ በልዩ
ልዩ ቀለማት /ሕፃናት/ በምን ዓይነት
ቀለማት /አሻንጉሊት/ ግድግዳው ቢጫ ነው
ወለሉ ቀይ ነው ጣሪያው አረንጓዴ ነው /ሕፃናት/
ደስ ብሎኛል /2/ አመሰግናለሁ።

## 35. የቀለማት ግጥም

ሰማይ ሰማያዊ ሳር አረንጓዴ ነው ደምም ቀይ
ሲሆንአደይ አበባ ቢጫ ነው በደንብ እናስተውል
ልጆች እንዳንረሳው

**36.** ልጆች ልጆች ስሙኝ እባካችሁ

ልጆች ልጆች እባካችሁ

ስሙኝ ልንገራችሁ ቆሻሻዎችን በየቦታው አትጣሉ

በሽታን ያመጣሉ ከተያዝን በበሽታ

እንቀራለን ከትምህርት ገበታ

አይኖርም ያ ጣፋጩ ጨዋታ

**37.** አደገኛ ነገሮች/ግጥም/

ክብሪትና ምላጭ መጫወቻ አይደሉም

ከአጠገባችን ይጥፉ ለእኛ አይጠቅሙም

ተወዳጆች ለእኛ ጠቃሚያችን

ኳሶቻችንና አሻንጉሊቶቻችን

አምጡአቸው ወደእኛ

እንወዳቸዋለን እኛ

**38.** የወላጆች ቀን

እኛን የምትወዱ ሰዎች እባካችሁ

ሙብታችን አስከብሩልን እናንተም አክብራችሁ

ስናጠፋ ከመምታት ይልቅ ምክሩን ከመሳደብ

ከመጮህ ይልቅ አስተምሩን ይገባናል እኮ ምንም

ትንሽ ብንሆን ደግሞም አትከልክሉን እባካችሁ

እንጫወት እንዝለል እንቦርቅ እንደሰት

ጊዜያችን ነው መፈንደቁ መቦረቁ

ትፈቅዱልን ነበር እኮ ሙብታችን መሆኑን ብታወቁ

## 2.1.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ት/ቤቱ ስም -------------------

የህጻኑ ስም ------------- ዕድሜ ----- ጾታ ---

የመምህር ስም ------- ዓመተ ምህረት ---- ግምገማው የተካሄደበት ወር ---

ስለ ህጻኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡

1/ የሚፈለገው ግብ ላይ አልደረሰም/አልደረሰችም -------------------

2/ የሚፈለገው ግብ ላይ በተወሰነ ደርሷል/ደርሳለች -------------------

3/ የሚፈለገው ግብ ላይ ደርሷል/ደርሳለች -------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሰንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ |
|---|---|

| | 1 | 2 | 3 |
|---|---|---|---|
| **1.** ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመንና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | | | |
| 1.3. ራሳቸውን መግለጽ ይችላሉ | | | |
| • ሕጻናት ራሳቸውን በቃላት መግለጽ መቻል | | | |
| 1.4ራሳቸውን ከሌሎች ጋር በማወዳደር መግለጽ ይችላሉ | | | |
| • ስለ ልደት አከባበር መናገር መቻል | | | |
| 1.3. በጨዋታ ሂደት የሚከሰቱትን አለመግባባቶችና ግጭቶች መፍታት ይችላሉ | | | |
| • የቡድን ጨዋታዎችን መጫወት መቻል | | | |
| **2.** የሰውነት ክፍሎችን መለየትና ተግባራቸውን መናገር | | | |
| | | | |
| 2.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ | | | |
| • የአካል ክፍሎችን የማዛመድ ጨዋታን መጫወት መቻል | | | |
| 2.2. የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውን የሚያከናውኗቸውን የተለያዩ ተግባራት በትክክል መግለጽ ይችላሉ | | | |
| • የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መናገር መቻል | | | |
| **3.** ዓይኖችን መንከባከብ | | | |
| 3.1. ዓይኖቻቸው በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ | | | |
| • የዓይንን ጥቅም መናገር መቻል | | | |
| **4.** ጆሮዎችን መንከባከብ | | | |
| 4.1. ጆሮዎቻቸውን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ ይችላሉ | | | |
| • የጆሮን ጥቅም መናገር መቻል | | | |
| **5.** የማሽተት ስሜት ሕዋስን መጠቀም አፍንጫን መንከበካብ | | | |
| 5.1. መጥፎና ጥሩ ሽታን መግለጽ ይችላሉ | | | |
| • መጥፎና ጥሩ ሽታን መለየት መቻል | | | |
| **6.** የመቅመስ ስሜት ሕዋስን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ | | | |
| 6.3. የተለያየ ጣዕም ያላቸውን የተለያዩ ምግቦች ማጣጣምና ማድነቅ ይችላሉ | | | |
| • በአፍ ውስጥ ስላሉ የአካል ክፍሎች መናገር መቻል | | | |
| 6.4. አፋቸውን በጥንቃቄና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ | | | |
| • ጥርሳቸውን በጥንቃቄ መያዝ መለማመድ መቻል | | | |
| **7.** በመዳሰስ ነገሮችንና ሁኔታዎችን መግለጽ | | | |
| 7.1. በቁሶች መካከል ያለውን ባህሪ፣ የሙቀት መጠንና ቅርጽ መለየት ይችላሉ | | | |
| • በመዳሰስ የነገሮችን ባህርይ መለየት መቻል | | | |
| 8. ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ሥርዓቶችን መለማመድ | | | |
| 8.1. ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን ለይተው መናገር ይችላሉ | | | |
| • የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን ማወቅ | | | |
| 8.3. የግል ንጽህናን መጠበቅ ይለማመዳሉ | | | |
| • የግል ንጽህናን መጠበቅ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ መገንዘብ | | | |
| 8.3. የራሳቸውን ንጽህን መጠበቅ ይችላሉ | | | |
| • የግል ንጽህናን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን መለየት መቻል | | | |
| 9. አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ | | | |
| 9.1. አካላቸውን መጠበቅና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ | | | |
| • አካልን ከጉዳት መጠበቅ መለማመድ | | | |
| 10. ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎችን መጠቀም | | | |
| 10.1. ትላልቅና ትናንሽ ጡንቻዎቻቸውን በመጠቀም የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ይችላሉ | | | |
| • ሚዛን ጠብቆ መራመድ መቻል | | | |
| 11. በነፃነት ፈጠራን መግለጽ | | | |
| 11.2. በአካባቢ ሊገኙ ከሚችሉ ቁሳቁሶች ልዩ ልዩ መጫወቻዎችን መሥራት ይችላሉ | | | |
| • ፈጠራን በስዕል መግለጽ መቻል | | | |

## 2.2.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ት/ቤቱ ስም -------------------

የህጻኑ ስም ------------- ዕድሜ ----- ጾታ ---

የመምህር ስም ------- ዓመተ ምሕረት ---- ግምገማው የተካሄደበት ወር ---

ስለ ህጻኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡

1/ የሚፈለገው ግብ ላይ አልደረሰም/አልደረሰችም -------------------

2/ የሚፈለገው ግብ ላይ በተወሰነ ደርሷል/ደርሳለች-------------------

3/ የሚፈለገው ግብ ላይ ደርሷል/ደርሳለች -------------------

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> የክትትል ሰንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ^ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት ለማወቅ ፍላጎት ማሣደርና መለየት | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1.1 . በቅርብ ለሚያገኙአቸው ሰዎች ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሣየት ይችላሉ | | | |
| • ከሌሎች ጋር በመተባበር መስራት መቻል | | | |
| 1.2. ስለ ጥሩና መጥፎ ስነምግባር መናገር ይችላሉ | | | |
| • የጥሩ ሥነ ምግባርን መገለጫዎች መረዳት | | | |
| **2.** ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ | | | |
| 2.1 ሰዎች እንዴት እንደሚጠነቀቁላቸውና እንደሚንከባከቧቸው መግለጽ ይችላሉ | | | |
| • ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየት መቻል | | | |
| **3.** ሌሎችን መንከባከብና ያለንን ነገር ማካፈል | | | |
| 1.4 . በቡድን ሥራ ውስጥ በተገቢው መንገድ መሣተፍና የሌሎችን ስሜት መጋራት ይችላሉ | | | |
| • የመደሰትና የመከፋት ስሜትን መለየት መቻል | | | |
| 3.2. በአካባቢያቸው ለሰዎች በሚደረግ በጐ ተግባር ላይ መሣተፍ ይችላሉ | | | |
| • በጨዋታ የሌሎችን ስሜት ማንጸባረቅ መቻል | | | |

## 2.3.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ት/ቤቱ ስም --------------------

የህጻኑ ስም ------------- ዕድሜ ----- ጾታ ---

የመምህር ስም ------- ዓመተ ምሕረት ---- ግምገማው የተካሄደበት ወር ---

ስለ ህጻኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡

1/ የሚፈለገው ግብ ላይ አልደረሰም/አልደረሰችም --------------------

2/ የሚፈለገው ግብ ላይ በተወሰነ ደርሷል/ደርሳለች--------------------

3/ የሚፈለገው ግብ ላይ ደርሷል/ደርሳለች--------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሰንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል፡፡

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | **1** | **2** | **3** |
| **1.** መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | | | |
| 1.1 በአካባቢ የሚደመጡ ድምፆችን መለየት ይችላሉ | | | |
| • ድምጾችን መለየት መቻል | | | |
| 1.2 በድምፆች መካከል ያለውን ልዩነት መለየት ይችላሉ | | | |
| • ሰዎችን በድምጽ መለየት መቻል | | | |
| 1.4 ለትዕዛዞችና ለመመሪያዎች ምላሽ መስጠት ይችላሉ | | | |
| • ለትዕዛዞችና መመሪያዎች ምላሽ መስጠት መቻል | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1.4 ተረቶችን አዳምጠው የተረዱትን መግለጽና መልሰው መተረክ ይችላሉ | | | |
| • የተረትን መልእክት መረዳታቸውን መገምገም | | | |
| **2.** በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግርና የምልክት ቋንቋ መግባባት | | | |
| 2.2 ቋንቋን በእርግጠኝነት መጠቀም ይችላሉ | | | |
| • የጠዋት ሪፖርት ማቅረብ መቻል | | | |
| 2.2 በንግግር ቋንቋ ደስታን ማግኘት ይችላሉ | | | |
| • በንግግር ቋንቋ ደስታን ማግኘት ይችላሉ | | | |
| **3.** በማንበብ መደሰት ዕውቀት ማግኘትና መረዳት | | | |
| 3.2 ቀላል ቃላቶችንና ዓ/ነገሮችን ማንበብ ይችላሉ | | | |
| • የስዕሎችን ተመሳሳይነትና ልዩነትን መናገር መቻል | | | |
| **4.** የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት | | | |
| 4.1 ፊደላትንና ቃላትን መፃፍ ይችላሉ | | | |
| • መሠረታዊ መስመሮችን በመስራት ለጽሁፍ መዘጋጀት | | | |

## 2.4.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመመደበኛ ት/ቤት ስም -------------------

የህፃኑ ስም ------------------------------------------እድሜ -------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም-------------------------------------ዓመተ ምሕረት-----------ግምገማው የተካሄደበት ወር------

ስለህፃኑ ምልከታዎንከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ

1/ የታለመው ግብ ላይ አልደረሰም/አልደረሰችም -------------------

2/ የታለመው ግብ ላይ በተወሰነ ደርሷል-------------------

3/ ከታለመው ግብ ላይ ደርሷል/ደርሳለች-------------------

ማሳሰቢያ:- የክትትል ሰንጠረዡ በየወሩ መሞላት ይኖርበታል::

| መድረሻ /ግብ | ምልከታ^ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 2 |
| **1.** የቁሳቁሶችን ባህሪ መፈተሽ መረዳትና መለየት | | | |
| 1.1. ነገሮችን በዓይነት መመደብ ይችላሉ | | | |
| • አንድ ዓይነት ነገሮችን ማዛመድ መቻል | | | |
| **2.** ነገሮችን በባህሪያቸው መሠረት ማወዳደር | | | |
| 2.1. በነገሮች መካከል ያለዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሣየት ይችላሉ | | | |
| • በነገሮች መሀከል ያለ ዝምድናን መግለፅ መቻል | | | |
| **3.** ቁጥሮችን ማስተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መሥራት | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3.1. በነገሮችና በቁጥሮች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት መናገር ይችላሉ | | | |
| • ተቆጣሪዎችን መቁጠር መቻል | | | |
| 3.2 እኩል ናቸው፣ ይበልጣል፣ያንሳል በማለት መናገር ይችላሉ | | | |
| • የይበልጣል እና ያንሳል ጽንሰ ሀሳቦችን መገንዘብ መቻል | | | |
| 3.3 ከ 1-20 አሃዞችን መለየት ይችላሉ | | | |
| • በተለያየ አቅጣጫ ቁጥር መቁጠር መቻል | | | |
| 3.4 ከ 1-20 መቁጠር መደመርና መቀነስ ይችላሉ | | | |
| • የመደመር ጽንሰ ሀሳብን መረዳት መቻል | | | |
| **4.** በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችንና መሣሪያዎችን መጠቀም | | | |
| 4.1 ቦታን፣ ርቀትንና አቅጣጫን መግለጽ ይችላሉ | | | |
| 4.2 ነገሮችን በሥርዓት መደርደርና ማወዳደር ይችላሉ | | | |
| • ትንሽና ትልቅ ቁሶችን ማወዳደር መቻል | | | |
| **5.** የጊዜ ፅንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም | | | |
| 5.1. በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየትና መከተል ይችላሉ | | | |
| • በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት መቻል | | | |
| **6.** የቦታ ጽንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም | | | |
| 6.1. የቁሳቁሶችን መገኛ ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር መናገር ይችላሉ | | | |
| • የቦታ ጽንሰ ሀሳብን መረዳት መቻል | | | |
| **7.** ገንዘብን መተዋወቅ፣ መለየት፣መግለጽና መጠቀም | | | |
| 7.1 የገንዘብን ዋጋ መናገር ይችላሉ | | | |
| • የገንዘብን መጠን መገንዘባቸውን ማረጋገጥ | | | |

## 2.5.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -------------------

የህፃኑ ስም ------------------------------------------እድሜ -------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም-----------------------------------ዓመተ ምሕረት-----------ግምገማው የተካሄደበት ወር------

ስለህፃኑ ምልከታዎን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ

1/ የታለመው ግብ ላይ አልደረሰም/አልደረሰችም-------------------

2/ የታለመው ግብ ላይ በተወሰነ ደርሷል-------------------

3/ ከታለመው ግብ ላይ ደርሷል/ደርሳለች-------------------

ማሳሰቢያ_:- የክትትል ሰንጠረዡ በየወሩ መሞላት ይኖርበታል::

| መድረሻ/ ግብ | | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 |
| **1.** የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | | | | |
| 1.1 | በቤታቸውና በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤታቸው የሚገኙትን ሰዎች፣ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት ይችላሉ | | | |
| • | ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን መለየት መቻል | | | |
| 1.2 | በአካባቢቸው በሚያገኛቸው ነገሮች ላይ ሙከራ ማካሄድ ይችላሉ | | | |
| • | በአካባቢያቸው የሚገኙ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን መለየት መቻል | | | |
| **2.** በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | | | | |
| 2.1 | የጠቃሚ ቦታዎችንና ሰዎች የስራ ድርሻ መናገር ይችላሉ | | | |
| • | ስለ አገልግሎት ተቋማትና በውስጡ ስለሚሰሩ ባለሙያዎች መናገር መቻል | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2.2 ሀገርን የመውደድ ስሜት ያድርባቸዋል | | | |
| • የኢትዮጵያ ካርታ ቅርጽ ማወቅ | | | |
| **3.** አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅና መንከባከብ | | | |
| 3.1 በአካባቢ ጽዳት ላይ መሳተፍ ይችላሉ | | | |
| • የጽዳት መሣሪያዎችን አገልግሎት መረዳት መቻል | | | |
| **4.** በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ | | | |
| 4.2 ራስን ከአደገኛ ነገሮች መጠበቅና አካባቢን ማፅዳት ይችላሉ | | | |
| • ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን መለየት መቻል | | | |
| 4.2 በደረጃቸው የህፃናት መብትን ተረድተው ራሳቸውን ከህፃናት ጥቃት ለመከላከል ይሞክራሉ | | | |
| • ራሳቸውን ከጥቃት መከላከል እንዳለባቸው መረዳት | | | |
| **5.** የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሃሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ | | | |
| 5.2 በአካባቢያቸው የሚገኙትን የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶች አንድነትና ልዩነት ማወዳደር ይችላል | | | |
| • የመጓጓዣ አይነቶችን መረዳታቸውን ማረጋገጥ | | | |
| **6.** በስነ ሥዕልና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅና ራስን መግለጽ | | | |
| 6.1 የተለያዩ ነገሮችን በመስራት የፈጠራ ችሎታን ያዳብራሉ | | | |
| • አስመስሎ መሳል መቻል | | | |